አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

# የባሌ ኦሮሞ ባህላዊ የግጭት አፈታት

በ
ለታሪክ ተሾመ

በኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ እና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት
ለኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጽሑፍ

አዲስ አበባ
ሰኔ 2003 ዓ.ም

# የባሌ ኦሮሞ ባህላዊ የግጭት አፈታት

በ

ለታሪክ ተሾመ

በኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ እና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት
ለኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጽሑፍ

አማካሪ

አብርሃም አለሙ

በሰብዓዊ ሳይንስ ፋኩልቲ
የኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት

አዲስ አበባ

ሰኔ 2003 ዓ.ም

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

# የባሌ ኦሮሞ ባህላዊ የግጭት አፈታት

በ

ለታሪክ ተሾመ

የፈተና ቦርድ አባላት

-----------------------------  -----------------------

አማካሪ  ፊርማ

-----------------------------  -----------------------

ፈታኝ  ፊርማ

# አበርክቶ

አለ በውስጣችን!

*አለ በውስጣችን*

*እውነት ፍጹም ሆና እምታበራበት*

*ደግሞ ማወቅ ማለት*

*ከውጪ ያለውን ሄዶ ከመፈለግ*

*ከውስጥ ያበራውን እንዲወጣ ማድረግ።*

- እጅግ እጅግ በጣም ለምወደውና ይህች የዚህን ጥናት አላማ ቀንበባ የያዘች ግጥም ለፃፈው ገጣሚና ሰአሊ ገብረ ክርስቶስ ደስታ፣ በጣም ለምወደው ገጣሚ ሰሎሞን ዴሬሳ እና የግጥምን ፍቅር በውስጤ ላጫረው ውዱ የእውቀት አባቴ ብርሃኑ ገበየሁ፤
- በማህበረሰቡ ውስጥ ግጭት ሲከሰት ግጭቱን ለመፍታት፣ ግጭት ውስጥ የገቡትን ወገኖች ለማስታረቅ እና የማህበረሰቡን ሰላም ለመጠበቅ የእለት ስራቸውን በመተው ከቆላ እስከ ደጋ በመጓዝ ሽምግልና ለሚቀመጡ ለባሌ ኦሮሞ ሽማግሌዎች፤

ይህን ጥናታዊ ዕሁፌን ለክብራችሁ ይሆን ዘንድ አበርክቻለሁ

# አጠቃሎ

ይህ ጥናት የባሌ ኦሮሞዎች በመካከላቸው ሆነ ከሌሎች ህዝቦች ጋር የሚከሰት ግጭቶችን ለመፍታት የሚጠቀሙባቸውን ባህላዊ ስርዓቶች የሚያሳይ ነው፡፡

ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች በቃለመጠይቅ፣ በተተኳሪ ቡድን ውይይት እና በምልከታ ተሰብስበዋል፡፡ በእነዚህ ዘዴዎች የተሰበሰቡ መረጃዎችን በጥናቱ ውስጥ በቅደም ተከተል ለመተንተን እንዲያስችል ገላጭ የጥናት ዘዴን፣ በጥናት ወቅት የተሰበሰቡ መረጃዎችን አውዳዊ ትርጓሜ ለመግለጽ የይዘት ትንተናን ተጠቅሟል፡፡ ማህበረሰቡ ውስጣዊም ሆኑ ውጫዊ ግጭቶችን ለመፍታት የሚጠቀምበት ስርዓት ሴረጉማ ይባላል፡፡ ሴረጉማ ለግድያ ግጭት ብቻ ሳይሆን ለእንስሳት፣ ለአካል ጉዳት እና ለሞራል መነካት የሚያገለግል ባህላዊ የግጭት መፍቻ ስርዓትም እንደሆነ ጥናቱ ያሳያል፡፡

በማህበረሰቡ ግጭት እንዲከሰት መንስኤ የሚሆኑ ጉዳዮች በአብዛኛው ከእርሻና ከከብት ማርባት ጋር የተያያዙ እንደሆኑ፣ ማህበረሰቡ የግድያ ግጭት አይነቶችን በግጭቱ ውስጥ ከተሳተፉት አካላት ማንነት በመነሳት በቤተሰብ ውስጥ፣ በዘመድ መካከል፣ በጎሳ ውስጥ፣ በጎሳዎች መካከልና ኦሮሞ ካልሆኑ ህዝቦች ጋር የሚደረግ በማለት በአምስት እንደሚከፋፈል ጥናቱ ያሳያል፡፡ ለግድያ ግጭት የሚከፈለው ጉማ እንደግድያው ሁኔታ፣ እንደተጋጪዎቹ ማንነት፣ እንደሟች ፆታ የተለያየ እንደሆነና የሚከፈለው ጉማም እንደየዘመኑ ሁኔታና እንደማህበረሰቡ የገቢ ምንጭ በሞት፣ በመሬት፣ በከብት እና በገንዘብ እንደነበር ከጥናቱ ለማወቅ ተችሏል፡፡

የሚከፈለው ጉማ በግድያው ሁኔታ ላይ በመመስረት'ኦኮኮ'፣ 'ሀምቢሳ' እና 'ረፌሳ' በመባል እንደሚከፈልና ጉማ የሚከፈልበት የሰውነት አካል ሶስት መቶ ስልሳ እንደሆነ ጥናቱ አመላክቷል፡፡ ግጭትን ለመፍታት የሚያገለግሉት ተቋማት የሃገር ጃርሳ ቢያ እና ራያ አምባ እንደሆኑ ከጥናቱ መረዳት ተችሏል፡፡

ማህበረሰቡ ለግድያ ግጭት ያለው አመለካከት የግድያ ግጭት መከሰት አይገባውም ከተከሰተም በፍጥነት መፍትሔ ማግኘት አለበት የሚል እንደሆነ፣ ባህላዊ የግጭት መፍቻ ተቋማቱ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ስነልቦናዊ ፋይዳ እንዳላቸው፣ ስነቃል በግጭት አፈታት ስርዓት ወቅት ከፍተኛ ሚና እንዳለው በጥናቱ ተመልክቷል፡፡

በባህላዊው ስርዓት እና በተቋማቱ የበለጠ ለመጠቀምና ማህበራዊ ፋይዳቸውን እንደያዙ እንዲቆዩ ለማድረግ፦ ለሀገር ሽማግሌዎች እውቅና መስጠት፣ በሞራልና በማቴሪያል ማገዝ፤ በስርዓተ ትምህርት ውስጥ ማካተት፣ ባህላዊ እውቀትን የሚፃረሩ አካላትን እንቅስቃሴ ማስወገድና ለፊልም፣ ለትውፊታዊ ቴአትር፣ ለስነፅሁፍ እና ለሙዚቃ ግብዓት የሚሆኑበትን ሁኔታ ማመቻቸት፤ ከዘመናዊ የህግ ሰነዶች ጋር ሊሰራ የሚችልበት ዘዴ መቀየስ፤የሀገር ሽማግሌዎች ከመደበኛ ፍርድ ቤት ዳኞች በመቀራረብ፣ የሚሰሩበትን ሁኔታ ማመቻቸት እንደሚገባ በጥናቱ ተመልክቷል፡፡

# ምስጋና

ከመጀመሪያ እስከመጨረሻ ድረስ ጥናቱን በማረም፣ በማስተካከል፣ ጠቃሚ ሀሳቦች እንዲገቡ በማድረግ እገዛቸው ሳይለየኝ ለረዱኝና ዘወትር አባታዊ ምክራቸው ላልተለየኝ መምህሬና አማካሪዬ አቶ አብርሃም አለሙ ላቅ ያለ ምስጋና አቀርባለሁ።

ለጥናቱ የሚሆነኝን መረጃ የማገኝበትን ሁኔታ በማመቻቸት ከፍተኛ እገዛ ያደረጉልኝን የባሌ ዞን ባህልና ቱሪዝም ቢሮ፣ የጎባ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ እና የሲናና ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ሰራተኞች በተለይ ለአቶ አማን አደም፣ አቶ ሀሰን አብዮ፣ አቶ ጃርሶ በልዳ፣ ወ/ሮ በድሪያ አማን፣ አቶ ሽምስዲን የከበረ ምስጋናዬን ይድረሳችሁ።

አስፈላጊውን ነገር ሁሉ በማሟላት ቤተሰባዊ ፍቅራቸውን በመስጠትና ይህንን ጥናት ስሰራ ከጎኔ ሳይለዩ የኦሮምኛ ቋንቋዬን በማቃናት፣ የጥናት ጥያቄዎችን በኦሮምኛ ፊር በማስያዝ ለረዱኝ አባቴ አቶ ተሾመ ግዛው፣ ለእናቴ ወ/ሮ ሰናይት ብሩ፣ ለወንድሞቼ ብርሃን ተሾመና ዮሐንስ አየለ፣ ለእህቶቼ ብርሃኔ ሞቱማና ትዕግስት ሲሳይ ምስጋናዬ ይድረሳችሁ።

ለዚህ ጥናት የሚሆን መረጃን ለመስጠት በቀጠርኳቸው ጊዜ ስራቸውን ትተው በመገኘትና በፍፁም ቅንነት ለተባበሩኝ ቁልፍ መረጃ አቀባዮቼ፡- አቶ ከድር ጀማል፣ አቶ ቲልሞ ሲዴ፣አቶ ጫጮ ከንፈልቻ፣ አቶ ማማ ቃሲም፣ አቶ በዳሶ በልዳከፍተኛ ምስጋና አቀርባለሁ።

ለዚህ ጥናት ማስኬጃ የሚሆን የገንዘብ ድጋፍ ስላደረገልኝ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲን አመሰግናለሁ።

ከመጀመሪያው ረቂቅ ጀምሮ የሚያስፈልገኝን ፅሁፍ በሙሉ በማተም፣ ከጥናቴ እንዳልዘናጋ በመምከርና በማስታወስ፣ ስለጥናቴ እንቅልፋን በማጣት በወንድማዊ ፍቅሩ ላልተለየኝ ኤፍሬም ዮሊ (ይህ ስም የዮኒ እና የሊዲ ጥምር መሆኑን ልብ ይሏል) ከልብ አመሰግናለሁ። ጥናቴን ተከታትላችሁ የፊደል ግድፈት በማረም ድጋፋችሁ ላልተለየኝ ወንድሞቼ እና እህቶቼ አብርሃም ወ/ዮሐንስ፣ አምደወርቅ እሸቱ፣ ሰናይት አዲሱ፣ ምስጋናዬ ይድረሳችሁ።

ከመስክ መረጃ መሰብሰቢያ ቴፕ ሪከርደር እና ካሜራ ለሰጡኝ ሃብታሙ አጥላውና ፋሲል አሰፋ ምስጋናዬ ከልብ ነው። በመስክ ቆይታዬ ከቤተሰብ ጋር ሆነህ መስራት አትችልም፣ ትዘናጋለህ በማለት ቤቱን ለጥናት ለለቀቀልኝ ብዙአየሁ ብርሃኑ ምስጋናዬ ከፍ ያለ ነው።

ማውጫ


አበርክቶ....................i
ምስጋና....................ii
አጠቃሎ....................iii
1. መግቢያ.................... 1
1.1. የጥናቱ ዓላማ.................... 3
1.2. የጥናቱ ጥያቄዎች.................... 4
1.3. የጥናቱ አስፈላጊነት.................... 4
1.4. የጥናቱ ወሰን.................... 5
1.5. የጥናቱ ዘዴ.................... 5
1.5.1 የመረጃ ምንጮች.................... 7
1.5.2. የመስክ ስራ ሂደት.................... 8
1.6. በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሔዎች.................... 10

2. የባሌ አካባቢያዊና ማህበረ- ባህላዊ ዳራ.................... 13
2.1. መስህብነት ያላቸው ቦታዎች.................... 21
2.2. ለጥናቱ የተመረጡ ወረዳዎች.................... 22

3. ንድፈ ሀሳባዊ መሰረትና የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት.................... 24
3.1. የግጭት ብያኔ.................... 24
3.2. የግጭት መንስኤ.................... 27
3.3. የግጭት አይነቶች.................... 29
3.4. የግጭት አፈታት.................... 30
3.5. የግጭት አፈታት ዘዴዎች ከመስኩ ምሁራን አንፃር.................... 31
3.5.1. ዘመናዊ ዘዴ (Modern Method).................... 33
3.5.2. ሀይማኖታዊ ዘዴ (Religious Method).................... 33
3.5.3. ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴ (Cultural Method).................... 33
3.6. የግጭት አፈታት ዘዴ ከዓለም፣ ከአህጉር አቀፍ ድርጅቶችና ከኢትዮጵያ የህግ ሰነዶች አንፃር.................... 35
3.6.1. የተባበሩት መንግስታት የህግ ሰነዶች.................... 36
3.6.2. የአፍሪካ ሕብረት የህግ ሰነዶች.................... 36
3.6.3. የኢትዮጵያ የህግ ሰነዶች.................... 37
3.2 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት.................... 38

4. የባሌ ኦሮሞ ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት.................... 42
4.1 የጉማ ምንነትና ታሪካዊ ዳራ.................... 43
4.1.1 ሴረ ጉማ ምንድነው?.................... 43
4.1.2 የጉማ ታሪካዊ ዳራ.................... 45
4.1.3 የጉማ አይነቶች.................... 46
4.1.3.1. የእንስሳት ጉማ.................... 46

4.1.3.2. የሰው ልጅ ጉማ .................................................... 47
4.2 የባሌ ኦሮሞ ባህላዊ የግጭት መፍቻ ተቋማት .................................... 48
4.2.1 የሀገር ሽማግሌ ( Jaarsa Biyyaa ) ........................................ 49
4.2.2 የቤተሰብ ሽማግሌ ( Jaarsa Warraa ) ...................................... 49
4.2.3 የአካባቢ ሽማግሌ (Jaarsa Ganda ) ........................................ 50
4.2.4 የጎሳ ሽማግሌ (Jaarsa Gosa ) ............................................. 50

5.የባሌ ኦሮሞ ባህላዊ የግድያ ግጭት አፈታት ........................................ 51
5.1 የግድያ ግጭት መነሻ ምክንያቶች ................................................ 52
5.2 የግድያ ግጭት አይነቶች ..................................................... 52
5.2.1.ውስጣዊ ግጭቶች ........................................................ 52
5.2.2.ውጫዊ ግጭቶች ......................................................... 53
5.3 ለግድያ ግጭት የሚከፈለው የጉማ አይነት ......................................... 54
5.3.1.ኦኮኮ (Okkoko) ........................................................ 54
5.3.2. ሀምቢሳ (Haambissa) .................................................. 55
5.3.3.ረፊሳ (Raffissa) ...................................................... 56
5.4 የግድያ ግጭት የሚፈታበት ባህላዊ ተቋም ........................................... 57
5.5 ባህላዊ የግድያ ግጭት መፍቻ ተቋሙ ለማህበረሰቡ የሚሰጠው ፋይዳ .......................... 58
5.5.1 ማህበራዊ ፋይዳ ........................................................ 59
5.5.2 ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ ....................................................... 60
5.5.3 ስነ ልቦናዊ ፋይዳ ...................................................... 60
5.6 የባሌ ኦሮሞ ማህበረሰብ ለግድያ ግጭት ያለው አመለካከት ................................ 61
5.7 ባህላዊ የግድያ ግጭት አፈታት አውዳዊ ክዋኔ ........................................ 62
5.7.1 ቅድመ እርቅ ክዋኔ ...................................................... 63
5.7.2 የእርቅ ክዋኔ .......................................................... 67
5.7.3 ድህረ እርቅ ክዋኔ ...................................................... 85

6. ስነቃል በግጭት አፈታት ያለው ሚና .............................................. 86
6.1. ምሳሌያዊ አነጋገር በግጭት አፈታት ወቅት ያለው ሚና ................................ 87
6.2. አፈታሪክ በግጭት አፈታት ወቅት ያለው ሚና ....................................... 96
6.3. ተረት በግድያ ግጭት አፈታት ወቅት ያለው ሚና ..................................... 98

7.ማጠቃለያና ይሁንታዎች ...................................................... 104
7.1. ማጠቃለያ .............................................................. 104
7.2 ይሁንታዎች ............................................................. 106
ዋቢ መፃህፍት (Reference)
አባሪዎች

# 1. መግቢያ

ግጭት ከሰው ልጅ የስነ ፍጥረት ታሪክ ጋር አቻ እድሜ ያለው የተፈጥሮ ክስተት ነው። ለዚህም በመጽሐፍ ቅዱስ በኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ 3 እና 4 እንደተጠቀሰው የመጀመሪያዎቹ ሰዎች አዳምና ሔዋን አታድርጉ የተባሉትን በማድረጋቸው ከፈጣሪያቸው ከእግዚአብሔር ጋር፣ ቀጥሎም በአዳም ልጆች በቃየልና በአቤል መካከል የተፈጠረው ግጭት ጥሩ ምሳሌዎች ይሆናሉ (እነ Rubin 1994):: ግጭት ተፈጥሮአዊና በማናቸውም ደረጃና አይነት ሰብዓዊ ግንኙነቶች ውስጥ የሚገጥም እጅግ የተለመደ ክስተት ነው። ከግለሰብ አንስቶ እስከ አለም አቀፍ ባሉ በሁሉም ደረጃዎች ይከሰታል (Dimostenis 2004):: ግጭት ግልፅና ድብቅ በሆነ መንገድ አዎንታዊና አሉታዊ የሆኑ ነገሮች እንዲፈጠሩ ምክንያት ይሆናል። ከዚህም የተነሳ ሰዎች ለግጭት ያላቸው አመለካከት የተለያየ ነው (Habtamu 1998; Deutsh, 1983):: የግጭት መነሻ ምክንያቶች የተለያዩ ናቸው። እንደ ኢትዮጵያ ባሉ አገሮች ደግሞ የግጭት መነሻ ምክንያት ከሳሳ፣ ከመደብና ከሀይማኖት ጋር በስፋት ግንኙነት አለው (Nhema 2004)::

ኢትዮጵያ ልዩ ልዩ ባህሎች ያሏቸው የተለያዩ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች የሚገኙባት ሀገር ናት። በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ የተከሰተ ግጭት ተባብሶ የከፋ ጉዳት ከማድረሱ በፊት እንደግጭቱ አይነት ባህርይ እና ደረጃ ህግና ደንብ በማውጣት ሊያደርስ የሚችለውን ቀውስ ለመከላከል ጥረት ይደረጋል።

ግጭትን ለመፍታት በዘመናዊ መልክ በመንግስት ተቋቁሞ በመላ ሀገሪቷ ከሚተገበረው የህግ ስርዓት ጎን ለጎን ከትውልድ ወደ ትውልድ በቃልና በክዋኔ የሚተላለፉ ባህላዊ ስርዓቶችና ደንቦች አሉ። እነዚህም ባህላዊ ዘዴዎች የማህበረሰቡን ሰላምና ደህንነት ለመጠበቅ ያስችላሉ። ባህላዊ የግጭት መፍቻ ስርዓት በማህበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ያለውና "ፍትሃዊ ነው" ተብሎ የሚታሰብም ስርዓት ነው።

በኢትዮጵያ ውስጥ ከሚገኙ ብሔር ብሔረሰቦች መካከል አንዱ የኦሮሞ ብሔረሰብ ነው። የኦሮሞ ብሔረሰብ እንደማንኛውም የኢትዮጵያ ብሔረሰቦች የሚታወቅባቸው የራሱ የሆነ ባህል፣ ልምድ፣ ታሪክ፣ ቋንቋ ወዘተ. አለው። ከዚህም ጋር ተያይዞ እርስ በእርሱም ሆነ ከሌሎች ህዝቦች ጋር በሚያደርገው ግንኙነት የሚፈጠሩ ግጭቶችን ለመቆጣጠርና ለመፍታት የሚጠቀምባቸው ስርዓቶችም አሉት (Habtamu 1998፣ Asefa 2001፣ Desalegn & et al

2005፣ Giday 2000፣ ሙሉጌታ 1997):: የኦሮሞ ህዝብ በተወሰነ አካባቢ ብቻ ተገድቦ የሚኖር ባለመሆኑ እደየመኖሪያ አካባቢው መለያየት ልዩ ልዩ ባህላዊ እሴቶች አሉት፡፡ የአንዱ አካባቢ ባህላዊ የግጭት አፈታት ከሌላው አካባቢ ሊለያይ ይችላል፡፡ ስለዚህ የአንዱ አካባቢ ባህላዊ መተዳደሪያ ደንብ ለሌላኛው አካባቢ የጋራ መተዳደሪያ መሆን አይችልም፡፡ ስለ ኦሮሞ ብሔረሰብ ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት በተጨባጭ ለመናገር የሁሉም አካባቢዎች ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓቶች በደንብ ተጠንተው አንድነታቸውና ልዩነታቸው በሚገባ መለየትና ለዘመናዊ የፍትህ ስርዓት የሚውሉበት ሁኔታ መመቻቸት ያለበት ይመስለኛል፡፡

በኦሮሚያ ክልል ውስጥ ከሚገኙት ዞኖች ውስጥ አንዱ የባሌ ዞን ነው፡፡ የባሌ ኦሮሞ ማህበረሰብ በርካታ ማህበራዊና ባህላዊ እሴቶች አሉት፡፡ ከማህበረሰቡ መንፈሳዊ ባህሎች ውስጥ በተለያዩ ምክንያቶች በግለሰብ፣ በቡድንና በጎሳ ደረጃ የሚከሰቱ ግጭቶችን ለመፍታት የሚጠቀሙባቸው ዘዴዎች ተጠቃሽ ናቸው፡፡ እነዚህን ባህላዊ የግጭት መፍቻ ዘዴዎችና ስርዓቶች ማጥናት የማህበረሰቡን አኗኗር፣ ፍልስፍናና ባህላዊ ጥበባት ለመረዳት ያግዛል፡፡ ሆኖም በዚህ ዐብይ ባህላዊ ጉዳይ ላይ ብዙ ጥናቶች አልተሰሩም፡፡ በባሌ ኦሮሞ ማህበረሰብ ላይ የተሰሩ ጥቂት ጥናቶች ቢኖሩም፣ የብዙዎቹ ትኩረት በማህበረሰቡ ስነቃል ላይ ነው፡፡ በማህበረሰቡ ውስጥ የሚከሰቱ ማህበራዊና ግላዊ ግጭቶችን ለመቆጣጠርና ለመፍታት የሚያገለግሉ ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓቶች በወጉ አልተጠኑም፡፡ ይህ ጥናት የባሌ ኦሮሞ በተለያየ ምክንያት የሚከሰቱ ግጭቶችን ለመፍታት የሚጠቀምበትን ባህላዊ የግጭት መፍቻ ስርዓት የሚያሳይ ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ ያለውን ክፍተት ለመሙላት ይረዳል፡፡

ጥናቱ በሰባት ምዕራፎች ተደራጅቶ የቀረበ ሲሆን አደረጃጀቱም እንደሚከተለው ነው፦ ምዕራፍ አንድ መግቢያ ሲሆን በውስጡም የጥናቱን ዳራ፣ የጥናቱን አነሳሽ ምክንያት፣ የጥናቱን አላማ፣ የጥናቱን ጥያቄ፣ የጥናቱን አስፈላጊነት፣ የጥናቱን ወሰን፣ የጥናቱን ዘዴ፣ የመረጃ አሰባሰብ፣ የናሙና አመራረጥ፣ የመረጃ ምንጮች፣ የመስክ ስራ ሒደት፣ በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች፣ የተወሰዱ መፍትሄዎች እና ጥሩ የመስክ ተሞክሮውን ይዟል፡፡ ምዕራፍ ሁለት ጥናቱ የተካሄደበትን አካባቢ አጠቃላይ ገፅታ የሚያሳይ ነው፡፡ በዚህ ምዕራፍ መልክዓምድራዊ አቀማመጥ፣ የሕዝብ ብዛት መተዳደሪያ፣ ቋንቋና እምነት፣ ጋብቻ፣ የዘር ሀረግና አሰፋፈር፣ የአካባቢው ስያሜ ኬትመጣ፣ መስህብነት ያላቸው ቦታዎችና ለጥናቱ የተመረጡ ወረዳዎች ትውውቅን የያዘ ነው፡፡

ምዕራፍ ሶስት የንድፈ ሃሳብ መሰረትና የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ሲሆን በውስጡም የግጭት ብያኔ፣ የግጭት እሳቤ፣ የግጭት መንስኤ፣ የግጭት አይነቶች፣ የግጭት አፈታት ዘዴዎች ከመስኩ ምሁራን አንፃር፣ ከአለምና ከአህጉር አቀፍ ድርጅቶች አንፃርና ከኢትዮጵያ የህግ ሰነዶች አንፃር የሚሉ የግጭት ንድፈ ሃሳባዊ ዳራዎች ቀርበዋል፡፡

ምዕራፍ አራት የባሌ ኦሮሞ ማህበረሰብን ባህላዊ የግጭት አፈታት የሚመለከት ሲሆን በውስጡም የሴረ ጉማን ምንነትና ታሪካዊ ዳራ፣ የጉማ አይነቶችና የባሌ ኦሮሞዎች ባህላዊ የግጭት መፍቻን ተቋማትን አካቷል፡፡ ምዕራፍ አምስት የባሌ ኦሮሞዎችን ባህላዊ የግድያ ግጭት አፈታት የሚቃኝ ነው፡፡ በውስጡም የግድያ ግጭት መነሻ ምክንያቶች፣ የግድያ አይነቶች፣ ለግድያ ግጭት የሚከፈለው ጉማ፣ የግድያ ግጭት የሚፈታበት ባህላዊ ተቋም፣ የግድያ ግጭት መፍቻ ተቋም ለማህበረሰቡ የሚሰጠው ፋይዳ፣ ማህበረሰቡ ለግድያ ግጭት ያለው አመለካከት፣ ባህላዊ የግድያ ግጭት አፈታት አውዳዊ ክዋኔን በንዑሳን ርዕስነት ይዟል፡፡

ምዕራፍ ስድስት ስነቃል በባህላዊ ግጭት አፈታት ስርዓት ያለውን ሚና የሚመለከት ሲሆን በውስጡም ምሳሌያዊ አነጋገር፣ አፈታሪክና ተረት ያላቸውን ሚና ይመለከታል፡፡ በምዕራፍ ሰባት ማጠቃለያና ይሁንታዎች ቀርበዋል፡፡ በመጨረሻም ዋቢ መፃህፍትንና የተለያዩ አባሪዎችን አካቷል፡፡

## 1.1. የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ የባሌ ኦሮሞ አባላት እርስ በእርስም ሆነ ከሌሎች ህዝቦች ጋር በሚያደርጉት ግንኙነት የሚፈጠሩ ግጭቶች የሚፈቱበትን ባህላዊ ስርዓት ማሳየት ነው፡፡

የጥናቱ ንዑሳን ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፦

1.በማህበረሰቡ ውስጥ የሚታዩ አበይት የግጭት ዓይነቶችን እና የግጭቶቹን መንስኤ መግለፅ፤

2.የማህበረሰቡን ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓቶችና አውዳዊ ክዋኔያቸውን መመርመር፤

3. ባህላዊ የግጭት መፍቻ ተቋማትን እና የደነገጓቸውን አበይት የግጭት መፍቻ ደንቦችና ህጎች መግለፅ፤

4. የባሌ ኦሮሞ ማህበረሰብ ውስጣዊና ውጫዊ ግጭቶችን ለመፍታት የሚጠቀሟቸውን ዘዴዎች መግለጽ፤

5. በማህበረሰቡ ውስጥ የሚከሰቱ ግጭቶችን ለመፍታት ስነቃል የሚጫወተውን ሚና መተንተን፤

### 1.2. የጥናቱ ጥያቄዎች

ከላይ ከተጠቀሱት አላማዎች ከግብ ለማድረስ በጥናቱ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ ተሞክሯል ::

1. የባሌ ኦሮሞ አባላት ውስጣዊና ውጫዊ ግጭቶችን የሚፈቱት እንዴት ነው?
2. በማህበረሰቡ ውስጥ የሚታዩ አበይት የግጭት አይነቶችና ምክንያቶች ምንድን ናቸው?
3. የማህበረሰቡ ባህላዊ የግጭት አፈታት ክዋኔ ምን ይመስላል?
4. በባህላዊ የግጭት መፍቻ ተቋማቱ የተደነገጉ አበይት የግጭት መፍቻ ደንቦችና ህጎች ምን ምን ናቸው? አፈፃፀማቸውስ ምን ይመስላል?
5. በማህበረሰቡ ውስጥ የሚከሰቱ ግጭቶችን ለመፍታት ስነቃል ያለው ሚና ምንድን ነው?

### 1.3. የጥናቱ አስፈላጊነት

ጥናቱ የባሌ ኦሮሞ ማህበረሰብ በተለያዩ አጋጣሚዎች የሚገባባቸውን ማህበራዊና ግላዊ ግጭቶች ለመፍታት የሚጠቀምባቸው ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴዎች ለማወቅ ይጠቅማል። ከዚህም ባሻገር ማህበረሰቡ ግጭትና የግጭት መፍትሔዎችን በተመለከተ ያለውን እውቀትና አመለካከት በማጥናት ለዘመናዊው የፍትህ ስርዓት የሚውልበትን ሁኔታ ለማሳየት ይጠቅማል።

በአካባቢው የሚሰሩ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ በተለይ በፍትህ፣ በሰላምና ደህንነት፣ በተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ዙሪያ የሚሰሩ ድርጅቶች ህብረተሰቡን በማስተባበር አላማቸውን ከግብ ለማድረስ የማህበረሰቡን ባህል፣ ጥበብና ፍልስፍና እንዲያውቁ ይረዳል።

ባህላዊ የግጭት መፍቻ ተቋማት በማህረሰቡ ውስጥ የሚከሰቱ ግጭቶችን ለመፍታት ከፍተኛ ሚና አላቸው፡፡ እነዚህ ተቋማት እንደ ግጭቱ አይነት፣ ባህርይና መጠን የሚደነግጉት የራሳቸው የሆነ ደንብ አላቸው፡፡ ይህ ጥናት የማህበረሰቡን የግጭት መፍቻ ደንቦች ለዘመናዊ ህግ አርቃቂዎች ባህልን መሰረት ያደረገ ማህበረሰቡን ያገናዘበ ህግ እንዲያረቁ መነሻ ይሆናል፡፡

ከሌሎች ማህበረሰቦች ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴ ጋር በማነፃፀር ጥናት ለማካሄድ ሆነ ስለአካባቢው ማህበረሰብ የአኗኗር ዘይቤ ማወቅ ለሚፈልጉ ተመራማሪዎች በመረጃ ምንጭነት ያገለግላል፡፡

ለተከታይ ጥናትም መነሻ ሊሆን ይችላል፡፡

### 1.4. የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት ከቦታ አንፃር በሁለት የባሌ ዞን ወረዳዎች ላይ ብቻ ያተኩራል፡፡ እነዚህም ወረዳዎች ጎባና ሲናና ናቸው፡፡ በማህበረሰቡ ውስጥ በተለያዩ ምክንያቶች የሚከሰቱ ግጭቶችን ለመፍታት ባህላዊ የግጭት መፍቻ ዘዴዎችና ዘመናዊ የህግ ስርዓት አገልግሎት ላይ ይውላሉ፡፡ የዚህ ጥናት ትኩረት ግን ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት (በተለይ የግድያ ግጭት) ላይ ብቻ የተወሰነ ነው፡፡

### 1.5. የጥናቱ ዘዴ

ይህ ጥናት ከባሌ ኦሮሞ ማህበራዊ፣ ባህላዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ህይወት ጋር የሚያያዙ ጉዳዮችን ይዳስሳል ፡፡ በተለይም በማህበረሰብ ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት ላይ ያተኩራል፡፡ ለዚህም ገላጭ የምርምር ዘዴ (Descriptive Study) መርጫለሁ፡፡ ይህ ዘዴ ነባራዊ ሁነቶች ያላቸውን ባህርይ በመለየት ለመግለፅ የሚስችል ዘዴ መሆኑን (Koul: 2006: 432) ይገልፃሉ፡፡ በጥናቱ ወቅት የሚሰበሰቡ መረጃዎችን አውዳዊ ትርጓሜ ለማሳየት ደግሞ የይዘት ትንተና (Content analysis) ዘዴን ተጠቅሜያለሁ፡፡ ይህ ዘዴ በገለፃ የቀረቡ መረጃዎች የቀረቡበትን አውዳዊ ትርጓሜ ለማየት የሚጠቅም ዘዴ መሆኑን (Miller and Brewer 2003:43) ይገልፃሉ፡፡

በፎክሎር ጥናት ከመስክ መረጃን ለመሰብሰብ የሚረዱ የተለያዩ ዘዴዎች አሉ (Kenneth Goldstine 1964፣ Mike and Cook 2007፣ ፈቃደ 1991 እ.ኢ.አ)፡፡ በዚህ ጥናት የእነዚህን

ምሁራን ስራዎች መሰረት በማድረግ ምልከታ፣ ቃለመጠይቅ እና የተተኳረ ቡድን ውይይት ዘዴዎችን በመጠቀም ለጥናቱ አስፈላጊ መረጃዎችን መሰብሰብ ተችሏል። መረጃዎቹም በቪዲዮ፣ በፎቶና በድምፀ-መቅረፅ ተቀርጸዋል።

ምልከታ (Observation)

ምልከታ ሁኔታውን በቀጥታ በማየት፣ በመስማት ወይም በሳይንሳዊ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች በመጠቀም መረጃ ለመሰብሰብ የሚያስችል ዘዴ መሆኑን (Goldstine 1964፣77) ይገልፃል። እኔም ለጥናቱ በተመረጡት አካባቢዎች በመገኘት ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓቱን በአውድ ውስጥ ተመልክቻለሁ። በዚህ መሰረት የባህላዊ ግጭት አፈታቱን ክዋኔ፣ የሀገር ሽማግሌዎችንና ግጭት ውስጥ የገቡትን ወገኖች ተግባርና ሚና፣ የግጭት አፈታት ስርዓቱ የሚከወንበትን አውድ ወዘተ. ለመመልከት ችያለሁ።

በፎክሎር የመረጃ አሰባሰብ ወቅት መረጃ ሰብሳቢው ተፈጥሮዓዊ (Natural)፣ አርቲፊሻል (Artificial) እና ቅንብር ተፈጥሯዊ (induced natural) የሚባሉ መቼቶችን ተጠቅሞ መረጃ መሰበስብ እንደሚችል (Goldstine፣ 1964፤ 80-90 እና ፈቃደ 1991ዓ.ም 122-123) ያስረዳሉ።በመስክ ቆይታዬ የግድያ ግጭት ባህላዊ አፈታት ስርዓት ክዋኔ ከ"ተፈጥሮአዊ" መቼት ማግኘት አልቻልኩም። ስለዚህ በተፈጥሮአዊ መቼቱ ያልተገኘውን ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት ክዋኔ በጎባ ወረዳ ፋሲል ሃንጋሶ ገበሬ ቀበሌ ማህበር ግንቦት 4፣ 2003 ዓ.ም "ቅንብር ተፈጥሮአዊ መቼት" በማዘጋጀትና በስርዓቱ በመሳተፍ መመልከት ችያለሁ።

ቃለመጠይቅ ( Interview )

ቃለመጠይቅ ሰዎች ስለ አንድ ርዕሰ ጉዳይ የሚያውቋቸውን የተለያዩ ጉዳዮች ጥያቄዎችን በመጠየቅ መረጃ ለመሰብሰብ የሚያስችል ዘዴ ነው (Goldstine 1964፣ 77-78፤ ፈቃደ 1991ዓ.ም፣ 90-91)። የምሁራኖቹን ስራዎች መሰረት በማድረግ በማህበረሰቡ ውስጥ ስለሚከሰቱት ግጭቶች አይነት፣ የግጭት መንስኤ ስለሆኑት ጉዳዮች፣ ስለባህላዊ የግጭት መፍቻ ተቋማቱ ወዘተ. የተለያዩ ጥያቄዎችን ለቁልፍ መረጃ አቀባዮች በማቅረብ መረጃ ተሰብስቧል። የቃለመጠይቅ አይነቶች /highly structured, semi structured and unstructured/ ናቸው (Mike and cook 2007)። ማህበረሰቡ ስለግጭት ያለው እሳቤ፣ ለግጭት የሚሰጠው ግምት፣ ግጭትን ለመፍታት ስለደነገጋቸው ደንቦች፣ ስለሚሰጠው ፍርድ፣

ቅጣት ወዘተ. semi structural እና unstructured የተባሉ የቃለመጠይቅ አይነቶችን በመጠቀም መረጃ ተሰብስቧል።( ቃለመጠይቅ የተደረገባቸው ቀናት እና ቦታዎችን የመስክ ስራ ሂደት ይመለከቷል።)

የተተኳሪ ቡድን ውይይት (Focus Group Discussion)

የተተኳሪ ቡድን ውይይት ከመስክ መረጃ ለመሰብሰብ ተመራጭ ዘዴ ነው(Mike and cook 2007)። በዚህ ጥናት በምልከታና በቃለ መጠይቅ ያልተመለሱ ጉዳዮች፣ የተለያየ አስተያየት የተገኙባቸው ምላሾችና በቃለ መጠይቅ ወቅት ቁልፍ መረጃ አቀባዮቹ እርግጠኛ ያልሆኑባቸውን ጉዳዮች ሚያዝያ 27፣ 2003 በሲናና እና ሚያዝያ 28፣ 2003 ዓ.ም በጎባ ወረዳ የተተኳሪ ቡድን ውይይት በማዘጋጀት መረጃ ተሰብስቧል።

### 1.5.1 የመረጃ ምንጮች

ይህ ጥናት ስለተካሄደበት አካባቢ ታሪክ፣ እምነት፣ የዘር ሀረግ፣ እንዲሁም የግድያ ግጭት አፈታት ስርዓት፤ በአካባቢው ማህበረሰብ እውቀት አላቸው የተባሉ የሀገር ሽማግሌዎች፣ የሃይማኖት አባቶች፣ የመንግስት ስራ ሀላፊዎች፣ ነጋዴዎች፣ ገበሬዎች፣ የቤት እመቤቶች ወዘተ. በጥናቱ ተሳታፊዎች ነበሩ።

በጥናቱ የመረጃ ምንጮች የተመረጡት በአካባቢው ባላቸው የሽምግልና ልምድ፣ ስለአካባቢው /ስለማህበረሰቡ/ ባህልና ታሪክ ባላቸው እውቀት፣ ባላቸው ጥሩ ስነምግባር እና ማህበራዊ ተሳትፎ ነው። በዚህ መሰረት እድሜያቸው ከ27-113 የሆኑ የሀገር ሽማግሌዎች፣ የሃይማኖት አባቶች፣ ገበሬዎች እና ነጋዴዎች በጥናቱ ተሳትፈዋል። በመንግስት መስሪያ ቤቶች ውስጥ የሚሰሩት ሰራተኞች ደግሞ የተመረጡት ለርዕሰ ጉዳዩ ካላቸው ቅርበት አንፃር ነው። በዚህ መሰረት የዞኑ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ፣ የወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤቶች፣ የወረዳዎች እና የከተማዎች ፖሊስ፣ የወረዳ ፍርድ ቤቶች፣ የወረዳ ሰላምና ደህንነት ቢሮዎች እና የዞን ስታስቲክስ ቢሮ ለጥናቱ የመረጃ ምንጭ በመሆን አገልግለዋል። በአጠቃላይ ጥናቱ የተካሄደው የዞኑ ወረዳዎች ውስጥ የሚገኙ 50 ሰዎች የጥናቱ የመረጃ ምንጮች ነበሩ። ከነዚህ ውስጥ 15 ቁልፍ የመረጃ ምንጭ በመሆን አገልግለዋል።

### 1.5.2. የመስክ ስራ ሂደት

ለዚህ ጥናት የሚያስፈልጉ መረጃዎች በሁለት ምዕራፎች ተከፍለው የተሰበሰቡ ናቸው፡፡ የመጀመሪያው ምዕራፍ ቅድመ መስክ ተግባር ነው፡፡ አንድ መስከኛ ወደ መረጠው አካባቢ ከመሄዱ በፊት ስለጥናቱ ርዕስ እና ጥናቱ ስለሚካሄድበት አካባቢ ጥናት ያደረጉ ሰዎችን ማነጋገር የመስክ ስራውን ቀና እንደሚያደርግለት እሙን ነው፡፡ ማንኛውም መስከኛ በባህሉ ወደዳበረ አካባቢ በመሄድ ያለምንም ጥርጥር ጠቃሚ የሆነ መረጃ ይዞ ሊመለስ ይችላል ( Mac Donald በ Dorson ውስጥ 1972፣407)፡፡ ይሁን እንጂ የተጠናከረ የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ የሚጀምረው በቤተ መጻህፍት ወንበር ላይ ተቀምጦ መጻህፍትን በማንበብና አርካይቮችን በማገላበጥ እንደሆነ ያስረዳል፡፡ ከዚህ በመነሳት መስከኛው ወደ መስክ ከመሔዱ በፊት ከርዕሱ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ጉዳዮች፣ ስለሚሄድበት አካባቢ ማህበረሰብ ባህል፣ እንዲሁም በመስክ ቆይታው ማከናወን ስለሚገባው ጉዳዩች ግንዛቤ ለማግኘት የቤተ መጻህፍት ንባብ የሚጠበቅበት መሆኑን እንረዳለን፡፡

በዚህ መሰረት ከየካቲት 1፣ 2003 እስከ መጋቢት 30፣ 2003 ዓ.ም ድረስ ከቤተ መፃህፍት እና ከድህረ ገፅ ስለ ግጭት ንድፈ ሀሳብ የተፃፉ መፃህፍት፣ ጆርናሎች፣ ጥንታዊ ጽሁፎች እና የጉባኤ ህትመቶችን አንብቤያለሁ፡፡ የቤተ መጻህፍት ምርምሩ በዋነኝነት የተካሔደው በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ዋናው ግቢ (6 ኪሎ) በሚገኙት የኬኔዲ፣ የኢትዮጵያ ጥናት ተቋም ( IES)፣ የቋንቋዎች ጥናት ተቋም (ILS)፣ የህግ የስነ-ሰብዕ እና የስነ-ማህበረሰብ (SOSA) ቤተ መፃህፍት ናቸው፡፡ ለንባብ የተመረጡት መጻህፍት ከግጭት እና ከፎክሎር የመስክ ምርምር ጋር ተያያዥነት ያላቸው ናቸው፡፡ ከእነዚህ ምንጮች የተውጣጡት እና ከጥናቴ ጋር ተያያዥነት ያላቸው መረጃዎች በተለይ በምዕራፍ አንድ እና በምዕራፍ ሶስት ተካተዋል፡፡

ወደ መስክ ከመሔዴ በፊት ማከናወን የሚጠበቅብኝን ተግባራት ጨርሼ ለመስክ ስራዬ በጣም የረዳኝን የትብብር ደብዳቤ ከትምህርት ክፍሉ አፅፌ ቅዳሜ ሚያዝያ 8፣ 2003 ዓ.ም ወደ መስክ ተንዝኩ፡፡ በዚህም መሰርት ከሚያዝያ 8፣ 2003 ዓ.ም እስከ ግንቦት 8፣2003 ዓ.ም በአጠቃላይ ለአንድ ወር ያህል ለጥናት በመረጥኩት አካባቢ በመቆየት ለጥናቱ የሚያስፈልገውን መረጃ ከቀዳማይ ምንጮች ሰብስቤያለሁ፡፡

የመስክ ስራዬን የጀመርኩት ቅዳሜ ማታ ለጥናት የተመረጠው አካባቢ ደርሼ በማግስቱ ነው፡፡ መጀመሪያ ለጥናት የመረጥኩት አካባቢ በደረስኩ ማግስት እለቱ እሁድ ስለሆነ እሁድ ደግሞ

የስራ ቀን ባለመሆኑ በጉዞ የደከመ ሰውነቴን ማሳረፍ ነበር ያሰብኩት፡፡ ይሁን እንጂ እለቱ በኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን የሆሳዕና በዓል የሚከበርበት እለት መሆኑ ሲነገረኝ ሀሳቤን ሰርዤ በጥዋት በዓለወልድ ቤተክርስቲያን ሔድኩ፡፡ በቦታውም ብዙ አባቶችን ማግኘት ችያለሁ፡፡ የማውቃቸውንም ከቤተክርስቲያን መልስ ስለጥናቴ አዋይቻቸው ጥሩ መረጃ ማግኘት ችያለሁ፡፡

ከሰኞ እስከ ሀሙስ ( ከሚያዝያ 10 እስከ 13፣ 2003 ዓ.ም ) በሰሞኑ ህማማቱ ካረፍኩበት የጎባ ከተማ 15 ኪ.ሜ ርቀት ላይ ወደምትገኘው ከተማ ሮቤ በመመላለስ ከዞኑ አስተዳደር እና ከዞኑ የባህልና ቱሪዝም ቢሮ ሀላፊዎች ጋር በመገናኘት ስለጥናቱ አላማና ስለጥናቱ ጠቀሜታ በመነጋገር ለጥናቱ ወደ ተመረጡት ወረዳዎች በማቅናት መረጃ ለመሰብሰብ የሚያስችሉ ሁኔታዎችን አመቻችቻለሁ፡፡

ቀጣዩን ሳምንት (ከሚያዝያ 17 - ሚያዝያ 21፣2003 ዓ.ም) ከዞኑ አስተዳደር እና የባህልና ቱሪዝም ቢሮ የተፃፉልኝን ደብዳቤዎች በመያዝ፣ ለጥናቱ ወደ መረጥኳቸው ወረዳዎች በመሄድ፣ ከየወረዳው አስተዳደር እና ከየወረዳው የባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤቶች ሀላፊዎችና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመገናኘት፣ ስለጥናቴ አላማ እና ጠቀሜታ በግልጽ በመነጋገር ጥናቱን ማካሄድ የምችልበትን ሁኔታ አመቻችቻለሁ፡፡

ከዚያም ከየወረዳዎቹ የባህልና ቱሪዝም ቢሮ ሀላፊዎች ጋር በመተባበር ስለማህበረሰቡ፣ ስለአካባቢው ታሪክ እና ባህል በደንብ ያውቃሉ የሚባሉ፣ ከዚህ በፊት የእርቅ ስርዓትን በማስፈጸም የሚታወቁ እና በማህበረሰቡ የተከበሩ የሀገር ሽማግሌዎችን፣ የሃይማኖት አባቶችን እና ለርዕሱ ጉዳዩ ቅርበት አላቸው የሚባሉ ሌሎች ሰዎችን የመለየት፤ የመፈለግ እና የመተዋወቅ ስራ ሰራሁ፡፡ በመቀጠል ከተመረጡ እና ከተዋወኩአቸው መረጃ አቀባዮቼ ጋር በተለያዩ ቀናት እየተገናኘሁ ስለ አካባቢው፤ ስለማህበረሰቡ ታሪክ፣ ባህል፣ እምነት፣እንዲሁም ስለማህበረሰቡ ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት መረጃዎችን መሰብሰብ ጀመርኩ፡፡

ሚያዝያ 27 እና ሚያዝያ 28፣ 2003ዓ.ም በየወረዳዎቹ የተተኳሪ ቡድን ውይይት አዘጋጀሁ፡፡ በዚያውም ቅንብር ተፈጥሯዊ መቼት ማዘጋጀት እንዳሰብኩ ለየወረዳዎቹ የባህልና ቱሪዝም ቢሮ ሀላፊዎች እና ለሀገር ሽማግሌዎች በማሳወቅ ፈቃዳቸውን አገኘሁ፡፡ ለዝግጅቱ የሚያስፈልገውን ነገር ጠይቄ ቀኑ ለማክሰኞ ግንቦት 2፣2003 ዓ.ም ተወሰነ፡፡ ነገር ግን ቅንብር ተፈጥሯዊ መቼት ሊዘጋጅ በታሰበበት ቀን ለህዳሴው ግድብ የድጋፍ ሰልፍ እንዲደረግ ከወረዳው

አስተዳደር በመታወጁ ቀኑ ለሀሙስ ግንቦት 4፣2003 ዓ.ም ተሸጋግሮ በዚህ እለት የቅንብር ተፈጥሯዊ መቼቱን በማዘጋጀት መረጃዎችን ለመሰብሰብ ችያለሁ፡፡

ከመስክ ቆይታዬም ጥሩ ተሞክሮ አግኝቻለሁ፡፡አንዳንድ የመስክ ምርምር ያካሄዱ ምሁራን በስራዎቻቸው እንደሚገልፁት መስክ ወጥተው ከመረጃ አቀባዮች መረጃን ለመሰብሰብ ለመረጃ አቀባዮቹ ገንዘብ፣ ስጦታ፣ ወዘተ. ይሰጣሉ፡፡ ይህም ከመረጃ አቀባዩቻቸው የሚፈልጉትን መረጃ ለማግኘት እንደጠቀማቸው ያስረዳሉ፡፡ ነገር ግን ይህ ዘዴ ሁል ጊዜ ተመራጭ ነው ማለት አይቻልም፡፡ ሰዎች ለገንዘብ (ለጥቅም) ሲሉ በደንብ ስለማያውቁት ነገር የተሳሳተ መረጃ ሊሰጡ ይችላሉ፡፡ ስለጉዳዩ ያውቃሉ ብለው በሀሰት ወዳጅ ዘመዳቸውንም ሊጠቁሙ ይችላሉ፡፡ ከዚህም በላይ ስለጉዳዩ እንኳ ቢያውቁ ሁሌ የለመዱትን ጥቅም ይፈልጋሉ፡፡ እኔ በዚህ ጥናት ከመረጃ አቀባዮች መረጃን ለማግኘት የተጠቀምኩት ‹‹ሰውን በሰው›› በመያዝ ነው፡፡ በዚህ መሰረት የወረዳ እና የዞን ሀላፊዎችን በቅድሚያ የትብብር ደብዳቤ በማሳየት፤ በመቀጠል በቅርብ በሚያውቋቸው (በጓደኞቻቸው) በመሄድ ፈጣን ምላሽ ማግኘት ችያለሁ፡፡

ሌላው የአካባቢውን ማህበረሰብ ወግ ልማድ ጠንቅቆ ማወቅ በጣም ጠቃሚ እንደሆነ ተረድቻለሁ፡፡ አንድ ቀን ስለ ባህላዊ የግድያ ግጭት አፈታት በጣም ያውቃሉ የተባሉ ሽማግሌ ጎባ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ እንደሚገኙ ተነግሮኝ ስገሰግስ ቢሮ ደረስኩ ሰላምታ ሰጥቼ ቁጭ እንዳልኩ ብዙም ሳናወራ የምሳ ሰዓት ደረሰ ከቢሮ ወጣን፡፡ በዚህ ጊዜ ቀደም ብዬ በመውጣት የሽማግሌውን ፈረስ ከታሰረብ ፈትቼ ይገፍላቸው መጣሁ፡፡ ሽማግሌው በጣም ነበር የተገረሙት፡ ፡ ከአዲስ አበባ ለጥናት የመጣ ሰው በማህበረሰቡ እንደሚደረገው የሽማግሌን ፈረስ ፈትቶ ያመጣል ብለው አልገመቱም መሰል በምርቃት አምበሸበሹኝ፡፡ ከዛማ ቁልፍ መረጃ አቀባይ ሆኑኝ፡፡የትኛውም ማህበረሰብ ባህሉን የሚያከብርን ሰው ያከብራልና ጥንቃቄ ማድረግ ወሳኝ ነው፡፡

## 1.6. በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሔዎች

ይህን ጥናት በማካሔድበት ወቅት ብዙ ችግሮች ገጥመውኝ ነበር፡፡ ከገጠሙኝ ችግሮች ውስጥ አብዛኞዎቹ ከወቅት ጋር የተያያዙ ናቸው፡፡ ከነዚህ ውስጥ አንዱ ለመስክ ስራ ወደ ጥናቱ አካባቢ የሄድኩበት ወቅት የፋሲካ በዓል ሰሞን መሆኑ ነው፡፡ በዚህ ምክንያትም በሰሞነ ህማማት ውስጥ ወደ ዞን እና ወደ ወረዳዎች የወረዳ እና የባህልና ቱሪዝም ቢሮዎች ስሄድ ሀላፊዎቹን ያለማግኘት፣ ከበዓሉ በኋላ የቢሮ ሀላፊዎች አግኝቼ ስራዬን ለመጀመር ስነሳ ቁልፍ

መረጃ አቀባዮች በበዓል ጥሪ በመጨናነቃቸው እና አክሩይ ወደ ሩቅ ቦታ በመሄዳቸው ምክንያት ላገኛቸው አልቻልኩም ነበር፡፡ ሌላው ከወቅቱ (ከፋሲካ በዓል ጋር) የተያያዘው ችግር ለቅንብር ተፈጥሯዊ መቼት ዝግጅት የሚያስፈልጉት ነገሮች ዋጋ ጣሪያ መድረስ ነው፡፡ በተለይ የበግ እና የቂቤ ዋጋ ከወትሮው በእጥፍ መጨመር ትልቅ ችግር ነበር፡፡

ሌላው ችግር የተፈጠረው በጣም ዘግይቶ በመጣው ክረምት ምክንያት ነው፡፡ የአብዛኛው የአካባቢው ነዋሪ መተዳደሪያ እርሻ ነው፡፡ እርሻው ደግሞ በዝናብ ላይ የተመሰረተ በመሆኑ በዝናቡ መምጣት ምክንያት ቁልፍ መረጃ አቀባዮቼ በእርሻ ተጠምደው ነበር፡፡ እርሻውን ትቶ ለቃለ መጠይቅም ሆነ ለቅንብር ተፈጥሯዊ መቼት የሚረዳኝ ሰው ማግኘት በጣም ከባድ ነበር፡፡ የክረምቱ መምጣት የፈጠረው ችግር የመረጃ አቀባዮቼ በእርሻ ስራ እንዲጠመዱ ማድረጉ ብቻ አልነበረም፤ የእርሻ ስራቸውን አስተጓጉለው እንዳገኛቸው የፈቀዱ ሰዎች በቀጠሩኝ ቀን እንዲያረፍዱ እና እንዲቀሩ አድርጓል፡፡

ዩኒቨርሲቲው ለጥናቱ የመደበው ገንዘብ ማነስ ከፋሲካ በዓል ጋር ሲገናኝ ነገሮችን በጣም አስቸጋሪ አድርጓቸው ነበር፡፡ ስለባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓቱ ያውቃሉ የተባሉት የሀገር ሽማግሌዎች በጣም በተራራቁ ገበሬ ቀበሌ ማህበራት ውስጥ መኖር እና ቀበሌ ገበሬ ማህበራቱ የሚገኙበት ቦታ ዳገታማ፣ በደን የተሸፈነ፤ ሌላ መንገድ የሌለው መሆን፣ በቅንብር ተፈጥሯዊ መቼት ዝግጅት ላይ የተገኙት ሰዎች እምነት የተለያየ መሆን የምግብ ዝግጅቱን ሁኔታ በጣም አስቸጋሪ አድርጎት ነበር፡፡

ለቅንብር ተፈጥሯዊ መቼት ዝግጅት በስንት ችግር በተገኘው ቀን የህዳሴው ግድብ ድጋፍ ሰላማዊ ሰልፍ እንዲደረግ ከወረዳው መታዘዙ ሌላ ችግር ነበር፡፡ ለቅንብር ተፈጥሯዊ መቼት ዝግጅቱ የተመረጠው የፋሲል አንገሶ ቀበሌ ገበሬ ማህበር በጣም ቀዝቃዛ መሆን ለወትሮ በእርግጠኝነት ሙሉ ቀን የምጠቀምበት የመቅረጸ ድምጽና ምስል (Rechargeable battery) በቅዝቃዜው ምክንያት በግማሽ ቀን ማለቁ እና በአካባቢው መብራት አለመኖር የምስል ቀረፃውን አስተጓጉሎት ነበር፡፡

በሕማማት ሰሞን ላገኛቸው ያልቻልኳቸውን የቢሮ ሀላፊዎች ከመስሪያ ቤቱ ስልካቸውን በመቀበል ማንነቴን አስተዋውቄ የጥናቴን ዓላማ በማሳወቅ በቅርብ ያሉት ሰዎች ጉዳዬን እንዲፈፅሙልኝ አድርገዋል፡፡

የትምህርት ክፍሉ ለጥናቱ የመደበው ገንዘብ አንስተኛ መሆን ከፋሲካ በዓል ጋር በመገናኘቱ ምክንያት ለቅንብር ተፈጥሯዊ መቼት ዝግጅት እና በየቦታዋቹ መንቀሳቀሻ ገንዘብ እጥረት ገጥሞኝ ነበር፡፡ ይህንንም ችግር ከወረዳው ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ሀላፊዎች እና ከሀገር ሽማግሌዎቹ ጋር በግልጽ በመነጋገር ለቅንብር ተፈጥሯዊ መቼት ዝግጅት ታስቦ የነበረው የ4000 (አራት ሺህ) ብር ዝግጅት ሳይታጠፍ ወደ 3000 (ሶስት ሺህ) ብር ዝቅ እንዲል ማድረግ ችያለሁ፡፡ ለመጓጓዣ እና ለአንዳንድ ነገር የሚያስፈልጉ ወጪዎችን ደግሞ ከቤተሰቦቼ በመውሰድ ችግሩን ለመፍታት ችያለሁ፡፡ ስለባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓቱ ያውቃሉ የተባሉትንና በበዓሉ ምክንያት ላገኛቸው ያልቻልኳቸውን ሰዎች ከዳግማ ትንሳኤ በኋላ እቤታቸው ድረስ በመሄድ ማግኘትና ማነጋገር ችያለሁ፡፡

## 2. የባሌ አካባቢያዊና ማህበረ- ባህላዊ ዳራ

በዚህ ምዕራፍ የአካባቢውን ስያሜ አመጣጥ፣ የባሌ ዞንን መልካምድራዊአቀማመጥ፣ ብሔር፣ የህዝብ ብዛትና መተዳደሪያ፣ ቋንቋ፣ እምነት፣ ጋብቻ፣ የዘር ሀረግ እና ለጥናቱ የተመረጡት ወረዳዎችን አንዳንድ ገፅታ እንመለከታለን።

የአካባቢው "ባሌ" የሚለው ስያሜ ምን ማለት እንደሆነና እንዴት እንደተገኘ የሚገልፁ ሁለት መረጃዎች አሉ። አንደኛው መረጃ ዞኑ "ባሌ" የሚለውን ስያሜ ያገኘው ከእቴጌ ጣይቱ ንግግር እንደሆነ የሚገልጽ ነው። አፄ ሚኒሊክ ሀገር የማቅናት ዘመቻ እያካሄዱ በነበሩበት ወቅት[1] ባለቤታቸው ንግስት ጣይቱ በደቡብ ምስራቅ አቅጣጫ ጉብኝት ያደርጉ ነበር። በጉዟቸውም አየር ንብረቷ ያመረ (የተለያየ የአየር ፀባይ ያላት) የተለያዩ እፅዋት በብዛት የሚገኙባት፣ የተለያየ የመሬት አቀማመጥ ያላት ሀገር ላይ ይደርሳሉ። ንግስቲቱ በቦታው በጣም በመደሰት "ይህ ሀገር ለባሌ ይገባዋል፤ ባሌ ይህን ሀገር ሊገዛ ይገባዋል።" በማለት በቦታው ሲደነቁ የሰሙ የአካባቢው ነዋሪዎች። "ባሌ" በማለት ንግስቲቱ ንጉሱን የጠሩበትን ስያሜ ለአካባቢው ሰጡትና ከዛ ጊዜ ጀምሮ ባሌ በመባል ይታወቃል። (ወ/ሮ ሰናይት አዲሱ፣ አቶ አለሙ ደስታ፣ ቃለመጠይቅ፣ ሚያዝያ 20፣2003፣ ጎባ)

ሁለተኛው መረጃ አካባቢው ስያሜዉን ያገኘው በአካባቢ ከነበሩ እስላማዊ የሱልጣን መንግስታት ከአንዱ እንደሆነ የሚያስረዳ ነው። የአሁኑ የባሌ ዞን አካባቢ ባሊ፣ ሐዲያ፣ ደዋሮ፣ ዋጅ፣ ገንዝ፣ አራባብኒ፣ ሺርካ (ሲርካ) የሚባሉ እስላማዊ የሱልጣን መንግስታት ግዛት ነበር። የባሌ ዞን "ባሌ" የሚለውን መጠሪያ ያገኘው "ባሊ" ከሚባለውና የአሁኗ የባሌ ዞን የምትገኝበትን አካባቢ ያስተዳድር ከነበረው እስላማዊ የሱልጣን መንግስት ነው።

የባሊ ግዛት በአሁኗ የባሌ ዞን ውስጥ እንደነበር የሚያስረዱ ብዙ የጽሁፍ መረጃዎች አሉ። ምሳሌ አባ ባህሪ "[ኦሮሞዎች] በዓፄ ወናግሰገድ ዘመን በምዕራብ በኩል በባሊ ወሰን ገላና የሚባል የአገራቸውን ወንዝ አቋርጠው መጡ" ይላሉ (ብረሃኑና ታቦር 1990፣ 5)። በዚህ ጽሁፍ ውስጥ የተቋጠረውን መረጃ ትርጉም ለማወቅ ስለ ባሌ ምንነትና መገኛ ማወቅ ያስፈልጋል። ከላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው ባሊ በመካከለኛው ዘመን በአሁኗ የኢትዮጵያ

---

[1] ዓፄ ሚኒሊክ ሀገር ለማቅናት ወደ አርሲና ባሌ ከ1873-1879 ዓ ም ዘመቻ ማድረጋቸውን ባህሩ ዘውዴ፣ የኢትዮጵያ ታሪክ ከ1874 እስከ 1983፣አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ፣ 1999፣ገጽ 71- 72 ይመለከቷል።

ግዛት ከተነሱ የእስላም መንግስታት መካከል አንዷ ነበረች፡፡ ከአባ ባህሬ ሀሳብ የባሊ ግዛት በአሁኗ ባሌ ዞን ይገኝ እንደነበር እና ባሌ የኦሮሞ ህዝብም ጥንታዊ መኖሪያ (አጽመ ርስት) መሆኗን እንረዳለን፡፡

የመካከለኛው ዘመን የባሊ ግዛት በአብዛኛው የአሁኗን የባሌ ዞን መስተዳድርን የሚያካትት መሆኑን በማረጋገጥ ፕ/ር ሪቻርድ ፓንክረስትን ጠቅሰው ብረሃኑና ታቦር የሚከተለውን ሀሳብ አስቀምጠዋል፡፡

> በዓጼ ልብነድንግል ዘመን የባሊ ግዛት የአጼውአካል ነበረች.... ይህ ደግሞ ከሰሜኑ ክርስቲያን ግዛት ጋር የቅርብ ትስስር እንዲኖራት በማድረጉ በርካታ ዐብያተ ክርስቲያናት ታንፀዋል፡፡ ከነዚህ መካከል እስካሁን በጎባ ከተማ አካባቢ የሚታይ ከቋጥኝ ድንጋይ ተፈልፍሎ የተሰራው ቤተክርስቲያን አንዱ ነው (1993፣ 3)፡፡

ይህም ሀሳብ የአሁና የባሌ ዞን መስተዳድር የምትገኘው በመካከለኛው ዘመን የባሊ ግዛት በነበረው ቦታ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡ የባሌ ዞን "ባሌ" የሚለውን መጠሪያ ከጥንታዊው የባሊ ግዛት ነው ያገኘችው የሚለውንም ሃሳብ ተቀባይነት እንዲያገኝ ያደርገዋል፡፡

በባሌ ዞን ሰፍረውየሚገኙት ኦሮሞዎች የአርሲ ጎሳዎች እንደሆኑ ይናገራሉ፡፡ አርሲ ሲኮ እና መንዶ በተባሉ ሁለት የዘር ሀረጎች ይከፈላል፡፡ እስካሁን በአርሲ ኦሮሞ ላይ የተደረጉ ጥናቶች ከሁለቱ የአርሲ ቅርንጫፎች ሲኮ አንጋፋ መሆኑን ይገልፃሉ፡፡[2]

ሲኮ አምስት ንዑሳን ጎሳዎች አሉት፡፡ እነሱም ቡላላ፣ዋጨሌ፣ጃዊ፣ ዋጂ እና ኢላኒ ይባላሉ፡፡ በዞኑ በብዛት ሰፍረው የሚገኙት የመንዶ ጎሳዎች ስለሆኑ የመንዶ ጎሳን አሰፋፈር በስፋት እንመለከታለን፡፡ መንዶ በአብዛኛው ሰፍሮ የነበረውና የሚገኘው ከዋቤ ወንዝ ባሻገር ባሁኑ ባሌ ዞን ውስጥ ነው፡፡ ይሁን እንጂ በዋቤ ወንዝ ወዲህና ወዲያ ማዶ መንዶና ሲኮ ተቀላቅለው ይኖራሉ፡፡ መንዶ ሰባት አብይ ጎሳ ቅርንጫፎች አሉት፡፡ እነሱም ራያ፣ ሀዋጡ፣ ከደዋ፣ ወነማ፣ ኡታ፣ ዋዩ እና ቢልቱ ናቸው፡፡

የአርሲ ኦሮሞ በአሁኑ የመኖሪያ ግዛቱ የሰፈረው መቼ ነው? የአርሲ አዛውንቶች ለዚህ ጥያቄ የተረጋገጠ ምላሽ ባይኖራቸውም በግምት ከአርባ ትውልድ በፊት ጀምሮ በከከባቢው እንደነበሩ ይናገራሉ፡፡ የአንድ ትውልድ አማካይ እድሜ በሃያ አምስት ዓመት ከተወሰደ በአዛውንቶቹ

[2] የኦሮሚያ ባህልና ቱሪዝም ኮሚሽን፤ የኦሮሞታሪክ- እስከ አስራ ስድስተኛ መቶ ክፍለ ዘመን፣ 1996፣ ገጽ 133፡፡

የተጠቀሰው አርባ ትውልድ ወደ አስራ አንደኛው ክፍለ ዘመን ማብቂያ ይወስደናል፡፡ ሺህ ሁሴን ዘንድ ሃይማኖታዊ ጉዞ ማድረግ የተጀመረው በአስራ ሁለተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ውስጥ ነው በማለት ያቀረበው አስተያየት ከአዛውንቶቹ የቀረበውን መረጃ የሚያጠናክር ነው፡፡

ከሁለቱ ምንጮች ከተገኘው መረጃ በመነሳት የአርሲ ኦሮሞ በአሁኑ የሰፈራ አካባቢ ከአስራ ሁለተኛ መቶ ክፍለ ዘመን በፊት ጀምሮ እንደነበረ መገመት ይቻላል፡፡በአሁኑ አካባቢ በሰፈሩበት ወቅት የመንዶ ቅርንጫፍ ከዋቢ በስተምስራቅ የአሁኗን የባሌ ዞን ዋና የሰፈራ አካባቢ ሲያደርግ ሲኮ ደግሞ ዋቢን ተሻግሮ በኋላ ላይ ቡላላ ብሎ በሰየመው አካባቢ ሰፈሯል፡፡

ባሌ በኦሮሚያ ክልል ውስጥ ከሚገኙ አስራ ሰባት ዞኖች ውስጥ አንዱ ነው፡፡ ዞኑ 63,555 ስኩዌር ኪ.ሜ ስፋት ሲኖረው አስራ ሰባት ወረዳዎች አሉት፡፡ የዞኑ ከተማ ሮቤ ስትሆን በደቡባዊ ምስራቅ አቅጣጫ ከአዲስ አበባ 430 ኪ.ሜ ርቀት ላይ ትገኛለች፡፡ የባሌ ዞን በደቡብ አቅጣጫ ከጉጂ ዞን፣ በደቡብ ምስራቅ ከደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል፣ በሰሜን በምዕራብ ከምዕራብ አርሲ ዞን ፣ በምስራቅ ከሀረርጌ እና ከሱማሌ ክልል ጋር ድንበር ይጋራል (የኦሮሚያ ሚሊኒየም ፣ 2000፣ 8)፡፡

በክልሉ ከፍተኛው እና ዝቅተኛው ስፍራዎች በዚህ ዞን ይገኛሉ፡፡ በኦሮሚያ ክልል በአንደኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ፣ በኢትዮጵያ ደግሞ ከራስ ዳሸን ቀጥለው በሁለተኛ እና ሶስተኛ ደረጃ ላይ የሚገኙት የቱሉ ዲምቱ እና የባቱ ተራራዎች በዚህ ዞን ይገኛሉ፡፡ የቱሉ ዲምቱ ተራራ 4377 ሜትር ከፍታ ሲኖረው የባቱ ተራራ ደግሞ 4297 ሜትር ይረዝማል፡፡ በክልሉ በጣም ዝቅተኛ የሆነው ስፍራም በዚሁ ዞን በጎባ ወረዳ የሚገኝ ሲሆን ከባህር ጠለል በላይ 1500 ሜትር ከፍታ አለው(ጥቁም ስራ ገፅ 9)፡፡

ዞኑ በአራት መልካምድራዊ አካባቢዎች ይከፈላል፡፡ እነሱም ደጋ 'በዳ' (Baddaa) ከ2300-3200 ሜትር፣ ወይና ደጋ 'በደደሬ' (Baddadaree) ከ1500-2300 ሜትር፣ ቆላ 'ገሞጂ'(Gammojjii) ከ500-1500 ሜትር እና ውርጭ 'ዳሞታ' (Dhamota) ከ3200 በላይ ናቸው፡፡ በዞኑ ተጠቃሽ ከሆኑት የዋቤ ሸበሌ እና የወይብ ወንዞች በተጨማሪ ሻያና ተጎናን የመሳሰሉ በርካታ ወራጅ ወንዞች ይገኛሉ፡፡ እነዚህ ወንዞች በዞኑ ለሚገኙ ነዋሪዎች፣ የቤትና የዱር እንስሳት የህይወት መሰረት በመሆን ያገለግላሉ (Bale Mountains A Guidebook 2002)፡፡

በኢትዮጵያ ውስጥ በጥቅጥቅ ደንነቱ በሁለተኛ ደረጃ ላይ የሚገኘው የ'ሀረና ቡሉቅ' ጥቅጥቅ ደን በዚሁ ዞን ይገኛል፡፡ ከዚህ ደን በተጨማሪ በዞኑ <u>በጥብቅ</u> ደንነት የተመዘገቡና አጠቃላይ

ስፋታቸው 662,740 ሄክታር የሆነ አምስት ጥብቅ ደኖች አሉ፡፡ በእነዚህ ጥብቅና ጥቅጥቅ ደኖች ውስጥ ባህር ዛፍ፣ ፅድ፣ ዋርካ፣ ቀረሮ፣ ብሳና፣ ኮሶ፣ ወይራ፣ ዋንዛ የመሳሰሉት የዛፍ ዝርያዎች በብዛት ይገኛሉ፡፡ በነዚህ ደኖች ውስጥ የተለያዩ የዱር አራዊቶችም ይገኛሉ፡፡ ዞኑ የተለያዩ የመሬት አቀማመጦች አሉት፡፡ ከዚህም ውስጥ ሜዳማ 55.89%፣ ረባዳማ 30.75%፣ ሸለቋማ 0.41%፣ ተራራማ 12.94% ነው (Atlas of Bale zone 2004)::

በ1999ዓ.ም በተደረገው ሀገር አቀፍ የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ ስታስቲክሳዊ መረጃ መሰረት በባሌ ዞን የሚኖረው ህዝብ ብዛት 1,312,686 እንደሆነ ተገልጿል፡፡ ከዚህ ውስጥ 660,383 ወንዶች ሲሆኑ 652,303 ደግሞ ሴቶች ናቸው፡፡ በባሌ ዞን ውስጥ የተለያዩ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ይገኛሉ፡፡ እነሱም፡- ኦሮሞ፣ አማራ፣ ሶማሌ፣ ወላይታ፣ ሲዳማ፣ ትግሬ፣ ጉራጌ ወዘተ. ናቸው፡፡ በዞኑ ውስጥ ከፍተኛውን ቁጥር የሚይዘው የኦሮሞ ብሔረሰብ ሲሆን የአማራ ብሔረሰብ ከኦሮሞ ቀጥሎ በስፋት ይገኛል፡፡

አብዛኛው የዞኑ ህዝብ የሚተዳደረው በግብርና ሲሆን የተቀሩት በመንግስት ስራ፣ በከብት ማርባት፣ በንብ ማነብ፣ በሽመና፣ በሸክላ ስራ፣ በጌጣጌጥ ስራና በተለያዩ ጥቃቅን እና አነስተኛ ማህበራት በመደራጀት የተለያዩ ስራዎችን በመስራት ህይወታቸውን ይመራሉ፡፡ ግብርና የአብዛኛው የዞኑ ነዋሪ መተዳደሪያ መሆኑ ከላይ ተገልጿል፡፡ የግብርና ስራ በግል ከሚሰራው በተጨማሪ በትላልቅ የእርሻ ልማት ድርጅቶችም ይከናወናል፡፡

የገጠር መሬት ይዞታን በተመለከተ አንድ ገበሬ አባወራ በአማካኝ አንድ ሄክታር መሬት ይኖረዋል፡፡ ዞኑ ሰፊ ለእርሻ የሚውል መሬት አለው፡፡ በዞኑ ውስጥ ሶስት የአዝመራ ወቅቶች አሉ፡፡ እነሱም በልግ 'አርፍሳ' (Arfaasaa)፣ ክረምት 'ገና' (Ganna) እና በጋ 'ቦና' (Bona) ናቸው፡፡ በልግ ከየካቲት እስከ ግንቦት ያለውን ወቅት የሚሸፍን ሲሆን በዚህ ወቅት የዞኑ ገበሬዎች ጤፍ፣ ስንዴ፣ ገብስ፣ በቆሎ የመሳሰሉትን እህሎች ይዘራሉ፡፡ በክረምት ወቅት ከሰኔ - ሐምሌ የቅባትና የብዕር እህሎች ይዘራሉ፡፡ በጋ ከህዳር አጋማሽ እስከ የካቲት አጋማሽ ባሉት ወራቶች ሲሆን ምርት የሚታጨድበት፣ የሚወቃበትና የሚሰበሰብበት ወቅት ነው፡፡

በዞኑ በስፋት የሚመረቱ አዝርቶች ስንዴ፣ ገብስ፣ አጃ፣ ጤፍ፣ በቆሎ፣ ማሽላና ዘንጋዳ ናቸው፡፡ ከጥራጥሬ ደግሞ ባቄላ፣ ቦሎቄ፣ ሽምብራ፣ ምስርና ጓያ በስፋት ይመረታሉ፡፡ ከዘይት እህሎች ደግሞ ኑግ፣ ሱፍ፣ ጎመን ዘር፣ ሰሊጥ በዞኑ በስፋት ይመረታሉ፡፡

ከዚህ በተጨማሪም በዞኑ ቅመማቅመም፣ ሸንኮራ አገዳ፣ ስራስር፣ አትክልትና ፍራፍሬ ይመረታል። በዞኑ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ የጀርባ አጥንት የሆነው ቡናም በስፋት ይመረታል። በዚህ መሰረት በ1997ዓ.ም 5130.0 ቶን ቡና ከዞኑ ለሃገር አቀፍ ቡናና ሻይ ባለስልጣን ቀርቧል። በ1998ዓ.ም ደግሞ 2986.8 ቶን ቡና ለተጠቀሰው ባለስልጣን ቀርቧል። የከብት ማርባት ስራም በስፋት ይካሔዳል። በዚህ መሰረት በዞኑ አህያ፣ ፈረስ፣ ግመል፣ በግ፣ ፍየል፣ በቅሎ፣ ላም፣ በሬ የመሳሰሉት በብዛት ይገኛሉ። የዶሮ እርባታም ይካሄዳል። ማህበረሰቡ ከከብት ማርባት በተጨማሪ የንብ ማነብ ስራም ይሰራል (የኦሮምያ ሚሊኒየም በድሬ ሼክ ሁሴን 2000፣ 9)።

በዞኑ የተለያዩ ብሔር ብሔረሰቦች እንደሚኖሩ ቀደም ብለን ጠቅሰናል። የተለያዩ ብሔር ብሔረሰቦች እንደመኖራቸው መጠን የተለያዩ ቋንቋዎች ሊነገሩ እንደሚችሉ መገመት ይቻላል።በ1999ዓ.ም በተደረገው ሀገር አቀፍ የህዝብና ቤቶች ቆጠራ ሪፖርት መሰረት በባሌ ዞን ውስጥ የኦሮምኛ፣ አማርኛ፣ ጉራጊኛ፣ ስልጢኛ፣ ትግረኛ ወዘተ. ቋንቋ ተናጋሪዎች ይገኛሉ። በዞኑ በብዛት የሚገኘው የኦሮሞ ብሔረሰብ ስለሆነ በተለይ በገጠሩ አካባቢ የኦሮምኛ ቋንቋ በስፋት ይነገራል። የኦሮምኛ ቋንቋ የክልሉም ሆነ የዞኑ የስራ ቋንቋ በመሆኑ በከተሞች አካባቢም ያለው ስርጭት ሰፊ ነው።

እንደ Bender (1976፣ 56) የቋንቋዎች ምደባ የምስራቃዊ ኩሺቲክ ቤተሰብ ከሆነው የኦሮምኛ ቋንቋ በመቀጠል የሰሜን ሴሜቲክ የቋንቋ ቤተሰብ የሆነው የአማርኛ ቋንቋ በዞኑ በተለይ በከተሞች አካባቢ በስፋት ይነገራል። ምንም እንኳ የኦሮምኛ ቋንቋ የዞኑ የስራ ቋንቋ ቢሆንም በከተሞች አካባቢ (በተለይ በጎባ ከተማ) በተለያዩ ማህበራዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ በስፋት ጥቅም ላይ ሲውል የሚስተዋለው የአማርኛ ቋንቋ ነው።

በባሌ ዞን ውስጥ የተለያዩ እምነቶች አሉ። እነዚህም እስልምና፣ ክርስትና እና ሀገር በቀል እምነት (ዋቄፈታ) ናቸው። በዞኑ የእስልምና ሀይማኖት ተከታዮች ቁጥር በጣም ከፍተኛ ሲሆን የዋቄፈታ እና የፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች ቁጥር አነስተኛ ነው።በ1999 ዓ.ም በተካሔደው የህዝብና ቤቶች ቆጠራ ሪፖርት መሰረት የእስልምና ሀይማኖት ተከታዮች (ሙስሊሞች) 76%፣ ኦርቶዶክስ ክርስቲያኖች 19.02%፣ የባህላዊ እምነት ተከታዮች (ዋቄፈታ) 2.77%፣ የፕሮቴስታንት ሀይማኖት ተከታዮች1.15% ሲሆኑ የቀሩት 0.22% ሃይማኖታቸው አይታወቅም ( የኦሮምያ ሚሊኒየም 2000፣ 8 )።

ዋቄፈታ የኦሮሞ ህዝቦች ከጥንት ጀምረው የሚከተሉት ባህላዊ እምነት ነው፡፡ የኦሮሞ ህዝብ በፖለቲካ በኩል የአስተዳደር የዳኝነት ህግ እንዳለው ሁሉ ከቀድሞ ጀምሮ ፈጣሪውን የሚያምንበት የራሱ የሆነ ሀይማኖት፣ እምነቱን የሚገልጥበት ስርዓትና ህግ እንዳለው ጀቤሳ ኤጀታ (1989፣ 93) ይገልፃሉ፡፡ የዚህ እምነት ተከተይ የሆኑ ዋቄፌታዎች በሰማይ የሚኖርና ፍጥረታትን ሁሉ የፈጠረ (uumaa uumama hundaati) (ኡማን ኡመመ ሁንዳቲ) አምላካቸውን 'ዋቃ' (waaqaa) ብለው ይጠሩታል፡፡

የዋቄፈታ እምነት በአፈፃፀሙ አሪታዊ ሀይማኖትን የሚከተል እንደሚመስል ጀቤሳ ኤጀታ በተጠቀሰው ገፅ ያስረዳሉ፡፡ በባሌ ዞን የሚገኙ የዋቄፈታ እምነት ተከታዮች አምላካቸውን ለማመስገን፣ ሀገራቸውን ሰላም እንዲያደርግላቸው ከችግር፣ ከመከራ፣ ከበሽታ፣ ከድርቅና ከውሃ ሙላት እንዲጠብቅላቸው፣ ልጆቻቸውን ሰላም እንዲያሳድግላቸው፣ ከብቶቻቸውን ከበሽታ እንዲጠብቅላቸውና እንዲያረባላቸው፣ አዝመራውን (ምርቱን) እንዲባርክላቸው፣ ዘመኑን ዘመነ ፍስሃ እንዲያደርግላቸው ለመለማመን በአቅራቢያቸው ወደሚገኝና እርጥብ ሳር (coqorsa)፣ ወራጅ ወንዝ (malkaa)፣ ሰፊ ቅርንጫፍ ያለው ዛፍ (odaa)፣ ተራራ[3] (ቱሉ) ወዳለበት ስፍራ የእርድ ከብት፣ ጠላ፣ ዳቦ፣ ቆሎ ወዘተ. ይዘው በመሄድ ለአምላካቸው (ለዋቃ) መስዋዕት እና ምስጋና ያቀርባሉ፡፡ አምላካቸውን ይለማመናሉ፡፡

የባሌ ኦሮሞዎች በተለያዩ ጊዜያት የሚያከናውኗቸው ባህላዊ እምነቶችም አሉ፡፡ ከነዚህ ውስጥ ኡቴቴ እና በረንቲቻ ዋነኞቹ ናቸው፡፡ ኡቴቴ የቤተሰብን ጤና፣ ሀብትና ደህንነት የምትጠብቅ ከእናትና ከአባት የምትተላለፍ ሴት ውቃቢ እንደሆነች ይነገራል (ወ/ሮ በድሪያ እና አቶ ከድር፣ ቃለ መጠይቅ፣ ሚያዚያ 20፣ 2003፣ ጎባ)፡፡ የባሌ ኦሮሞዎች ሆነው ይህን እምነት የሚከተሉ ሰዎች በቤተሰቦቻቸውና በከብቶቻቸው ላይ የሚመጣውን ክፉ ነገር ለማስወገድ የሚከውኑት ባህላዊ የእምነት ሥርዓት ነው፡፡ ማህበረሰቡ እነዚህን ባህላዊ እምነቶች በማካሄድ ግጭት እንዳይፈጠር ይለማመናል፡፡

---

[3] ቴዎድሮስ ገብሬ፤ በይነ-ዲሲፕሊናዊ የስነ ጽሑፍ ንባብ፣ በተሰኘው መጽሀፍ ላይ ተራራ (የምድር እናት? ) ሁሉን ለማየት ተቆጣጥሮ ለመግዛት (ስጋን ለማሸነፍ ) ስልታዊ ጠቀሜታ [እንዳለው]ይገልጻሉ(2000፣117)፡፡ ተራራ በመጽፍ ቅዱስም ወስጥ ታላላቅ ተዓምራት የሚከሰቱበት ከፍ ያሉ ተግባሮች የሚከናወኑበት ቦታ ነው፡፡ ዘጸ.24፣ ዘፍ.22፣ ማር.9፥ 1 እስከ 8ን ልብይሏል፡፡

## ጋብቻ

በዚህ ክፍል በባሌ ኦሮሞዎች የሚተገበሩ የጋብቻ አይነቶችን እንመለከታለን። ጋብቻ የማህበረሰብ መሰረት የሆነው የቤተሰብ መገኛ፤ ስርዓት ባለው መንገድ ትውልድ ማስቀጠያ በመሆኑ ትኩረት ከሚደረግባቸው ጉዳዮች ውስጥ አንዱና ዋነኛው ነው። በባሌ ኦሮሞዎች ዘንድ የሚተገበሩ የተለያዩ የጋብቻ አይነቶች አሉ። እነሱም፦ 'ቡታ' (buta)፣ 'ባልቶኬ' (Baltokee)፣ 'ሀዊ' (hawii) እና የእርቅ ጋብቻ ናቸው።

### ቡታ (buta)

በጠለፋ የሚፈፀም የጋብቻ አይነት ነው። አንድ እድሜው ለጋብቻ የደረሰ ወንድ አንዷትን ልጃገረድ ለትዳር ቢፈልጋትና የሱ የኑሮ ደረጃ ከልጅቷ ቤተሰቦች የኑሮ ደረጃ በጣም ያነሰ ቢሆን፣ ስጡኝ ብዬ ሽማግሌ ብልክ አይሰጡኝ ይሆናል በሚል ሀሳብ ተነሳስቶ፣ ሌሎች ጎሮምሳ ጓደኞቹን አሰባስቦ ልጅቷ ብቻዋን የምትሆንበትን አጋጣሚ (ውሃ ልትቀዳ፣ ጭራሮ፣ ከብት ልትለቅም ስትሔድ) ጠብቆ ይጠልፋታል። በጠለፋ ወቅት የልጅቷ ፍላጎት ሊኖርም ላይኖርም ይችላል። የልጅቷ ፍላጎት ካለ የጠለፋውን ሂደት በጣም ቀላል ያደርገዋል። ነገር ግን በጠለፋው ላይ የልጅቷ ፍላጎት ቢኖር እንኳ ጎሳው ወይም ቤተሰቦቿ ስለማያውቁና እንደነውር ስለሚቆጠር ይፋ አይወጣም።

ጠለፋ በተለይ የሴቷ ፍቃድ ከሌለ በጠለፋው ወቅት መጮኋ ስለማይቀር በጠላፊውና በልጅቷ ወገኖች መካከል ግጭት ይከሰታል። በጠለፋው ላይ የልጅቷ ፍላጎት ቢኖርም ጉዳዩ እንደተሰማ የልጅቷ ወገኖች ወደጠላፊው መኖሪያ በመሄድ በተደፈርን ስሜት ግጭት ይቀሰቅሳሉ። በዚህ ጊዜ የሀገር ሽማግሌዎች ጣልቃ በመግባት ከጠላፊው ላይ በሃገሩ ባህል መሰረት ጉማ (gumaa) ተቀብለው ለልጅቷ ወገኖች በመስጠት ያስታርቋቸዋል። አሁን አሁን ጠለፋ ወንጀል መሆኑ በመገናኛ ብዙሀንና በተለያዩ ዘዴዎች በስፋት እየተሰራጨ ቢሆንም በአካባቢው ግን አልቀረም።

### ባልቶኬ (Baltokee)

ይህ የጋብቻ አይነት አንድ ሰው ለልጁ ሚስት ለማጨት በሚፈልግበት ጊዜ ልጅህን ለልጄ በማለት ሽማግሌዎች ወደ ልጅቷ ቤተሰቦች ልኮ የልጅቷን ቤተሰቦች ፍቃድ ካገኘ በኋላ የሚፈፀም ነው። ጋብቻ ጥየቃ የተላኩት ሽማግሌዎች የልጅቷን ቤተሰቦች ፍቃድ ማግኘታቸውን

ስልጁ ቤተሰቦች ሲገልፁ የልጁ ቤተሰቦች ለቤተዘመድ ትውውቅ የሚሆን አነስተኛ ድግስ ጭብሳ (cibsaa) አዘጋጅተው የሰርጉን ቀን በጋራ ይወስናሉ፡፡

በዚህ የጋብቻ አይነት ብዙው ስራ የሚሰራው በልጆቹ ወላጆች ነው፡፡ በተለይ የወንዱ ወላጆች ለልጃቸው ሚስት የምትሆን ፣ የጥሩ ቤተሰብ ልጅ የሆነች፣ በመልኳ፣ በምግባሯ ጥሩ የተባለች ልጅ ከመምረጥ ጀምረው የልጅቷን ቤተሰቦች ፍቃድ እስኪያገኙ ድረስ ብዙ ይጥራሉ፡፡ የሚጋቡት ልጆች ሁኔታውን የሚያውቁት በጭብሳ ድግስ ላይ ነው፡፡ ከዛ በፊት ለወንዱም ሆነ ለሴቷ ምንም የሚነገር ነገር የለም፡፡ በአሁን ጊዜ ግን አዲሱ ትውልድ ባህሉን እየለቀቀ ዘመን አመጣሹን ልማድ (ተዋውቀን፣ ተዋደን፣ ተግባብተን፣ ተፈቃቅደን) ስለተከተለ ይህ አይነቱ የጋብቻ አይነት ብዙ አይሰራበትም፡፡

**ሀዊ** (hawii)

ይህ የጋብቻ አይነት በዞኑ በስፋት እየተተገበረ የሚገኝ ሲሆን በሁለቱ ተጋቢዎች ፍላጎትና መፈቃቀር ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ይህን አይነት ጋብቻ የሚፈልጉት የሚጋቡት ልጆች ናቸው፡፡ ልጁ እና ልጅቷ በተለያዩ ማህበራዊ ጉዳዮች ሰርግ፣ ለቅሶ፣ አመታዊ በዓላት ወዘተ. ላይ ይተዋወቁና ግንኙነታቸው ተጠናክሮ ይቀጥላል፡፡ ሲፈቃቀዱ በፍቅር አይን በመተያየትና የቃል ጨዋታ በመለዋወጥ ፍቅር በልባቸው ይመሰርታሉ፡፡ ከጋብቻ በፊት በሚያፈቃቅሩ ሁኔታዎች እንደ ቀብዶ (Qeebdoo) (የከንፈር ወዳጅነት) ይገናኙና ፍቅራቸው ፀንቶ ስሜቱ እየበረታባቸው ይሔድና ወደ ጋብቻ ያመራሉ፡፡

**የጉማ ጋብቻ (የእርቅ ጋብቻ)**

የጉማ (የእርቅ) ጋብቻ የሚባለው አንድ ሰው የአንድን ሰው ነፍስ አጥፍቶ በገለልተኛ ወገን ሽማግሌዎች አማካኝነት ከሟች ወገኖች ጋር እርቅ ሲፈፅም ለእርቁ ማፅኛ በሚል ከገዳይ ወገን (የቅርብ ዘመድ፣ እህት፣ የአክስት፣ የአጎት ልጅ) ለሟች ዘመዶች የምትሰጥበት የጋብቻ ስርዓት ነው፡፡ በዚህ ስርዓት ሴት ልጅ የምትሰጠው ለጠፋው ነፍስ ምትክ ተደርጋ አይደለም፡፡ በሁለቱ ጎሳዎች መሀከል የተከሰተው ግጭት ተባብሶ እንዳይቀጥል በሁለቱ ወገኖች መካከል ዝምድናን ለመፍጠር ነው፡፡ አንዳንድ ሰዎች ይህ የጋብቻ አይነት አይደለም ይላሉ፡፡[4] ምክንያታቸው ደግሞ ይህ ጉማ እንጂ ጋብቻ አይደለም ነው፡፡ ሌሎች ደግሞ ይህም ከጋብቻ አይነቶች ውስጥ

[4] አቶ ሀሰን አቢዮ፣ አቶ አማን አብዶ፣ ቃለመጠይቅ፣ ሚያዝያ 22፣ 2003፣ ሲናና፡፡

ይካተታል ይላሉ።[5] በዚህ ስርዓት የሚፈፀመው ጋብቻ ከሌሎቹ የጋብቻ ስርዓቶች የሚለይበት (የሚያንስበት) ምንም ምክንያት የለም። በዚህ ስርዓት ሴት የምትሰጠው ወዳጅነትን፣ ዝምድናን፣ ሰላምን ወዘተ. ለማጠናከር ነው። በባሌ ኦሮሞ ጋብቻ በአንድ መልኩ የግጭት መነሻ ምክንያት ሲሆን (ጠለፋን ይመለከቷል) በሌላ መልኩ ደግሞ የግጭት መፍቻ ስልት ነው (የእርቅ ጋብቻን ልብ ይሏል)።

### 2.1. መስህብነት ያላቸው ቦታዎች

ባሌ ተፈጥሮ ያደለቻት ሀገር ናት። ለዚህም ብዙ የተፈጥሮ መስህቦችን መጥቀስ ይቻላል። በኢትዮጵያ ከራስ ዳሽን ተራራ በመቀጠል በሁለተኛ እና በሶስተኛ ደረጃ ላይ የሚገኙት የቱሉ ዲሞቱ እና የባቱ ተራሮች በባሌ ነው የሚገኙት። የቱል ዲምቱ ተራራ 4377 ሜትር ከፍታ ሲኖረው የባቱ ተራራ ደግሞ 4297 ሜትር ከፍታ አለው።

የባሌ ተራሮች ብሔራዊ ፓርክ ሌላው የዞኑ የቱሪስት መስህብ ስፍራ ነው። ፓርኩ ሲናና ዲንሾ፣ ጎባ፣ አዳባና መናአንጌቱ ወረዳዎች ውስጥ የሚገኝ ሲሆን በውስጡ በሌላው አለም የማገይኙ (ብርቅዬ የሆኑ) እንደ ቀይ ቀበሮ፣ ኒያላ፣ የሚኒልክ ዱኩላ፣ ትላልቅ ፀጉራማ አይጠመጎጦች ይገኛሉ (Bale Mountains A Guidebook, 2002)።

አበበ (2000) የኢትዮጵያ ቴሌቪዥንን "ሀገሬ" ፕሮግራምን በመጥቀስ ፓርኩ ከባህር ጠለል በላይ 2500 ሜትር ከፍታ እንዳለውና በፓርኩ ውስጥ ካሉት ከ2000 በላይ የአእዋፋት ዝርያ 16ቱ በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኙ መሆናቸውን ገልጿል። እንደ Atlas of Bale Zone መፀሀፍ ገለፃ ደግሞ ፓርኩ በኢትዮጵያ ከሚገኙት አጥቢ እንስሳት ውስጥ 50% ያህሉን አጥቢ እንስሳት እና 60% ያህሉን የወፍ ዝርያዎች የያዘ ነው።

ከዚህ በተጨማሪ 1.5 ኪ.ሜ ርዝመት ያለውና የወይብ ወንዝ በውስጡ የሚያልፈው የሶፍ ዑመር ዋሻ፣ የመንፈሳዊ ጉዞ መዳረሻ የሆነው የድሬ ሼህ ሁሴን ገዳም፣ መዳ የተፈጥሮ ምንጭ፣ በኢትዮጵያ በሁለተኛ ደረጃ ላይ የሚገኘው የሀረና ቡሉቅ ጥቅጥቅ የተፈጥሮ ደን እና በአፍሪካ ተጠቃሽ የሆነው የሳነቴ አንባ መገኛ ነው።

---

[5] አቶ ከድር ጀማል፣ አቶ ጫጮ ከንፈልቻ፣ የቃላሚ ቡድን ውይይት፣ ሚያዝያ 28፣ 2003፣ ጎባ።

## 2.2. ለጥናቱ የተመረጡ ወረዳዎች

የባሌ ዞን አስራ ሰባት ወረዳዎች አሉት፡፡ ከነዚህ ውስጥ በዚህ ጥናት የተመረጡት የጎባ እና የሲናና ወረዳዎች ናቸው፡፡ ወረዳዎቹ የተመረጡበት ምክንያት አጥኚው በደንብ የሚያውቃቸው ስለሆነ ነው፡፡ ጎባ ተወልጄ ያደግኩበት፣ ቤተሰቦቼ፣ ዘመዶቼ የሚኖሩበት ወረዳ ሲሆን ሲናና ደግሞ አብዛኛውን የክረምት ጊዜዬን አሳልፍበት የነበረ ወረዳ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ወረዳዎች በጣም የተቀራረቡ (በመካከላቸው ያለው ርቀት 15 ኪ.ሜ) በመሆናቸው ለትራንስፖርትና ተመላልሶ ለመስራት አመቺ ስለሆኑ ነው፡፡

የጎባ ወረዳ በባሌ ዞን ውስጥ ከሚገኙ አስራ ሰባት ወረዳዎች ውስጥ አንዱ ነው፡፡ የወረዳው ከተማ ጎባ ስትሆን በደቡባዊ ምስራቅ አቅጣጫ ከአዲስ አበባ በ445 ኪ.ሜ ርቀት ላይ ትገኛለች (የጎባ ወረዳ አስተዳደር ቢሮ 2005 እ.ኤ.አ፣ ያልታተመ መረጃ)፡፡

የጎባ ወረዳ በሰሜን ከሲናና፣ በደቡብ ከመና አንጌቱ፣ በምስራቅ ከአዳባ፣ በምዕራብ ከጎሮ እና በርበሬ ወረዳዎች ይዋሰናል፡፡ የወረዳው አጠቃላይ የቆዳ ስፋት 1799 ኪ.ሜ ነው፡፡ የመሬት አቀማመጡን ስንመለከት ከደቡብ አቅጣጫ የሚገኘው የመሬት አቀማመጥ ተራራማ፣ ዳገታማ፣ አባጣ ጎርባጣ፣ ቁልቁለትና ገደላ ገደል ሲሆን ከወደ ሰሜናዊ ምዕራብ ደን ለበስ ዳገትና ሜዳን አጣምረው የያዙ ቦታዎች አሉት፡፡ ከምስራቅና ከሰሜን አቅጣጫ ሲታይ ደግሞ ሜዳማነት ይበዛበታል፡፡ ጠቅለል ባለ ሁኔታ ካለው የቆዳ ስፋት 35% ከፍታ፣ ቁልቁለትና ገደላ ገደል፣ 50% ተራራማ ሲሆን የቀረው 15% ደግሞ ሜዳማ ነው፡፡ ወረዳው ለአስተዳደር እንዲመች በ15 የቀበሌ ገበሬ ማህበራት እና በሁለት የከተማ ቀበሌዎች የተዋቀረ ነው(2005፣ 1 እ.ኤ.አ)፡፡

ሲናና በባሌ ዞን ውስጥ ከሚገኙት አስራ ሰባት ወረዳዎች ውስጥ አንዱ ሲሆን በሰሜን ምዕራብ የዞኑ ክፍል ይገኛል፡፡ የሲናና ወረዳ በደቡብ ከጎባ እና ከበርበሬ ወረዳዎች፣ በሰሜን ከአጋርፋ እና ጋስራ ጎሎልቻ ወረዳዎች፣ በምዕራብ ከዲንሾና ከአሊ ወረዳዎች፣ በምስራቅ ከጊነር እና ጎሮ ወረዳዎች ጋር ድንበር ይጋራል፡፡ የሲናና ወረዳ ከተማ ሮቤ ስትሆን የዞኑም ከተማ በመሆን ታገለግላለች፡፡ የወረዳው የአየር ፀባይ የተለያየ ነው፡፡ በወረዳው ካለው የአየር ፀባይ 1% ቀዝቃዛ (ውርጭ)፣ 47% ደጋ፣ 50% ወይና ደጋ የቀረው 2% ደግሞ ቆላ ነው (Bale, 2002; 95)፡፡

## በባሌ ዞን የሚገኙ የአርሲ ጎሳዎችን የዘር ሃረግ የሚያሳይ ሰንጠረዥ




ምንጭ፡- የኦሮሚያ ባህልና ቱሪዝም ኮሚሽን፤ የኦሮሞታሪክ- እስከ አስራ ስድስተኛ መቶ ክፍለ ዘመን (1996፣ ገጽ 133-150)፣ ጀቤሳ ኤጀታ (1989፣ ገጽ 211- 248 )፣ ሰለሞን ተሾመ (2002፣ 22) አቶ ቲልሞ ሲዶ፣ አቶ ጫሜ ከንፌልቻ፣ ቃለመጠይቅ፣ ሚያዝያ 27፣ 2003፣ ጎባ፤ አቶ ሀሰን አቢዮ፣አቶ አማን አሎ፣ ቃለመጠይቅ፣ ሚያዝያ 22፣2003፣ ሲናና፡፡ ከነዚህ ምንጮች በመነሳት በአጥኚው የተዘጋጀ፡፡

---

[6] የራያ ጎሳ 32 ንዑሳን ጎሳዎች አሉት ፡፡ ንዑሳን ጎሳዎቹ ብዙ ስለሆኑ በሰንጠረዥ ማስቀመጥ አልተቻለም፡፡

## 3. ንድፈ ሀሳባዊ መሰረትና የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

በዚህ ምዕራፍ የግጭት ብያኔ፣ የግጭት እሳቤ፣ የግጭት መንስኤ፣ የግጭት አይነቶች፣ የግጭት አፈታት እንዲሁም ከዚህ ጥናት ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ጥናቶች ቅኝት ይቀርባል፡፡

### 3.1. የግጭት ብያኔ

"ግጭት ምንድነው?" ለሚለው ጥያቄ አንድና ሁሉን በእኩል ሊያስማማ የሚችል ብያኔ ማስቀመጥ አስቸጋሪ ይመስላል፡፡ ምክንያቱም የግጭትን ምንነት መዝገበ ቃላት ጠቅለል ባለ መልኩ[7] ሲበይኑት ከግጭት ጥናት ጋር ቀረቤታ ያላቸው ምሁራን ደግሞ በጥናቶቻቸው ውስጥ ከሙያቸው ጋር በታያያዘ ይበይኑታል፡፡ ስለዚህ በዚህ ጽሁፍ ውስጥ ስለግጭት ምንነት የተለያዩ ምሁራን የሰጡትን ብያኔ በመመልከት ለዚህ ጥናት የሚስማማውን ብያኔ ይሰጣል፡፡

የተለያዩ የህብረሰብ ሳይንስና የስነ ልቦና የጥናት ዘርፎች ግጭትን ስራዬ ብለው መመርመር ከጀመሩ ከግማሽ ምዕተ ዓመት በላይ ሆኗቸዋል፡፡ እንደ ጥናት ዘርፎቹ እና ምሁራኖቹ የትኩረት አቅጣጫ የተለያዩ የግጭት ብያኔዎች ተሰንዝረዋል፡፡ ባለሙያዎቹ ለግጭት የሰጡትን ብያኔ ማየቱ የግጭትን ምንነት ይበልጥ እንድንረዳ ያደርገናል፡፡ ከዚህ በመቀጠል በመስኩ ምሁራን ስለግጭት ምንነት የተሰጡትን ብያኔዎች እንመለከታለን፡፡

Fisher (1982፣567) ግጭት ማህበራዊ ሲሆን አንዱ ከሌላው ጋር የጠላትነት ስሜት ባላቸውና አንዱ ሌላውን ለማሸነፍ በሚፈልጉ ሁለትና ከሁለት በበለጡ ሰዎች ወይም ቡድኖች መካከል አንድ ላይ ተስማምቶ ለመሄድ የማያስችል የተለያየ ፍላጎትና አላማ ሲኖር የሚከሰት እንደሆነ

[7] በደስታ ተክለወልድ ሀዲስ የአማርኛ መዝገበ ቃላት (1962፡249) መሰረት ግጭት ‹‹መግጨት፣ መገጨት፣ ድንገተኛ ጥል፣ ፅለት ጠብ፣ ያልታሰበ አደጋ፣ የጊዜ ጦርነት›› የሚል ፍቺ ተሰጥቶታል፡፡ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል (2001፡510) ያዘጋጀው መዝገበ ቃላት ደግሞ ግጭትን ‹‹ጥል፣ ጠብ›› በማለት ይፈታዋል፡፡ መዝገበ ቃላቱ ለግጭት የሰጡት ፍቺ የጠበበ ቢሆንም ከመዝገበ ቃላቱ ፍቺ በመነሳት ግጭት ሰዎች ሳያስቡት፣ በአጋጣሚ የሚከሰትና በግጭቱ ተሳታፊዎች ላይ ጉዳት ሚያደርስ ክስተት መሆኑን እንገነዘባለን፡፡

ገልጸዋል፡፡ ከዚህ ብያኔ ግጭት ማህበራዊ እንደሆነና የማይጣጣም ፍላጎትና አላማ ባላቸው ሁለትና ከዚያ በላይ በሆኑ ሰዎች መካከል የሚከሰት እንደሆነ እንረዳለን፡፡

Augsburger (1992:20) ደግሞ የተፈጥሮ ሀብት እጥረት፣ ማህበረሰቡ የሚሰጠው የሥራ ክፍፍል እና ማህበራዊ የስልጣን ደረጃ ባለበት ሁኔታ ውስጥ የሰው ልጅ ለህይወቱ አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችንም ሆነ በስልጣን ረገድ ከሌሎች በበለጠ ተጠቃሚ ለመሆን በሚያደርገው ውድድር ወይም ስልጣንን ለፍላጎቱና ለዓላማው መሟላት የመጨረሻ አማራጭ ማድረግ ሲጀምር ግጭት እንደሚከሰት ይገልፃሉ፡፡ ከዚህ ብያኔ የምንረዳው ግጭት ሰዎች ውስን የሆነ የተፈጥሮ ሀብቶችን ለመቆጣጠር እና የስልጣን የባላይ ለመሆን ሲያስቡ የሚከሰት እንደሆነ ነው፡፡

Tirsit Girshaw (2004) እነ Siomo Dekha (2000)ን ጠቅሰው ግጭት በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ ያለ ተፈጥራዊ ክስተት መሆኑን እና ተቃራኒ አላማ ባላቸው እና አለን ብለው በሚያስቡ ሁለት ወይም ከሁለት በላይ በሆኑ አካላት መካከል የሚፈጠር ግንኙነት መሆኑን "Conflict is a natural phenomenon in human history. Conflict is relationship between two or more parties who have or think they have incompatible goals." በማለት ይገልጹታል፡፡

ከዚህ ብያኔ ግጭት በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ ያለ የነበረና ወደ ፊትም የሚኖር የተፈጥሮ ክስተት እና የማይጣጣም ዓላማ ባላቸው ሁለት ወይም ከሁለት በላይ በሆኑ ወገኖች መካከል የሚፈጠር መስተጋብር መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ከዚህም በላይ ግጭት ውስጥ የሚገቡት አካላት ወደ ግጭቱ የሚገቡት የማይጣጣም ወይም ተፃራሪ አላማ ስላላቸው ብቻ ሳይሆን አካላቱ የማይጣጣም አላማ ያላቸው መስሎ ሲሰማቸውም ሊከሰት መቻሉን እንረዳለን፡፡

ግጭቶች በአይነትና በመጠን የተለያዩ ናቸው፡፡ በሁለት የማይጣጣም አላማ እና አመለካከት ባላቸው ወገኖች መካከል ከሚነሳው የዕለት ውዝግብ አንስቶ ለንብረት ውድመት እና ለበርካታ ሰዎች ህልፈት መንስኤ የሚሆኑ አመጾችን እና ጦርነቶችን ይጠቀልላል፡፡ ግጭቶች በዓይነትና በመጠን የተለያዩ መሆናቸው የሚያስከትሉትም ውጤት የዚያኑ ያህል የተለያየ ሊሆን እንደሚችል ያስገነዝባል፡፡

በግጭት ላይ ጥናትና ምርምር ባደረጉ የማህበራዊ ሳይንስና የስነ ልቦና ምሁራን ዘንድ ግጭት በሰዎች የዕለት ተዕለት ህይወት ውስጥ በሚያስከትለው ውጤት ላይ ያላቸው አመለካከት የተለያየ እንደሆነ ከምርምር ስራዎቻቸው እንረዳለን።

አንዳንዶቹ ምሁራን ግጭት ግለሰቦችንም ሆነ ማህበረሰቡን ሊጠቅም የሚችልና ለለውጥና ለእድገት አስፈላጊ በመሆኑም ላይ አጠቃላይ ስምምነት መኖሩን ይገልፃሉ። ለምሳሌ Coser (1970፣20) ግጭት ከዝቅተኛ የአስተሳሰብ ደረጃ ተላቀን ለተሻለ አስተሳሰብ እንድንዘጋጅ፤ የልማት ተጠቃሚ እንድንሆንና መልካም ነገርን የመፍጠር ችሎታ እንዲኖረን የማድረግ ሀይል አለው። ማንኛውም ህብረተሰብ ደግሞ በለውጥ ሂደት የሚሳተፍና የተሻለ የአስተሳሰብ ባለቤት የሚሆነው በውስጡ ባሉ ግጭቶች አነሳሽነት እንደሆነ ይገልፃሉ። ይህንኑ ሀሳብ ሲያጠናክሩ (1956፣ 25) ያለ ግጭት የሚኖር ወይም ግጭት አልባ ሆኖ የኖረ የማህበረሰብ አባል አለ ማለት አይቻልም። የግጭት መኖር ደግሞ የማህበረሰቡ መገለጫና የዕድገት ምልክት ነው። ስለዚህ ህብረተሰቡ የሚያድገውና ለውጥም የሚያመጣው በውስጡ በተነሱ ግጭቶች ምክንያት መሆኑን ያስረዳሉ። በተመሳሳይ Habtamu (1998፡ 24) በዘመናዊ አስተሳሰብ ግጭት ጠቃሚና አስፈላጊ ነው። አንዳንድ ግጭቶች የሰውን ልጅ ለእድገት እና ለአዎንታዊ ለውጥ እንዲነሳሳ የሚረዱ ናቸው። ለእድገትና ለማህበራዊ ለውጥ መሰረት ይሆናሉ። ግጭቶችና ውጥረቶች ብዙውን ጊዜ የሠው ልጅ የተነሳሽነት መንፈስ እንዲያዳብርና ሙሉ ሀይሉን ስኬታማ ለሆነ የፈጠራና የለውጥ ተግባር እንዲያውል ይረዳዋል። የሰው ልጅ በመቀራረብ የሚነጋገርባቸው ግጭት አዘል ጉዳዩችም ብዙውን ጊዜ የአዳዲስ ሀሳቦች መገኛ ሲሆኑ፤ የሃሳብ ልዩነቶችም ጠቃሚ የሆኑ ነገሮች እንዲፈጠሩና ውስን የሆነውን የተፈጥሮ ሀብትም በጋራ ለመጠቀም የሚረዳ እውቀት እንዲኖረን የሚያደርጉ መሆናቸውን ገልጸዋል።

ሌሎች የዘርፉ አጥኚዎች ደግሞ በተቃራኒው ግጭት የግለሰቦችንም ሆነ የማህበረሰቡን ሰላም የሚያደፈርስ፣ በህይወት እና በንብረት ላይ ጉዳት የሚያደርስ በመሆኑ ሊኖር እንደማይገባው ይገልጻሉ።

ከነዚህ መሀከል Toumani (1998፡58) ግጭት የሰውን ልጅ ሀብትና ህይወት ያውድማል፣ ማህበራዊ ተቋማትን ያፈርሳል፣ ማህበራዊ ትስስርን ያናጋል በማለት ይገልፃሉ። መስፍን ይልማና መስፍን ባንታየሁ (2007፣1) በበኩላቸው Rummel (2007)ን ጠቅሰው ግጭት

የማህበረሰቡን ሰላም የሚያደፈርስ፣ እሴቶችን የሚያናጋ፣ የማያስፈልግና በሰው ልጅ ህይወት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚፈጥር እንደሆነ ይገልጻሉ።

አንዳንድ ምሁራን ደግሞ ግጭት ጉዳትም ጥቅምም እንዳው በመግለጽ ጉዳቱን እና ጥቅሙን ጎን ለጎን ያስቀምጣሉ። Deutsch (1973:17) ግጭት ልዩነትን ስለሚያመጣ፣ ተፃራሪ ወገኖች ለየብቻቸው እንዲኖሩ ስለሚያደርግ እና ውድመትን ስለሚያመጣ ጎጂ ነው። ስለራሳችንም ሆነ ስለተቀናቃኞችን ማንነት በደንብ እንድናውቅ በማድረጉ ደግሞ ጠቃሚ እንደሆነ ይገልፃሉ። Bowman and Ray (2002:59) ም ግጭት በንብረት እና በህይወት ላይ ጉዳት በማስከተሉ ጎጂ ሲሆን ለለውጥ አነሳሽ በመሆኑ ደግሞ ጠቃሚ ነው ይላሉ።

ምሁራኖቹ ካስቀመጧቸው የግጭት እሳቤዎች በመነሳት ግጭት ሁለትና ከዚያ በላይ በሆኑ ሰዎች ወይም ቡድኖች መሃከል በዓላማ፣ በእሴት፣ በጥቅምና በባህርይ አለመጣጣም የተነሳ የሚከሰት ማህበራዊና ተፈጥሯዊ ክስተት ነው ማለት ይቻላል። በግለሰብም ይሁን በማህበረሰቡ የእለት ተዕለት ህይወት፣ የእርስ በእርስ ግንኙነት፣ የማህበራዊ መዋቅር ቀጣይነት እና እድገት ላይ አሉታዊ እና አውንታዊ ውጤት ሊያመጣ የሚችል መሆኑንም እንገነዘባለን።

### 3.2. የግጭት መንስኤ

ሰዎች ወይም ቡድኖች ለምን ወደ ግጭት ይገባሉ? ወይም የግጭቶች መነሻ ምክንያት ምንድነው? የሚለውን ጥያቄ የሚመልስ አንድ ቁርጥ ያለና ሁሉን በእኩል ሊያስማማ የሚችል ምላሽ ማግኘት ከባድ ይመስላል። ምክንያቱም ሰዎችን ወይም ቡድኖችን ወደግጭት እንዲያመሩ የሚያደርጉ ጉዳዮች እንደየአካባቢው፣ እንደየባህሉ ወዘተ. የተለያዩ ሊሆኑ ስለሚችሉ ነው። የተለያዩ የግጭት ተመራማሪዎች ዋና ዋና የግጭት መንስኤ ናቸው ያሏቸውን በጥናቶቻቸው አቅርበዋል። ከነዚህ ውስጥ፡-

Bills, Frank (2002) የግጭት መነሻ ምክንያቶች በአራት ንድፈ ሀሳቦች ውስጥ እነደሚጠቃለሉ ያስረዳሉ። የመጀመሪያው የሰው ልጅ ፍላጎት ትውር (Human need theory) ሲሆን በዚህ ትውር መሰረት የሰው ልጆች መሰረታዊ (አካላዊ፣ ማህበራዊ፣ ስነልቦናዊ) መብቶች መጣስ ለግጭት መፈጠር ከፍተኛ ድርሻ እንዳለው የሚያመለክት ነው። ሁለተኛው ግንኙነታዊ ትውር (Relation theory) ነው። በዚህ ቲዋሪ መሰረት የግጭት መነሻ ምክንያቶች በባህል፣ በግለሰባዊ እሴቶች እና በአላማ መለያየት እንዲሁም ዘረኝነት፣ ጎሰኝነት እና ብሔርተኝነት እንደሆኑ

የሚገልጽ ነው። ሶስተኛው ደግሞ ፓለቲካዊ ትውር (Political theory) ነው። በዚህ ቲዎሪ መሰረት ግጭት የሚፈጠረው ፖለቲካዊ ስልጣን ለመያዝ በሚደረጉ ሽኩቻዎች እና ስልጣንን ለግለሰብና ለወገን ጥቅም ማስከበሪያ ሲያደርጉ ነው። አራተኛው እና የመጨረሻው የሽግግር ትውር (Transformation theory) ሲሆን እንደቲዎሪው ሀሳብ ግጭት የሚከሰተው በአንድ ሀገር ወይም ማህበረሰብ ውስጥ የሚታዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊ እና ባህላዊ መዋቅሮችንና አሰራሮችን ለመቀየር በሚደረጉ ጥረቶች ነው።

Taumani (1998:1-52) በበኩላቸው የተለያዩ የግጭት መነሻ ምክንያቶችን ጠቅሰዋል። ከነዚህ ውስጥ የተፈጥሮ ሀብትን በበላይነት ለመቆጣጠር የሚደረጉ ሽኩቻዎች፣ የሰዎች ለባህላዊ ደንቦች አልገዛም ማለት ይጠቀሳሉ። የTaumani ሀሳብ ከBills አምብዛም የራቀ አይደለም።

Dejene እና Abdurahman (2002፣1) ጥናታቸውን ባድረጉበት አካባቢ ለሰዎች፣ ለእንስሳት እና ለመለስተኛ መስኖ የሚውል ውሃ ለማግኘት እና ለእርሻና ለግጦሽ የሚሆን መሬትን ለመቆጣጠር የሚደረጉ ፋክክሮች (ሽኩቻዎች) ለግጭት መንስኤ መሆናቸውን ጠቅሰዋል።

የማህበራዊ ግጭት መፈጠር ምክንያቶች አንድን የተወሰነ ነገር የራስ መጠቀሚያ ሀብት ለማድረግ መጣር፣ የአላማ መለያየትና ያልተመጣጠነ የማህበራዊ የእድገት ደረጃ መኖር መሆናቸውን (Kuper 1996,124) ሲገልጹ፤ Habtamu (2008,87) ደግሞ ራስ ወዳድነትና ወሰን የለሽ ፍላጎትን ለማሟላት መሞከር፣ የሥልጣንና የሌሎች የበላይ ለመሆን መፈለግ፣ የሀብት ምንጮችን ለመቆጣጠር መፈለግና የሌሎችን መብት አለማክበር የግጭት መነሻ ምክንያቶች መሆናቸውን ያስረዳሉ።

Levionsan (1996, 237) የግጭት መፈጠር ምክንያት የሰዎች የፍላጎት አለመጣጣም እነደሆነ ሲያስረዳ፣ Woodhouse እና ሌሎች (2000፣178) ደግሞ Buron ጠቅሰው ግጭት የሚፈጠረው መሰረታዊ የሆኑ የሰው ልጅ ፍላጎቶች ሳይሟሉ ሲቀሩ እነደሆነ ይገልፃሉ።

ከላይ ከቀረበው ከዘርፉ ምሁራን ሀሳብ መረዳት እንደሚቻለው ሰዎችን ወይም ቡድኖችን ወደግጭት የሚመሩ ጉዳዮች ብዙ ናቸው። አንዳንድ ምሁራን ለግጭት መፈጠር ምክንያት ከማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ ጉዳዮች ጋር የተያያዙ ነገሮች እንደሆኑ ገልጸዋል። ሌሎች ደግሞ የግጭት መንስኤ የሰብዓዊ መብት መጣስ እንደሆነ አስረድተዋል። የሰው ልጅ ስግብግብነት እና የራስ ወዳድነት ባህርይም ለግጭት መፈጠር ምክንያት እንደሚሆን የገለጹም አሉ።

### 3.3. የግጭት አይነቶች

የዘርፉ ምሁራን የግጭት አይነቶችን ከተለያዩ መመዘኛዎች አንፃር በተለያዩ መንገዶች ይከፋፍሏቸዋል። አንዳንዶቹ ምሁራን ግጭቱ ከተከሰተበት ደረጃ (Based on the Level of their occurres)፣ ግለሰብ ከግለሰብ (Intra-personal)፣ የቡድን ውስጥ (Intra group)፣ ቡድን ከቡድን (Inter-group)፣ የሀገር ውስጥ (Intra- state) እና የሀገራት (Inter-state) በማለት ይመድቧቸዋል (Nader, 1968:236፣ መድህኔ 2004፣3)።

ሌሎች ደግሞ በግጭት ውስጥ ከሚሳተፉት ሰዎች ማንነት በመነሳት (Based on the kind of actors in the Conflict) የብሔር ግጭት (Ethnic conflicts) የቤተሰብ ግጭት (Family conflicts) እና የጎሳ ግጭት (Clan conflicts) በማለት ይከፋፍሏቸዋል(ለምሳሌ Assefa Abebe 2001፣ 24)።

አንዳንድ ምሁራን ደግሞ ግጭቱ ከሚያስከትለው ውጤት በመነሳት ገንቢ ግጭት (constructive Conflict) እና አውዳሚ ግጭት (Destructive conflict) በማለት በሁለት ይከፋፍሉታል (Deutsch 1973፣17፤ Augsburger 1992፣ 47)።

ገንቢ ግጭት (Constructive Conflict) የሚባለው የግጭቱ ተሳታፊዎች በጠቅላላ በግጭት አፈታት ሂደቱና በሚገኘው መፍትሔ የሚረኩበትና በፍፃሜውም ሁሉም አካላት ተጠቃሚ (ደስተኛ) የሚሆኑበት የግጭት አይነት መሆኑን ይገልፃሉ። አውዳሚ ግጭት (Destructive Conflict) ደግሞ በግጭቱ የተሳተፉት ሁሉም አካላት ግጭቱ በሚያስከትለው ውጤት በጣም የሚጎዱበት (ተጠቃሚ የማይሆኑበት) የግጭት አይነት እንደሆነ ያስረዳሉ።

ሌሎች ደግሞ በግጭቱ ውስጥ ተሳታፊ የሆኑት ሰዎች በማህበረሰቡ ወስጥ ካላቸው ደረጃ አንፃር ጎናዊ ግጭት (horizontal Conflict) እና ተዋረዳዊ ግጭት (Vertical conflict) በማለት ይመድቧቸዋል (Deusdendit 2003:2 መስፍን 1999፣27-31)። ጎናዊ ግጭት (horizontal Conflict) የሚባለው በተመሳሳይ ማህበራዊ ደረጃ ላይ በሚገኙ፤ በመሀከላቸው የሃብት፣የስልጣን፣ የዘር የባላይነት በሌላቸው ግለሰቦችና ቡድኖች መካከል የሚፈጠር የግጭት አይነት ነው። ተዋረዳዊ ግጭት (Vertical conflict) የሚባው ደግሞ ማህበራዊ ደረጃቸው በተለያዩ ሰዎችና ቡድኖች መሀከል የሚፈጠር የግጭት አይነት ነው። በሌላ አገላለጽ የበታች

እና የበላይ ባለበት ማህበረሰብ ውስጥ በበላዩ እና በበታቹ ጎሳ ወይም ግለሰብ መሀከል የሚከሰት የግጭት አይነት ነው።

ከላይ እንደተመለከትነው የዘርፉ ምሁራን የግጭት አይነቶችን ከግጭቱ ደረጃ፣ ግጭቱ ውስጥ ከተሳተፉት ሰዎች ማንነት፣ ግጭቱ ከሚያስከትለው ውጤት እና የግጭቱ ተሳታፊዎች በማህበረሰቡ ውስጥ ካላቸው ማህበራዊ ደረጃ አንፃር ይከፋፍሏቸዋል።

### 3.4. የግጭት አፈታት

ግጭት ሁለት እና ከሁለት በላይ በሆኑ ሰዎች ወይም ቡድኖች መካከል በተለያዩ ምክንያቶች የሚከሰት ማህበራዊ ክስተት እንደሆነ ቀደም ብለን ገልጸናል። የትኛውም ማህበረሰብ በውስጡ የተከሰተውን ግጭት እንዳየ ግጭቱ ደረጃና አይነት ህግና ደንብ በማውጣት ግጭቱ ተፋፍሞ በአካል፣ በንብረትና በህይወት ላይ የከፋ ጉዳት ከማድረሱ በፊት ግጭቱን የሚፈታበት መንገድ አያጣም።

ግጭትን መፍታት ማለት ላለመስማማት ምክንያት የሆኑትን ነገሮች አጣርቶ እና አጥርቶ ግጭት ውስጥ የገቡ አካላትን ከግጭቱ በፊት ወደነበሩበት ሁኔታ እንዲመለሱ ማድረግ ነው። Habtamu (2005:8) ግጭት መፍታትን "Conflict resolution refers to the process of Creatively responding to a conflict in order to find ways to solve the problem. The term resolution suggest a solution which returns all parties and the community to a stable status, concerning the basic human needs of all parties in conflict." በማለት ይገልጹታል። Assefa (2001፣ 31) ደግሞ conflict resolution refers to addressing root couse of conflicts and resolving them. በማለት ይበይኑታል።

የተለያዩ መንግስታትና ድርጅቶች በግለሰብ፣ በቡድን፣ በጎሳ፣ በአገር ወዘተ. ደረጃ በተለያዩ ምክንያቶች የሚቀሰቀሱ ግጭቶችን የተለያዩ የግጭት አፈታት ዘዴዎችን በመጠቀም ይፈታሉ። በዚህ ክፍል የግጭት አፈታት ዘዴዎች ከመስኩ ምሁራን፣ ከአለም፣ከአህጉር እና ከኢትዮጵያ የህግ ሰነዶች አንፃር ይቃኛሉ።

### 3.5. የግጭት አፈታት ዘዴዎች ከመስኩ ምሁራን አንፃር

የዘርፉ ምሁራን የግጭት አፈታት ዘዴዎችን በተመለከተ ከዘዴዎቹ አይነት፣ ዘዴዎቹ መሰረት ከሚያደርጉት ህግና ደንብ፣ ከአስታራቂዎቹ ሚና፣ ከታራቂዎቹ ሚና እና ከውሳኔ አሰጣጥ ስርዓቱ አንፃር የተለያዩ መንገዶች መኖራቸውን ይጠቁማሉ።

Mitchell (2003፣75) በግጭት መፍታቱ ሂደት ውስጥ በግጭቱ የተሳተፉት ወገኖች ከሚወስዱት አቋም በመነሳት ሊቀርቡ ሚችሉት የመፍትሔ ሀሳቦች አምስት መሆናቸውን ይገልጻሉ። እነሱም፡- ጥሎ ማለፍ (Compeing)፣ መቀበል (Accamodating)፣ መተባበር (Callaborating)፣ ማስወገድ (Avoiding ) እና መደራደር (campromising) ናቸው።

Imbighe (2003:67) እና woodhouse and Ronsbothom (2000:40-41) ሶስት የግጭት መፍቻ መንገዶች መኖራቸውን ገልፀዋል። እነሱም በህግ አግባብ(right contest)፣ በእርቅ (reconciliation) እና በሀይል (power contest) ናቸው። የዘዴዎቹን ብቃትና ተመራጭነት ሲገመግሙም እርቅ (reconciliation) ተቀናቃኞቹ ፊት ለፊት ተገናኝተው በመሀከላቸው የተፈጠረውን ግጭት የሚፈቱበት ዘዴ በመሆኑ ተመራጭነት እንዳለው ያስረዳሉ። እርቅ እንደ ግጭቱ አይነት፣ እንደ ተቀናቃኞቹ ማንነት ሊቀያየር እና ሁሉንም ሊያስማማ የሚችል ዘዴ በመሆኑ ከሌሎቹ ዘዴዎች በተሻለ ተመራጭ እንደሆነም ይገልፃሉ።

ሌሎች የዘርፉ ምሁራን በግጭት አፈታቱ ላይ ከሚሳተፉ አካላት ማንነት እና ከሚያከናውኗቸው ተግባራት በመነሳት የግጭት አፈታት ዘዴዎችን ድርድር (Negotiation)፣ ሽምግልና (Mediation)፣ እርቅ (Arbitration) እና የህግ ድንጋጌ (Adjucation) በማለት ይከፍሏቸዋል (Jeong 2000፡168-177፣ Augsburger 1992፡192-194 Sahw 1997፣ 720)።

#### ድርድር (Negotiation)

ድርድር የግጭቱ ተሳታፊ ከሆኑት ወገኖች ሌላ ተጨማሪ ሶስተኛ ወገን እገዛ ሳያስፈልግ ግጭቶች የሚፈቱበት የግጭት አፈታት ዘዴ ነው። በድርድር የግጭት አፈታት ዘዴ አጠቃላይ ድባብ (setting) የጥላቻ ወይም የትብብር መንፈስ ሊሰፍንበት የሚችል ሲሆን ስምምነት ላይ መድረስ የሚቻለውም ሆነ የግጭቱ ቀጣይነት የሚወሰነው በግጭቱ ተሳታፊ በነበሩት ወገኖች ፈቃደኝነት ነው። ሆኖም ግጭቱ ውስብስብ ከሆነና በተለይም በግጭቱ ተሳታፊዎች መካከል ስሜታዊነት አይሎ ጥሉ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ከደረሰና መግባባት ከጠፋ ይህንን የግጭት አፈታት

ዘዴ ተጠቅሞ ግጭትን መፍታት አዳጋች እንደሚሆን እንረዳለን፡፡ በዚህ ዘዴ የሚገኘው ውጤት እንደተደራዳሪዎቹ ፈቃደኝነት ሊለዋወጥ ይችላል፡፡

### ሽምግልና (Mediation)

ሽምግልና የግጭቱ ተሳታፊ ከነበሩት ወገኖች በተጨማሪ ፈቃደኛና ሁሉንም ጠበኞች በእኩል አይን የሚመለከት ሶስተኛ ወገን (ሽማግሌ በድርድሩና በግጭት አፈታት ሒደቱ ውስጥ በመገኘት የግጭቱ ተካፋይ ወገኖች ግጭታቸውን እንዲፈቱ እገዛ የሚያደርጉበት የግጭት አፈታት ዘዴ ነው፡፡ ሆኖም ሽማግሌዎቹ የሚያቀርቡትን ሐሳብ ሁለቱም የግጭቱ ተካፋይ ወገኖች እንዲቀበሉ የማስገደድ ስልጣን የላቸውም፡፡ በሽምግልና የግጭት አፈታት ዘዴ ስምምነት ላይ ለመድረስ የሁለቱ በግጭት ውስጥ የተሳተፉ ወገኖች ፈቃደኝነት የግድ ቢሆንም፤ መፍትሄ ፍለጋ ሒደቱ የሁለቱም የግጭት ተሳታፊ ወገኖች ተሳትፎ የጎላ ስለሆነ አጠቃላይ ድባቡ (setting) የትብብር መንፈስ የሚታይበት የግጭት አፈታት ዘዴ ነው፡፡ በዚህ ዘዴ ብዙውን ጊዜ የሚገኘው ውጤት ሁሉም ወገን ተጠቃሚ የሚሆንበት ነው፡፡

### እርቅ (Arbitration)

እርቅ የግጭቱ ተሳታፊ ወገኖች የግጭታቸውን መነሻ ምክንያት እራሳቸው በጋራ ስምምነት ለመረጧቸው ወይም ተስማምተው መምረጥ ባልቻሉበት ጊዜ በፍትህ አካላት የሚወከሉና ሁለቱንም ወገኖች ያለአድሎ ያገለግላሉ ተብለው ለሚታመንባቸው የቤተዘመድ የሽምግልና ዳኞች በማቅረብ የሚሰጠውን ውሳኔ እንዲቀበሉ የሚደረግበት የግጭት አፈታት ዘዴ ነው፡፡ ሆኖም በእርቅ የግጭት አፈታት ዘዴ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ስለማይሆን ቅር የተሰኘ ወገን ወደ ፍርድ ቤት የመሄድ መብት አለው፡፡ የእርቅ የግጭት አፈታት ዘዴ አጠቃላይ ድባብ በጥላቻ መንፈስ የተሞላ ሲሆን በመፍትሄ ፍለጋ ሂደቱ የግጭቱ ተሳታፊ ወገኖች ተሳትፎ የተገደበ ነው፡፡ በእርቅ የግጭት አፈታት ዘዴ የሚገኘው ውጤት ብዙውን ጊዜ አንድን ወገን ተጠቃሚ ሌላውን ወገን ደግሞ ተጎጂ የሚያደርግ ነው፡፡

### የህግ ድንጋጌ (Adjucation)

የህግ ድንጋጌ የግጭቱ ተሳታፊ ከሆኑት ወገኖች መካከል በአንዱ ወይም በሌላው ወገን አቤቱታ በህግ ስልጣን ለተሰጠው አካል (ፍርድ ቤት) ቀርቦ ይህው ህጋዊ አካል ውሳኔ በመስጠት ግጭቱ መፍትሔ እንዲያገኝ የሚደረግበት የግጭት አፈታት ዘዴ ነው፡፡ የዚህ ዘዴ አጠቃላይ

ድባብ የጠላትነት መንፈስ የሰፈነበት ሲሆን በመፍትሄ መፈለጉ ሂደት ላይም የግጭቱ ተሳታፊ ወገኖች ቀጥተኛ ተሳትፎ የተገደበ ነው። በመሆኑም የግጭቱ ተሳታፊ ወገኖች በፍትህ አካላቱ የሚሰጠውን ማንኛውንም ውሳኔ እንዲቀበሉ የሚገደዱበት የግጭት አፈታት ዘዴ ነው። በህግ ድንጋጌ የሚገኘው ውጤትም አንዱ ወገን ተጠቃሚ ሌላው ወገን ተጎጂ የሚሆንበት ነው።

አንዳንድ የግጭት ዘርፍ ተመራማሪዎች ደግሞ የግጭት መፍቻ ዘዴዎቹ መሰረት ከሚያደርጉት ህግ በመነሳት የግጭት አፈታት ዘዴዎችን ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴ (Cultural Conflict resolution method)፣ ዘመናዊ የግጭት አፈታት ዘዴ (Modern Conflict resolution method) እና ሀይማኖታዊ የግጭት አፈታት ዘዴ (Religious conflict resolution method) በማለት የከፋፈሉም አሉ። ለምሳሌ Assefa (2001,37-39)::

### 3.5.1. ዘመናዊ ዘዴ (Modern Method)

ከመንግስት መዋቅሮች ጋር ተያይዥነት ያለው ነው። ዘመናዊ የግጭት መፈቻ በህግ ባለሙያዎች የረቀቀ፣ ከተለያዩ ሀገራት የተገኙ ልምዶች የተካተቱበት፣ በጽሁፍ የሰፈረና በበላይ ምክር ቤቶች የጸደቀ፣ ለተግባራዊነቱም በዳኝነት (በህግ ሙያ) የሰለጠነ የሰው ሀይል የሚመደብበት እና በአንድ ሀገር ውስጥ በአንድ አይነት ሁኔታ የሚያገለግል ለሁሉም ሰው (ማህበረሰብ) የሚሰራ ነው።

### 3.5.2. ሀይማኖታዊ ዘዴ (Religious Method)[8]

ሀይማኖታዊ የግጭት አፈታት ዘዴ የሚባለው መሰረቱን በታወቁ የአለም ሀይማኖቶች (ክርስትና፣ እስልምና) ወይም በተለያዩ ሀገር በቃል እምነቶች ላይ ያደረገ የግጭት አፈታት ዘዴ ነው።

### 3.5.3. ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴ (Cultural Method)

ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴ የአንድ ማህበረሰብ አባላት በማህበረሰቡ ውስጥ የሚከሰት ማንኛውንም አይነት ግጭት ለመፍታት እና የማህበረሰቡን ሰላምና ደህንነት ለመጠበቅ የሚገለገሉበት ዘዴ ነው። ባህላዊ የግጭት መፍቻ ዘዴ የጽሁፍ መሰረት የሌለው፣ በቃል እና በመከወን ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፍ የማህበረሰቡ መንፈሳዊ ሀብት ነው።

---

[8] በእስልምና ሀይማኖት የትዳርን፣ የፍቺን እና የውርስን ጉዳይ የሚመለከተው የሸሪያ ህግ እና የኦሮሞዎች የቃሉ ስረዓት ለዚህ ጥሩ ምሳሌዎች ይመስሉኛል።

በርካታ የዘርፉ ምሁራን ባህላዊ የግጭት መፍቻ ዘዴ ግጭትን ለመፈታት ከሚፈጀው ጊዜ፣ ግጭቱን ለመፈታት ከሚጠይቀው ገንዘብ፣ ለተቀናቃኞቹ አካላት ከሚሰጠው ነፃነት፣ ካለው ግልጽነት፣ ሶስተኛ ወገኖቹ ግጭትን ለመፍታትና ዘላቂ ሰላምን ለማምጣት ካላቸው ብቃት አንፃር ሲታይ ከዘመናዊው የግጭት መፍቻ ስልት የተሻለ እነደሆነ ይናገራሉ።

Beneman(2007:137) ባህላዊ የግጭት መፍቻ ስልት ከህገመንግስታዊ የግጭት መፍቻ ስልት የተሻለ አማራጭ ነው። ምክንያቱ ደግሞ በዝቅተኛ ወጪ በከፍተኛ ፍጥነት ውጤታማና ዘላቂ መፍትሄ ማስገኘቱ እነደሆነ ያስረዳሉ። Pendergast (2004:405) የአጥቢያ ሽምጋዮች (local mediators) ከማህበረሰቡ ጋር አብረው የኖሩ በመሆናቸው ግጭቱን ለመፍታት የሚያስችል ከዘመናዊ ዳኞች የበለጠ እውቀት እንዳላቸውና ግጭቱንም ከመሰረቱ ማጥፋት እንደሚችሉ ይገልጻሉ።

ከላይ የተጠቀሱትን የግጭት መፍቻ ዘዴዎች ለመጠቀም የግጭቶቹን አይነትና መንስኤ ማወቅ በጣም ጠቃሚ እንደሆነ (Sechellenberg 1996፣13) ያስረዳሉ። ስለዚህ እንደግጭቶቹ አይነት እንደመነሻ ምክንያቶቻቸው እና እነደየግጭቶቹ ሁኔታ ተስማሚ የሆነውን ዘዴ መጠቀም ይገባል። Assefa (2001:387) ባህላዊ ዘዴ ግጭቱን ለመፍታት የተፃራሪ አካላቱን ድርድር (Negotiation) እና በሶስተኛ ወገን መዳኘትን (Mediation) ሊያጠቃልል እንደሚችል ያስረዳሉ።

ባህላዊ የግጭት መፍቻ ስልቶች ልምጥ (Flexible) ናቸው። እንደ ግጭቱ መነሻ፣ እንደ ግጭቱ አይነት፣ እንደ ተቀናቃኞቹ አቋም፣ እንደ ግጭቱ ሁኔታ የተለያዩ ዘዴዎችን ይጠቀማሉ። ዘመናዊው የግጭት መፍቻ ዘዴ ግን የተፃፈ ህግ ላይ የሚመሰረትና ቁጥርና አንቀጽ እየተጠቀሰ የሚደነገግ በመሆኑ ሌሎች ዘዴዎችን አይጠቀምም። ስለዚህ ትክክለኛውን መፍትሄ ላያመጣ ይችላል።

በአፍሪካ ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ ጎሳዎች በውስጣቸው የሚከሰቱ ግጭቶችን ባህላዊ ዘዴዎችን በመጠቀም እየፈቱ የማህበረሰቡን ሰላም ለዘመናት ሲጠብቁ እንደቆዩ (Ogundipe, 1999,41) ይገልፃሉ። በአፍሪካ ባህላዊ የግጭት መፍቻ ዘዴዎች ከማህበረሰቡ ህይወት ጋር በእጅጉ የተሳሰሩ እና በማህበረሰቡ ባህልና ታሪክ ውስጥ ስር የሰደዱ መሆናቸውን (Radar and Karimi) እንደሚከተለዉ ይገልጻሉ።

> Traditional conflict resolution mechanisms in African are generally closely bound with socio-politically and economic realities of the lifestyles of the communities. These mechanisms are rooted in the culture and history of the Africa people, and are in one way or another unique of each community. The customary courts rely on good will of the society to adhere to its ruing (2004, 78)

Malan (1999:1) ይንን ሀሳብ በመደገፍ በአፍሪካ ውስጥ ያሉ ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴዎች በሁሉም ማህበራዊ ተቋማት መሀከል ዘላቂ ሰላምን ለማስፈን እና ባህላዊ እሴቶችን ለመጠበቅ ከፍተኛ ሚና አላቸው። በማህበረሰቡ ውስጥ የሚነሱ ግጭቶችን ሰላማዊ በሆነ መንገድ ለመፍታት የሚያስፈልጉ መቻቻል፣ መነጋገር፣ መደጋገፍ፣ እውነት፣ መከባበርና ነፃነት በአፍሪካ ሃገራት ባህላዊ የግጭት መፍቻ ስልቶች ውስጥ በስፋት እንደሚገኙ ያስረዳሉ።

ኢትዮጵያ በአፍሪካ ማህበረ-ፖለቲካዊ አውድ ውስጥ እንደመገኘቷ በኢትዮጵያም ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴዎች የማህበረሰቡን ሰላምና መረጋጋት ለማስጠበቅ እንደሚያገለግሉ መገመት ይቻላል። በኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኙ የተለያዩ ማህበረሰቦች ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴ ላይ ጥናት ያደረጉ ምሁራን እንዳረጋገጡት የሀገር ሽማሌዎች ህብረተሰቡ ለደንቡ ተገዢ እንዲሆን፣ ደንብ የሚጥሱ በደንቡ መሰረት እንዲሰሩና መልካም ስነምግባር እነዲዳብር በማስተማር ማህበረሰቡን ይመራሉ። ስርዓት የሚጥሰውን ይቀጣሉ፣ ያወግዛሉ፣ ይረግማሉ (ሰለሞን፣ 1999፣የወንድወሰን፣ 1998፣ ብርሃኑ፣ 2002)።

## 3.6. የግጭት አፈታት ዘዴ ከዓለም፣ ከአህጉር አቀፍ ድርጅቶችና ከኢትዮጵያ የህግ ሰነዶች አንፃር

በዓለም ላይ በተለያዩ ምክንያቶች በሀገራት፣ በብሔረሰቦች፣ በጎሳዎች፣ በፖለቲከኞች እና በተቃዋሚ ድርጅቶች መካከል ግጭቶች ይፈጠራሉ። እነዚህን ግጭቶች ለመፍታት የተለያዩ አለም አቀፍ ድርጅቶች፣ የአለም መንግስታት፣ አህጉራት እና ሀገራት መተዳደሪያ ህጎችና ደንቦችን በማውጣት ይሰራሉ። በዚህ ክፍል የተባበሩት መንግስታት ድርጅት፣ የአፍሪካ ህብረትና የኢትዮጵያ የህግ ሰነዶችን ከግጭት አፈታት አንፃር እንመለከታለን።

### 3.6.1. የተባበሩት መንግስታት የህግ ሰነዶች

የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ሁለተኛው የዓለም ጦርነት በሕይወትና በንብረት ላይ ያደረሰው ከፍተኛ ውድመት ዳግመኛ እንዳይከሰት ለመከላከልና የዓለምን ሰላም ለመጠበቅ ሲባል በ1945 እ.ኤ.አ የተመሰረተ ድርጅት ነው። ድርጅቱ ዓለምአቀፍ ሰላምና ደህንነትን ማስከበር፣ ሰላምን ለማደፍረስ የሚደርጉ ሙከራዎችን በጋር መከላከል፣ ፀረ ሰላም እንቅስቃሴዎችን በዓለም አቀፍ ህግ መሰረት መዳኘት፣ እና ግጭቶችን በሰላማዊ መንገድ መፍታት የሚሉ ዓላማዎች እንዳሉት በቻርተሩ (አንቀጽ 1 ቁጥር 3፣ 1945፣1) ላይ ተገልፇል። በተጨማሪም ዓለም አቀፍ የሆኑ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ባህላዊ ችግሮችን መፍታት እና የሰው ልጆች መሰረታዊ ነፃነቶች ያለምንም መድሎ (ልዩነት) እንዲከበሩ የማድረግ አላማም እንዳለው በተጠቀሰው አንቀጽ ተገልጿል። በድርጅቱ የዓለም ሰላምና ደህንነትን የሚያደፈርሱ ድርጊቶችን በመከታተልና በመመርመር የውሳኔ ሀሳብ የማቅረብና የመወሰን ስልጣን የተሰጠው የፀጥታው ምክር ቤት (international security council) ነው (ምዕራፍ 3 አንቀጽ 7)። ድርጅቱ በሀገራት መካከል የሚከሰቱ ግጭቶችን ሰላማዊ በሆኑ መንገዶች፣ በስምምነት፣ በአጣሪ ኮሚቴ፣ በግልግል፣ በእርቅ፣ በዲፕሎማሲያዊ መንገድ እንዲፈቱ ያደርጋል። ድርጅቱ የዓለምን ሰላም በመጠበቅ ያለው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው። ነገር ግን ለባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴዎች የሰጠው ቦታ ከፍተኛ እንዳልሆነ ከዓላማዎቹ እንረዳለን።

### 3.6.2. የአፍሪካ ሕብረት የህግ ሰነዶች

የአፍሪካ ህብረት የሚለውን ስያሜ ከመያዙ በፊት ድርጅቱ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ይባል ነበር። የአፍሪካ አንድነት ድርጅት በ1963 እ.ኤ.አ በአዲስ አበባ ነው የተመሰረተው። የድርጅቱ አላማዎች የአፍሪካ ሀገራትን አንድነትና ወዳጅነት ማጠናከር፣ ትብብሮችን ማዳበር፣ የሕዝቦችን የኑሮ ደረጃ ማሻሻል፣ የአፍሪካ ሀገሮችን ሉዓላዊነትና የግዛት አንድነትን ማስከበር እና ነፃነታቸውን ማስጠበቅ፣ ከመላው አፍሪካ የቅኝ አገዛዝ ስርዓትን ማጥፋት፣የተባበሩት መንግስታት ስምምነቶችና የዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ድንጋጌዎችን ማስከበር እነደሆኑ በቻርተሩ አንቀጽ 2 ቁጥር 1(1963) ላይ ተገልጿል። በአፍሪካ ሀገራት መሀከል በተለያዩ ምክንያቶች የሚከሰቱ ግጭቶች ሰለማዊ በሆነ መንገድ በስምምነት፣ በሽምግልና፣ በእርቅና በዳኝነት መፍታት እንዳለባቸው አንቀጽ 3 ላይ ተቀምጧል።

የአፍሪካ ሕብረት በሚል በ 2000 እ.ኤ.አ በቶጎ ሎሜ የተመሰረተው ድርጅት ከቀዳሚው ድርጅት ከመጠሪያው ባለፈ በዓላማው እምብዛም የተለየ አይመስልም። በዚህ ድርጅት

በቅድሚያ በአፍሪካ ሰላምና ደህንነትን ማስፈን ከፍተኛ ትኩረት እንደተሰጠው በአንቀጽ 3 ላይ ከሰፈሩት ዓለማዎች እንረዳለን፡፡ በአፍሪካ ባህላዊ የግጭት አፈታትን በተመለከተ የተሰሩ ጥናቶች በአፍሪካ ውስጥ የሚኖሩ የተለያዩ ጎሳዎች ባህላዊውን የግጭት አፈታት ዘዴ በስፋት እንደሚጠቀሙ ይናገራሉ፡፡ በሕብረቱ ቻርተር ግን ለነዚህ ዘዴዎች ትኩረት አልተሰጣቸውም፡፡

### 3.6.3. የኢትዮጵያ የህግ ሰነዶች

በኢትዮጵያ ህገ መንግስት፣ የወንጀለኛ መቅጫ እና የፍትሐብሔር ህጎች ተቀርጸው ስራ ላይ ከመዋላቸው በፊት ህዝቡ የሚዳኝበት የህግ ሰነድ ፍትሐ ነገስት ነበር፡፡ ፍትሀ ነገስት ኢትዮጵያዊ መሰረት የለውም፡፡ በ15ኛው ክፍለ ዘመን አካባቢ ከአረብኛ ቋንቋ ወደ ግዕዝ ተተርጉሞ ወደ ኢትዮጵያ የገባ ህግ ነው (አምሳሉ 1976፣63-65) ፍትሐ ነገስት መንፈሳዊና ስጋዊ ህጎች ነበሩት፡፡ ስጋዊ ህጎቹ አካላዊ ቅጣቶችን ያካተቱ ነበሩ፡፡ በጣም ከባድ ለሚባል ጥፋት የሞት ቅጣትም ነበረው፡፡ የሞት ቅጣት የሚታየው የማህበረሰቡን ሰላም፣ የተጎጂዎችን ስነልቦና እና ለጥፋት የሚያነሳሳን ሁኔታ ከመጠበቅ አንፃር ነው፡፡ ምሳሌ የግድያ ግጭት ሲከሰት የአገዳደሉን ሁኔታ፣ ገዳዩ ለግድያ የተጠቀመውን መሳሪያ፣ አነሳሽ ምክንያቶች መሰረት በማድረግ እስከ ሞት ቅጣት የሚወስን ህገ ነበረው (አንቀጽ 40 ቁጥር 7 1958፣544፡555)፡፡ በመቀጠል ባህላዊ የግጭት መፍቻ ተቋማትና ደንቦች በዘመናዊ የኢትዮጵያ የህግ ሰነዶች ውስጥ ምን ቦታ እንደተሰጣቸው እንመለከታለን፡፡

በ1923 ዓ.ም በኢትዮጵያ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ በዘመናዊ መልክ የተቀረጸው ህገ መንግስት ከጃፓን መንግስት የተወሰደ ነው፡፡ ይህ ህገመንግስት ስለባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት የሚያነሳው ምንም አይነት ጉዳይ አልነበረውም፡፡ በ1948 ዓ.ም ተሻሽሎ የወጣው ህገ መንግስት የዳኝነት ሥልጣኑ በህግ ለተቋቋሙ ፍ/ቤቶች የተሰጠና ፍ/ቤቶቹም በህጉ መሰረት በንጉሰ ነገስቱ ስም እንደሚሰሩበት (የኢ.ሕ.መ 1948፣ አንቀጽ 108) ይገልፃል፡፡ ነገር ግን ስለባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓትና ስለባህላዊ ደንቦች ምንም እውቅና አልሰጠም፡፡

በ1980 ዓ.ም በዘመነ ደርግ ኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ የራሷን ህገ መንግስት መቅረጽ ችላ ነበር፡፡ ይህ ህገመንስት አንቀጽ 23 ላይ “መንግስትና ህብረተሰቡ የባህልና የታሪክ ቅርሶችን እዲጠብቁ” የሚል ሀሳብ ቢያሰፍርም ስለባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴ ምንም ያነሳው ሀሳብ የለም፡፡ በ1983 ዓ.ም በተዘጋጀው የሽግግር መንግስቱ ቻርተር ላይም ስለባህላዊ የግጭት መፍቻ ተቋማት እና ደንቦች የተነሳ ጉዳይ አልነበረም፡፡

በ1987 ዓ.ም የጸደቀውና አሁንም በስራ ላይ ያለው የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት እንደቀዳሚዋቹ ሁሉ ስለ ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት በግልጽ ያስቀመጠው ነገር የለም፡፡ ነገር ግን አንቀጽ 78 ቁጥር 5 ላይ "የተወካዮች ምክር ቤትና የክልል ም/ቤቶች የሃይማኖትና የባህል ፍ/ቤቶችን ሊያቋቁሙ ወይም እውቅና ሊሰጡ ይችላሉ፡፡" ስለሚል በተወሰነ መልኩም ቢሆን ከሌሎቹ በተሻለ ለባህላዊ የግጭት መፍቻ ተቋማት ትኩረት ሰጥቷል ማለት ይቻላል፡፡

በ1953ዓ.ም ስራ ላይ በዋለው የፍትሐብሔር ህግ ከሌሎቹ በተሻለ መልኩ ለባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴ ትኩረት ተሰጥቷል፡፡ ምሳሌ በአንቀጽ 4 ተራ ቁጥር 624፣641፣ 676 ላይ በጋብቻ ላይ የሚፈጠሩ አለመግባባቶችን በሽምግልና መፍታት እንደሚቻል ሲገልጽ፤ ውል ባፈረሰ ወገን ላይ ደግሞ የህሊና ጉዳት በሚል በተራ ቁጥር 192 እና 572 ላይ በተገለጸው መሰረት በአገሩ ልማድ ካሳ እንዲከፈል ተደንግጓል፡፡ የጎሳ፣ የመንደር ወይም የህብረት በሆኑ የእርሻ መሬቶች፣ መንገዶችና የውሃ ጉድጓዶች አጠቃቀምና አገልግሎት ላይ የአገሬዎቹ ልማድ የተጠበቀ እንደሆነ በተራ ቁጥር 1589፣ 149፣ ላይ ተጠቅሷል፡፡ በወንጀለኛ መቅጫ ህጉ ላይ ግን ስለበህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴ በግልጽ የተጠቀሰ ነገር የለም፡፡

ከላይ እንደተመለከትነው በ1987 ዓ.ም በጸደቀው ህገ መንግስትና በፍትሐብሔር ህጉ ከሌሎቹ በተሻለ ለባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴ በተወሰነ መልኩም ቢሆን ትኩር ተሰጥቷል፡፡ ነገር ግን ኢትዮጵያ የተለያዩ መንፈሳዊ ባህል ያላቸው ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች የሚገኙባት ሀገር በመሆኗ ለባህላዊው የግጭት አፈታት ዘዴ የተሰጠው ትኩረት ዝቅተኛ ነው ማለት ይቻላል፡፡

### 3.2 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

ኢትዮጵያ የተለያዩ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች የሚኖሩባት ሀገር ናት፡፡ እነዚህ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ኑራቸውን የራሳቸው በሆኑ ባህላዊ መተዳደሪያ ተቋማት፣ ደንቦችና ስርዓቶች ይመራሉ፡፡ ባህላዊ ተቋማቱ፣ ደንቦችና ስርዓቶች በማህበረሰቡ ውስጥ የሚከሰቱ ችግሮችን በመፍታት፣ ሰላምን በመፍጠርና ደህንነታቸውን በመጠበቅ በኩል ከፍተኛ ጠቀሜታ አላቸው፡፡ በኢትዮጵያ ውስጥ ባህላዊ የግጭት አፈታትን በሚመለከት የተለያዩ ጥናቶች ተሰርተዋል፡፡

ይህ ጥናት "የባሌ ኦሮሞ ባህላዊ የግጭት አፈታት" በሚል ርዕስ የቀረበ ነው፡፡ ከዚህ ጥናት ጋር በቀጥታ ተዛማጅነት ያለው ጥናት በትምህርት ክፍሉም ሆነ ከትምህርት ክፍሉ ውጪ ማግኘት አልተቻለም፡፡ ነገር ግን የባሌ ኦሮሞዎችን ባይመለከቱም በሌሎች ማህበረሰቦች

ባህላዊ የግጭት አፈታት ላይ የተሰሩ የተወሰኑ ጥናቶች አሉ፡፡ በመቀጠል በሌሎች ማህበረሰቦች ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት ላይ የተሰሩ ጥናቶችን እንመለከታለን፡፡

ግደይ ደገፉ በ2000 "Traditional mechanisms of conflict resolution in Ethiopia" በሚል ርዕስ መጽሃፍ አሳትሟል፡፡ መጽሃፍ የአራት ብሔረሰቦችን (አማራ፣ ኦሮሞ፣ ትግሬ እና ጉራጌ) ባህላዊ የግጭት መፍቻ ተቋማትን እና የግጭት አፋታት ዘዴን የመረመረ ነው፡፡ የግደይ ስራ የተለያዩ ብሔረሰቦችን ባህላዊ የግጭት አፋታት ዘዴ የተመለከተ ነው፡፡ ትርሲት ግርሻው በ2004 `indigenous conflict resolution mechanisms in Ethiopia" በሚል ርዕስ ለመጀመሪያው ሀገር አቀፍ የፌደራሊዝም ጉባዔ ያቀረበችው ጥናት እንደ ግደይ ጥናት የተለያዩ ብሔረሰቦችን ባህላዊ የግጭት አፋታት ዘዴ የሚያስተዋውቅ ነው፡፡ ይህ ጥናት (የኔ) ከአንድ ብሔረሰብ የአንድን ማህበረሰብ ባህላዊ የግጭት አፋታት ብቻ በጥልቅ የሚመረምር መሆኑ ከሁለቱ ስራዎች የተለየ ያደርገዋል፡፡

ደሳለኝ ጨመዳ እና ሌሎች በ2005 "indigenous systems of conflict resolution in oromia Ethiopia" በሚል ርዕስ ለአንድ አለም አቀፍ ጉባዔ ያቀረቡት ጥናት የኦሮሞ ብሔረሰብ የገዳ ስርዓት ግጭትን በመፍታት ረገድ ያለው ሚና የዳሰሰ ነው፡፡

Dejene Gemechu 2002 "Some Aspects of conflict, and conflict resolution among waliso oromo of eastern Mecha, with particular emphasis on the Guma" በሚል ርዕስ ያቀረበው ጥናት በማህበረሰቡ ውስጥ የሚከሰቱ የግጭት አይነቶችን ያስተዋወቀ እና ግጭቶቹ የሚፈቱበትን ባህላዊ ስርዓት የገለፀ ነው፡፡

የእነ ደሳለኝ እና የደጀኔ ጥናት በኦሮሞ ብሔረሰብ ላይ ያተኮሩ መሆኑ ከኔ ጥናት ጋር ቢያመሳስላቸውም የኔ ጥናት የሚካሔድበት አካባቢ መለየቱ፣ ከገዳ ውጪ ያሉትን ባህላዊ ዘዴዎች መመልከቱ ከነዚህ ጥናቶች የተለየ ያደርገዋል፡፡ ጥናቶቹ ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓትን ቢያነሱም የባህላዊ ስርዓቱን ክዋኔ፣ ለማህበራሰቡ ያለውን ፋይዳ፣ ባህላዊና ማህበራዊ ሙቼቱን፣ ባህላዊ ትዕምርቶችን የመረመሩ አይደሉም፡፡ ይህ ጥናት እነዚህን የሚመለከት በመሆኑም ከነዚህ ጥናቶች ይለያል፡፡

በኢትዮጵያ ስነጽሁፍና ፎክሎር የድህረ ምረቃ መረሃ ግብር ባህላዊ የግጭት አፋታት ስርዓትን በተመለከተ ከ1997ዓ.ም እስከ 2003ዓ.ም ድረስ በሙልጌታ ነጋሳ 1997፣ ነፃነት መኮንን 1998፣ ዮሴፍ ጌትነት 1998፣ ተመስገን ምንዋጋ አለው 1998 አየለ ፍቅሬ 1998፣ ዓለሙ

ካሳዬ 1998፣ አብረሃም ታደሰ 1999፣ አበበ ሀይሉ 1999፣ ደበበ ዘውዱ 2001፣ ዮናስ ተሾመ 2002፣ ሰለሞን ተሾመ 2002 ፣ስለሺ አባተ 2002 ፣ብርሃን አስፋው 2002 እና ሐፍታይ 2003 በአጠቃላይ አስራ ሰባት ጥናቶች ቀርበዋል። የሁሉም ጥናቶች ትኩረት ባህላዊ የግጭት አፈታት መሆኑ ከዚህ ጥናት ጋር ያመሳስሾዋል። የሰለሞን ተሾመ ጥናት ትኩረት የግድያ ግጭት (የደም ማድረቅ እርቅ) ነው። የኔ ጥናት ግን ከግድያ ግጭት በተጨማሪ በባሌ ኦሮሞ ማህበረሰብ ውስጥ የሚከሰት ማንኛውም ግጭት እና ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት የሚመለከት በመሆኑ ከነዚህ ጥናቶች ይለያል። ከዚህ በተጨማሪ የሰለሞን ተሾመ ጥናት በአንድ አካባቢ የሚኖሩ የሁለት ብሔረሰቦችን (አማራና ኦሮሞ) የግድያ ግጭት ባህላዊ አፈታት በንጽጽር የሚያጠና በመሆኑ ከዚህ ጥናት ይለያል።

የነፃነት፣ የተመስገን፣ የየወንድወሰን፣ የሐፍታይ እና የብርሃን ጥናቶች ትኩረት ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት መሆን ከዚህ ጥናት ጋር ያመሳስላቸዋል። ነገር ግን ይህ ጥናት ከባህላዊ የግጭት አፈታቱ ስርዓት በተጨማሪ ስነቃል በግጭት አፈታት ስርዓት ላይ ያለውን ፋይዳ የሚመለከት መሆኑ የተለየ ያደርገዋል።

ሰለሞን ሳህሌ 1998 ባህላዊ የግጭት አፈታት በሲቡ ሲሬ ኦሮሞዎች በሚል ርዕስ የቀረበው ትናታዊ ጽሁፍ የሲቡ ሲሬ ኦሮሞዎች ባህላዊ የግጭት አፋታት ዘዴን በመጠቀም በውስጣቸው የሚከሰት ማንኛውንም ዓይነት ግጭት የሚፈቱ መሆናቸውን አመላክቷል። ባህላዊ ስርዓቱ ከሰውና ከእንስሳት ጉማ፣ ከባልና ሚስት ጠብ እንዲሁም ከጠለፋ ወንጀል አንፃር ምን እንደሚመስ አሳይቷል። በማህበራሰቡ ውስጥ የተለያዩ ምክንያቶች የሚነሱ ግጭቶችን ለመፍታት የሚያስገለግሉ ሽማግሎዎችን ብዛት ገልጿል። የአገር ሽማግሌዎች በማህበረሰቡ ውስጥ የሚከሰቱ ግጭቶችን ለመፍታት ምን አይነት ስልቶችን እንደሚጠቀሙና ባህላዊ የግጭት አፈታቱ ምን እንደሚመስል አሳይቷል። የሰለሞን ጥናት በኦሮሞ ብሔረሰብ ላይ ያተኮረ መሆኑ ከኔ ጥናት ጋር ቢያመሳስለውም የኔ ጥናት የሚካሔድበት አካባቢ መለየት፣ ከገዳ ውጪ ያሉትን ባህላዊ ዘዴዎች መመልከቱ ከዚህ ጥናት የተለየ ያደርገዋል።

አየለ ፍቅሬ 1998 ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴ በባህር ዳር ነገደ ወይጦ ኅብረተሰብ በሚል ርዕስ ባቀረበው ጥናት በባህር ዳር ከተማ ውስጥ የሚኖሩ ነገዴዎች በመካከላቸው እና ከሌሎች ነዋሪዎች ጋር የሚፈጠረውን ግጭት በባሕላዊ መንገድ እንዴት እንደሚፋቱ አሳይቷል። የነገደ ወይጦ ህብረተሰብ ለግጭት የሚሰጠው ብያኔ በህበረተሰቡ ውስጥ የሚከሰቱ የግጭት አይነቶች

ጠብ እና ደም/ግድያ በማለት እንደሚከፈል ገልጿል፡፡ የግጭት መፍቻ ዘዴዎቹ ማስታረቅ፣ ፍቺ እና አካባቢ ማስለቀቅ እንደሆኑ ጠቁሟል፡፡ እንዲሁም ፎክሎር በህብረተሰቡ ውስጥ ግጭትን ለመፍታት ያለውን አስተዋጽኦ ገልጿል፡፡

አየለ የተጠቀመው የጥናት ዘዴ (descriptive study) ገላጭ ዘዴን ብቻ ነው፡፡ ዘዴዎችን ማስተጋገዝ (triangulate) ጥናቱን የተሻለ ያደርጋል የሚል እምነት አለኝ፡፡ መረጃን ለመሰብሰብ የተጠቀመው ዘዴ የጽሁፍ መረጃዎችን እና ምልከታን ነው፡፡ ይህ ማለት ከመስክ መረጃን ለመሰብሰብ የተጠቀመው ምልከታ ብቻ ነው፡፡ ሙሉ የሆነ ዘዴ የለም ሁሉም የራሱ ቀርነት አለው ይህን ክፍተት ደግሞ መሙላት የሚቻለው ዘዴዎችን በማስተጋገዝ ነው፡፡ በአንድ ዘዴ ብቻ የተሰበሰበ መረጃ ሙሉ ነው ለማለት ይከብዳል፡፡

ከላይ የቀረቡትን ጥናቶች Conceptual framework ስንመለከት እንደ ጥናት ዓላማቸው የግጭትን ምንነት ብያኔ፣ የግጭት መከሰቻ መንስኤዎች፣ የግጭት አይነቶች እና አፈታት ዘዴዎችን በስፋት ተመልክተዋል፡፡

በንድፈሀሳብ መሰረት (Theoretical framework) በሁሉም ጥናታዊ ጽሁፎ ለጥናቱ የተጠቀሙት ቲዎሪ አልተገለፀም፡፡ ነገር ግን ሙሉ ጥናት በጥንቅቄ ሲነበብ ለጥናቱ የተጠቀሙት የቲዎሪ መሰረቶች ይታወቃሉ፡፡ እነዚህ ጥናቶች እንደ ርዕሳቸው እንደ ጥናት አላማቸው መቀራረብ ለጥናቱ የተጠቀሙት ቲዎሪ/ዎችም ተመሳሳይ ናቸው፡፡ በጥናቶቹ ውስጥ አውዳዊ (contextual) እና (functional) ተግባራዊ ቲዋሪዎችን በብዛት ተጠቅመው ይገኛሉ፡፡ የኔ ጥናት አውዳዊ (contextual)፣ ክዋኔ(performance) እና ተግባራዊ functional ቲዋሪዎች መሰረት ያደርጋል::

የተለያዩ theory ዎችን triangulate በማድረግ ተጠቅመዋል፡፡ ነገር ግን የtheory ዎቹን ትኩረት በሚገባ ተከትለዋል ለማለት ይከብዳል፡፡ የcontextual አውዳዊ ትውር አቀንቃኞች የfolklore text ከ context ተለይቶ መታየት እንደሌለበት ይገልፃሉ፡፡ የዚህ ትውር የመስክ ትኩረቶች የክዋኔ አውዶች ናቸው፡፡ እነዚህን አውዶች ማህበራዊ እና ባህላዊ በሚል ይከፈላሉ፡፡ በእያንዳቸው ስር ሶስት የአውድ እና የግንኙነት ደንቦች ይገኛሉ፡፡ ማህበራዊ አውድ ሁኔታዊ አውድን፣ ማህበራዊ መዋቅርን፣ የገቢ ምንጭን (መተዳደሪያን) ይይዛል፡፡

ጥናቶቹ ከማህበራዊ አውድ social organization እና economic base በደንብ በስፋት ተመልክተዋል፡፡ ሁኔታዊ አውድን ግን ትኩረት የሰጡት አይመስልም፡፡ ባህላዊ አውድንም ተመልክተዋል ማለት ይከብዳል፡፡

Function ሲመለከቱ ባህላዊ የግጭት መፍቻ ስርዓቱ ማህበራሰቡን እንደሚጠቅም፡፡ ጊዜና ገንዘብ እንደሚቆጥብ፡፡ የማህበረሰቡ አባላት ተስማምተውና ተቻችለው እንዲኖሩ ያደርጋል፡፡ በመካከላቸውም የሚከሰት ማንኛውም ግጭት በሰላማዊ መንገድ እንደሚፈታ ገልፀዋል፡፡

ስነቃል (Oral literature) ግጭትን በመፍታት ያለውን ሚና በገለፁበት ክፍል ግን ስነቃል ግጭትን በመፍታት ረገድ ያለውን ሚና ከማሳየት ይልቅ አንዳንዶቹ ስለግጭት ምንነት፣ ስለሽማግሌዎች መከበር የሚገልጹ ወዘተ. እያሉ ወደ መመደብ ያዘነበሉ ናቸው፡፡ አንዳንዶቹ ደግሞ ስነቃል ግጭትን በመፍታት ያለው ፋይዳ ትንተና ብለው ትንተናቸው ግን ስነቃሉ (ተረቱ፣ ምሳሌያዊ ንግግሩ) የያዘውን ጭብጥ ይሆናል፡፡ በአብዛኞቹ ጥናቶች ስነቃሉ ከመከሰቻ አጋጣሚው አንፃር አልተተነተነም፡፡

Performance የተመለከቱትም ቅድመ እርቅ፣ በእርቅ ጊዜ እና ድህረ እርቅ ያለውን ቅደም ተከተል ከመግለፅ ባለፈ ጠለቅ ብሎ እያንዳንዱን ሁኔታ የመረመሩ አይደሉም፡፡ event of performance situation የሚያጠቃልላቸውን ሁሉንም ነገሮች በጥልቀት ተመልክተው የተተነተኑ ናቸው ማለት አይቻልም፡፡

# 4. የባሌ ኦሮሞ ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት

የኦሮሞ ህዝብ እንደሌሎች የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች የሚታወቅባቸው ቋንቋ፣ ታሪክ እና ባህል አሉት፡፡ የኦሮሞ ህዝብ መልከዓምድራዊ አሰፋፈርን፣ ጎሳዊ የደም ትስስርን እና ጥንታዊ የባህልና የፖለቲካ አደረጃጀትን መሰረት አድርገው በተዋቀሩ በርካታ አበይት ጎሳዎች የተከፋፈለ ነው፡፡ ከእነዚህ አበይት ጎሳዎች ውስጥ አንዱ የአርሲ ጎሳ ነው፡፡ የአርሲ ጎሳዎች በስፋት ሰፍረው ከሚገኙበት ስፍራዎች አንዱ የባሌ ዞን ነው፡፡ በባሌ ዞን የሚኖሩ ኦሮሞዎች እንደሌሎቹ የኦሮሞ ማህበረሰቦች ተለይተው የሚታወቁባቸው የተለያዩ ቁሳዊና መንፈሳዊ ባህሎች አሏቸው፡፡ የባሌ ኦሮሞ ማህበረሰብ ለረጅም ዘመን ከትውልድ ወደ ትውልድ እያስተላለፈ ሲጠቀምባቸውና ሲጠብቃቸው ከቆዩ በርካታ መንፈሳዊ ባህሎች ውስጥ አንዱ ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት ነው፡፡ በማህበረሰቡ ውስጥ በተለያዩ ምክንያቶች የሚከሰቱ የተለያዩ ግጭቶችን (በተለይ የግድያን) ለመፍታት የሚጠቀሙበት ባህላዊ ስርዓት 'ሴረ ጉማ' (seera Gumaa) ይባላል፡፡

በዚህ ክፍል የባሌ ኦሮሞ ማህበረሰብን ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት (በተለይ የግድያን) እንመለከታለን፡፡

## 4.1 የጉማ ምንነትና ታሪካዊ ዳራ

### 4.1.1 ሴረ ጉማ ምንድነው?

ሴረ ጉማ (Seera Gumaa) "Seera" እና "Gumaa" ከተሰኙ ሁለት የኦሮምኛ ቃላት የተገነባ ቃል ነው፡፡ ሴረ (Seera) ደንብ ፣ ስርዓት ፣ የአሰራር ዘዴ ፣ ልማዳዊ ህግ ከሚሉት የአማርኛ ቃላት እና ሀረጋት ጋር ተመሳሳይነት ወይም ተቀራራቢነት አለው፡፡

ሴረ የኦሮሞ ማህበረሰብ የሚተዳደርበት፣ ባህላዊ፣ ስነምግባራዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች የሚዳኙበትና በማህበረሰቡ ውስጥ የሚከሰቱ መሰናክሎችና ግጭቶች የሚፈቱበት ቃላዊ ደንብ ነው፡፡ የባሌ ኦሮሞዎች ሴረን የሚደነግጉበትና የሚፈፅሙበት የአሰራር ስልቶች አሏቸው፡፡ ከልዩ ልዩ የሴረ አይነቶች ውስጥ አንዱ ሴረ ጉማ ነው፡፡

ጉማ ምንድነው? ለሚለው ጥያቄ የተለያዩ ብያኔዎችን እናገኛለን፡፡

በ1996ዓ.ም የታተመው የኢትዮጵያ ህዝቦች አካዳሚ የኦሮምኛ መዝገበ ቃላት ጉማን እንደሚከተለው ይገልፀዋል፡፡

"Gumaa (ma). Gatii ykn baasaa nabsee nama harkatti baddee." (ጉማ በእጅ ለጠፋ ነፍስ የሚከፈል ክፍያ ወይም ዋጋ ነው)፡፡ ጉማ ማውጣት ደግሞ Gumaa baasuu (go)1. Nabsee nama harkatti baddeeti gatii kennu (በእጅ ለጠፋ ነፍስ ዋጋ መክፈል) ፣ 2 nama fira namaa ajjeese jalaa fira isaa ajjeesani gado ofii baasu . (ወገን ዘመድን የገደለን ሰው ወይም የገዳይን ዘመዶች በመግደል ሀዘንን ማውጣት ፣ ደም መመለስ)

መዝገበ ቃላቱ ለጉማ የሰጠው ብያኔ ውሱን ነው፡፡ ጉማ በእጅ ለጠፋ ነፍስ ብቻ የሚሰጥ (የሚከፈል) አይደለም፡፡ ከመረጃ አቀባዮቼ ባገኘሁት መረጃ መሰረት ጉማ ብዙ ግዜ ለነፍስ ግድያ የሚከፈል ቢሆንም ከነፍስ ግድያ ውጪ ለአካል ጉዳት እና ለሞራል መነካትም ይከፈላል፡፡[9] መዝገበቃላቱ ለጉማ ማውጣት የሰጠው ሁለተኛ ብያኔም በኦሮሞ (በተለይ በባሌ ኦሮሞ) ማህበረሰብ ውስጥ የተለመደ አይደለም፡፡ በባሌ ኦሮሞዎች ባህል መሰረት በቂም በቀል ተነሳስቶ ሰው መግደል ውጉዝ ነው፡፡ በተለይ ራያ አንባ (Rayaa Anbaa) የገለልተኛ ጎሳ ሽማግሌዎች መሀል ከገቡ በኃላ፡፡

በኦሮሚያ ባህልና ማስታወቂያ ቢሮ በ1991ዓ.ም "SADAA" በሚል ርዕስ በታተመ መፅሀፍ ላይ ደግሞ የጉማ ብያኔ እንደሚከተለው ተገልጿል፡፡

> Gumaa yoo jennu jireenya hawaasummaa saba Oromoo keessatti iddoo olaanaa kan qabu Seera Duudhaati (social institution) jechuun ni danda'ama. Namoota lama gidduutti, maatiifi gareewwan adda addaa gidduutti wall dhabiinsa uumamuuń kan ka'e dhiigni dhangala'ee lubbuun nama yoo darbe dhugaan qulqullaa'ee, araarri bu'ee nagaan mirkanaa'ee yaanni firoomaafi jaalalaa akka dagaagu kan gargaru tooftaa gadoofi haaloo ittiin haqanii mala jireenyaa akka kan ittiin uumaniidha(1991፡ 39 ).

[9] አቶ ከድር ጀማል፣ ወ/ሮ በድሪያ አወል፣ አቶ ቲልሞ ሲዶ፣ የቃላሚ ቡድን ውይይት፣ ሚያዝያ 28፣ 2003፣ ጎባ፡፡

> ጉማ በኦሮሞ ማህበረሰብ ማህበራዊ ህይወት ውስጥ ከፍተኛ ቦታ የሚሰጠው ማህበራዊ ተቋም ነው ማለት ይቻላል፡፡ በሁለት ሰዎች መሀከል ፣ በቤተሰብና በተለያዩ ቡድኖች መሀከል በሚከሰት ግጭት ምክንያት ደም ሲፈስና የሰው ነፍስ ሲጠፋ ፣ እውነታውን በማጣራት ፣ እርቅ በማውረድ ፣ ሰላም በማስፈን የዝምድና እና የሰላም መንፈስ እንዲወርድ በማድረግ የሀዘንና የበቀልን መንፈስ በማስወገድ ሰላማዊና የተረጋጋ ህይወት የሚፈጠርበት ስርዓት ነው፡፡

ይህ ብያኔ ጉማ ምን እንደሆነ በደንብ የገለፀው ይመስላል፡፡ ከመረጃ አቀባዮቼ ያገኘሁትም የጉማ ብያኔ ከዚህ የራቀ አይደለም፡፡ የጉማ ስርዓት ግጭት ውስጥ የገቡ ሰዎችን ፣ ቡድኖችንና ጎሳዎችን ፊት ለፊት በማምጣት ፣ በእውነትና በሃቅ ላይ በመመስረት ፣ ግድያ ወይም ጉዳት ከፈፀመው ላይ (ከብት ፣ ገንዘብ ፣ መሬት) በመቀበል ለተበደለው በመስጠት ፣ የተሳሳተውን በመመምከር ፣ የጥላቻ ፣ የበቀልና የሀዘን መንፈስን በማጥፋት ፣ የዝምድና ፣ የፍቅር እና የወዳጅነት መንፈስን መፍጠሪያ ስርዓት ነው፡፡

### 4.1.2 የጉማ ታሪካዊ ዳራ

የጉማ ስርዓት መቼ ፣ የትና በማን እንደተጀመረ በእርግጠኝነት መናገር ባይቻልም በጥንታዊ የኦሮሞ አባቶች አማካኝነት ኦሮሞዎች መካከል በቂም በቀል ሳቢያ ሰላም እንዳይደፈርስ ለማድረግ የተደነገገ ደንብ እንደሆነ እንገነዘባለን፡፡

ከመረጃ አቀባዮቼ [10]ባገኘሁት መረጃ መሰረት በድሮ ጊዜ በጉማ ስርዓት የሰው ነፍስ ላጠፋ የተቀመጠው ቅጣት የሞት ቅጣት ነበረ፡፡ ሰው የገደለ ይገደላል፡፡ በሒደት ግን ሰው የገደለ ሰው በሞት መቀጣቱ ቀርቶ በመሬት ፣ በከብትና በገንዘብ እንዲቀጣ እየተደረገ መጥቷል፡፡ የጉማ ስርዓት ከሞት ቅጣት ወደ ከብት ፣ መሬትና ገንዘብ የተቀየረበት ጊዜ በውል አይታወቅም፡፡

የሰውን ነፍስ በከብት የመተካቱ ስርዓት (seera daloo) 'የዳሎ ስርዓት' በመባል ይታወቃል፡፡ ከዳሎ ስርዓት በፊት የነበረው (የሰውን ነፍስ በሰው ነፍስ የመመለስ) ስርዓት (seera qucee) 'የቁጬ' ስርዓት ይባል ነበር፡፡ የቁጬ ስርዓት በአንድ ጊዜ የሁለት ሰው ነፍስ ስለሚያሳጣ ነው በዳሎ ስርዓት የተቀየረው፡፡ አሁን የሚሰራበት ስርዓት የዳሎ ስርዓት ቢሆንም ሰው የተገደለበት ጎሳ ወይም ቤተሰብ በገለልተኛ ወገን ሽማግሌዎች አማካኝነት ከገዳይ ጎሳዎች የሚጠይቀው ከብት፣ ገንዘብ ወይም መሬት አይደለም፤ እንዲሰጣቸው የሚጠይቁት የገዳዩን ሰው ነፍስ ነው፡፡

---

[10] አቶ በዳሶ በልዳ፣ አቶ ሀሰን አቢዮ ሚያዝያ 27፣ 2003 ሲናና እና ጎባ፡፡

በዚህ ጊዜ የገዳይ ጎሳዎች በጉማው ስርዓት ፈፃሚ ሽማግሌዎች አማካኝነት Daloo ይጠይቃሉ፡፡ ሽማግሌዎች የሟች ቤተሰቦችን (Naaf dali, horitti naa geedari) በክብት ቀይሩልን በማለት ይለምናሉ፡፡ ከዚህ በኋላ የጉማ ማውጣቱ ስርዓት ይከናወናል፡፡

ቀደም ብለን ለመግለፅ እንደሞከርነው ጉማ በነፍስ ማጥፋት (ለግድያ) ብቻ የሚከፈል ስጦታ አይደለም፡፡ ጉማ ከነፍስ ማጥፋት በተጨማሪ ለሞራል መንካትና ለአካል ማጉደልም ይከፈላል፡፡ ጉማ የሚወጣው ለሰው ልጅ ብቻም አይደለም ለእንስሳትም ጉማ ይከፈላል፡፡ ከዚህ በመቀጠል የጉማ አይነቶችን እና የጉማውን አፈፃፀም እንመለከታለን፡፡

### 4.1.3 የጉማ አይነቶች

#### 4.1.3.1. የእንስሳት ጉማ

በዚህ ንዑስ ክፍል በቤትና በዱር እንስሳት ላይ ጉዳት ሲደርስ የሚከፈለውን የጉማ አይነት እና አፈፃፀም እንመለከታለን፡፡

በባሌ ኦሮሞዎች ዘንድ የእንስሳት ጉማ 'ባሳ' (Baasa) ይባላል፡፡ ባሳ ማለት ማውጣት ማለት ነው፡፡ አንድ ሰው የቤትም ይሁን የዱር እንስሳትን ያለአግባብ የደበደበ ወይም የገደለ እንደሆነ ጉማ እንዲከፍል ይደረጋል፡፡ ለዱር አራዊት እና ለቤት እንስሳት የሚከፈለው ጉማ የተለያየ ነው፡፡ በመቀጠል በባሌ ኦሮሞዎች ባህል መሰረት ጉማ የሚከፈልባቸውን የቤት እንስሳት እና የዱር አራዊቶች፣ የጉማውን አይነትና አሰጣጥ እንመለከታለን፡፡

ሀ) የቤት እንስሳት ጉማ

የቤት እንስሳት ለአካባቢው ማህበረሰብ የገቢና የምግብ ምንጭ ፣ ማጓጓዣና ጠባቂ በመሆናቸው ከፍተኛ ጠቀሜታ አላቸው፡፡ ጠቀሜታቸውም በባለቤቱ ብቻ የተገደበ አይደለም፡፡ የአካባቢው ማህበረሰብ ለእርሻ በሬ ፣ ለጭነት አህያ ፣ ፈረስ ፣ በቅሎ ይዋዋል፡፡ አንድ ሰው የተዋሰውን እንስሳ ከደበደበ ወይም ከገደለ ጉማ ይከፍላል፡፡ በሌላም ምክንያት የሰው ከብት ከገደለ ጉማ ይከፍላል፡፡ የቤት እንስሳት የጉማ ዋጋ የተለያየ ነው፡፡ በባሌ ኦሮሞዎች ዘንድ ለእንስሳት የሚሰጠው ጉማ በአብዛኛው በተደበደበው ወይም በተገደለው እንስሳ ምትክ የዛኑ እንስሳ አይነት መስጠት ነው፡፡ ምሳሌ በሬ በከፍተኛ ደረጃ የደበደበ ወይም የገደለ በሬ ፣ እርጉዝ ላም የገደለ እርጉዝ ላም ፣ በግ የገደለ በግ እንዲሰጥ ይደረጋል፡፡

በባሌ ኦሮሞዎች ባህል ለየት ያለ ጉማ የሚከፈልባቸው ወይፈን እና ውሻ ናቸው፡፡ አንድ ሰው የሌላ ሰው ወይፈን ቢገድል ከላይ እንደተመለከትነው ሌላ ወይፈን አይደለም የሚከፍለው፡፡ በማህበረሰቡ ውስጥ አንድ ወይፈን ቢያንስ ስምንት ወይፈኖች ያስወልዳል ተብሎ ስለሚታመን ወይፈን የገደለ (የደበደበ) ሰው ስምንት ከብቶች እንዲከፍል ይደረጋል፡፡

የውሻ ጉማ አንድ ሰው የሰው ውሻ ከገደለ መጀመሪያ ለውሻው ባለቤት ስምንት ጡጢላ(ቡችላ) እንዲሰጥ ይደረጋል፡፡ ከዚያም የውሻው ደም እንዲለቅለት ስምንት ወንዝ በእግሩ እንዲያቋርጥ ይደረጋል( አቶ ሽምሰዲን ሺፋ፣ አቶ ጅይሉ አማን፣ ሚያዝያ 20፣ 2003፣ ሲናና )፡፡

## ለ) የዱር አራዊት ጉማ

በባሌ ኦሮሞዎች እምነት ቁም የሚይዙ ፣ ለበቀል የሚነሱ የዱር አራዊት አሉ፡፡ እነዚህን የዱር አራዊት የገደለ ያቆሰለ ሰው ጉማ ማውጣት አለበት፡፡ ጉማ ከሚከፈልባቸው የዱር አራዊት መካከል አንዱ ጅብ ነው፡፡ ጅብ የደበደበ ወይም የገደለ ሰው ጅብ ይኖርበታል ተብሎ በሚገመት አካባቢ አንድ በግ አርዶ ስጋውን መጣል ይጠበቅበታል፡፡

### 4.1.3.2. የሰው ልጅ ጉማ

(Gumaa ilma Nama )

ጉማ በአብዛኛው ለነፍስ ግድያ የሚሰጥ ክፍያ (የደም ካሳ) ቢሆንም ከነፍስ ግድያ ባለፈ ለሞራል መነካትና ለአካል ጉዳትም እንደሚከፈል ቀደም ተብሎ ተገልጿል፡፡ በዚህ ክፍል ከሰው ልጅ ጋር በተያያዘ የሞራል እና የአካል ማጉደል ጉማን እንመለከታለን፡፡

## ሀ) የሞራል ጉማ ( Gumaa Hamilee ilma Nama )

የሞራል ጉማ የሚከፈለው አንድ ሰው ወይም ቡድን ሌላውን ሰው ወይም ቡድን ሲሰድብ፣ ሲያንቋሽሽ፣ ሲያስፈራራ፣ ስም ሲያጠፋ፣ ሚስጢር ሲያወጣ፣ ከሌላ ጋር ሲያጣላ ወዘተ. ነው፡፡ የሞራል ጉማ በሁለት ይከፈላል፡፡ እነሱም 'ጎራ' (GORA)ና 'ሰዴታ' (SADDEETA) ናቸው( አቶ ጃርሶ በልዳ፣ አቶ ሀጂ በከር፣ሚያዝያ 23፣ 2003፣ ጎባ )፡፡

GORA፡- ጎራ በሴት ምክንያት ለሚከሰት የሞራል መነካት የሚከፈል ጉማ ነው፡፡ የሰው ሚስት የቀማ፣ የደፈረ፣ ልጃገረድ የደፈረ፣ የጠለፈ የሚከፍለው ጉማ ጎራ ነው፡፡ በወንጀሉ አፈፃፀም ላይ ተመስርቶ ሞራሉ ለተነካ ሰው የሚከፍለው ጉማ እስከ አስር ከብት ሊደርስ ይችላል፡፡

SADDEETA:- ሰዴታ የሚባለው አንድ ሰው የገዛ ጎሳውን ፣ ሲዋሽ ፣ በውሸት ሰዎችን ሲያጋጭ ፣ ሲወነጅል ፣ ጎሳን ሲያቃልል ፣ የጎሳን ሚስጢር ሲያወጣ የሚቀጣበት ነው፡፡ ይህ ስርዓት አሁን አሁን እየቀረ እንደመጣ ይነገራል፡፡ ሰውን ያንኳሰሰ፣ የሰደበ፣ የሰረቀ፣ ለቤተሰብ አልታዘዝ ያለ በሙሉ በዚህ (ሰዴታ) ነው የሚቀጣው፡፡

ለ) የአካል ማጉደል ጉማ (Gumaa Miidha Qaama ilma Nama)

መረጃ አቀባዮቹ እንደነገሩኝ ጉማ የሚከፈልባቸው የሰው ልጅ አካላት 360 ናቸው፡፡ ለተጎዳ አካል የሚከፈለው ጉማ የተለያየ ነው፡፡ የአካል ጉማ ከሚለያይባቸው ምክንያቶች ውስጥ የተጎዳው የሰውነት አካል ከሌሎቹ አካላት በተሻለ በግልፅ የሚታይ ጠቀሜታ ሲኖረው፣ የጎደለው አካል ያለው ሁኔታ (ማስቀየም)ና የጎደለው አካል በማህበረሰቡ ውስጥ የሚፈጥረው የሞራል ጉዳት ይጠቀሳሉ፡፡

በባሌ ኦሮሞዎች ዘንድ በጭንቅላት፣ በአይን፣ በጆሮ፣ በአፍንጫ፣ በእጅ፣ በእግር፣ በጥርስ ላይ ለሚደርስ ጉዳት ከፍተኛ ጉማ ይከፈላል፡፡ በማህበረሰቡ በጣም የሚወገዙ ቅጣታቸውም ከፍተኛ የሆነ የአካል ጉዳቶች የሴት ልጅን ጡት እና የወንድን ብልት መቁረጥ ናቸው፡፡

የሴት ጡት የቆረጠ ሰው የአርሲን ሁለት ልጆች ሲኮ እና መንዶን (siikko fi mando) እንደገደለ ስለሚቆጠር በጣም ይወገዛል፡፡ ቅጣቱም በከብትና በገንዘብ የሚተመን አይደለም፡፡ በቀደመው የጉማ ስርዓት እንዲህ ያደረገ ሰው የሚቀጣው በሞት ነበር፡፡ የወንድ ብልት የቆረጠም በጣም ይወገዛል፣ ጡት ከቆረጠ አይለይም፡፡

ሐ) የግድያ ጉማ (Guma Lubbuu (nafsee))

የግድያ ጉማ 'ጉማ ሉቡ ወይም ነፍሴ' (Gumaa Lubbuu /nafsee) አንድ ሰው ወይም ቡድን ሌላውን ሰው ሲገድል ላጠፋው ነፍስ ምትክ ከብት ወይም ገንዘብ እንዲሰጥ ይደረጋል፡፡ የግድያ ጉማ በእጅ ለጠፋ ነፍስ የሚከፈል ዋጋ ወይም የደም ካሳ ነው፡፡

የግድያ ጉማን "የባሌ ኦሮሞዎች ባህላዊ የግድያ ግጭት አፈታትን" በምንመለከትበት ምዕራፍ በስፋት የምናየው ይሆናል፡፡ በመቀጠል ከላይ የተጠቀሱትን የጉማ አይነቶች (ከግድያ ውጪ) ለመፍታት የሚገለገሉበትን ተቋማትና የተቋማቱን ሚና እንመለከታለን፡፡

## 4.2 የባሌ ኦሮሞ ባህላዊ የግጭት መፍቻ ተቋማት

የባሌ ኦሮሞዎች በማህበረሰቡ የዕለት ተዕለት ህይወት ውስጥ በተለያዩ ምክንያቶች የሚከሰቱ ግጭቶችን ለመፍታት የሚጠቀሙባቸው ባህላዊ ተቋማት የሀገር ሽማግሌዎች (jaarsa Biyyaa) እና የገለልተኛ ጎሳ ሽማግሌዎች (Rayyaa Anbaa) ናቸው፡፡ ተቋማቱ የሚመለከቱት ጉዳይና የሚቋቋሙበት ሁኔታ የተለያየ ነው፡፡ የገለልተኛ ጎሳ ሽማግሌዎች (Rayyaa Anbaa)የግድያ ግጭትን ነው የሚመለከቱት፣ የሚመርጡት ከሟች እና ከገዳይ ጎሳ ውጪ ከሆነ ጎሳ ነው፡፡ ስለ ራያ አምባ የባሌ ኦሮሞዎች ባህላዊ የግድያ ግጭት አፈታትን በምንመለከትበት ምዕራፍ በስፋት የምናይ ይሆናል፡፡ በዚህ ክፍል የሀገር ሽማግሌዎች (Jaarsa Biyyaa) የሚቋቋሙበትን ደረጃ ፣ የሚመለከቷቸውን ጉዳዮችና የሚመርጡበትን መስፈርት እንመለከታለን፡፡

### 4.2.1 የሀገር ሽማግሌ ( Jaarsa Biyyaa )

የሀገር ሽማግሌ የሚባለው ባህላዊ የግጭት መፍቻ ተቋም በማህበረሰቡ ውስጥ በተለያዩ ደረጃዎች በመቋቋም በማህበረሰቡ ውስጥ የሚከሰቱ ግጭቶችን በመከላከል ፣ በመቆጣጠርና በመፍታት ፣ ሰላም እና መረጋጋት እንዲኖር ፣ ሰዎች በሰላም ወጥተው እንዲገቡ ፣ ሀይል ያለው የሌለውን እንዳይጎዳ ፣ ሴቶች እንዳይበደሉ ፣ ንብረት እንዳይዘረፍ ፣ ውርስ በስርዓት እንደፈፀም ወዘተ. በማድረግ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል፡፡

የሃገር ሽማግሌዎች ተቋም በማህበረሰቡ ውስጥ በተለያዩ ደረጃዎች ማለትም በቤተሰብ (Warraa) ፣ በአካባቢ (Ganda) ፣ በጎሳ (Gosa) ደረጃ ይቋቋማሉ( አቶ ከድር ጀማል፣ አቶ ቲልሞ ሲዴ፣ቃለመጠይቅ ሚያዝያ 27፣ 2003፣ ጎባ )፡፡

### 4.2.2 የቤተሰብ ሽማግሌ ( Jaarsa Warraa )

የቤተሰብ ሽማግሌዎች በቤተሰብ (በቤተ ዘመድ) መሀከል የሚከሰትን ግጭት ይፈታሉ ፡፡ ብዙ ጊዜ ከውርስ ጋር ፣ ከባልና ሚስት ጋር የተያያዙ ግጭቶች በዚህ ተቋም መፍትሔ ያገኛሉ፡፡

በአጠቃላይ በቤተሰብ (በዘመዳሞች) መሀከል የሚነሳ ግጭትን ለመፍታት የሚያገለግል ተቋም ነው፡፡ በቤተሰብ ሽማግሌዎች እልባት ያላገኘ ጉዳይ ወደ አካባቢ ሽማግሌዎች (Jaarsa Ganda) ይመራል፡፡ ብዙ ጊዜ ግን ከቤተሰብ ሽማግሌዎች የሚያልፉ የቤተሰብ ግጭቶች አይስተዋሉም፡፡ የቤተሰብ ሽማግሌዎች ብዙ ጊዜ ሶስት በመሆን ነው ሽምግልና የሚያካሒዱት፡፡ የዚህ ምክንያት

ደግሞ ሽማግሌው አንድ ብቻ ከሆነ ሊያዳላ፤ ትክክል ላይፈርድ ይችላል የሚል ነው፡፡ ውሳኔው የግሉ ስለሚሆን እና የሚያማክረው ባለመኖሩ ሊሳሳት ይችላል፡፡ ሁለት ከሆኑ ደግሞ ካልተግባቡ ወይም አንዱ ሌላ አንዱ ሌላ ከፈረደ እርቅ አይኖርም ተብሎ ስለሚታሰብ እንደሆነ ነው መረጃ አቀባዮቼ የገለጹልኝ ( አቶ ሀሰን አቢዮ ፣ አቶ ከድር ጀማል፣ ቃለመጠይቅ፣ ሚያዝያ 22፣ 2003፣ ጎባ )፡፡

### 4.2.3 የአካባቢ ሽማግሌ (Jaarsa Ganda )

በአንድ አካባቢ ፣ ሰፈራ መንደር ፣ ቀበሌ ገበሬ ማህበር ወይም ቀበሌ በሚኖሩ ሰዎች ወይም ቡድኖች መካከል በተለያየ ምክንያት የሚከሰት ግጭት ተባብሶ በህይወትና በንብረት ላይ ጉዳት እንዳያደርስ በመከላከል ግጭት ውስጥ የገቡትን አካላት በማስታረቅ ሰላምና መረጋጋት እንዲኖር የሚያደርግ ተቋም ነው፡፡ የአካባቢ ሽማግሌዎች በቤተሰብ ሽማግሌዎች መፍትሔ ያላገኙ ጉዳዮችንም ይመለከታሉ፡፡ እልባትም ይሰጣሉ፡፡ የአካባቢ ሽማግሌዎች ብዙ ጊዜ 3 ሆነው ነው ሽምግልና የሚቀመጡት፡፡ ነገር ግን እንደነገሩ ክብደት ቁጥራቸው አምስት የሚሆንበት ጊዜ እንዳለ መረጃ አቀባዮቼ ገልፀውልኛል፡፡

### 4.2.4 የጎሳ ሽማግሌ (Jaarsa Gosa )

የአርሲ ጎሳ በርካታ ንዑሳን ጎሳዎች አሉት፡፡ እያንዳንዱ ጎሳ በውስጡ የሚከሰቱ ግጭቶችን የሚፈታበት ባህላዊ ተቋም አያጣም፡፡ በባሌ ውስጥ የሚገኙት የአርሲ ጎሳዎችም በጎሳው ውስጥ የታወቁ ሽማግሌዎች አሏቸው፡፡ እነዚህ ሽማግሌዎች በጎሳው አባላት መካከል ጠብ እንዳይከሰት ፣ አንዱ የሌላውን ሀብትና ንብረት እንዳይዘርፍ የተፈጥሮ ሀብትን በጋራ እና በመተዛዘን እንዲጠቀሙ ፣ ወግ ልማድ እንዳይጣስ ይመክራሉ፤ ያስተምራሉ፡፡ በጎሳው ውስጥ ግጭት ሲከሰትም የግጭቱን መነሻ ምክንያት መርምረው ተበዳይን ይክሳሉ፤ በዳይን ይመክራሉ፤ ይቀጣሉ፡፡ የጎሳ ሽማግሌዎች ሽምግልና ሲቀመጡ እንደ ጉዳዩ ቅለትና ክብደት ሶስት ፣ አምስት ወይም ሰባት ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

የሀገር ሽማግሌዎች የሚመረጡት ለጉዳዩ ባላቸው ቅርበት፣ ማህበራዊ ደረጃ፣ በእድሜያቸው፣ በእውነት ተናጋሪነታቸው፣ በትዕግስተኝነታቸው፣ ስለማህበረሰቡ ባህልና ታሪክ ባላቸው የጠለቀ እውቀት ነው፡፡

በባሌ ኦሮሞዎች (በአጠቃላይ ኦሮሞ ማለት ይቻላል) ሽማግሌ ትልቅ ቦታ ይሰጠዋል። ሽማግሌ የእውነት ፍርድ ያውቃል ይባላል። ከእድሜ ባሻገር ባላቸው ማህበራዊ ደረጃ የሀይማኖት አባቶችና ባለሀብቶች ከፍተኛ ተቀባይነት አላቸው።

በአጠቃላይ ጉዳዩ ለሀገር ሽማግሌዎች የሚደርሰው በሁለት መንገድ ነው። አንደኛ ግጭት ውስጥ በገቡት አካላት፣ በዘመዶቻቸው እና በጎሳቸው አማካይነት ነው። ሁለተኛው ደግሞ የሀገር ሽማግሌዎቹ በራሳቸው ግጭት መከሰቱን አውቀው የተጋጨትን አካላት ወደ እርቅ የሚያመጡበት ነው። ግጭት ውስጥ የገቡት አካላት ፍቃደኛ ባይሆኑ እንኳን ማሳመን ከሀገር ሽማግሌዎቹ ይጠበቃል። አንድ ግጭት ተከስቶ እርቅ ሳይወርድ ብዙ ጊዜ ከቆየ የአካባቢው ነዋሪዎች (Jaarsa Biyyaa hinjiruu) የሀገር ሽማግሌ የለም ይላሉ። ከዚህ ሀሳብ ሽማግሌዎቹ ግጭት መኖሩ ከተጋጨት አካላት ባይገለፅላቸው እንኳን ከሚታዩ ሁኔታዎች በመነሳትና ጎረቤቶችን በመጠየቅ የተከሰተውን ግጭት የመፍታት ሃላፊነት እንዳለባቸው እንረዳለን።

ከዚህ በተጨማሪ የፍትህ አካላት (ፖሊስና ፍርድ ቤት) እንደ ግጭቱ ክብደትና ቅለት፣ በሽማግሌዎች ቢፈታ ከሚያመጣው ዘላቂ መፍትሄ ወዘተ. በመነሳት ግጭቶችን ወደ ሽማግሌዎች ይመራሉ።[11] በዚህም ሁኔታ ግጭቱን እንዲፈቱ ሽማግሌዎቹ የሚመረጡት በሁለት መንገድ ነው። አንደኛ በፍርድ ቤቱ ወይም በፖሊስ የሚመረጡ ሲሆን ሁለተኛው ግጭት ውስጥ የገቡት አካላት የሚመርጡበት ነው። በብዛት በሀገር ሽማግሌዎች የተፈቱት የግጭት አይነቶች የድንበር ግፊ፣ ስድብ፣ ድብድብ፣ ስም ማጥፋት፣ የግጦሽ ሳር ማስበላት፣ የባልና ሚስት የንብረት ይገባኛል ወዘተ. ናቸው። የጎባ ወረዳ ፖሊስ ጣቢያ የወንጀል ምርመራ ቡድን መሪ የሆኑት ኢንስፔክተር ሀጂ ዋሪዮ ወደ ፖሊስ ጣቢያ የመጡ ብዙ ግጭቶች በሽምግልና እንደተፈቱ ገልፀውልኛል። በ 'C.R' መዝገባቸው ከመስከረም 1/2003 ዓ.ም ጀምሮ እኔ እስከተመለከትኩበት ሚያዚያ 25፣ 2003ዓ.ም ድረስ ከተመዘገቡ 119 ክሶች ውስጥ 27ቱ በሽምግልና ያለቁ ናቸው። ከዚህም በዞኑ ዘመናዊውና ባህላዊ የእርቅ ስርዓት በጋራ እንደሚሰሩ መረዳት እንችላለን።

[11] ኢንስፔክተር ሀጂ ዋሪዮ፣ ሻምበል ተስፋዬ ፣ ሚያዝያ 25፣ 2003፣ ጎባ።

## 5. የባሌ ኦሮሞ ባህላዊ የግድያ ግጭት አፈታት

በዚህ ምዕራፍ በባሌ ኦሮሞ ማህበረሰብ ውስጥ የሚከሰቱ የግድያ ግጭቶችን መነሻ ምክንያት፣ የግድያ ግጭት አይነቶች፣ ለግድያ ግጭት የሚከፈለው ጉማ አይነት፣ የግድያ ግጭት የሚፈታበት ባህላዊ ተቋም፣ ባህላዊ የግድያ ግጭት መፍቻ ተቋሙ ለማህበረሰቡ የሚሰጠው ፋይዳ፣ የባሌ ኦሮሞ ማህበረሰብ ለግድያ ግጭት ያለው አመለካከትና ባህላዊ የግድያ ግጭት አፈታት አውዳዊ ክዋኔ እንመለከታለን።

### 5.1 የግድያ ግጭት መነሻ ምክንያቶች

በምዕራፍ ሁለት እንዳየነው የባሌ ኦሮሞዎች የገቢ ምንጭ በአብዛኛው ከእርሻ እና ከከብት እርባታ ጋር የተያያዘ ነው። በማህበረሰቡ ውስጥ የሚከሰቱ የግድያ ግጭቶችም በአብዛኛው የሚነሱት ከእርሻ መሬት ድንበር መገፋፋት፣ ከሰብል ማስበላት፣ ከግጦሽ ሳር ድንበር መገፋፋት፣ ከግጦሽ ሳር ማስበላት ፣ ከከብት መስረቅ ጋር በተያያዙ ምክንያቶች ነው።

ከዚህ ሌላ ከሰው የወሰዱትን ብድር አለመመለስ ፣ የሰው ሚስት መድፈር ፣ ማስኮብለል ፣ ቅናት ፣ ንቀትና ስድብ በማህበረሰቡ ውስጥ የግድያ ግጭት እንዲከሰት ያደርጋሉ።

### 5.2 የግድያ ግጭት አይነቶች

የግጭት ዘርፍ ምሁራን የግጭት አይነቶችን በግጭቱ ውስጥ ከተሳተፉት ሰዎች (ቡድኖች) ብዛትና ማንነት፣ ግጭቱ ከተከሰተበት ደረጃ እና ግጭቱ ከሚያስከትለው ውጤት አንፃር እንደሚከፋፏቸው በምዕራፍ ሶስት ተመልክተናል።

የባሌ ኦሮሞዎች የግድያ ግጭት ዓይነቶችን የሚከፋፈሉበትን መንገድ ስንመረምር ምሁራኑ ከከፋፈሉበት መንገድ እምብዛም የራቀ አይደለም። እንዲያውም የባሌ ኦሮሞዎች የግድያ ግጭት አከፋፈል በምዕራፍ ሶስት ከቀረበው የአሰፋ አበበ (2001) የግጭት አከፋፈል ጋር የተቀራረበ ነው።

የባሌ ኦሮሞዎች የግድያ ግጭትን የሚከፋፍሉት በግድያ ግጭቱ ከተሳተፉት ሰዎች ወይም ቡድኖች ማንነት በመነሳት ነው። በዚህ መሰረት የግድያ ግጭቶችን ውስጣዊና ውጫዊ ግጭቶች በማለት በሁለት አበይት ክፍሎች ይከፍሏቸዋል።

በመቀጠል እያንዳንዱን የግድያ ግጭት አይነት በቅደምተከተል በዝርዝር እንመለከታለን፡፡ ለግድያው አይነት የሚከፈለውንም ጉማ እናያለን፡

### 5.2.1.ውስጣዊ ግጭቶች

**በቤተሰብ አባላት መካከል** (warra giddutti)

በቤተሰብ አባላት መካከል የተከሰተ የግድያ ግጭት የሚባለው በእህትማማቾች፣ በወንድማማቿች፣ የወንድምና እህት፣ የባልና ሚስት፣ በእናትና ልጆች፣ በአባትና ልጆች መካከል የሚከሰት የግድያ ግጭት ነው፡፡ መረጃ አቀባዮቹ እንደነገሩኝ እንዲህ ያለው ግጭት ብዙ ጊዜ በወንድማማቾች መካከል ነው የሚከሰተው፡፡ በቤተሰብ አባላት መካከል የሚከሰት ግጭት የደም ካሳ ወይም ጉማ አያስከፍልም፡፡ በዚህ ጊዜ የ (Rakkoo) ስርዓት ብቻ ይደረጋል፡፡

**በቤተዘመድ መካከል**(fiira giidutti)

በዘመዳሞች መካከል የሚከሰት የግድያ ግጭት የሚባለው በስጋም ሆነ በጋብቻ ዝምድና ባላቸው ሰዎች መካከል የተከሰተ ግድያ ነው፡፡ የስጋም ሆነ የጋብቻ ዘመዱን የገደለ ሰው ሌላ (ዘመድ ያልሆነን) ከገደለ ሰው እኩል አይቀጣም፡፡ የወንጀሉ ደረጃም ዘመድ ያልሆነውን ሰው ከገደለው ያነሰ ነው፡፡ የዚህ ምክንያት በዘመዳሞች መካከል ግድያ ግጭት ብዙ ጊዜ አይፈጠርም ድንገት ቢገዳደሉ እንኳ የተለያዩ ስራዎችን በጋራ ሲያከናውኑ ወይም ባህላዊ ጨዋታዎችን ሲጫወቱ በድንገት የሚከሰት ነው ተብሎ ስለሚታሰብ ነው፡፡

**በአንድ ጎሳ ውስጥ** (Gosa Keesati)

የአንድ ጎሳ አባላት የሆኑ ሰዎች እርስ በእርስ ሲገዳደሉ በጎሳ ውስጥ የተከሰተ ግድያ ይባላል፡፡ የራሱን ጎሳ የገደለ የሚቀጣው ቅጣት የሌላን ጎሳ ሰው ከገደለ ጋር ሲነፃፀር ዝቅተኛ ነው፡፡ ጉማን የሚከፍለው ጎሳ ነው፡፡ የአንድ ጎሳ አባላት እርስ በእርስ ሲጋደሉ ጉማ ከፋዩም ጉማ ተቀባዩም ጎሳ አንድ ስለሚሆን ክፍያው በስምምነት ላይ ይወሰናል፡፡

**በተለያዩ ጎሳዎች መካከል**(Gosa adda addaa giidutti)

አንድ ሰው የሌላ ጎሳ የሆነ ሰው ሲገደል (በተለያዩ ጎሳዎች አባላት መካከል) የሚከሰት የግድያ ግጭት አይነት ነው፡፡ እንዲህ አይነቱ ግጭት የሚፈቱት ሽማግሌዎች ከሁለቱም ጎሳ ውጪ የሆኑ ሽማግሌዎች ናቸው፡

### 5.2.2.ውጫዊ ግጭቶች

በኦሮሞ እና በሌላ ብሔር መካከል (oromo fi oromo hinta'in wallin )

አንድ የኦሮሞ ብሔር ኦሮሞ ባልሆነ ሰው ሲገደል ወይም የሌላ ብሔር አባል ሲገድል የሚከሰት ነው። የጉማ ስርዓት የተደነገገው በኦሮሞዎች ነው። ፋይዳውም የኦሮሞዎችን ሰላም እና ደህንነት መጠበቅ ነው። በዚህ ጊዜ ሰው የሞተበት (የተገደለበት) የኦሮሞ ጎሳ ኦሮሞ ካልሆነው ማህበረሰብ የሚቀበለው ምንም አይነት ጉማ የለም። እዚህ ጋር አንድ መረጃ አቀባዬ የነገሩኝን ማቅረቡ ጉዳዩን ግልፅ ለማድረግ ይረዳል።

> Qaamni Oromoo hin ta'in lubbuu Oromtichaa yoo balleesse baasii gumaan Oromtichaa kaffaluuf hin jiru. Qaamni akkanaa kun Sidii jedhamee beekama. Oromoon sidii irraa gumaa hin nyaatu. Qaamni kun qucee (ajjeechaa lubbuu) malee gumaa irraa nyaatan hin qabu. Ni qucama yookaan ni ajjefam(አቶ ሀሰን አቢዮ፣ ሚያዝያ 20፣ 2003፣ጎባ ).

> ኦሮሞ ያልሆነ ሰው የኦሮሞን ነፍስ ቢያጠፋ ለዚህ የሚከፍለው ጉማ የለም። እንዲህ ያለው አካል 'ሲዲ' (Sidii) በመባል ይታወቃል። ኦሮሞ ከ'ሲዲ' (Sidii) ላይ ጉማ አይበላም። እንዲህ ያለው አካል በሞት ይቀጣል እንጂ የሚከፍለው ጉማ የለም።

አሁን አሁን ግን በተለይ በድንበር አካባቢ በሚገኙ ከተሞች የሚኖሩ ኦሮሞዎች ከሌሎች ማህበረሰቦች ጋር በጋራ በሰላም ይኖራሉ። በመካከላቸው የሚከሰቱ ግጭቶችንም በጋራ በመፍታት አብረው እንደሚኖሩ መረጃ አቀባዮቼ ገልፀውልኛል። የግድያ ግጭትን በተመለከተ ግን አሁንም ድረስ ኦሮሞዎች ከሌላ ብሔረሰብ ጉማ አይቀበሉም። በዚህ ሁኔታ የሚፈጠር ግጭት የሚፈታው በመንግስት አካላት ነው።

### 5.3 ለግድያ ግጭት የሚከፈለው የጉማ አይነት

ለግድያ ግጭት የሚከፈለው የደም ካሳ (Gumaa) የተለያየ ነው። የባሌ ኦሮሞዎች የግድያ ጉማን ከግድያው አፈፃፀም ሁኔታ እና ከሟች ፆታ በመነሳት በተለያየ መልኩ ይከፍሉታል።

የግድያ ጉማን የሚከፍሉበት አንዱ መንገድ ከግድያው አፈፃፀም ሁኔታ በመነሳት ነው። በዚህ መሰረት የግድያ ጉማን 'ኦኮኮ'(Okkoko)፣ 'ሀምቢሳ' (Hambissa) እና 'ረፊሳ' (Raffisa)በማለት

በሶስት ይከፍሉታል፡፡ በመቀጠል የእያንዳንዱን የግድያ ጉማ አይነት፣ የግድያውን አፈፃፀም ሁኔታ እና የጉማ መጠን በዝርዝር እንመለከታለን፡፡

### 5.3.1. ኦኮኮ (Okkkoko)

ኦኮኮ የሚባለው የጉማ አይነት በአንዳንድ መረጃ አቀባዮቼ ለምሳሌ አቶ ሀሰን አቢዮ (Dhaadhatta፣ Adii) በመባል ይጠራል፡፡ ስያሜው ይለያይ እንጂ የአገዳደል ሁኔታውን ግን ተመሳሳይ ነው፡፡ ኦኮኮ የሚባለው የግድያው አይነት ቀደም ብሎ በመካከላቸው ጠብ ባለ ሰዎች ዘንድ የሚከሰት ሲሆን ግጭት ውስጥ የገቡት አካላት (ገዳይና ሟች) በመካከላቸው ለረጅም ወይም ለአጭር ጊዜ በነበረ ውዝግብ ምክንያት የሚከሰት የግድያ ግጭት ነው፡፡ ገዳይ ከሟች ጋር በነበራቸው ጠብ ተነሳስቶ፣ ሟችን ለመግደል ሆን ብሎ፣ ተዘጋጅቶ፣ አስቦበት የሚፈፅመው ግድያ የሚከፈልበት ጉማ አይነት ነው፡፡

እንደዚህ አይነት ግድያ ሲከሰት የሚከፈለው ጉማ ሟች ወንድ ከሆነ መቶ ከብት ወይም የመቶ ከብት ተመን ገንዘብ ሲሆን የተገደለችው ሴት ከሆነች ደግሞ ሀምሳ ከብት ወይም የሀምሳ ከብት ተመን ገንዘብ ነበር፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን የማህበረሰቡ የከብት መጠን እየቀነሰ በመምጣቱ ጉማ የሚሰጠው የከብት ቁጥር ከነበረው ያነሰ ሆኗል፡፡ ይህም በስምምነት የሚከፈል ይሆናል፡፡

### 5.3.2. ሀምቢሳ (Haambissa)

ሀምቢሳ የሚባለውም የጉማ አይነት በተለያዩ ቦታዎች በተለያየ ስያሜ ሲጠራ ይሰማል፡፡ ከዚህ ውስጥ (Barruu ፣ Raffissa) ይጠቀሳሉ፡፡ ልክ እንደ 'ኦኮኮ' ሁሉ 'ሀምቢሳም' በተለያዩ ስያሜዎች ይጠራ እንጂ የግድያው ሁኔታ ግን ተመሳሳይ ነው፡፡ አንድ ሰው ሆን ብሎ ሰው ለመግደል አስቦ ሳይሆን ለሌላ ነገር መሳሪያ ሲወረውር ድንገት ሰው ከገደለ የጉማው አይነት 'ሀምቢሳ' ይባላል፡፡ ለምሳሌ አንድ ሰው የያዘው መሳሪያ ባርቆ የሰው ነፍስ ካጠፋ ወይም ሜንጫ፣ ባንጋ፣ ጦር፣ ቢላዋ ለሌላ ጉዳይ (ከማሳ ውስጥ አውሬ ለማባረር፣ ቁልቋል ለመቁረጥ ለአደን ወዘተ.) ሲወረውር በድንገት ሰው መትቶ ከገደለ የግድያው ሁኔታ ሀምቢሳ ይባላል፡፡ በዚህ የግድያ አይነት በሟች እና በገዳይ መካከል ጠብ፣ ቂም የለም፡፡ እንዲያውም ሟችና ገዳይ ላይተዋወቁም ይችላሉ፡፡ ይሁን እንጂ የሰው ነፍስ ሊያጠፋ የሚችል መሳሪያን ያለጥንቃቄ በመወርወሩ ገዳይ ከተጠያቂነት አያመልጥም፡፡ ጥንቃቄ ሳያደርግ በመቅረቱ የሰው ነፍስ ስላጠፋ ከወንጀለኝነት አይድንም፡፡

በራሱ ላይ የተሰነዘረን ጥቃት ለመከለከል (እራስን ለመከላከል) ሲሞክር የሰው ነፍስ ያጠፋ ከሆነም በዚህ ስር ነው የሚመደበው። የ'ሀምቢሳ' ጉማ ከ'ኦኮኮ' ያነሰ ነው። የሀምቢሳ ክፍያ ብዙ ጊዜ በገዳይና በሟች ወገኖች ስምምነት ላይ ተመስርቶ የሚወሰን በመሆኑ አንድ ወጥ ተመን የለውም። መረጃ አቀባዮቼም የገለፁልኝ ክፍያው ከ'ኦኮኮ' እንደሚያንስ ብቻ ነው።

#### 5.3.3.ረፊሳ (Raffissa)

እንደ 'ኦኮኮ' እና 'ሀምቢሳ' ሁሉ 'ረፊሳ'ም በተለያዩ ሰዎች ዘንድ 'ጉራቲ' (Gurraatii) በሚል ስያሜ ይጠራል። ረፊሳ በድንገት ለሚከሰት ግድያ የሚከፈል የጉማ አይነት ነው። የታሰበበት ግድያ አለመሆኑ ከ 'ሀምቢሳ' ጋር ያመሳስለዋል። ነገር ግን የ 'ረፊሳ' ጉማ የሚባለው አንድ ሰው በመካከላቸው ምንም አይነት የቀደመ ጥላቻ ሳይኖር ፣ የሰው ነፍስ ሊያጠፋ የሚችል መሳሪያ ሳይጠቀም ፣ በድንገት ሰው ሲገድል ነው። አንድ ሰው ምንም አይነት የጦር (የሰውን ነፍስ ሊያጠፋ የሚችል) መሳሪያ ሳይጠቀም ሰውን መግደል እንደሚችል መገመት አይከብድም። (ማነቅን ፣ ማፈንን ፣ ስስ ብልት መምታት ይመለከቷል)። ነገር ግን በ'ረፊሳ' ገዳይ የነበረበት ሁኔታም ይታያል። ከተለመደው እንቅስቃሴ ፣ ግንኙነት ውጪ መሆን የለበትም። በሌላ አነጋገር መሳሪያ አለመጠቀሙ ብቻ ሳይሆን ግድያው የተፈፀመበት ሁኔታም ይታያል። ለምሳሌ አንድ ሰው እንደ የፈረስ ግልቢያ (gombissa) ፣ ባህላዊ አደን (adamo) ፣ እና ትግል (wal'ansoo) ሲጫወት በድንገት ሰው ቢገድል የጉማው አይነት 'ረፊሳ' ነው። የጉማው አይነት 'ረፊሳ' ከሆነ ገዳይ (የገዳይ ጎሳ) ምንም የደም ካሳ (Gumma) ለሟች ቤተሰቦች እና ጎሳ አይከፍልም። ከገዳዩ ግለሰብ (ጎሳ) የሚጠበቀው በመጨረሻው የእርቅ ቀን የምትታረድ አንድ ከብት መስጠት ብቻ ነው።

ሌላው የጉማውን አይነት የሚከፋፍሉበት መንገድ ከሟች ፆታ በመነሳት ነው። በዚህ መሰረት የጉማውን አይነት የወንድ ጉማ (Gumma dhiirra) እና የሴት ጉማ (Gumma dubartii) በማለት በሁለት ይከፍሉታል።

ከመረጃ አቀባዮቼ ባገኘሁት መረጃ መሰረት በባሌ ኦሮሞዎች የጉማ ስርዓት ሴት እና ወንድ ሲሞት የሚከፈለው የደም ካሳ (ጉማ) እኩል አይደለም። በዚህ መሰረት ሟች ወንድ ከሆነ የሚከፈለው ጉማ አንድ መቶ ከብት ሲሆን ሴት ከሆነች የወንድን ግማሽ ሀምሳ ከብት ነው።

ጉማ የሚከፈለው ጉማ በሚያስከፍሉ የሰውነት አካላት ልክ መሆኑን መረጃ አቀባዮቼ ገልፀውልኛል። በዚህ መሰረት ጉማ የሚከፈልበት የሰውነት ክፍል ሶስት መቶ ስልሳ (Humnii

Gumma 360) ነው፡፡ ሽማግሌዎቹ ሴትም ወንድም ያላቸው ጉማ የሚከፈልበት የሰውነት አካል እኩል ሶስት መቶ ስልሳ እንደሆነ ይስማማሉ፡፡ ታዲያ እንዴት የሴት ጉማ ከወንድ ጉማ አነሰ ለሚለው ጥያቄ የሚከተለውን ምላሽ ይሰጣሉ፡፡

> Gumaa dhiira fi dubartii addaa kan godee dubarti seeri anbaa kaa'ii waarraan qabadhu duulii hin jedhuu. Sinqee qabadhu garaa dullaa eggii, dulchiisi jedhan mallee. Seera anbaati waarran qabadhu duullii hin jedhan. Behii nama awallii hin jedhan. kanaan wal caalaan malee humni nama tokkotuuyyuu (አቶ ከድር ፣ቃለመጠይቅ፣ ሚያዝያ 19፣ 2003 ፣ጎባ).
> የወንድና የሴትን ጉማ የተለያየ ያደረገው ሴት በማህበረሰቡ ወግ ልማድ መሰረት ጦርነት ሄዳ እንድትዋጋ አይፈቅድም፡፡ ሴት ልጅ ጦር ይዛሽ ተዋጊ አትባልም፡፡ ሲንቄዋን ይዛ መለማመንና የዘማችን ቤት መጠበቅ ፣ ለዘማች ስንቅ ማዘጋጀት ነው የሚጠበቅባት፡፡ እንዲሁም ሰው ሲሞት ቀብር አትሄድም ፣ መሬት ቆፍራ ሰው አትቀብርም፡፡ ጉማውም የሚለያየው በዚሁ ምክንያት ነው፡፡ እንጂ ሁሉም ሰው ያለው ጉማ የሚከፈልበት አካል [እኩል 360] ነው (አቶ ከድር፣ሚያዝያ 19፣2003፣ ጎባ)፡፡

## 5.4 የግድያ ግጭት የሚፈታበት ባህላዊ ተቋም

በቀደመው ምዕራፍ የባሌ ኦሮሞዎች በውስጣቸው (በማህበረሰቡ ውስጥ) የሚከሰትን ግጭት ለመፍታት የሚጠቀሙባቸወ የተለያዩ ተቋማት እንዳሉ ተመልክተናል፡፡ በዚህ ክፍል የግድያ ግጭት የሚፈታበትን ባህላዊ ተቋም ፣ በተቋሙ ውስጥ የሚሳተፉ አካላትን ብዛትና ማንነት እንመለከታለን፡፡

በባሌ ኦሮሞዎች ዘንድ የግድያ ግጭትን የሚፈታው ባህላዊ ተቋም 'ራያ አንባ' (Rayyaa Anbaa) ይባላል፡፡ ራያ አንባ ማለት ከገዳይና ከሟች ጎሳ ውጪ የሆነ (ገለልተኛ ወገን) ማለት ነው፡፡ የግድያ ግጭትን የሚመለከቱት ሽማግሌዎች ከገዳይ እና ከሟች ጎሳ ውጪ የሆኑ ናቸው፡፡ የግድያ ግጭት በጎሳ ፣ በቤተሰብ ፣ በአካባቢ ሽማግሌዎች አይታይም፡፡ የግድያ ግጭትን የሚያዩት (የሚፈቱት) የገለልተኛ ጎሳ ሽማግሌዎች ብቻ ናቸው፡፡

የግድያ ግጭትን የሚያዩት የገለልተኛ ወገን ሽማግሌዎች ብዛት 25 ሲሆን ከዚህ ውስጥ ስምንቱ ቆርቱ (qorrtu)፣ ስምንቱ 'ጮይቱ' (Cooyitu)፣ ስምንቱ ደግሞ 'ቆፐቱ' (qoophtu) ናቸው። የቀረው አንዱ የሁሉም ሰብሳቢ ሲሆን 'ቀራ' (qara) ይባላል። የስራ ድርሻቸውም እንደሚከተለው ነው።

ቆርቱ የሚባሉት በጥላ ስር የገዳይና የሟች ወገኖችን በመሰብሰብ የግጭቱን መነሻ ምክንያት መርምረው ተገቢውን ፍርድ በመስጠት ግጭት ውስጥ የገቡትን አካላት ወደ እርቅ ያመጣሉ። ቆርቱዎች ብዙ ጊዜ የመናገርና የማሳመን ችሎታ ያላቸው ናቸው።

ጮይቱ የሚባሉት ደግሞ በቆርቱዎች የተወሰነውን የጉማ ከብት ለማምጣት ቃል ገብቶ ካላመጣ የገዳይ ጎሳ ላይ በመቀበል የሚሰበስቡ ናቸው። በአንዳንድ መረጃ አቀባዮቼ ዘንድ "ሰዴት ካኩራ" በመባል ይጠራሉ። ጮይቱዎች በጣም ጠንካራ፣ የተደላደለ ሰውነት ያላቸው ናቸው። በቀጠሮ ቀን የማይገኝ ሰው ካለም ያለበት ድረስ በመሄድ ይዘውት ይመጣሉ። የጮይቱዎች ተግባር በዘመናዊ የፖሊስ ሀይል ከሚያከናውነው ጋር ተቀራራቢ ነው።

ቆፐቱ የሚባሉት ስምንቱ ደግሞ በጉማ የተፈረደው የከብት መጠን ተሰብስቦ እስኪጠናቀቅ ድረስ ከገዳይ ወገን እና ከጮይቱዎች የሚመጣውን ከብት ተቀብለው የሚቆጣጠሩ ናቸው። የተፈረደው የከብት መጠን በሙሉ ከገባ በኋላ በቀጠሮው ቀን ለሟች ጎሳዎች ይሰጣል።

የቀረው አንዱ ቀራ ደግሞ የሁሉም የበላይ ሰብሳቢ በመሆን ሙሉ የሽምግልናውን ሂደት የሚመራ ነው። 'ወሊቲ ቀባ ያአ ሰኒቲ' (wallitti qabaa yaa'a sanniti) ይሉታል።

ምንም እንኳን የራያ አምባዎች ብዛት 25 ቢሆንም ሁሉም በሽምግልናው ሒደት (በውሳኔ መስጠት) ይሳተፋሉ ማለት አይደለም። ከላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው ሁሉም የየራሱ ድርሻ አለው። የማስታረቁን ስራ የሚሰሩት (የሚሸመግሉት) ስምንቱ ቆርቱዎችና የሁሉም ሰብሳቢ የሆነው አንዱ ቀራ በአጠቃላይ ዘጠኙ ናቸው። በባሌ ኦሮሞዎች ባህል መሰረት የሽማግሌዎች ቁጥር ጎዶሎ መሆን ይኖርበታል ይህም ፍርድ ለመስጠት ካለው አመቺነት የሚመነጭ ነው (አቶ ከድር ሚያዝያ 27፣2003ዓ.ም ጎባ፤ አቶ አብዱ ከማል ሚያዝያ 28፣2003ዓ.ም ሲናና)።

### 5.5 ባህላዊ የግድያ ግጭት መፍቻ ተቋሙ ለማህበረሰቡ የሚሰጠው ፋይዳ

የባሌ ኦሮሞዎች የግድያ ግጭትን ለመፍታት የሚጠቀሙበት ተቋም ለማህረሰቡ የሚሰጠው በርካታ ፋይዳዎች አሉት፡፡ በዚህ ክፍል ባህላዊ ተቋም የሚሰጠውን ማህበራዊ፣ኢኮኖሚያዊ፣ እና ስነልቦናዊ ፋይዳ እንመለከታለን፡፡

#### 5.5.1 ማህበራዊ ፋይዳ

የግድያ ግጭት መከሰት በራሱ አሳዛኝ ከመሆኑ ባለፈ የማህረሰቡን ሰላምና ደህንነት ችግር ውስጥ ይከተዋል፡፡ የግድያ ግጭቱን የሚፈታው ተቋም ባይኖር በተከሰተው ግጭት ጉዳት የደረሰባቸው (የሟቹ ወገኖች) በንዴትና በቂም በቀል ተነሳስተው ደማቸውን ለመመለስ እንዲዘጋጁ ይሆናሉ፡፡ በዚህ ምክንያት የተከሰተው ግጭት እየተባባሰ ሄዶ የማህበረሰቡ ሰላም እንዲደፈርስ፣ ህይወትና ንብረት እንዲወድም ያደርጋል፡፡

ይህ እንዳይሆን ባህላዊ ተቋሙ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል፡፡ የግድያ ግጭት የሚፈቱት ሽማግሌዎች ችግሩ እንደተፈጠረ ከገዳይ ወገን ከተነገራቸው ጊዜ አንስቶ እርቅ ወርዶ ሰላም እስኪሰፍን ድረስ እረፍት የላቸውም፡፡ ገዳይን ደብቀው፤ የገዳይ ወገኖች ከሟች ወገኖች እንዳይገናኙ መክረው፤ እነሱ በነገሩ መሀል ገብተው፣ ዳገት ወጥተው ቁልቁለት ወርደው የሟችና የገዳይ ወገኖችን ወደ እርቅ ለማምጣት ደፋ ቀና ይላሉ፡፡ የሟችና የገዳይ ወገኖችን ፊት ለፊት በማምጣት የተበደለውን ያስክሳሉ፣ የበደለውን ይቀጣሉ፣ ይመክራሉ፣ በዚህም የማህበረሰቡ ሰላም እንዲረጋገጥ ያደርጋሉ፡፡

የተለያዩ ስርዓቶችን በማከናወን የሟችና የገዳይ ወገኖች በመሀከላቸው የተፈጠረውን ግጭት ረስተው ሰላማዊ ወደሆነ ማህበራዊ ህይወት እንዲመለሱ ያደርጋሉ፡፡ የሟችና የገዳይን ወገኖች ለማቀራረብ፣ ለማዛመድ፣ ለማወዳጀት ከሚከናወኑ ስርዓቶች አንዱ "ሴት ልጅ የመስጠት" ስርአት ነው፡፡ ይህ ስርዓት የሟችና የገዳይ ወገኖች ደም እንዲቀላቀል፣ እንዲዛመዱ በማረጉ በቂም በቀል መፈላለጋቸው ቀርቶ እንዲተጋገዙ፣ በሀዘን በደስታ ጊዜ አንድ ላይ እንዲሆኑ፣ስራን በጋራ እንዲያከናውኑ፣ መሳሪያዎችን እንዲዋዋሱ ወዘተ. ያደርጋል፡፡

ሴት ልጅ መስጠት በማይቻልበት ቦታ የሚከናወነው ስርዓት ደግሞ የጡት ማጥባት (harma wal-hoosisu) ስርዓት ነው፡፡ ሽማግሌዎች የሟችና የገዳይ ወገኖችን አንድ ልብስ አልብሰው ጡት እንዲጣቡ ያደርጋሉ፡፡ የተጋጩት ወገኖችም "harma hodhe kana ani lammata

deebi'ee dubbi tana hin kassu,halo hin bau ,harna kan wal-hin gannu" (በጠባሁት ጡት ላይ ዳግመኛ እንዲህ ያለ ችግር አልፈጥርም፣ቂም በቀል አልይዝም፣ከጠባሁት ጡት አልለይም) በማለት ቃል ይገባሉ። ጡት ከተጣቡ በኃላ ግንኙነታቸው "soddaa-soddaatii" የመከባበር፣ የመተጋገዝ፣የመረዳዳት ይሆናል። ሀዘን፣ መከራና ደስታ የጋራ በማድረግ በሀዘንና በደስታ እንዲደራረሱ ያደርጋል። በዚህም መሰረት የማህበረሰቡን ህይወት የተረጋጋ፣ ሰላምና ደስታ የሰፈነበት እንዲሆን ያደርጋሉ።

### 5.5.2 ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ

የጉማ ስርዓት የሚፈጸሙ ሽማግሌዎች ያለምንም ክፍያ በራሳቸው ተነሳሽነት ስለቸን፣ ደከመን ሳይሉ የሚችና የገዳይ ወገኖች ወደ እርቅ እንዲመጡ ያደርጋሉ። ህግና ደንቡን ተመርኩዞው ግጭት ውስጥ የገቡት አካላት ሳይጉላሉ ጊዜ ገንዘብና ጉልበታቸው ሳይባክን ለችግርና ለመከራ ሳይዳረጉ በፍጥነት ወደ ተረጋጋ ህይወት እንዲመጡ ያደርጋሉ።

የጉማ ክፍያ የሚከፈለው በጎሳ ነው። ይህ ደግሞ "ህምሳ ሎሚ ለአንድ ሰው ሸክሙ ለሀምሳ ሰው ጌጡ" እንደሚባለው አንድ ሰው ብቻ እንዳይጎዳ ያደርጋል። ለምሳሌ በባሌ ኦሮሞ ባህል መሰረት ከፈተኛው የግድያ ጉማ እስከ አንድ መቶ ከብት ይደርሳል። አንድ ሰው ብቻውን እንዲከፍል ቢደረግ ያን ያህል ከብት ላይኖረው ይችላል። ቢኖረውም በአንድ ጊዜ በድህነት አረንቋ ውስጥ ይዘፈቃል። የጉማ ክፍያ በጎሳ መሆኑ አንድ ሰው እንዲከፍል (እንዲያዋጣ) የሚጠበቅበትን የከብት መጠን እጅግ ከማሳነሱም በላይ በጎሳው ውስጥ የአንድነት፣የመረዳዳት፣የወዳጅነት ስሜት እንዲኖር ያደርጋል።

### 5.5.3 ስነ ልቦናዊ ፋይዳ

የጉማ ስርዓት አንቀጽ ወጥቶለት በወረቀት ሰፍሮ የሚገኝ ባይሆንም በቃልና በክዋኔ ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲተላለፍ የቆየ በመሆኑ፣ ስርዓቱን የሚፈጽሙት ሽማግሌዎች የሚያስተላልፋት ውሳኔ በሀቅ ላይ የተመሰረተ በመሆኑ የሰላም ምንጭ እንደሆነ ይታመናል።

የጉማን ስርዓት የሚመሩት ሽማግሌዎች ከሟችም ሆነ ከገዳይ ጎሳ ውጪ የሆኑ ገለልተኛ ወገኖች በመሆናቸው የሚሰጡት ፍርድ በሁለቱም ወገን ተቀባይነት አለው። የሟችም ሆነ የገዳይ ጎሳዎች መድሎ ይፈጽማል፣ ፍትህ ይዛባል፣ የሚል ፍራቻ እንዳይኖራቸው ያደርጋል።

የሚች ወገኖች ከገዳይ ወገን ጥቃት ይደርስብን ይሆን ከሚል ስጋት እንዲላቀቁ የግድያ ግጭቱ እርቅ በፍጥነት ይካሄዳል፡፡ የእርቅ ስርዓቱ በፍጥነት መካሄዱ በገዳይ ወገኖች አእምሮ ውስጥ የሚመላለሰውን የስጋትና የፍርሀት ስሜት ያጠፋል፡፡ በሚች ወገኖች ውስጥም የጥላቻ፣ የብቀላና የሀዘን ስሜት እንዳይመላለስ ያደርጋል፡፡

የሚች ወገን የገዳይን ወገን የትአግኝቼ ልበቀለው፣ የት አግኝቼ ላጥፋው እያለ አእምሮውን እንዳያስጨንቅ ሲያደርግ ፣ የገዳይ ወገንም የሚች ወገኖች በቤተሰቦቼ፣በንብረቴ ላይ ጥፋት ያደርሱብኝ ይሆን በማለት እንዳይጨነቅ ያደርጋል፡፡

በመጨረሻም የእርቅ ቀን የሚካሄደው 'የረኮ' (Rakkoo) ስርዓት በተቀደደ ቆዳ ውስጥ ማለፍና ከእጅ ላይ የመብላት ስርዓት የሚችና የገዳይ ወገኖች በቀጣይ መጥፎ ነገሮች እንዳያስቡ ያደርጋል፡፡ ከሀጥያት የነጻ ሰው ዳግም ሌላ ሀጥያት ለመስራት አይጣደፍም፡፡ ከሰው እጅ ላይ በልቶ ከእጁ ልይ የበሉትን ሰው ማጥቃት ነውር በመሆኑ እና እጁ ላይ ይጥለኛል ተብሎ ስለሚታሰብ ዳግም ግጭት እናዳይፈጠር ያደርጋል፡፡ በዚህ የተነሳ የገዳይ ወገኖች ስነ ልቦናዊ መረጋጋት እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡

የጉማ ስርዓት የማህበረሰቡ ርዕዮተ አለማዊ አተያይ መገለጫ በመሆኑ የማህበረሰቡ እምነት፣አስተሳሰብና ፍልስፍና ይንጸባረቅበታል፡፡ በዚህ ምክንያት ባህላዊ ስርዓቱ ከእምነትና ከተፈጥሮ ጋር ግጭት ሳይፈጠር ከዙሪያው ካሉ ነገሮች (ከእንስሳቱ፣ከአራዊቱ) ጋር የሚፈጠሩ የስነ ልቦና ግጭቶች በመፍታት ሰላማዊ ህይወት እንዲኖር ያደርጋል፡፡

ለምሳሌ አንድ ሰው ጅብ ቢገድል ወይም ቢደበድብ፣ ጅብ ቂመኛ መሆኑ በማህበረሰቡ ውስጥ ስለሚታመን ከስጋት ነጻ አይሆንም፡፡ ማታ መጥቶ ልጆቼንና ከብቶቼን ይበላብኝ ይሆን፣ መንገድ ጠብቆ ይበቀለኝ ይሆን ወዘተ. እያለ መጨነቁ አይቀርም፡፡ በዚህ ጊዜ የጉማ ሽማግሌዎች ከብት አርዶ የጅብ ጎሬ አለበት ወደሚባል አካባቢ እንዲጥል ያደርጋሉ፡፡ ጅብ ስጋውን ማን ያምጣ ማን ይጣል አይረዳ ይሆናል፡፡ ሰውዬው ግን ከዚህ ወዲያ ከጭንቀት ነጻ ይሆናል፡፡

### 5.6 የባሌ ኦሮሞ ማህበረሰብ ለግድያ ግጭት ያለው አመለካከት

የባሌ ማህበረሰብ ለግድያ ግጭት ያለው አመለካከት በምዕራፍ ሶስት ከተጠቀሰውና ግጭት ጎጂ ነው ከሚሉት ምሁራን ጋር ተቀራራቢ ነው፡፡ በተለይ Habtamu (1998) ባህላዊ አመለካከት

(Traditional view) ከሚለው ጋር ተመሳሳይ ነው። በአካባቢው ማህበረሰብ የግድያ ግጭት በጣም ነውር የሆነ ጉዳይ ነው። የግድያ ግጭት የፈፀመ ሰውም እንደ ሰይጣን (ክፉ መንፈስ) ነው የሚታየው። እዚህ ጋር አቶ ጎበና የተባሉ መረጃ አቀባዩ ነገሩኝ ማቅረብ ጉዳዩን የበለጠ ግልፅ ለማድረግ ይረዳል።

> በባሌ ኦሮሞ ማህበረሰብ ዘንድ ግድያ የፈፀመው የመጥፎ (የክፉ) መንፈስ ማደሪያ እንደሆነ ተደርጎ ነው የሚታሰበው። የሰው ነፍስ ሊያጠፋ የሚችለው በዚሁ ሳቢያ ነው። እንዲያውም 'በቁጩ' ደንብ መሰረት ሰው የገደለ ሰው በሞት ነበር የሚቀጣው። ምንም እንኳን አሁን ያ ባይሆንም በተለይ ከ 'ረኮ' ስርዓት ክዋኔ በፊት የሰው ነፍስ ያጠፋው ሰው እንደሰው ልጅ አይታይም። (አቶ ጎበና ባቲ፣ ሚያዝያ 26፣ 2003ዓ.ም)

ግጭቱ ከተከሰተበት ጊዜ አንስቶ የእርቅ ስርዓቱ እስኪፈፀም ድረስ ገዳዩ የሚያልፍበት ሁኔታም ይህን ሀሳብ የሚያጠናክር ነው። ግድያው መፈፀሙ የተነገራቸው የገለልተኛ ጎሳ ሽማግሌዎች የሟች ወገን አግኝተው እንዳይገሉት በማለት ገዳዩን ይደብቁታል። ገዳይ የሚደበቀው በተመቻቸ ቤት ውስጥ አይደለም ከራያ አንባዎቹ የእድሜ የበላይ (ሀንገፉ) የሆነው ሽማግሌ መኖሪያ አቅራቢያ በሚገኝ ዋሻ ወይም ኦና ቤት ውስጥ ነው የሚደበቀው። የእርቅ ሂደቱ የሚፈጀውን ያህል ጊዜ ገዳይ በተደበቀበት ይቆያል። የሚሰጠውም ምግብ ማህበረሰቡ ለገዳይ ያለውን አመለካከት ያሳያል። ገዳይ ሽምግልናው ተጠናቆ ከተደበቀበት መውጣት እስኪፈቀድለት ድረስ የሚሰጠው ምግብ ከአመድና ከዱቄት ድብልቅ የሚዘጋጅ ነው። ምግቡን ከሚያቀብለው ሰው ጋር እንኳን ማውራት አይፈቀድለትም። ምግቡን ከሚያቀብለው ሰው እጅ አይቀበልም።

ከዚህ በመነሳት የአካባቢው ማህበረሰብ ለግድያ ግጭት ያለው አመለካከት የግድያ ግጭት መከሰት የሌለበትና በግለሰብም ሆነ በጎሳ ላይ ከፍተኛ ጉዳትን የሚያስከትል ነው። ከተከሰተም በቶሎ መፈታት ያለበት ጉዳይ መሆኑን መገንዘብ እንችላለን ግድያ የፈፀመው ሰው እንደጀግና ሳይሆን እንደ እርኩስ፣ እንደሰይጣን እንደሚታይ እንረዳለን።

### 5.7 ባህላዊ የግድያ ግጭት አፈታት አውዳዊ ክዋኔ

በዚህ ክፍል የገዳይና የሟች ወገኖች ሚና፣ የሚፈፀሙ ድርጊቶች፣ ድርጊቶቹ የሚፈፅሙባቸውን መቼቶች፣ የሚጠቀሙባቸውን ባህላዊ ትዕምርቶች፣ የአስታራቂ ሽማግሌዎቹን ሚና ወዘተ. እንመለከታለን። ለዚህም ያመች ዘንድ የባህላዊ የግድያ ግጭት

አፈታቱን አውዳዊ ክዋኔ ቅድመ እርቅ፣ የእርቅ እና ድህረ እርቅ ክዋኔ በቅደም ተከተል እንመለከታለን፡፡

### 5.7.1 ቅድመ እርቅ ክዋኔ

በዚህ ክፍል ግጭቱ (ግድያው) ከተከሰተበት ጊዜ አንስቶ እስከ "ከጥፋት የመንፃት" ረኮ ስርዓት ያለውን ዓውዳዊ ክዋኔ እንመለከታለን፡፡

በቅድሚያ የግድያ ግጭቱ እንደተከሰተ ገዳይ፣ የገዳይ ቤተሰቦች ወይም የገዳዩ ጎሳዎች ሁኔታውን ፈጥነው ከነሱ እና ከሟች ጎሳ ውጪ ለሆነ ጎሳ ሽማግሌዎች በማሳወቅ እንዲያስታርቋቸው (ጉማ እንዲያወጡላቸው) ይጠይቃሉ፡፡

የግድያ ግጭትን የሚፈቱት ከሟች እና ከገዳይ ጎሳ ውጪ የሆኑ ሽማግሌዎች እንደሆኑ ደጋግመን ገልጸናል፡፡ እነዚህ ሽማግሌዎች በአካባቢው ማህበረሰብ 'ራያ አንባ' (Rayyaa anbaa) ይባላሉ፡፡

ገለልተኛ ሽማግሌዎቹ ጉዳዩ እንደተነገራቸው ፈጥነው የሚያደርጉት ነገር የገዳይ ወገኖች ከሟች ወገኖች እንዲርቁ ማድረግ ነው፡፡ በዚህም ገዳይ (የሰው ነፍስ ያጠፋውን ሰው) ከገለልተኛ ሽማግሌዎች በእድሜ ታላቅ የሆነው ሽማግሌ ቤት አቅራቢያ የሚገኝ ዋሻ ውስጥ፡ ዋሻ ካልተገኘ ኦና ቤት ውስጥ ይደብቁታል፡፡

ገዳይ የሽምግልናው ስርዓት ተሳክቶ ከደም የመንፃት ስርዓት ረኮ እስከሚፈፀምበት እለት ድረስ ከተደበቀበት አይወጣም፡፡ የሚመገበው እዛው ይሰጠዋል፡፡ ምግብ የሚሰጠውን ሰው እንዲያይ አይደረግም፡፡ ለገዳይ የሚሰጠው ምግብ የአመድና የዱቄት ድብልቅ ነው፡፡ ምግቡን የሚያቀብለው ሰው በቀዳዳ ያስቀምጥለታል፡፡ ገዳይ እጅ ላይ ደም አለ ተብሎ ስለሚታሰብ ያ ደም ደግሞ በንክኪ ስለሚተላለፍ ማንም አይጠጋውም፡፡ ማንም አይነካውም፡፡ ምግብም በእንጨት ራቅ ተብሎ ይሰጠዋል፡፡

ገለልተኛ ሽማግሌዎቹ ገዳዩን በኦና ቤት ወይም በዋሻ ውስጥ የሚደብቁት እሱን ከአደጋ ለመጠበቅ ብቻ አይደለም፡፡ ገዳይ ነፃ እንዳልሆነ ወይም ወንጀኛ መሆኑንም ለማሳየት ጭምር ነው፡፡

የሱ መደበቅ ብቻ በቂ አይደለም። የሟች ወገኖች ካገኙ የሚገሉት ገዳይን ብቻ አይደለም። የገዳይ ቤተሰቦችን እና የገዳይ ጎሳዎችንም ካገኙ ይገድላሉ። ስለዚህ ገለልተኛ ሽማግሌዎቹ የገዳይ ወገኖች የሟች ወገኖችን እንዲሸሹ፣ አንድ ገበያ እንዳይገበያዩ፣ ክብት አብረው እንዳያስማሩ፣ ክብት በሚያጠጡበት ክብት እንዳያጠጡ፣ በሚሄዱበት መንገድ እንዳይሄዱ ወዘተ. ያሳስባሉ።

ገለልተኛ ሽማግሌዎቹ ቀድመው የሚያከናውኑት ነገር ቢኖር የቀብሩን ስርዓት ማስፈፀም ነው።በባሌ ኦሮሞ ማህበረሰብ ዘንድ በሰው እጅ የሞተ ሰው የሌላ ጎሳ ሽማግሌ ሳያየው አይቀበርም። ስለዚህ ሽማግሌዎቹ ለቀብር የሚያስፈልጉ ጉዳዮችን በማሟላት ወደ ሟች ቤት ይሄዳሉ። ሽማግሌዎቹ ለቀብር የሚያስፈልጉ ነገሮችን ከገዳይ ወገኖች ነው የሚቀበሉት። በቅድሚያ የሚቀበሉት የከፈን ጨርቅ ‘ሁጩ አዋላ’ (huucuu awwala) ነው። የሟች ቤተሰቦችም የሚጠየቁትን የከፈን ጨርቅ (huucuu awwala) በፍጥነት ይሰጣሉ። ሽማግሌዎቹ የከፈን ጨርቁን ከተቀበሉ በኃላ የቀብር ክብት ‘ሎን አዋላ’ (Loon awwala) ይጠይቃሉ። ይህንን ከያዙ በኃላ ወደ ሟች መንደር በመገለጥ የሟችን አስከሬን ይመለከታሉ። አስከሬኑን በደንብ ካዩ በኃላ የከፈን ጨርቅ ይሰጣሉ። ራያ አንባዎች አስከሬኑን ማየታቸው በኃላ ለሚሰጡት ፍርድም ይረዳቸዋል።

የሟች ቤተሰቦች ጨርቁን ተቀብለው አስከሬኑ ተገንዞ የቀብር ስርዓት ይፈፀማል። ከቀብር ስርዓት በኃላ ራያ አንባዎቹ ከገዳይ ወገኖች የተቀበሉትን የቀብር ክብት ለሟች ወገን ይሰጣሉ። ለቀብር የሚሰጠው ክብት አንድ ሲሆን እንደ ጉማ ክብቶች ያስገመድ የሚነዳ አይደለም። ከገመድ ጋር ነው የሚሰጠው። ገመድ መደረጉም አዲስ በመሆኑ ወደ መጣሁበት እያለ እንዳያስቸግር ነው። የቀብር ክብት መስጠት ማስተዛዘኛ እንደመስጠት የሚቆጠር ነው። የሟች ወገኖች ከደረሰባቸው መሪር ሀዘን እንዲፅናኑ ማድረጊያ ነው።

የገለልተኛ ጎሳ ሽማግሌዎቹ የገዳይ ጎሳዎችን ወደ አንድ የዛፍ ጥላ ‘ኦዳ’ (odaa) ስር ጠርተው “አንተ የሰው ሰው ገድለሃል መንገድሕ የስህተት ነው (የጥፋት ነው) ፣ እጅህ ላይ ደም አለ ፣ እጅህ የደም እጅ ነው ፣ አንተ ጉማ ያለብህ ሰው ነህ ፣ ጉማ ታወጣለህ።” በማለት ከላይ የተጠቀሱትን ለቀብር የሚያስፈልጉ ነገሮች እንዲያመጣ ከገዳይ ጎሳ ሀንገፋ (ታላቅ) የሆነውን ሰው ያዛሉ። ከዚህ በኃላ ከገዳይ ጎሳዎች የተቀበሉትን ያስከሬን መሸፈኛ ጨርቅ እና የቀብር

ከብት ይዘው ወደቦታው ደርሰው አስከሬኑን በደንብ ተመልክተው ካበቁ በኃላ ከሚች ጎሳ ሽማግሌዎችን ወደ ዛፍ ጥላ ስር ጠርትው የሚከተለውን ይናገራሉ፡፡

"የሞተው መከታህን አይቻለሁ ፣ የገደለው የእነእገሌ ጎሳ ነው ፣ የእነእገሌ ቤተሰብ ነው፡፡ አንተ ደግሞ አሁን በእኔ በጎሳ ሽማግሌ (በራያ አንባ) እጅ ውስጥ ነህ ፣ በኔ ራስ ላይ ነህ ፣ መንቀሳቀስ አይገባህም ፣ የሰው አይን አትውጋ ፣ ቢላዋህን ከሃፎቱ መልስ ፣ የጦርህን ጫፍ ቁልቁል መልስ ፣ እጄ ላይ ነህ ያለኸው፡፡ የሞተብህን ሰው ጉማ እኔ ተከታትዬ አስወጣልሀለሁ ፣ አንተ አርፈህ ተቀመጥና ጉማህን ከኔ ጠብቅ" ይላሉ፡፡ ከዛም የቀብር ስርዓቱ በሰላም ተፈፅሞ ራያ አንባዎቹ የቀብር ከብቱን ለሚች ወገን ሰጥተው ይሄዳሉ፡፡ በዚህም የገለልተኛ ወገን ሽማግሌዎች ጉዳዩ መሃል መግባታቸውን በማሳወቅ የሚች ጎሳ አባላት በገዳይ ጎሳዎች ላይ ጥቃት እንዳያደርሱ ይገዘታሉ፡፡

በባሌ ኦሮሞ ማህበረሰብ ሽማግሌ ትልቅ ቦታ ይሰጠዋል፡፡ እንደውም የሽማግሌን አስፈላጊነት ብቻ ሳይሆን የግድነት በምሳሌ ሲናገሩ "Lafa namni guddaan hinjireefii lafa mukni guddaan hinjiree hinjiraatan" (ትልቅ ሰውና ትልቅ ዛፍ የሌሉበት አይቀመጡበት/አይኖሩበት) ይላሉ፡፡ ሽማግሌ ለተረጋጋ ማህበራዊ ህይወት መኖር ከፍተኛ ድርሻ አለው፡፡ ማንም ምንም ያህል በደረሰበት ከፍተኛ ሀዘን ለበቀል ቢነሳሳም ገለልተኛ የሆኑ ሽማግሌዎች መሀል ከገቡ በኃላ ግን በዛ አይቀጥልም፤ ይተዋል፡፡ ማንም የሽማግሌን ቃል አይጥስም፡፡

ከዚህ የሚቀጥለው የረፊሳ ስርአት (Raffisa) (የቀጠሮ ስርዓት) ነው፡፡ የረፊሳ ስርዓት ማለት በጉማ ስርዓት የቀጠሮ ጊዜ ደርሶ የከብትም ሆነ የገንዘብ ክፍያ ተደርጎ እርቅ እስከሚወርድ ድረስ የሚችና የገዳይ ጎሳዎች የባሰ ችግር ውስጥ እንዳይገቡ ለጊዜው ሰላም የማስፈን ሂደት ነው፡፡ በሌላ አነጋገር ረፊሳ ማለት የጉማ ስርዓት ቀብድ[12] ነው፡፡

የቀብር ስርዓት ካለቀ በኃላ በማግስቱ የጉማ ሽማግሌዎች ተሰብስበው የገዳይን ጎሳ ያወያያሉ፡፡ ጎሳው በቂ ሃብት ካለው የጉማ ክፍያው በቶሎ ይከናወናል፡፡ ነገር ግን ጎሳውም ሆነ ገዳዩ በቂ ሃብት ከሌላቸው ጉማ የሚከፈልበት ቀጠሮ ይሰጣል፡፡ የሚሰጠው ቀጠሮ ከአንድ እስከ ሁለት ወር ሊደርስ ይችላል፡፡ይህን ሁሉ ጊዜ የሚችና የገዳይ ወገኖች እርቅ ሳያወርዱ እንዲቆዩ

---

[12] አቶ ማማ፣ አቶ ሀጂ ፣ ቃለመጠይቅ፣ ሚያዝያ 22፣ 20003 ፣ጎባ፡፡

አይፈቀድም፡፡ ሽማግሌዎቹ ነገሮች በቶሎ ተጠናቀው የሟች እና የገዳይ ጎሳዎች በረከ ስርዓት መሰረት በተቀደደ ቆዳ ውስጥ እንዲሾሉኩና ከእጅ ላይ የመብላት ስርዓት እንዲፈፅሙ ለማድረግ ይጥራሉ፡፡ ይህ ስርዓት በፍጥነት እንዲከናወን ደግሞ የሟች ወገኖች ፍቃድ መገኘት አለበት፡፡ የሟች ወገኖች ጉማ እንዲከፈላቸው ይፈልጋሉ፡፡ ለዚህም ሙሉ ጉማው እስኪወጣ ድረስ የ Raffisa ስርዓት ይደረጋል፡፡

ረፊሳው በከብት ወይም በገንዘብ ሊከፈል ይችላል፡፡ መረጃ አቀባዮቼ እንደነገሩኝ የ Raffisa ዋጋ በድሮው በoddaa Roobaa ውሳኔ መሰረት 50 ከብት ነበር፡፡ በሂደት ግን ወደ25 ከብት ዝቅ ብሎ ነበር፡፡ በአሁኑ ጊዜ ያለው የ Raffisa ዋጋ ከ5-10 ከብት ሲሆን በገንዘብ የሚከፈል ከሆነ ደግሞ በሟችና በገዳይ ወገኖች ስምምነት የሚወሰን ይሆናል፡፡

ጉማ የሚከፈለው በጎሳ (በህብረት) ነው፡፡ የሚበላውም በጎሳ ነው፡፡ Raffisa ግን ለሟች ቤተሰቦች ብቻ የሚሰጥ ስጦታ ነው፡፡ የጉማ ሽማግሌዎች ለRaffisa የሚያስፈልገውን ከብት ከገዳይ ጎሳ ተቀብለው ለሟች ቤተሰቦች ይሰጣሉ፡፡ በቅድሚያ ሽማግሌዎቹ የሟችን ጎሳ ወደ ጥላ ስር ወስደው ያስቀምጧቸዋል፡፡ ከዛ በኃላ እንዲህ ይላሉ፡፡

"ወገንህን የገደለውን ትላንት ነግሬው ለቀብር የሚሰጠውን ሁሉ ትላንት ሰጥቼሀለሁ፡፡ በእጄ ነው ያለሀው፣ ትላንት ጉማህን አወጣልሀለሁ ብዬህ ነበር፣ ጠብቅ በጥላው ስር ደርሼ ጉማህን አወጣልሀለሁ" በማለት ከሟች ወገን የተቀበሉትን ረፊሳ ለሟች ቤተሰቦች ይሰጣሉ፡፡

ሽማግሌዎቹ ለሟች ቤተሰብ ረፊሳ ከሰጡ በኃላ የረጅም ጊዜ ጉማ እንዲፈቅዱላቸው የሟችን ጎሳ ይጠይቃሉ፡፡ በዚህም ሽማግሌዎቹ ከሟች ወገን ከ2 ወር ያልበለጠ ጊዜ ይጠይቃሉ፡፡ ይህ ጊዜ ሙሉ ጉማውን ከገዳይ ወገኖች ተቀብለው ለሟች ወገኖች የሚሰጡበት ነው፡፡

ከዚህ በኃላ ሽማግሌዎቹ ወደ ገዳይ ወገን ይመለሱና የገዳይ ወገኖችን በጠቅላላ እንዲሰበሰቡ ያዛሉ፡፡ የገዳይ ጎሳ አባላት ከተሰበሰቡ በኃላ ሽማግሌዎቹ የሚከተለውን ይናገራሉ፡፡

"የገዳይን ስም በመጥራት እገሌ እገሌን (የሟችን ስም ጠርተው) መግደሉን ሰምታችኋል ጉማ ወጥቷል፣ የቀብር ቀኑን አውጥተናል፣ ረፊሳ ሰጥተናል፣ የቀረን ረጅሙ ጉማ ነው፡፡ ለረጅሙ ጉማ የሚያስፈልገው 90 ከብት ነው ይህንን ተከፋፍላችሁ አውጡ፡፡"

በዚህ ጊዜ የጎሳው አባላት ከተሰበሰቡበት ሳይበተኑ 90 ከብት ተከፋፍለው ለማውጣት ቃል ገብተው እዛው ይከፋፈላሉ፡፡ ሽማግሌዎቹ በሰጧቸው የቀጠሮ እለትም ከብቶቹን ይዘው ለመምጣት ይስማማሉ፡፡

የገዳዩ ጎሳ አባላት ስምምነታቸውን ከገለፁ በኃላ ሽማግሌዎቹ አንድ ማስጠንቀቂያ ይናገራሉ፡፡ ማስጠንቀቂያው ሁሉም ቃል የገባውን ከብት ማምጣት ይጠበቅበታል በቀጠሮው ቀን ከብቱን ያላመጣ ሰው ላይ ቅጣት ይጣላል የሚል ነው፡፡

ሽማግሌዎቹ ይህንን ማስጠንቀቂያ የሚናገሩበት ምክንያት በቀጠሮ እለት የተመደበባቸውን ከብት ባላመጡ ወገኖች ላይ 'ሰዴት ካኩራ' (saddeeta kaakuuraa)[13] እንደሚልኩባቸው ለመግለፅ ነው፡፡ saddeeta kaakuuraa የሚባሉት ከጉማ ሽማግሌዎቹ ጎሳ የተውጣጡ ስምንት ጠንካራ ሰዎች ናቸው፡፡ እነዚህ ስምንት ሰዎች የተመደበበትን ከብት በጊዜው ካላመጣው የገዳይ ጎሳ ላይ ከብት የሚወስዱ ናቸው፡፡ ሰዴት ካኩራዎች የተመደደበበትን ከብት በቀጠሮው እለት ያላመጣው ሰው ቤት ይሄዱና በቅድሚያ "Bulti" ቡልቲያችንን አምጣ ብለው ግቢው ውስጥ አንድ ከብት አርደው ይበላሉ፡፡ ከዛ በኃላ የተመደበበትን ያህል ከብት ነድተው ይሄዱና ለሽማግሌዎቹ ያስረክባሉ፡፡ ሰውዬው ፍቃደኛ ካልሆነ ደብድበውት ከብቱን ይነዳሉ፡፡ ይህንን ከግንዛቤ በማስገባት ቃል የገቡትን ከብት በቀጠሮው እለት እንዲያመጡ ያስጠነቅቃሉ፡፡

### 5.7.2 የእርቅ ክዋኔ

ገለልተኛ ወገን የሆኑት ሽማግሌዎች (Rayyaa Anbaa) በገዳይ እና በሟች ጎሳዎች መካከል ገብተው ሟችን በሰላም አስቀብረው ፣ በቀብር ዕለት ለሟች ወገኖች የሚሰጠውን አሰጥተው ፣ ለሙሉ ጉማው ቀብዲ (Raffisa) አሰጥተውና የሟች ወገኖችን አሳምነው በፍጥነት ወደ እርቅ እንዲመጡ ያደርጋሉ፡፡

የግድያ ግጭት ባህላዊ የእርቅ ክዋኔ የሚካሄደው በቀን ነው፡፡ በምሽት የግድያ ግጭት እርቅ ማካሄድ ፍፁም የተከለከለ ነው፡፡ የግድያ ግጭት በአንድ ቀን ላይጠናቀቅ ይችላል፡፡ እንዲህ ያለ ሁኔታ ሲያጋጥም የጉማ ሽማግሌዎቹ የሟች እና የገዳይ ወገኖችን ለቀጣይ ቀን ቀጥረው በጊዜ ያሰናብቷቸዋል፡፡

---

[13] saddeeta kaakuuraa የሚለው ሀረግ ከጮይቱ ጋር በተለዋዋጭ ይጠቀሙበታል፡፡

ለእርቅ በመረጡት ቀን የገለልተኛ ወገን ሽማግሌዎቹ ማልደው ይሰበሰቡና የእርቅ ሒደቱ የሚከናወንበት አካባቢ ያዘጋጃሉ፡፡ የግድያ ግጭት የእርቅ ስርዓት የሚካሄደው በሶስት ጥላ ስር ነው፡፡ አቶ ከድር የተባሉ መረጃ አቀባዬ የግድያ ግጭት እርቅ የሚካሄድበት ጥላ በሶስት እንደሚከፈልና 'ጋዲሳ ጉማ' (Gaaddisaa Gumaaa) እንደሚባል ከነገሩኝ በኃላ ጥላዎቹን እንደሚከተለው ይከፍልዋቸዋል፡፡ (ቃለ መጠይቅ፣ ሚያዚያ 22፣ 2003ዓ.ም ጎባ)

1. Kan waarii namni irra dhu'e ta'uu
2. Kan namni nama ajjeese ta'uu
3. Kan qari ta'u /Raayyaa anbaa ta'uu

   1. የሟች ወገኖች የሚቀመጡበት
   2. የገዳይ ወገኖች የሚቀመጡበት
   3. የገለልተኛ ጎሳ ሽማግሌዎች የሚቀመጡበት

የኦሮሞ ህዝብ የእርቅ ስርዓት ብቻ ሳይሆን ሌሎችም ማህበራዊ እና ሀይማኖታዊ ጉዳዮችን የሚያከናወነው በዛፍ ጥላ ስር ነው፡፡ በብዙ ፅሁፎች ውስጥ እንደተገለፀው የኦሮሞ ህዝብ ማህበራዊ ፣ ፖለቲካዊ ፣ ሀይማኖታዊ ጉዳዮችን ለማካሄድ የሚሰበሰበው የ'ኦዳ' (odaa) ዛፍ ስር ነው፡፡ ኦዳ የኦሮምኛ ቃል ሲሆን በጥሬ ትርጉሙ ሰፊ ቅርጫፍ ያለው የዛፍ አይነት ማለት ነው፡፡

ኦዳ በአብዛኛው የኦሮሞ ህዝብ ዘንድ ከፍተኛ ባህላዊ እሴት ያለው ትዕምርት ነው፡፡ በማህበረሰቡ ውስጥ የተለያዩ ግለሰቦች ወይም ቡድኖች መሃላ ፣ እርግማን ፣ ምርቃት ወዘተ ሲፈፅሙ የኦዳ አይነቶችን ይጠራሉ፡፡ የኦዳ አምላክ እንዲረዳቸው ይማፀናሉ፡፡ ከሚጠሩት ኦዳዎች ውስጥ አንዱ ኦዳ ሮባ (odaa roobaa) በባሌ ዞን ውስጥ በጊኒርወረዳ ይገኛል፡፡

ኦዳን የኦሮሚያ ክልላዊ መንግስትም የራሱ አርማ አድርጎ ይጠቀምበታል፡፡ የኦዳ ግንድ በሁለት ተከፍሎ ይወጣና አንድ ሰፊ ቅርንጫፍ ይኖረወዋል፡፡ ከታች ያለውና በሁለት የተከፈለው ቦረና እና ባሬንቱ የሚባሉትን አበይት የኦሮሞ ጎሳዎች የሚወክል ሲሆን የቅርንጫፎቹ መብዛትና መስፋት ደግሞ አያሌ የኦሮሞ ጎሳዎችን ይወክላል፡፡ (አቶ ሀሰን፣ አቶ አማን ቃለ መጠይቅ፣ ሚያዚያ 20፣ 2003 ሲናና)

አዳ የእምነት ስፍራ ብቻ ሳይሆን የማህበረሰቡ ሴረዎች (አስተዳደር ስርዓቶች) የሚደነገጉበት፣ በገዳ ስርዓት አባ ገዳዎች ፍርድ የሚሰጡበት ቦታ ሆኖ ሲያገለግል የቆየ መሆኑን ሽማግሌዎቹ ይናገራሉ። በሌላ በኩል ህዝቡ ራሱን የሚገዛበት፣ የአኗኗር ደንብ የሚደነግግበት፣ ሽማግሌዎች ጥፋት የሰሩ ሰዎችን የሚመክሩበት፣ የተጎዱ ወገኖችን የሚያፅናኑበት፣ የሚክሱበት የውሳኔ መስጫ ቦታ ነው። አዳ ማህበረሰቡ ለገጠመው ችግር መፍትሄ ያገኝ ዘንድ ወደ አምላኩ የሚፀልይበት፣ አምላኩ ክፋውን እንዲያርቅለት፣ ሰላሙን፣ ከብቱን፣ ምርቱን እንዲጠብቅለት የሚለማመንበት ስፍራም ነው።

ከላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው አዳ የአንድ ዛፍ አይነት (የሾላ፣ የዋርካ) መጠሪያ ብቻ አይደለም። አዳ ትልቅና ሰፊ ቅርጫፍ ያለው የዛፍ አይነት ነው። ለዚህ ጥናት የተመረጡት የሲናና እና የጎባ ወረዳዎች የአየር ፀባያቸው ደጋ እና ወይና ደጋ ነው። በዚህ ምክንያት ማህበረሰቡ አንዳንድ ማህበራዊም ሆነ እምነታዊ ጉዳዮችን ለማካሔድ በብዛት የሚሰበሰቡበት በፅድ (Gaattirra) ጥላ ስር ነው።

ፎቶግራፍ 1 የባሌ ኦሮሞ ማህበራዊም ሆነ እምነታዊ ጉዳዮችን ለማካሔድ የሚሰበሰብበት የዛፍ ጥላ (ግንቦት 4፣ 2003ዓ.ም ጎባ)



ፎቶግራፍ 2 ቁልፍ መረጃ አቀባዮች በፅድ ጥላ ስር ተሰብስበው (ግንቦት 4፣ 2003ዓ.ም ጎባ)



የጉማ ሽማግሌዎቹ ቀድመው መገኘታቸው ስርዓቱ የሚከናወንበት ቦታ ለመምረጥ ብቻ አይደለም። የግድያ ግጭቱ ከተከሰተ ወዲህ ለመጀመሪያ ጊዜ ፊት ለፊት የሚገናኙት የገዳይና የሟች ወገኖች መሀከል ሌላ ግጭት እንዳይነሳ ለመከላከልም ነው። የሟች ወገኖች በቁም በቀል

ተነሳስተው የገዳይ ወገኖች ላይ ጥቃት እንዳያደርሱ ሽማግሌዎቹ ይመክራሉ። ጦር ፣ ጩቤ ፣ ገጀራ የመሳሰሉትን መሳሪያዎች እንዲጥሉ የገዳይ ቤተሰቦችን አፍጥጠው እንዳያዩ ያስጠነቅቃሉ፤ ይማፀናሉ።

የባሌ ኦሮሞ ማህበረሰብ ሌሎች የእለት ግጭቶችን ለመፍታትም የሚሰበሰበው በዛፍ ጥላ ስር ነው። ነገር ግን እንደ ግድያ ግጭት ሶስት ጥላ ስር አይሰበሰቡም። ሶስት ጥላ የሚጠቀሙት ለግድያ ግጭት ብቻ ነው። ሌሎች ግጭቶች የግድያ ግጭትን ያህል ለቂም በቀል ስለማያስነሱና የተጋጩትም አካላት እውነታን እና ካሳን ብቻ ስለሚፈልጉ ነው።

በግድያ ግጭት ግን የሟች ወገኖች በቆዳ ውስጥ የመሹለክ እና ከእጅ ላይ የመብላቱ ስርዓት እስኪፈፀም ድረስ የሟች ወገናቸውን ደም ለመመለስ በቂም በቀል እንደሚነሳሱ ስለሚገመት ከዚህ ስርዓት በፊት ከገዳይ ወገኖች ጋር እንዳይገናኙ ለማድረግ ነው።

ሽማግሌዎቹ የሚያዘጋጁት ቦታ ከሶስት ጥላ ባለፈ "ደረቅ ወንዝ" ወይም "ደረቅ ዛፍ" ያለበት አካባቢ መሆን አለበት። ምክንያቱም በባሌ ኦሮሞ ማህበረሰብ ባህል መሰረት የግድያ ግጭት የመጨረሻው የእርቅ ስርዓት የሚካሄደው በ"ደረቅ ዛፍ" ስር ወይም "በደረቅ ወንዝ" ውስጥ ስለሆነ ነው።

በባሌ ኦሮሞ ማህበረሰብ ባህል መሰረት የግድያ ግጭት እርቅ የመጨረሻው ስርዓት ረኮ (Rakkoo) ይባላል። ይህ ስርዓት በሌሎች የኦሮሞ ማህበረሰቦች ዘንድ ሐርካ ባፈታ (Harka baafata)[14] በመባል ይታወቃል።[15]

በማህበረሰቡ ባህል በግድያ ወቅት የከብት እርድ (ደም ማፍሰስ) የማይቀር ነው። በረኮ ስርዓትም አንድ በግ ይታረዳል።

ሽማግሌዎቹ የእርቅ ስርዓቱ የሚፈፀምበትን ቦታ ካስተካከሉ በኃላ ቦታቸውን (Gaaddissaa Raayyaa anbaa) ይይዛሉ። ይህ ጥላ የጉማ ሽማግሌዎች የሚቀመጡበት ጥላ ከሟች ወገኖች ጥላ (Gaaddissaa kan waarii namni irra dhu'ee ta'uu) እና ከገዳይ ወገኖች ጥላ (Gaaddissaa kan namni nama ajjeese ta'uu) መካከል ላይ ነው የሚገኘው። የሟችና

---

[14] ሀርከ ባፈታ እጅ ማንፃት ከሚለው የአማርኛ ሀረግ ጋር ይመሳሰላል።

[15] ሰለሞን ተሾመ፣ የግድያ ግጭት ባህላዊ አፈታት በሰሬ ኦሮሞዎችና አማራዎች ንፅፅራዊ ጥናት 2002ዓ.ም፣ ሙሉጌታ ነገሳ፣ በአደአ ሊበን ወረዳ የኦሮሞ ሴረ ጉማ ከግጭት አፈታት አንፃር 1997ዓ.ም የኤም.ኤ. ዲግሪ ማሟያ ፅሁፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢ.ቋ.ስ ት/ክፍል።

የገዳይ ወገኖች የሚቀመጡበት ቦታ የታወቀ ነው። እንደ አመጣጣቸው፣ እንደፍላጎታቸው አይቀመጡም። የሚች ወገኖች ጥላ ከሽማግሌዎቹ ጥላ በስተቀኝ ሲገኝ የገዳይ ወገኖች ጥላ ደግሞ ከሽማግሌዎቹ ጥላ በስተግራ ይገኛል። የሚችና የገዳይ ወገኖች ጥላ መገኚያ ስፍራ በራሱ ባህላዊ ትዕምርት አለው።

ፎቶግራፍ 3 የግድያ ግጭት አፈታት ስርዓት የሚካሄድባቸው ሶስት ጥላዎች(ግንቦት 4፣ 2003ዓ.ም ጎባ)




የሚች ወገኖች ከሽማግሌዎቹ ጥላ በስተቀኝ በሚገኝ ጥላ ስር መቀመጥ የሚች ወገኖች ንፁህ፣ ከጥፋት የራቁ፣ የተከበሩ፣ የተመሰገኑ፣ የተባረኩ፣ ጥሩዎች እንደሆኑ የሚገልፅ ነው። የገዳይ ወገኖች ከሽማግሌዎቹ በስተግራ መቀመጥ ደግሞ የገዳይ ወገኖች እጃቸው በደም ያደፈ፣ የእርኩስ መንፈስ፣ የክፋት ማደሪያዎች፣ የሃጢያት ማደሪያዎች፣ የመጥፎ እድል እና የመጥፎ መንፈስ ተምሳሌቶች እንደሆኑ የሚያሳይ ነው።

ሁለቱም ወገኖች (የሚች እና የገዳይ) በቀጠሮው ሰዓት በስፍራው በመገኘት ቦታ ቦታቸውን ይይዛሉ። በሚች ወገን የሚች የቅርብ ዘመዶች (አባት፣ ወንድም፣ አጎት ወዘተ.) የጎሳው የእድሜ ባለፀጋ "ሀንጋፋ" እና ሌሎች ሽማግሌዎች ይገኛሉ። በገዳይ ወገኖች ጥላ ስርም ገዳይ እና የገዳይ የቅርብ ዘመዶች (አባት፣ ወንድም፣ አጎት ወዘተ.) የጎሳው የእድሜ ባለፀጋ እና ሌሎችም የጎሳው ሰዎች ይገኛሉ።

በዚህ ጊዜ ሽማግሌዎቹ የሚከተለውን አዋጅ /ማሳሰቢያ/ ይናገራሉ:- "Egga gaadissa nagattee maare marxoo na hikadhu, biilaa mudhi nahiikadhu, affrii nagaddeebbisi

ijja gaddi naqaababuu." (በጥላው ስፍራ ከተገኘህ ትጥቅህን ፍታልኝ፣ ጨቤህን ከወገብህ አውርድልኝ፣ የጦርህን ጫፍ ቁልቁል መልስ፣ አይንህን ስበርልኝ) ይላሉ፡፡

የጉማ ሽማግሌዎቹን ብዛት ቀደም ብለን ገልፀናል፡፡ በዚህ ጊዜ ግን በጥላው ስር የሚገኙት ሽማግሌዎች ብዛት ዘጠኝ ሲሆን ስምንቱ ቆርቱ የሚባሉትና የእርቅ ስርዓቱን የሚያከናውኑት ሲሆኑ አንዱ የሁሉም የሃያ አራቱ ሽማግሌዎች ሰብሳቢ ነው፡፡ የጉማ ሽማግሌዎች የሚሆኑት ከገዳይና ከሟች ጎሳ ውጪ የሆኑ ገለልተኛ ወገኖች ናቸው፡፡ የጉማ ሽማግሌዎች የሚመረጡት ከሟችና ከገዳይ ጎሳ ውጪ በመሆናቸው ብቻ አይደለም፡፡ የሌላ ጎሳ ከመሆናቸውም ባለፈ የጉማ ሽማግሌዎች የሚመረጡት ባላቸው ማህበራዊ ተቀባይነት፣ በእድሜ ባለፀጋነት፣ ባላቸው ሀብት ንብረት፣ በባህል እውቀታቸው፣ በነገር አዋቂነታቸው፣ በትዕግስተኝነታቸው፣ በሀቀኝነታቸው ወዘተ. ነው፡፡

የሁሉም ሽማግሌዎች ሰብሳቢ የሆነው ቀራ ቡልኮ ለብሶና አለንጌውን ይዞ መሀከል ላይ ይቀመጣል፡፡ የተቀሩት ሽማግሌዎችም ነጭ ጋቢያቸውን ለብሰውና አለንጋቸውን ይዘው ከቀራው ግራና ቀኝ ይቀመጣሉ፡፡ ሁሉም ሰው መገኘቱን ካረጋገጡ በኃላ ሁሉም ከተቀመጡበት ይነሱና እጆቻቸውን በመዘርጋት ምርቃት ያደርጋሉ፡፡ በባሌ ኦሮሞ ማህበረሰብ ዘንድ የትኛውም ማህበራዊ ጉዳይ በአባቶች ምርቃትነው የሚጀመረው፡፡

የምርቃቱን ስርዓት የሚጀመረው ቀራው ነው፡፡ ቀራው ሲመርቅ የተቀሩት ሽማግሌዎች ፣ የሟች ወገኖችና የገዳይ ወገኖች ተነስተው እጃቸውን ወደፊት ዘርግተው አሜን በማለት ይቀበላሉ፡፡

Waaqayyo araara kana ati nurraa fudhu

(ፈጣሪ ሆይ ይህንን እርቅ ተቀበለን፡፡)

Lubbuu ilma keenya du'ee nuuf fayyisi

(የሟች ልጃችንን ነፍስ ማርልን፡፡)

Laphee warra jalaa du'ee jabeessi

(የሟችን ወገን ልብ አፅናና፡፡)

Osoo hin beekin lubbuu dhala namaa kan balleesseef dhiifama godhi

(ሳያውቅ የሰው ነፍስ ላጠፋው ልጃችን ይቅርታ አድርግለት፡፡)

በማለት ምርቃት ካደረሱ በኃላ ሁሉም ይቀመጣሉ፡፡ ከዛም ሽማግሌዎቹ ጥቂት ይነጋገሩና በቅድሚያ የሟች ወገኖችን ስለጠቡ መነሻና ስለሟች እና ገዳይ የቀደመ ግንኙነት የሚያውቁት ነገር ካለ እንዲናገሩ ይጠይቃሉ፡፡ በሟች ወገን የቀረቡት ሽማግሌዎች እና የሟች ዘመዶች የነበረውን እና የሚያውቁትን ሁኔታ በሙሉ ያስረዳሉ፡፡ የሟች ወገኖች ሲናገሩ የገዳይ ወገኖች ጣልቃ መግባትና አግባብ ያልሆነ እንቅስቃሴ ማድረግ አይፈቀድላቸውም፡፡

በመቀጠል ሽማግሌዎቹ ለገዳይ ወገኖች ስለገዳይና ሟች ግንኙነት፣ ስለግድያው ሁኔታ እንዲናገሩ እድል ይሰጣሉ፡፡ የገዳይ ወገኖችም ስለሁኔታው የሚያውቁትን ይናገራሉ፡፡ በዚህ ጊዜ የሟች ወገኖች በንግግር ጣልቃ መግባት ፣ መናደድ ፣ መበሳጨት አይፈቀድላቸውም፡፡ ጣልቃ መግባት እንደህግ ይቀመጥ እንጂ ለረጅም አመት የጉማ ሽማግሌ ሆነው ሲሰሩ ይህ ነው የሚባል የጣልቃ መግባት ፣ የመነጫነጭ ፣ የመበሳጨት ሁኔታ ከገዳይም ሆነ ከሟች ወገን እንዳልገጠማቸው አቶ ከድር የተባሉ መረጃ አቀባዩ ገልፀውልኛል[16]፡፡ ይህን ጉዳይ በተመለከተ ጀቤሳ ኤጀታ (1989፣ 36) ላይ "ኦሮሞዎች…በነገር እልህ አይዛቸውም፡፡ ተው ብሎ የሚያስታርቃቸው ሰው ካጋጠማቸው ሽማግሌን አይጋፉም፡፡" በማለት ፅፈዋል፡፡

ሽማግሌዎቹ የጉማውን ክፍያ ወስነው ነው የረፋሳ ስርዓቱን የሚያከናውኑት፡፡ የጉማ ዋጋ ቀድሞ የታወቀ ነው፡፡ ዋጋውን የሚወስነው የግድያው ሁኔታና የሟችና የገዳይ ቀረቤታ ነው፡፡ በዚህ ቀንም ከፍተኛው ክርክር የሚደረገው በጉማ ክፍያው ላይ ነው፡፡ የሟች ወገኖች የጉማው ክፍያ ከፍ እንዲልላቸው፣ የገዳይ ወገኖች ደግሞ እንዲቀንስላቸው የተለያዩ የመከራከሪያ ሀሳቦችን እያነሱ ይከራከራሉ፡፡

የጉማ ሽማግሌዎቹ የግራ ቀኙን ከሰሙ በኃላ በጋራ ይመክሩና የደረሰበትን ውሳኔ ያሳውቃሉ፡፡ ውሳኔውን የሚናገረው ቀራው ነው፡፡ ቀራው ሽማግሌዎቹ የደረሱበትን ውሳኔ ድምፁን ከፍ አድርጎ ሲያሰማ የሟችም ሆኑ የገዳይ ወገኖች የማይስማሙበት ጉዳይ ካለ መንጫጫት ፣ መናገር አይፈቀድላቸውም፡፡ ልክ የማይስማሙበት ነገር ሲነገር የገዳይም ሆነ የሟች ወገኖች አለንጋቸውን ወደላይ ያነሳሉ፡፡ ስምምነት ያልተደረሰበትን ጉዳይ ሽማግሌዎቹ ደግመው ያዩትና

[16] አቶ ከድር፣ ቃለ መጠይቅ፣ ሚያዚያ 20፣ 2003ዓ.ም ጎባ)

ካመኑበት ያሻሽሉታል። በዚህ ጊዜ ቀድሞ ተቃውሞ ያሰማው አካል በተሻሻለው ጉዳይ ከተስማማ ስምምነቱን የሚገልፀው ወደላይ የያዘውን አለንጋ በፈገግታ ታጅቦ መሬት ላይ በማስቀመጥ ነው። ሽማግሌዎቹ ሁሉንም ወገኖች ካስማሙ በኋላ ቀጣዩ ስርዓት የሚሆነው "ረኮ" ስርዓት ነው።

የረኮ ስርዓት ግጭት ውስጥ የገቡት አካላት በመካከላቸው ያለውን መጥፎ የጥላቻ መንፈስ የሚያርቁበት ፣ በቀጣይ በቂም በቀል ስሜት እንዳይፈላለጉ አንዱ ከአንዱ እጅ የሚበላበት ፣ ወደፊት በመካከላቸው ያለው ግንኙነት ፍፁም የወዳጅነት እንዲሆን ከገዳይ ወገን ሴት ልጅ ለሟች ወገን የምትሰጥበት ስርዓት ነው።

የግድያ ግጭት እርቅ የሚካሄደው "በደረቅ ዛፍ ስር ወይም በደረቅ ወንዝ[17] ውስጥ" ነው። የግድያ ግጭቱ እርቅ "በደረቅ ዛፍ ስር ወይም በደረቅ ወንዝ" ውስጥ መደረጉ የራሱ የሆነ ትዕምርት አለው። የደረቀ ዛፍ አይበቅልም፣ አያለመልምም፣ ፍሬ አያፈራም። የባሌ ኦሮሞዎች የግድያ እርቅ በዚህ (በደረቅ ዛፍ) ስር ከተካሄደ ጉማው (ደሙ) አይቀጥልም፣ ወደ ቀጣይ ትውልድ አይተላለፍም፣ እንደዛፉ የደረቀ ይሆናል የሚል ዕምነት አላቸው።

የግድያ እርቅ በደረቀ ወንዝ ውስጥ መካሄዱም ደሙን ያደርቀዋል ተብሎ ይታሰባል። ወንዙ ውሃ ካለው ደሙን ይዞ በመሄድ ለሌሎችም ያደርሳል። ወንዙ እስኪደርቅም ለሚመጡት ትውልዶች ሁሉ እንዲተላለፍ ያደርጋል። በደረቅ ወንዝ ውስጥ ከተካሄደ ግን ወንዙ ስለማይሄድ ደሙም የረጋ፣ የደረቀ ይሆናል። ለሌሎች ሰዎችም ሆነ ለቀጣይ ትውልድ አይተላለፍም ደርቆ ይቀራል የሚል እምነት አላቸው።

በቅድሚያ ለስርዓቱ የተዘጋጀው በግ ይታረዳል። ለስርዓቱ የሚታረደው በግ ሁለት አይነት የቆዳ ቀለም ያለው ነው። ጥቁርና ነጭ። ከግንባሩ እስከ ወገቡ ድረስ ጥቁር ሆኖ ከወገቡ እስከ ላቱ

[17] በሌሎች የኦሮሞ ማህበረሰቦች ላይ ጥናት ያደረጉ ምሁራን ምሳሌ ሰለሞን 2002 እና ሙሉጌታ 1997ዓ.ም ባጠኑት ማህበረሰብ ባህል መሰረት የረኮ (ሀርከ ባፊታ) ስርዓት ከብት የሚታረደው በወራጅ ወንዝ ውስጥ እንደሆነ ይገልፃሉ። በወራጅ ወንዝስ ውስጥ መካሄዱ ጉማው (ደሙ) እንዲሄድ ያደርገዋል ይላሉ። የባሌ ኦሮሞዎች ባህል ግን በተቃራኒው በደረቅ ወንዝ ውስጥ ነው። ምክንያቱ ደግሞ ጉማው ደርቆ እንዲቀር ነው። የባሌ ኦሮሞዎች ፍልስፍና ከህንዶች የቀብር ስርዓት ጋር ተመሳሳይ ይመስለኛል። ሕንዶች አንድ ሰው ሲሞት አስከሬኑን አቃጥለው ወራጅ ወንዝ ውስጥ ይረጩታል (ቴዎድሮስ ገብሬ በ classical literature caurse የክፍል ማብራሪያ) ምክንያታቸው ደግሞ አመዱ በወንዙ ውስጥ ሲሰራጭ ውሃውን እንስሳት፣ ሰዎች፣ እፅዋት ይጠጡታል። ያ (የሞተው) ሰው በነዚህ ነገሮች ሁሉ ውስጥ ህልው ይሆናል ብለው ያምናሉ። በወራጅ ወንዝ መወሰዱ ነገሩን ቀጣይ ያደርገዋል የሚለው የህንዶች እምነት በተቃራኒው ደረቅ ወንዝ ውስጥ መሆኑ አያስቀጥለውም ከሚለው የባሌ ኦሮሞዎች እምነት ጋር ተቀራራቢ ይመስላል።

ያለው ደግሞ ነጭ መሆን አለበት። የበጉ የቆዳ ቀለም በራሱ ትዕምርታዊ ነው። ከግንባሩ እስከ ወገቡ ድረስ ያለው ጥቁር ቀለም በተጋጪዎች መካከል የተፈጠረውን አደጋ፣ ቅራኔ፣ ቂም፣ መከራ፣ ጥላቻ ይወክላል። ከወገቡ እስከ ላቱ ያለው ነጭ ቀለም ደግሞ በተጋጪዎች መካከል ተከስቶ የነበረውን ቅራኔ፣ጥላቻ፣ ቂም ተወግዶ እርቀ ሰላም መውረድን፣ ግጭት ውስጥ ገብተው የነበሩት አካላት ሰላም፣ መቻቻል፣ አንድነት ዝምድና መመስረታቸውን ያሳያል።

**ፎቶግራፍ 4** በባሌ ኦሮሞ ባህል በረኮ ስርዓት የሚታረደው በግ (ሚያዚያ 29፣ 2003ዓ.ም ጎባ)



ይህ በግ የተፈፀመው ወንጀል ማርከሻ ነው። የተከሰተው ችግር ዳግመኛ እንዳይመለስ ፣ ሰላም እንዳይደፈርስና ዕርቅ እንዲመጣ ለማድረግ የተጋጪዎቹን ጦስ ይዞ የሚሄድ ነው[18]።

በጉን በሚያርደው ሰው ላይ ሁለት የተለያዩ ሀሳቦች ገጥሞኛል። አንደኛው በጉን የሚያርደው ቀጥቃጭ ነው የሚል ነው።[19] ምክንያቱም ለግድያ ወንጀል ማካሔጃ የሚሆኑ እንደ ጦር፣ ጩቤ ፣ ባንጋ...የመሳሰሉትን መሳሪያዎች ስለሚሰራ ነው። የረኮ ስርዓትን በግ ማረድ የገዳይና የሟችን ጦስ መውሰድ ነው ተብሎ ይታመናል። የቀጥቃጩ ማረድም ግድያው የተፈፀመው እሱ በሰራው መሳሪያ ስለሆነ ሃላፊነት እንደመውሰድ ይቆጠራል።

---

[18] በዚህ ስርዓት የሚታረደው በግ ከእየሱስ ክርስቶስ ጋር ይመሳሰልብኛል። "በእርሱ ቁስል እኛ ተፈወስን" ኢሳ 53፣4-5 ይመለከቷል።

[19] ወ/ሮ በድርያ፣ ሚያዚያ 20፣ 2003ዓ.ም ጎባ፣ አቶ ሽምስዲን፣ ሚያዚያ 22፣ 2003ዓ.ም ሲናና።

ሁለተኛው ሀሳብ በጉን የሚያርደው “ወገቡ የደረቀ” መውለድ የማይችል ሽማግሌ የሚል ነው፡፡ [20] በዚህ ጉዳይ ላይ ባደረኩት የታላሚ ቡድን ውይይትም ትክክለኛው ሁለተኛው መሆኑ ተገልፆልኛል፡፡ በጉን መውለድ የማይችል ሽማግሌ ካረደው ጉማው ቀጣይ አይሆንም፡፡ ምክንያቱም ሰውየው ዘር መተካት ስለማይችል ደሙ ቢነካውም ከሱ ወደ ሌላ አይተላለፍም ተብሎ ስለሚታመን ነው፡፡

የእርድ ስርዓቱ ከተከናወነ በኃላ የበጉ ቆዳ ይገፈፍና ለራያ አምባዎች ይሰጣል፡፡ ሽማግሌዎቹ የበጉን ቆዳ ሁለት ኢንች ያህል ስፋት እንዲኖረው አድርገው አንድም ሳይበጠስ ዙሪያውን ቀደው ያወጡታል፡፡ ግማሾቹ ሽማግሌዎች ደግሞ የበጉን ስጋ በፍጥነት በልተው ከበጉ የፊት እግሩን እና የጎድን ስጋ[21] ወስደው በእሳት ይጠብሱታል፡፡ ከዛም የተጠበሰውን ስጋ፣ ማር እና ጨው ይዘው ወደ ጥላቸው ይሄዳሉ፡፡ ሁሉም ሽማግሌዎች ተቀዶ የተዘጋጀውን ቆዳ፣ ማር እና ጨውን ይዘው ከጥላቸው ወጣ ብለው የሚች እና የገዳይ ወገኖች ካሉበት ጥላ መካከል ላይ ይቆማሉ፡፡ ሁለቱ ሽማግሌዎች ተቀዶ የተዘጋጀው ቆዳ ሰዎችን እንዲያሳልፍ ከግራ ከቀኝ ወጥረው ይይዛሉ፡፡ ሌሎች ሽማግሌዎች በአንዱ አቅጣጫ ይሆናሉ፡፡

ፎቶግራፍ 5 ራያ አምባዎች በረኮ ስርዓት የገዳይና የሚች ወገኖች የሚሾልኩበትን ጎልጋ ይዘው (ግንቦት 4፣ 2003ዓ.ም ጎባ)



[20] አቶ ከድር ቃለ መጠይቅ፣ ሚያዚያ 28፣ 2003ዓ.ም ጎባ፡፡

[21] የፊት እግር እና የጎድን ስጋ በአንዳንድ ማህበራዊ ዝግጅቶች ላይ ለእድሜ ባለጠጎች የሚሰጥ የክብር ምግብ ነው፡፡ የፊት እግሩ መሄጃው፣ ጎድኑ ደግሞ መተኛው፤ ማረፊያው ነው፡፡ የፊት እግሩ እና የጎድን ስጋ ለሽማግሌዎች መስጠት ብርታቱን ይስጣችሁ፤ ኑሩልን ለማለት ነው፡፡ በዚህ ስርዓት ለሚች እና ለገዳይ ወገኖች የጎድን እና የፊት እግሩ ስጋ መስጠት አንድም የሽማግሌዎቹን ክብር ለነሱ ለመስጠት፤ በመታረቃቸው ለማክበር ለማመስገን ሲባል ነው፡፡ አንድም እንቅስቃሴያችሁ (ገበያ፣ እርሻ፣ ከብት ማስማራት ወዘተ) ሰላም ይሁን ለማለትም ነው፡፡

የእርቁ ሂደት በበላይነት ሲመራ የነበረው ሽማግሌ ቀራ ድምፁን ከፍ አድርጎ የገዳይ እና የሟች ወገኖች ወደነሱ እንዲመጡ ይጠይቃል፡፡ የሟች እና የገዳይ ወገኖችም ወደ ሽማግሌዎቹ ይቀርባሉ፡፡ እንደመጡበት አቅጣጫም የበጉን የተቀደደ ቆዳ ይዘው በቆሙት ሰዎች አቅራቢያ ይቆማሉ የገዳይ ወገኖችና ገዳይ ከቆዳው ትይዩ በስተግራ በኩል ፣ የሟች ወገኖችም ከቆዳው ትይዩ በስተቀኝ በኩል በተርታ ተደርድረው ይቆማሉ፡፡ በዚህ ጊዜ ቀራው የሚከተለውን ይናገራሉ፡፡

> Akkaataan nuu amma dhaabnu kun dhuma gumaati. Egaa kana guyyaa rakkoon kun harraa, wanna kanaaf deebinee isiniin jenna. Mukni gogeessi kun, huccuun gogeessi kun, adda rakkoo itti baatu. Xumurri Laggaa googessa yookaan muka gogeessa irratti dhuma. Waaan kanaaf muka gogeessa kana dhufne malee, silaa osoo falaa biraa taatee bakka gogeessa kana hin dhufnu. Bakka isiin itti xuurramtu kana kan amma akkanaatti muulifnee Goolga. Warri Gumaa irra bafnu garrana hulluuqa, waarri baafnuuf achii hulluuqa( አቶ ከድር፣ቅንብር ተፈጥሯዊ መቼት፣ግንቦት 4፣2003 ጎባ).
>
> አሁን የምናከናውነው ስርዓት የግድያ እርቅ ፍፃሜ ነው፡፡ ዛሬ የRakkoo ስርዓት የሚካሄድበት ቀን ነው፡፡ ይህ የደረቀ ልብስ (ብልኮውን እያሳዩ) እና ይህ የደረቀ ግንድ የረኮ ስርዓት የሚካሄድበት ነው፡፡ የግድያ እርቅ ስርዓት ፍፃሜ የሚካሄደው በደረቅ ወንዝ ውስጥ ወይም በደረቅ ዛፍ ስር ነው፡፡ ለዚህ ነው ወደዚህ የደረቀ ዛፍ ስር የጠራናችሁ፡፡ (ሽማግሌው የደረቀ ዛፍ በማለት የጠቆሙት ዛፍ ተቆርጦ ጉቶው የቀረ ነው፡፡ ጉቶው በጣም ደረቅ ከመሆኑ የተነሳ በላዩ ምንም የሚታይ እርጥብ ነገር የለም፡፡) የገባችሁበት ግጭት ግድያ ባይሆን ኖሮ እዚህ ቦታ አንጠራችሁም ነበር፡፡ እናንተ ነፃ የምትሆኑበትን ፣ ጥፋታችሁ የሚስተሰረይበት ቦታ ይህ ነው፡፡ ይህ የምትመለከቱት (ተቀዶ ወደ ተወጠረው ቆዳ እያሳዩ) Goolga ነው፡፡ ስለዚህ ጉማ የምናወጣላችሁ ወደዚያ ጉማችሁን የምናወጣላችሁ ደግሞ ወደዚህ ትሾልካላችሁ፡፡

ከዚህ በመቀጠል የገዳይና የሟች ወገኖች በሽማግሌው በታዘዙት መሰረት በጎልጋዉ ውስጥ ይሾልካሉ፡፡ በቅድሚያ የሚሾልኩት የገዳይ ወገኖች ናቸው፡፡ የገዳይ ወገኖች በቆዳው ውስጥ ሲሾልኩ (ሲያልፉ) ሽማግሌዎቹ ይመርቋቸዋል፡፡ በመቀጠል የሟች ወገኖች በጎልጋዉ ውስጥ ያልፋሉ፡፡ አሁንም ሽማግሌዎቹ በምርቃት ያጅቧቸዋል፡፡ የገዳይ ወገኖች መሹለክ ሰው ሆኖ የማይሳሳት ክፉ የማያስብ የለም ተብሎ ስለሚታመን በወገናቸው ሞት ምክንያት በውስጣቸው

ካሰቡት መጥፎ ነገር (ቂም በቀል) የነፁ እንዲሆኑ ነው፡፡ በቅድሚያ ተራ በተራ ከሾለኩ በኃላ የሚች እና የገዳይ ወገኖች በጋራ በመሆን በተቀደደው ቆዳ ውስጥ ይሾልካሉ፡፡

ፎቶግራፍ 6 የገዳይና የሚች ወገኖች በጎልጋው ውስጥ ሲሾልኩ (ግንቦት 4፣ 2003ዓ.ም ጎባ)



በዚህ ጊዜ ሽማግሌዎቹ በአንድነት ይመርቋቸዋል፡፡ ምርቃቱ ለብቻ ሊሾልኩ ከሚባለው ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡

Falamaa, falamaa

(ንፁህ ሁኑ! ንፁህ ሁኑ!)

Gumaan hindeebi'en

(ጉመ /ደም/አይመለስ)

Gortoon hindeebi'en

(ጎርቶ/አደጋው አይመለስ)

የሚሉትን ሀረጋት በብዛት በመደጋገም ይመርቋቸዋል፡፡

የጎልጋ መሹለክ ስርዓት የተጋጩት አካላት ወደ ሰላም፣ ወደ አንድነት የሚሸጋገሩበት ስርዓት ነው፡፡ የጎልጋ ስርዓት ከነባር ሁናቴ ወደ አዲስ ሁኔታ፣ ከነባር ልማድ ወደ አዲስ ልማድ፣

የመቀየር ስርዓት ነው። ጎልጋ በዘወትሩ ኑሮ የሚቃረኑና ሚጠፋፉ ሁነቶችና ጉዳዮች በአንድ አውድ ውስጥ ተጎራብተውና ተዛምደው የሚመጡበት እንግዳ ስርዓት እንደሆነ ከሚነገርለት፤ "ክቅዐር መዝለቅ" ጋር ተመሳሳይ ነው።[22]

በጎልጋ ውስጥ መሹለክ በማህበረሰቡ ባህል መሰረት የራሱ የሆነ ተምሳሌታዊ ትርጉም አለው። የሚች እና የገዳይ ወገኖች በጎልጋው ውስጥ ሲሾልኩ ከሃጢያታቸው ይነፃሉ፣ ችግራቸው ሁሉ ይፈታል፣ ይባረካሉ። በነሱ ላይ የነበረው ሃጢያት፣ መከራ ቆዳውን ሲሾልኩ በቆዳው ላይ ይቀራል፣ ከጥፋታቸው የነፁ ይሆናሉ ተብሎ ይታመናል። ጎልጋውን መሹለክ ለሚች ወገኖች የታላቅ በረከት መገኛ ነው። በሽማግሌዎቹ ይመረቃሉ፤ በባህል አክባሪነታቸው ይሞገሳሉ። የገዳይ ወገኖችም በእጃቸው ከነበረው ደም የነፁ ይሆናሉ። ከሚች ወገን የሚመጣባቸው የበቀል እርምጃ አይኖርም። ከፀፀትም ሆነ ከስጋት የነፁ ይሆናሉ። አዲስ ህይወት ይጀምራሉ። ይህ በጎልጋ ውስጥ የመሹለክ ሂደት በፌሳሎጎስ መፅሀፍ ስለእባብ ከቀረበው 11ኛ ትርጓሜ ጋር ተመሳሳይነት አለው።

"እባብ ሲያረጅ አይኖቹ ይሸፈናሉ። መታደስ ሲፈልግ ቆዳው እስኪላቀቅ (እስኪፋፋቅ) ድረስ 40 ቀን 40 ሌሊት በትጋት ይፆማል። ወዲያው ገዝም ይላል። ጠባብ ሽንቁር ያላት ድንጋይ ፈልጎ ፣ እዚያው ገብቶ እራሱን ያስጨንቃል (ያጣብቃል) በመጨረሻም ይሾልካል። ከዚያም ጎልማሳ ይሆናል።"[23]

ማህበረሰቡ በአመት ሁለቴ ሐይማኖታዊ ጉዞ በሚያደርግበት በድሬ ሼህ ሁሴንም እንዲህ ያለ እምነት እንዳለ አቶ ጃርሶ ነግረውኛል።[24] ድሬ ሼህ ሁሴን ሀይማኖታዊ ጉዞ አድርጎ የደረሰ ሰው በቅዐር ግቢው ውስጥ ከሚገኙት ስፍራዎች ውስጥ አንድ ሰው ብቻ የምታሳልፈዋን የድንጋይ ሽንቁር እንዲያልፍ ይደረጋል። ያ ሰው በቀዳዳው ክፍቱ ድንጋይ ውስጥ ካለፈ ከሃጢያት ነፃ እንደሆነ ይታመናል። ድንጋዩ ሀጢያተኛ ሰው ከመጣ አያሳልፍም ሰው በውስጡ መጥፎ ነገር

---

[22] ቅዐር መዝለቅ ከአንድ ስፍራ ወደሌላ ስፍራ በሚደረግ ጉዞ የሚፈፀም ድንበር ማቋረጥን፣ ከነባር ሁናቴ ወደ አዲስ ሁናቴ፤ ከነባር ልማድ ወደ አዲስ፣ ከዘወትር ዓለም ልዩ ወደ ሆነ ዓለም የሚደረግ ሽግግርን የሚወክል ሀረግ ነው። የተቃራኒዎች ግጥምጥም፣ አንድ ፅንሰ ሃሳብ በዘወትሩ ኑሮ የሚቃረኑና የሚጠፋፉ ሁነቶችና ጉዳዮች፤ በአንድ አውድ ውስጥ ተጎራብተንና ታዛምደው በመምጣት የሚፈጥሩት እንግዳ ስርዓት ነው። ቴዎድሮስ ገብሬ፣ <u>በይነ ዲስፐሊናዊ የስነፅሁፍ የስነጥበብ ንባብ</u>፡ አዲስ አበባ፣ አ.አ.ዩ ፕሬስ፣ 2000ዓ.ም ገፅ 21-28

[23] ገዛኸኝ ያልታተመ ገፅ 12፣ ለክላሲካል ሊትሬቸር ኮርስ የሰጠው ድራጎት

[24] አቶ ጃርሶ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ግንቦት 5፣ 2005፣ ጎባ

እያሰበ፣ ቂም ይዞ ወዘተ. በድንጋዩ ውስጥ ማለፍ አይችልም። እንዲህ ያለ ሰው በድንጋይ ውስጥ ለማለፍ ቢሞክር ጠቦ አንጀቱን አጣብቆ ይገድለዋል ተብሎ ይታመናል።

ከዚህ የማህበረሰቡ እምነት በመነሳት ቆዳው የድንጋዩ ምሳሌ ነው ማለት ይቻላል። የገዳይም ሆነ የሟች ቤተሰቦች በጎልጋው ውስጥ ሲያልፉ በውስጣቸው የሚመላለስን መጥፎ ስሜት አስወግደው በንፁህ ልብ ማለፍ እንዳለባቸው ያሳያል። ከዚህ በኃላ ቂም፣ ጥላቻ ብሎ ነገር አይታሰብም።

በመጨረሻም ሽማግሌዎቹ የሟች እና የገዳይ ወገኖች የሾለኩበትን ቆዳ ጎልጋ ይሰበስባሉ። ከዚያም ከሽማግሌዎቹ ውስጥ በእድሜ የገፋው ወይም ቀራ በመሆን ሽምግልናውን የመራው ሰው ቆዳውን ሰብስቦ ይይዝና ተሰብስበው የቆሙትን የሟችና የገዳይ ወገኖች አንድ ጊዜ ዞሮ ቆዳውን ራቅ ወዳለ ቦታ ይጥለዋል። የዚህ (ቆዳውን በተጋጪዎች አዙሮ የመጣል) ተምሳሌታዊ ትርጉም በመሹለኩ ስርዓት ከያዘው ትርጉም እምብዛም የተለየ አይደለም። ቆዳውን (ጎልጋውን) በተጋጪዎች ዙሪያ ማዞር የተጋጪዎቹን ሀሂያት፣ ክፉ እድል፣ ጥፋት እንዲሁም ጦስ ወደጎልጋው ማሳለፍ ነው።ካዞሩት በኃላ አርቀው መጣላቸው ደግሞ የገዳይ እና የሟች ወገኖች ክፉ እድል፣ ሀሂያት፣ ጦስ ወዘተ. ዳግም እንዳይመለስ ከነሱ ለማራቅ ነው። ሽማግሌው ቆዳውን ይዞ ሲዞር ሌሎቹ ሽማግሌዎች በጋራ

Haamttun issiinniit hiin deebiin

(ክፉ ነገር ዳግም አይግጠማችሁ)

Gumaan issiinniit hiin de biin

(የሰው ደም ዳግም አይግጠማችሁ)

Ississnniraa baafnee

(አወጣንላችሁ)

በማለት ይመርቃሉ።

በመቀጠል ሁለቱ ወገኖች ወደ ቂም በቀል እንዳይሄዱ "ከእጅ ላይ የመብላት" ስርዓት ይካሄዳል። በዚህ ስርዓት በቅድሚያ የሟች ወገኖች በቀኝ በኩል በተርታ እንዲደረደሩ ይደረጋል። የገዳይ

ወገኖችም በሚች ወገኖች ትይዩ በግራ በኩል በተርታ ይደረደራሉ፡፡ በዚህ ጊዜ በገዳይና በሚች ወገኖች መካከል የሚኖረው ርቀት ከሁለት እርምጃ አይበልጥም፡፡

ከዛም ሽማግሌዎቹ በእሳት የተጠበሰውን የጎድን እና የፊት እግር ስጋ ለመጉረስ በሚመች መልኩ ቆራርጠው የገዳይ እና የሚች ወገኖች የቀኝ እጅ ላይ ያስቀምጣሉ፡፡

ፎቶግራፍ 7 ራያ አምባዎች ከእጅ ላይ በመብላት ስርዓት የገዳይና የሚች ወገኖች አንዱ ከአንዱ እጅ ላይ የሚበሉትን የፊት እግርና የጎድን ስጋ ሲጠብሱና ሲያዘጋጁ(ግንቦት 4፣ 2003ዓ.ም ጎባ)



በመቀጠል የገዳይ ወገኖች ወደ ሚች ወገኖች እንዲቀርቡ በሽማግሌዎች ይታዘዛሉ፡፡ የገዳይ ወገኖችም ወደ ሚች ወገኖች በመቅረብ በቅድሚያ በግራ እጃቸው ከሚች ወገኖች ጋር (ይጨባበጣሉ)[25] ይያያዛሉ፡፡ ከዛም በቀኝ እጃቸው መዳፍ ላይ ያለውን ስጋ ወደ ሚች ወገኖች አፍ ያስጠጋሉ፡፡ የሚች ወገኖችም በቀኝ እጃቸው ላይ ያለውን ስጋ ወደ ገዳይ ወገኖች አፍ ያስጠጋሉ፡፡ በመጨረሻም አንዱ ከሌላው (የሚች ወገን ከገዳይ ወገን) መዳፍ ላይ ያለውን ስጋ በአፍ እየወሰዱ ይበላሉ፡፡ በዚህ ጊዜ ገዳይ ከሚች የቅርብ ዘመድ (አባት፣ ወንድም፣ አጎት ወዘተ.) ጋር ነው ስርዓቱን የሚፈፅመው፡፡ የተጋጨት ወገኖች ከእጅ ላይ የመብላቱን ስርዓት ሲያከናውኑ ሽማግሌዎቹ "namni wallin nyaate wallhin nyaatu" (አብሮ የበላ ሰው አይጠፋፋም) የሚለውን ምሳሌያዊ አነጋገር በመደጋገም የባህላዊ ስርዓቱን ተምሌታዊ ትርጉ ግጭት ውስጥ ለገቡት አካላት ያሳስባሉ፡፡

---

[25] መጨባበጥ በዚህ አገባቡ መያያዝን እንዲወክልልኝ ነው የተጠቀምኩት፡፡ ከሰላምታ መለዋወጡ ጋር አይመሳሰልም፡፡ በግራ መጨባበጥ በማህበረሰቡ ባህል (ለሰላምታ) ነውር ነው፡፡

የዚህ ስርዓት ዓላማ በሚችና በገዳይ ወገኖች መሀከል በቀጣይ የሚኖረው ግንኙነት ሰላማዊ እንዲሆን ማድረግ ነው። በቀጣይ በመሀከላቸው ቂም በቀል እንዳይኖር የሚያደርግ ነው።[26] ሽማግሌዎቹ እንዳሉት እንኳን ከእጅ የበላ ይቅርና አብሮ የበላ በክፉ አይፈላለግም። አብሮ የበላ ሰው አይካካድም። በችግር ወቅት ይደራረሳል። አብሮ መብላት በማህበረሰቡ ዘንድ ከፍተኛ ግምት ይሰጠዋል። ከእጅ ላይ መብላት ደግሞ በጣም ከባድ ነው። ከእጁ ላይ የበላኸውን /ያጎረሰህን/ ሰው ከከዳህ ፣ ባጎረሰህ ሰው ላይ ክፉ ካሰብክ ፣ ካደረክ ያጎረሰህ እጁ ይጥልሀል ተብሎ ይታመናል። ይህ እምነት አሁንም ድረስ በአካባቢው ማህበረሰብ ተቀባይነት አለው።

በመጨረሻ ራያ አምባዎቹ የስርዓቱን መቋጫ ማር 'ፊጣ ዳይማ' (fixaa dayimaa) እና ጨው 'ሶጊዳ' (sogidaa) በቅምሻ ያህል ወደ አፋቸው በማስገባት ወደ ሚች እና ገዳይ ወገኖች በመትፋት 'ቢፋን' (bifun) ይመርቋቸዋል። የማርና የጨው ተምሳሌታዊ ትርጉም መጣፈጥ፣ ጥሩ እድል ማግኘት፣ ሰላማዊ ኑሮ መኖርን ያመለክታል። ግጭት ውስጥ ገብተው የነበሩት አካላት ግንኙነት መልካምና ጤናማ ይሁን ለማለት ነው። ማር የጣፋጭ ነገር ተምሳሌት ሲሆን ጨው ደግሞ የማጣፈጫ ተምሳሌት ነው። ጨው የማይገባበት ምግብ አለ ለማለት ይከብዳል። ምግብ የሰው ልጅ የኑሮ መሰረት ነው። ያለምግብ መኖር አይቻልም። የሰው የኑሮ መሰረት የሆነው ምግብ ውስጥ ጨው መኖሩ ያጣፍጠዋል። ከዚህ በመነሳት የጨው ተምሳሌት ኑሮአችሁ የጣፈጠ ይሁን ለማለት ነው።

| | |
|---|---|
| Gumaa hin deebiin | ( ጉማው አይመለስ) |
| Gorton hin deebiin | ( ችግር አይመለስ ) |
| Gorii hin deebiin | ( መከራ አይመለስ ) |
| Issiin lamman jiduti guro hin gallin | ( በመሀከላችሁ ችግርአይግባ) |
| Halo wal hin eggatina | ( ቂም በቀል አትያያዙ ) |
| Malkan keessan tokkoo | ( ወንዛችሁ አንድ ነው ) |
| Boban keesan tokko | ( መስካችሁ አንድ ነው ) |
| Manii keesan tokko | ( ቤታችሁ አንድ ነው ) |
| Gabaan keesan tokko | ( ገበያችሁ አንድ ነው ) |

[26] አቶ ቲልሞ፣ አቶ ማማ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ሚያዚያ 27፣ 2003ዓ.ም

Yattii keesan tokko ( መሰማሪያችሁ አንድ ነው )

Batii keesan tokko ( መውጫችሁ አንድ ነው )

Haara'a irra haalon jiddu keesan lamaan hin jiirttu.

(ከዛሬ ጀምሮ በመካከላችሁ እልህ (ቂም) የለም)

ከዛም የሚችና የገዳይ ወገኖች እርስ በእርስ እንዲመራረቁ ይደረጋሉ፡፡ እነሱም ልክ እንደሽማግሌዎቹ ማሩን እና ጨውን ወደ አፋቸው በማስገባት አንዱ ወደ አንዱ እየተፉ (መትፋት በዚህ አገባቡ አውንታዊ ፍቺ ይይዛል) ይመራረቃሉ፡፡ መትፋት (biffa) የሚከናወነውን አፍ ገጠም ተደርጎ ፋጨት በሚመስል መልኩ ከንፈር በማሾል አየርና ጥቂት ማርና ጨው የተቀላቀለበት ምርቃ ወደሌላው በመትፋት ነው፡፡ ከዚህ በመቀጠል የሚችና የገዳይ ወገኖች እንዲሳሳሙ በሽማግሌዎች ይታዘዛሉ፡፡ እነሱም በታዘዙት መሰረት አንዱ ከአንዱ በየተራ እየተቃቀፉ ይሳሳማሉ፡፡

ከዚህ በኃላ "Ama mana tokkoti galla" (አሁን ወደ አንድ ቤት እንገባለን) በማለት ሽማግሌዎቹ የሚች እና የገዳይ ወገኖችን በአቅራቢያቸው ወደሚገኝ የገዳይ የቅርብ ዘመድ ቤት ይዘዋቸው ይሔዳሉ፡፡ የተመረጠው የሚች ወገኖች ቤት ውስጥ የሚች ወገኖች አቅማቸው በፈቀደ መጠን ዝግጅት ያዘጋጃሉ፡፡ ብዙ ጊዜ ገንፎ እና ቡና አይቀርም፡፡ የተዘጋጀውን ምግብ በፍቅር እየተጎራረሱ ከበሉ በኃላ ሽማግሌዎቹ ምርቃት ይሰጣሉ፡፡

Mana tokko bultanni bultiin keesan issini habattu

(በአንድ ቤት ኑሯችሁ ይስመር)

Hamtuun issinniti hin deebiin

(ክፉ ዳግም አያግኛችሁ)

Lagnii keesan tokko hata'u

(ወንዛችሁ አንድ ይሁን)

Bobban keesan tokko hata'u

(ማሰማሪያችሁ አንድ ይሁን)

Gabaan keesan tokko hata'u

(ገበያችሁ አንድ ይሁን)

Hamtun issin irra habbatu

(ክፉ ከእናንተ ይራቅ)

Hamtun issiin irraa batte issin hindeebiin

(ክፉ ዳግም አይመለስባችሁ)

Toltun issiin seente issin irraa hinbahin

(የገባው በረከት አይውጣባችሁ)

Issin obbaleya garra tokkoti

(እናንተ የአንድ እናት ልጆች ናችሁ)

የስርዓቱ ማብቂያ የሚሆነው የሴት ልጅ መስጠት ነው።[27] ከገዳይ ወገን የገዳይን የቅርብ ዘመድ እህት፣ የአክስትና የአጎት ልጅ ሆና ለአቅመ ሄዋን የደረሰች ልጃገረድ ለሟች ወገን ይሰጣል። ሴት ልጅ የጉማ ስጦታ አትደረግም። ለጉማ እንደሚሰጠው ከብት፣ መሬት፣ ገንዘብ የምትሰጥ አይደለችም። ይህን ጉዳይ ሽማግሌዎቹ አፅንኦት ሰጥተው ሲናገሩ "Intalan gummaa hin fixaan" ይላሉ[28]። ሴት ልጅ የሚሰጥበት ምክንያት መረጃ አቀባዮቼ ሲነግሩኝ ሴት ልጅ ጉማ አይደለችም። ሴት ልጅ የሚሰጠው ሁለቱን ጎሳዎች ለማዛመድ ነው። ይህን ጉዳይ ሲያብራሩ

> "Intala gummaa hin fixanii intalla walli keenan wani intalla wani keenanif dhigoon gama gamaana wallitti hajjirtu jeechuff. Egga kana wara irra ajjeesef warra irra ajjese ille intalti sun yoo dhaltee kan issin dhaltee suni jagna dhalti sun gnoti dhallti gossa lamma iyuu dhigoo. Namni dhigoo sun birra tarre walliti deebi'e dhiiga walliti hinjisku; haloo hin jirtu.
> በሴት ጉማ አይወጣም ሴት አብሮ ይሰጣል እንጂ። ሴት ልጅ የሚሰጥበት ምክንያ በሁለቱ ጎሳዎች ዘንድ ዝምድና እንዲኖር ለማድረግ ነው። ያቺ ሴት ከሟች ጎሳ ስትወልድ ሁለቱ ጎሳዎች ዘመድ ይሆናሉ። ሁለቱ

---

[27] ይህ ስርዓት ከፖለቲካዊ ትዳር (political marriages) ጋር ተመሳሳይ ነው። ለፖለቲካዊ ትዳር ጥሩ ምሳሌ የሚሆነው በ18ኛው ክፍለ ዘመን መቀመጫው ጎንደር የነበረው የጠንካራው ኦሮሞ የራስ ጉግሳ ልጆች ትዳር ነው። ራስ ጉግሳ አራት ሴት ልጆች ነበሩት ወለተተክል ከደጃች ማሩ ጋር ተዋግተው እርቅ ከወረደ በኋላ ለደጃች ማሩ ተዳረች። ለሰሜኑ ደጃዝማች ኃይለማርያም ደግሞ ሒሩትን ዳሩ። ትርንጎ ለዋቅሹም ክንፊ ተዳረች። አስቴር ደግሞ ለትግራዩ ደጃዝማች ገብረሚካኤል ተዳረች። (መስፍን 1999 ገፅ 145 ይመለከቷል)

[28] አቶ ከድር፣ ቅንብር ተፈጥሯዊ መቼት (ምልከታ)፣ ግንቦት 4፣ 2003ዓ.ም ጎባ

ጎሳዎች መካከል ዝምድና ይኖራል፡፡ ማንም ሰው በመካከላቸው ያለውን ዝምድና ተላልፎ ደም አይፋሰስም፡፡ ቂም፣ ሀዘን አይኖርም (ወ/ሮ በድሪያ፣ ሃጂ ረሺድ፣ በዳሶ በልዳ፣ አለቃ ተስፋዬ 23፣07፣2003)፡፡

በመጨረሻም ተጨዋውተው ተመራርቀው ይለያያሉ፡፡

### 5.7.3 ድህረ እርቅ ክዋኔ

እርቅ ከወረደ በኃላ የሚችና የገዳይ ወገኖች በሰላም እና በፍቅር አብረው መኖር ይጀምራሉ፡፡ አንድ ወንዝ ከብት ያጠጣሉ ፣ አንድ ገበያ ይገበያያሉ ፣ አንድ መስክ ላይ ከብት ያሰማራሉ ፣ በሃዘን በደስታ ጊዜ ይጠራራሉ፤ ይተጋገዛሉ፡፡

የገዳይ ወገኖች የተፈጠረው ሰላም እንዳይደፈርስ ቃል የገቡትን ከብት ለሽማግሌዎች ያስረክባሉ፡፡ ከብቶቹ በአንዴ ለሽማግሌዎቹ አይሰጡም፡፡ የሚች ወገን እስከ ቀጠሮው ቀን ድረስ በፈቀደው ቀን ቃል የገባውን ያህል ከብት ለሽማግሌዎቹ ማስረከብ ይችላል፡፡ ሽማግሌዎቹ ከብቶቹ መሰብሰብ ሲጀምሩ ጠባቂ ያደርጋሉ፡፡ ያመጣውን ሰው ይመዘግባሉ፡፡ ከገዳይ ወገን የሚቀበሏቸውን ከብቶች ሙሉ አካል ያላቸው መሆናቸውን ያረጋግጣሉ፡፡ እንደ ሽማግሌዎቹ ገለፃ የጉማ ከብት ጉድለት ካለው በ4 ቦታ ይመለሳል

1. ላመጣው ሰው እምቢ/አንቀበልም ተብሎ ይመለሳል
2. የገዳይ ወገን ሽማግሌ ይመልሳል
3. ሽማግሌዎች አይሆንም ብለው ይመልሳሉ (Rayyaa Anbaa)
4. የጉማው ጌታ /ጉማ ተቀባይ/ አንቀበልም ብሎ ይመለሳል

በዚህ መሰረት ሽማግሌዎቹ ጉድለት የሌለው ከብት ብቻ ተቀብለው ጠባቂ ይቀጥራሉ ከዚህ በመቀጠል የረጅሙ ጉማ ቀጠሮ ሲደርስ የሚችን ወገን ጥላ ስር ጠርተው የገዳይን ወገኖች ከብቱን አምጡ ይላሉ፡፡ ከዚህ በመቀጠል ጉዳዩን የያዙት ሽማግሌዎች ለሚች ወገን ከብቱ ይኸውላችሁ ውሰዱ ይላሉ፡፡ የቀረ ከብት ካለም በዚሁ መሰረት ቀጠሮ አስይዘው ይሰጣሉ ፡፡ ሽማግሌዎቹ መቶ ከብት ከሰጡ በኃላ 1 ከብት ለራሳቸው ያስቀራሉ ይህም የሚሆነው ጉማው የወንድ ከሆነ ነው፡፡ የሚቀረው ከብት ጥቁር ቀለም ያለው ነው ፡፡ ከላይ እንደተገለፀው የወንድ ጉማ 101 ከብት ነው፡፡፡ ሽማግሌዎቹ ለሚች ወገኖች 100 ከብት ጉማ ካወጡ በኃላ አንድ ጥቁር ከብት ለራሳቸው ያስቀራሉ፡፡

ሽማግሌዎቹ ይህን ጥቁር ከብት Bullalla ለሚባሉት ጎሳ ይሰጣሉ የቡላላ ጎሳ አባል የሆነው ሰው ደግሞ Baddana የሚባል ዛፍ ቆርጦ ሰዎቹን፣ ከብቶቹን አዙሮ ያርደዋል፡፡ እሱ አርዶ ከጨረሰ በኃላ ሽማግሌዎቹ /Labsi/ አዋጅ ይናገራሉ፡፡ ከዚህ አዋጅ በፊት ለሚች ወገኖች እንደዚህ ይላሉ፡-

"የደም ጦር የለም ቁልቁል ተመልሷል፣ የደም ቢላ የለም ወደ አፎቱ ገብቷል፣ የደም እጅ ታጠቡ፣ አፉችሁን ተጉመጥመጡ መሪር ሀዘን /ቅሬታ/ በመሀከላችሁ የለም ካሁን ጀምሮ አንድ ወገን ናችሁ፤ የእከሌም ወገን የእከሌም ወገን ሰላም ይሰማችሁ" ይላሉ፡፡ የሚችና የገዳይ ጎሳዎችን በመጥራት እነደዚሁ ለገዳይ ወገኖች አዋጅ ይናገራሉ፡፡

"ስሙ ዝግ በራች በጉማ ተከፍቷል፡፡ ወንዛችሁ ሰላም ነው፣ የፍለጋችሁበት ከብት አጠጡ፣ መንገዳችሁ ሰላም ነው፣ ወደ አሻችሁ ሒዱ፣ ተጋቡ ፣ አንዱ ጎሳ ከአንዱ ይጋባ ፣ በጋራ ብሉ፣ አንድ ላይ ጠጡ፣ ከዚህ በኃላ እናንተ ሰላማዊ ሰው ናችሁ፣ በጋራ ኑሩ ይላሉ ሽማግሌዎቹ፡፡ እንደዚሁም ሽማግሌዎቹ የሚጋቡትን ይናገራሉ፡፡ ለሃገር የሚያውጁትም እንዲህ በማለት ነው፡፡

ትልቅ ነው ትልቅ የሆነው በሰላም ተናገረ ደረስኩ ጉማው አለቀ መጥፎ መንገድ የለም፣ የመጠፋፋት መንገድ የለም፣ የሰውን ሀዘን የሚጠብቅ ሰው የለም፣ ሙቶ አልቆ ታልፏል በላይ የሚገባ በላይ ይግባ በታች የሚገባ በታች ይግባ፣ በቀኝ በግራ የሚገባም በዛ ይግባ፣ ካሁን ጀምሮ ሰላም ነው፣ የደም በር የለም ሰላም ይሰማ፡፡ በማለት ጉማው ለሀገር ተነግሮ ይጠናቀቃል፡፡ ይህም ለሁሉም ሰው ይታወጃል፡፡

በዚሁ መሰረት ሽማግሌዎቹ ጉማው በአዋጅ ተነግሮ ሲያበቃ የሚችና እና የገዳይ ወገኖችን ከእንግዲህ በሰላም ኑሩ ይላሉ፡፡ መታረቃቸውም ለሀገር በአዋጅ ይናገራሉ፡፡ በመጨረሻም ጉማው ሲያልቅ ለሽማግሌዎቹ "mooraa migittii" በማለት ስጦታ ይሰጣቸዋል፡፡ ለሽማግሌዎቹ የሚሰጠው ስጦታ የከብት ስጦታ ነው፡፡

ሽማግሌዎቹን ከብት አርደው አብልተው ነው የሚያሰናብቷቸው፡፡ በፊት በፊት በስጦታ መልክም ለእያንዳነዱ ሽማግሌ ከብት ይሰጣል፡፡ አሁን ግን ኑሮ ስለከበደ ያ አይደረግም፡፡

## 6. ስነቃል በግጭት አፈታት ያለው ሚና

Dorson (1972) እና ፊቃደ (1991) ፎክሎርን ስነቃል (oral literature) ፣ቁሳዊ ባህል (material culture) ማህበራዊ ልማድ (social folk custom) እና ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት (perfroming folk arts) በሚባሉ አራት ዋና ዋና ክፍሎች እንደሚከፈልና በያንዳንዱ ዋና ዋና ክፍል ስር በርካታ ዝርዝር ጉዳዮች እንዳሉ ይገልጻሉ፡፡

ከፎክሎር አብይ ዘርፎች መካከል አንዱ በሆነው ስነቃል ስር ከሚካተቱ በርካታ ርዕስ ጉዳዮች ውስጥ አፈታሪክ፣ እንቆቅልሽ፣ ሚት፣ ምሳሌያዊ ንግግር እና ተረት ይገኙበታል፡፡ እነዚህ የስነቃል ዘርፎች የአንድን ማህበረሰብ ልማድ፣ እምነት፣ ፍልስፍና፣ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ሁነቶች ምን እንደሚመስሉ ለማሳየት ይረዳሉ፡፡ በተለይ በተለያዩ ማህበራዊ ግንኙነቶች (ስብሰባ፣ውይይት፣ ጨዋታ፣ ሽምግልና፣ የተለያዩ ባህላዊ ስርአቶች ወዘተ.) ሰዎች እርስ በእርሳቸው በሚኖራቸው መስተጋብር ሀሳባቸውን በአጭሩ ለማስተላለፍና አድማጭ መልእክቱን በውል እንዲረዳ በማድረግ ረገድ ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ፡፡

በዚህ ክፍል በባሌ ኦሮሞ ማህበረሰብ ዘንድ በተለያዩ ምክንያቶች በማህበረሰቡ ውስጥ የሚከሰቱ ግጭቶችን ለመፍታት፣ ለማብረድ፣ ውሳኔ (ፍርድ) ለመስጠት፣ በዳይን ለመውቀስ፣ ተጎጂውን ወገን ለማጽናናት፣ ዘላቂ ሰላምን ለማስፈን፣ የግጭትን መጥፎነት ለመግለጽ፣ የሽማግሌዎችን ሀይልና ሚና ለማሳየት ወዘተ ምሳሌያዊ አነጋገሮች ተረቶችና አፈታሪኮች ያላቸው ሚና ምን እንደሚመስል በትንታኔ ለማሳየት ተሞክሯል፡፡ በማህበረሰቡ ውስጥ እነዚህ የስነ ቃል ዘርፎች ግጭትን ከመፍታት አንጻር ስላላቸው ሚና የሚነገሩትንም እንመለከታለን፡፡

### 6.1. ምሳሌያዊ አነጋገር በግጭት አፈታት ወቅት ያለው ሚና

ምሳሌያዊ አነጋገሮች አንድ ጥቅል ሀሳብ በአጭር የሚገለጽባቸው ዘይቤያዊ አባባሎች ናቸው፡፡ ምሳሌያዊ አነጋገሮች በቁጥብና በምርጥ ቃላት በአጭሩ የሚነገሩ፣ ትልቅ ሀሳብን የሚያስተላልፉ የስነቃል አይነቶች ናቸው፡፡ ምሳሌያዊ አነጋገር ሀሳብን ለማጠናከር፣ ለመቋጨትና ለማጉላት እና ግልጽ ለማድረግ ይጠቅማል፡፡ ሰዎች ቅሬታቸውን ይገልጹበታል፣ አስነዋሪ ተግባራትን ይነቅፉበታል፣ እኩይ ድርጊትን ያንቋሽሹበታል፣ ሰናዩን ያሞግሱበታል፣ እንዲሁም በማህበረሰቡ የእለት ተእለት ሕይወት ላይ ሂስ ይሰጡበታል (ዘሪሁን 1992)፡፡ ምሳሌያዊ አነጋገሮች በርካታ ተግባራት አላቸው፡፡ ከተግባራቱ አንዱ በማህበረሰቡ ውስጥ በተለያዩ ምክንያቶች ግጭት ውስጥ የሚገቡ ሰዎች ለማስታረቅ ከፍተኛ ሚና መጫወታቸው

ነው፡፡ ቀደም ባለው ጊዜ ምሳሌያዊ አነጋገሮች በንግግር ውስጥ በማካተት መሟገትም ሆነ ፍርድ መስጠት ከፍተኛ ጠቀሜታ እንደነበረው ማህተመ ስላሴ ሲገልጹ የሚከተለውን ብለዋል፡፡

> የቀድሞ ዳኞችም፣ የዛሬዎቹ እንደ ገዳዩ አይነት ክፍሉንና አንቀጽ አስማምተው ህግ ጠቅሰው እንደሚፈርዱ ሁሉ ከነዚሁ ከምሳሌዎች ውስጥ ማስረጃ በሆኑት ሲሰሩባቸው ቆይተዋል፡፡ ይኸውም ህግን ተመርኩዞ ፍትህ ነገስትን ጠቅሶ እንደመናገር ያለ መስሎ ይገመታል (1961፣6)፡፡

በባሌ ኦሮሞዎች ዘንድ በተለያዩ ምክንያቶች የሚከሰቱ ግጭቶችን ለመፍታት ምሳሌያዊ አነጋገሮች ከፍተኛ ሚና እንዳላቸው ይገመታል፡፡ ይህንን ጉዳይ ከምሳሌያዊ አነጋገራቸውም መረዳት ይቻላል፡፡ምሳሌያዊ አነጋገሮች አንድን ነገር ለመጨረስ ያላቸውን ሚና ለመግለጽ "yoo mammakan waa hikanii akk yoo jeduan waa tufanii" (ከተረቱ ችግር ይፈታሉ አክ ካሉ ይተፋሉ) የሚል ምሳሌያዊ አነጋገር አላቸው፡፡ ከምሳሌያዊ ንግግሩ በተለያዩ ምክንያቶች የተከሰተ ችግርን (ግጭትን) ለመፍት ምሳሌያዊ አነጋገር ከፍተኛ ሚናእናዳለው እንረዳለን፡፡ በመቀጠል የባሌ ኦሮሞዎች ግጭትን በባህላዊ መንገድ ሲፈቱ የሚናገሯቸው ምሳሌያዊ አነጋገሮችንና የምሳሌያዊ አነጋገሮቹ መነገር ያለው ፋይዳ እንመለከታለን::

Lafa namno guddaan hinjireefii lafa mukni

Guddaan hinjiree hinjiraatn

"ትልቅ ሰውና ትልቅ ዛፍ የሌለበት ቦታ አይኖርበት"

ይህ ምሳሌያዊ አነጋገር በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ የሽማግሌ መኖር አስፈላጊ እንደሆነ ያሳያል፡፡ በባሌ ኦሮሞዎች ዘንድ ሽማግሌና ትልቅ ዛፍ ትልቅ ቦታ ይሰጣቸዋል፡፡ ትልቅ ዛፍ ሀይማኖታዊ ስርዓቶችን ለማከናወን፣ ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ ለመወያየት በጥላነት ያገለግላል፡፡ ሰው ደግሞ ማህበራዊ ፍጡር ነው፡፡ የሚያጋጥመውን ችግር ጊዜ ሰጥቶ ተወያይቶ መፍታት አለበት ለዚህ ደግሞ እንደዛሬ የስብሰባ አዳራሾች ባልተሰሩበት ወቅት እንደመሰብሰቢያ አዳራሽ በመሆን የሚያገለግለው ዛፍ ነበር፡፡ ትልቅ ዛፍ በትዕምርታዊ ትርጉም ሽማግሌን ይወክላል፡፡ (በህልም ፍቺ ወቅት ትልቅ ዛፍ መገንደስ (መውደቅ የሽማግሌን ሞት መወከሉ እዚህ ጋር ልብ ይሏል፡፡)

ሽማግሌ በባሌ ኦሮሞዎች ዘንድ ከፍተኛ ቦታ ይሰጠዋል። ሽማግሌዎች የጎሳ ታሪክን በማስተማር፣ ባህልን ጠብቆ ለቀጣይ ትውልድ በማስተላለፍ፣ የተጋጩ ወገኖችን በማስታረቅ ፣ወዘተ. ከፍተኛ ሚና አላቸው። ለዚህም ነው በምሳሌያዊ አነጋገሩ በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ የሽማግሌ እና የትልቅ ዛፍ መኖር አስፈላጊ ብቻ ሳይሆን የግድ መሆኑን የተገለፀው። የባሌ ኦሮሞ ሽማግሌዎች የግድያ ግጭትን በሚፈቱበት ወቅት ግጭት ውስጥ የገቡት አካላት ሽማግሌዎችን አክብረው፣ ቃላቸውን ሰምተው ወደ እርቅ እንዲመጡ ያደርጉበታል።

በማህበረሰቡ ውስጥ የሚከሰትን ግጭት ግራ ቀኙን አይቶ የጉዳዩን ጥልቀት መርምሮ እርቅ የሚያወርደው ሽማግሌ ነው። ሽማግሌ ባይኖር ግጭቶች ተባብሰው የከፋ ጉዳት ይደርሳል። ይህን ለማስረዳት ነው በምሳሌያዊ አነጋገሩ የትልቅ ሰው መኖር ለማህበረሰብ መኖር መሰረት እንደሆነ የሚነገረው።

Yabbuu jiidhatti maran

**ቆዳ የሚታጠፈው በእርጥብነቱ ነው።**

የከብት ቆዳ የተለያዩ መገልገያ ቁሳቁሶችን ለመስራት ያገለግላል። አንድ ሰው ከከብት ቆዳ አንድ ነገር (መጫኛ፣ወንበር፣ልብስ ፣ጌጣጌጥ ወዘተ.) መስራት ሲፈልግ ቆዳው ገና እርጥብ እያለ ለሚፈልገው ጉዳይ ይውል (ይሆን) ዘንድ ማስተካከል ይጠበቅበታል። ቆዳውን በርጥብነቱ ለሚፈለገው ጉዳይ እንዲሆን አድርጎ ካላስተካከለው ከደረቀ በኃላ አይታዘዝለትም። ለሚፈልገው ነገር ማዋል አይችልም ። በባሌ ኦሮሞዎች ዘንድ ግጭት ከዚህ አንጻር ይታያል። ሽማግሌዎች ይህንን ምሳሌያዊ አነጋገር የሚናገሩት ማንኛውም ሽማግሌ አንድ ግጭት መፈጠሩን ካወቀ በፍጥነት ለተፈጠረው ግጭት እልባት መፈለግ እናዳለበት ለመጠቆምና ግጭት ውስጥ የገቡትም አካላት ሽምግልና የሚቀመጡትን ሽማግሌዎች ምክር ሰምተው ጉዳዩ እንዳይጓተት በማድረግ በቶሎ ወደ እርቅ እንዲመጡ ለማሳሰብ ነው።

ምሳሌያዊ አነጋገሩ በአንድ ግላዊ ይሁን ማሕበራዊ አጋጣሚ በተለያዩ ምክንያቶች አንድ ግጭት ቢፈጠር ያ ግጭት በተቻለ መጠን በፍጥነት መፈታት እንዳለበት ያሳያል። የተከሰተው ችግር በጊዜ እልባት ካላገኘ ግን እየከረረ ሄዶ የከፋ ጉዳት ላይ ያደርሳል። ልፍታህ ቢባልም ውሉ ይጠፋል። ሽማግሌዎች የነገር ውሎ ማደር የሚያስከትለውን ችግር ለመፍታት ይህን ምሳሌያዊ አነጋገር ይጠቀማሉ። የባሌ ኦሮሞዎች ይህንን ሀሳብ ለማስተላለፍ የሚጠቀሙበት ሌላ

ምሳሌያዊ አነጋገርም አላቸው። "Tiruun bulte, Lafee Taate" (ያደረጉበት ይሆናል አጥንት) ይኸኛው ምሳሌዊ አነጋገር ለጉዳዩ አፅንኦት ይሰጠዋል።

Abbaan dhoyfatu ireetu hima

ባለቤቱ የደበቀውን ፊቱ ይናጋራል

የሰዎችን ፊት በመመልከት ማዘን፣ መተከዛቸውን፣ መደሰት፣ መከፋታቸውን መገመት ከባድ አይመስልም። ነገር ግን አንዳንዴ ሰዎች ሀዘናቸውን በሳቅ ደስታቸውን በለቅሶ ሲገልጹ ይታያሉ። በዚህ ጊዜ ያለቀሰው አዝኗል የሳቀው ተደስቷል ብሎ መናገር ያዳግታል። (የሰው ሆዱ የወፍ ወንዱ አይታወቅም የሚለውን ምሳሌያዊ አነጋገር ልብ ይሏል።)

የባሌ ኦሮሞ ሽማግሌዎች ይህንን ተረት የሚናገሩት ግጭትን በሚፈቱበት ወቅት አጥፊው ጥፋቱን አላምን ሲል ነው። አንድ ሰው የሰራው ጥፋት የሚያደርስበትን ቅጣት በመፍራት እውነታ ሊደብቅ ይችላል። ቢሆንም ግን ከእውነት ጋር በሚያደርገው ትግል ሊቀበጣጥር፣ ሊደነግጥ፣ ሊያልበው ይችላል። ሽማግሌዎች ብዙ ነገር ያውቃሉ ተብሎ ስለሚታመን ማንም የደበቀው ነገር ተደብቆ ለመቅረቱ እርግጠኛ አይሆንም።

ሽማግሌዎችም ይህንን ምሳሌያዊ አነጋገር የተደበቀ እውነታ እንዲወጣ ለማረግ ይናገሩታል።

Citaa fi ibidda wal hingain

Bishaaniifii ibidda malee

እሳትና ጭድን አያገናኙም ውሀና እሳትን እንጂ

ከዚህ ምሳሌያዊ አነጋገር ሁለት ሊጠፋፉ የሚችሉ ነገሮች አንድ ላይ ማረግ እንደማይገባ እንገነዘባለን። እሳት ጭድ ካገኘ ሀይሉ ከነበረው መጠን በከፍተኛ ሁኔታ ይጨምራል። የመቀጣጠልና የመስፋፋቱ ሁኔታ የጨመረ ይሆናል። ነገር ግን ውሀ ቢያገኝ ነገሩ ተቃራኒ ይሆናል።መቀጣጠሉ ቀርቶ ይጠፋል።

የባሌ ኦሮሞ ሽማግሌዎች በተለይ የግድያ ግጭትን የሚፈቱ የገለልተኛ ጎሳ ሽማግሌዎች (Rayyaa Anbaa) ይህን ምሳሌያዊ አነጋገር የሚናገሩት ገና የግድያ ግጭቱ እንደተከሰተ ሲነገራቸው ነው። የራያ አምባዎች የመጀመሪያ እርምጃ የሚችና የገዳይ ወገኖች እንዳይገናኙ

ማድረግ ነው። በዚህ መሰረት የገዳይ ወገኖች እንዲሸሹ ፣ ከሟች ወገኖች ጋር አንድ መስክ ላይ ከብት እናዳያስማሩ ፣ አንድ ወንዝ ከብት እንዳያጠጡ፣አንድ ገበያ እንዳይገበያዩ፣አንድ መንገድ እንዳይሄዱ .ወዘተ ያውጃሉ። ይህን ተረትም የሚናገሩት ለአዋጁ አጽንኦት ለመስጠት ነው። የገዳይ ቤተሰቦች ወይም ወገኖችጥንቃቄ እንዲያደርጉ ለመምከር ይጠቀሙበታል። የተከሰተው ግጭት እንዳይስፋፋ እና ወደ ባሰ ደረጃ እንዳይሄድለማድረግ ጥንቃቄ እንደሚያስፈልግ ያሳስቡታል።

ይህ ምሳሌያዊ አነጋገር የግድያ ግጭት መፍታት ያለበት አካል ማን እንደሆነም ያመለክታል።ሁሉም ጎሳ ያራሱ የታወቁ የሀገር ሽማግሌዎች አሉት። እነዚህ ሽማግሌዎች በጎሳው ውስጥ የሚከሰት ማንኛውንም ግጭት በመፍታት ተጋጪዎችን ወደ እርቅ ያመጣሉ። ይሁን እንጂ የአንድ ጎሳ አባል የሌላን ጎሳ አባል ሲገድል የገዳይን ጎሳ ሽማግሌዎች መሸምገል አይችሉም። ምክንያቱም የሟች ጎሳ አባላት ያገኙትን የገዳይ ጎሳ አባል ስለሚገድሉ ነው። የገዳይ ጎሳ ሽማግሌዎች ወደ ሟች ጎሳ ሽምግልና ጥየቃ መሄድ እሳት ውስጥ ጭድ እንደመጨመር መሆኑን ያስረዱበታል። ለዚህ ነው የግድያ ግጭቶችን የሚመለከቱት የገለልተኛ ጎሳ ሽማግሌዎች የሆኑት። ይህንን ሃሳብ ለማስተላለፍ (የገለልተኛ ወገን ሽማግሌዎች በቅድሚያ ሁለቱ ወገኖች እንዳይገናኙ ማድረግ እንዳለባቸው ለመግለፅ የሚጠቀሙበት ሌላም ምሳሌያዊ አነጋገር አላቸው። “Qerransaafi ra’e walitti hinttiksanni” (ፍየልና ነብርን በአንድ ላይ አያሰማሩም)

Namaa wajjin nyaatanii hinnyaatan

## አብረው የበሉትን ሰው አያጠፉትም/አይገሉትም

በባሌ ኦሮሞዎች አብሮ መብላት አብሮ መስራት ከፍተኛ ቦታ ይሰጠዋል። አብሮ መብላት የአንድነት፣የወዳጅነት ተምሳሌት ነው። አብረው የበሉ ሰዎች በሀዘን በደስታ ጊዜ አይለያዩም። ችግርን በጋራ ያልፋሉ ይበዳደራሉ፣ይተጋገዛሉ፣ ይረዳዳሉ። የባሌ ኦሮሞ ሽማግሌዎች በተለይ የግድያ ግጭትን የሚፈቱት Rayyaa Anbaaዎች በግጭት አፈታት ሂደት ውስጥ ይህን ምሳሌዊ አነጋገር ይናገሩታል። ይህንን ምሳሌያዊ አነጋገር በብዛት የሚናገሩት በረኮ ስርዓት ወቅት ከእጅ ላይ የማብላት ስርዐት ሲከናወን ነው። በጥናቱ እንደተገለፀው የሟችና የገዳይ ወገኖች በተዘጋጀው የበግ ቆዳ ውስጥ ከሾለኩ በኃላ ከእጅ ላይ ይበላሉ (የሟች ወገኖች ከገዳይ ወገኖች እጅ ላይ ይበላሉ)።

ምሳሌያዊ አነጋገሩ የስርአቱን ትዕምርታዊ ትርጉም ለማሳወቅ ይረዳል፡፡ የሚችና የገዳይ ወገኖችም ከእጁ ላይ የበሉትን ሰው (ጎሳ) ማጥቃት እንደሌለባቸው የሁለቱ ግንኙነት የጠላትነት ሳይሆን የወዳጅነት መሆኑን እንደሚገባው ለማስገንዘብ ሽማግሌዎቹ ይህንኑ ምሳሌያዊ አነጋገር ይናገራሉ፡፡

Coommaa siraammessa daarraa situullesaa

**ጮማ አተላልህለው፣አመድ ኮሲ አደርግልህለው**

ይህንን ምሳሌያዊ አነጋገር የሚናገሩት የጉማ ፈጻሚ ሽማግሌዎች ራያ አንባዎች ናቸው፡፡ ራያ አንባዎች ይህንን ምሳሌያዊ አነጋገር የሚናገሩት የገዳይ ወገኖች ወደ እነሱ መጥተው ከሚቹ ወገኖች እንዲያስታርቋቸው በሚጠይቁበት ጊዜ ነው፡፡ የገዳይ ወገኖች በቶሎ ከሚች ወገኖች መታረቅ ይፈልጋሉ፡፡ የሚች ወገኖች ጉማ ከመውጣቱ በፊት የገዳይ ጎሳዎችን ካገኙ ይገድሏቸዋል፡፡ ከሚች ወገን ጥቃት ባይደርስባቸው እንኳን የስነ ልቦና መረጋጋት አይኖራቸውም፡፡ የፍራቻና የስጋት ማደሪያ ነው የሚሆኑት፡፡ ስለዚህ ሽማግሌዎቹ ቶሎ እንዲያስታርቋቸው ይለምናሉ፡፡

የግድያ ግጭት በፍጥነት መፍትሄ ማግኘት የሚገባው ቢሆንም በአንድ ጀምበር የሚጠናቀቅ ባለመሆኑ ጊዜ እንደሚያስፈልጋቸው ለማስረዳት ሚናገሩት ምሳሌያዊ አነጋገር ነው፡፡

ስጋ በአንድ ቀን ታርዶ አይተላም፡፡ ለመትላት ደግሞ ጊዜ ይፈልጋል፡፡ አመድ በአንድ ቀን ማገዶ ኮሲ አይሆንም፡፡ ለብዙ ቀናት የተደፋ አመድነው ኮሲ የሚሆነው፡፡ እንደዚሁ የግድያ ግጭት በአንድ ቀን እልባት አያገኝም፡፡ የጉማ ስርዓት የራሱ የሆነ አካሄድ አለው፡፡ ጉማ የሚወጣው ስርዓቱን ጠብቆ እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡ አዋጃቸውን ተቀብለው፣ ከሚቹ ጎሳ እርቀው በትእግስት እንዲጠብቋቸው ያሳስቡበታል፡፡

Gaddi qabanii ilaalani tafkiin ija qabdi

**አገላብጠው ከተመለከቱ የቁንጫን አይን ይመለከታሉ፡፡**

ቁንጫ እንደሚታወቀው በጣም ትንሽ መጠን ነው ያላት፡፡ የቁንጫ አይን ምን ያህል ረቂቅ ሊሆን እንደሚችል መገመት አይከብድም፡፡ ይሁን እንጂ ለነገሩ ትኩረት ሰጥቶ የቁንጫን አይን

ማየት አለብኝ ብሎ አገላብጦ የተመለከተ ሰው ሊያይ እንደሚችል የሚገልጽ ነው። ምሳሌያዊ አነጋገሩ።

የባሌ ኦሮሞ አባቶች ይህንን ምሳሌያዊ አነጋገር የሚናገሩት በተለያዩ ምክንያቶች በማህበረሰቡ ውስጥ የሚከሰቱ ግጭቶችን ለመፍታት የሚቀመጡ ሽማግሌዎች የግጭቱን መነሻ ምክንያት፣ግጭቱ ያስከተለውን ጥፋት በደንብ መመርመርና ለግጭቱ መፍትሄ መፈለግ፣በግጭቱ ውስጥ የገቡትን አካላት ወደ እርቅ ማምጣት እንዳለባችው ለማሳሰብና ለመምከር ነው። ከዚህ በተጨማሪም በጥልቀት ከታየ ሁሉም ችግር መፍትሄ ማግኘት እንደሚችል ለማስረዳት ነው።

Jaarsi ajjeesee nama kaasa

**ሽማግሌ ገድሎ ያነሳል/ያድናል**

ፍርድ ሁሉን አያስደስትም። አንዱን ሲያስደስት ሌላውን ያሳዝናል። ሽማግሌዎች የሚሰጡት ፍርድ ግን መጀመሪያ ላይ ጎጂ ቢመስልም ውሎ እያደር ጠቀሜታው ይታያል። የባሌ ኦሮሞዎች ይህንን ምሳሌያዊ አነጋገር የሚናገሩት ሁሉም ግጭት ውስጥ የገቡት አካላት ውሳኔው ምንም ይሁን ምን በጸጋ መቀበል እንዳለባቸው ለማሳሰብ ነው። የሽማግሌዎች ውሳኔ መጀመሪያ ላይ ከባድ ቢመስልም የኃላ ኃላ ግን ከፍተኛ ጠቀሜታ እንደሚኖረው ያስረዳል።

ገድሎ ማንሳት በጣም ከባድ ተግባር ነው። ምናልባትም ይህንን ተግባር ከፈጣሪ ውጭ ማንም ሰው ሊያከናወነው አይችልም።በተጨማሪም በዚህ ምሳሌያዊ አነጋገር ሽማግሌዎች የጠለቀ እውቀት እንዳላቸው፣በጣም ከባድ ሊባሉ የሚችሉ ጉዳዮችን ማድረግ እንደሚችሉ ያስረዳሉ።

Hareef haareen wall dhiitu, ilkaan wall hin cabssitu.

**አህያ ለአህያ ቢራገጥ ጥርስ አይሰበር**

የባሌ ኦሮሞ ሽማግሌዎች ይህን ምሳሌያዊ አነጋገር የሚናገሩት በአንድ ጎሳ ወይም በአንድ ቤተሰብ አባላት መሀከል የተከሰተን ግጭት በሚዳኙበት ወቅት ነው። በጉማ ስርዓትም እንደተገለጸው አንድ ሰው የራሱን ጎሳ ወይንም ዘመድ ሲገድልና የሌላ ጎሳ አባል ሲገድል የሚከፍለው ጉማ ተመሳሳይ አይደለም።የራሱን ጎሳ ሲገድል ጉማ የሚያወጣውም ጉማ የሚወስደውም አንድ ጎሳ ስለሚሆን ክፍያው በስምምነት ላይ ነው የሚወሰነው።በጎሳ ወይም

በቤተሰብ ውስጥ የሚነሳ ግጭት ለጉዳት እንደማይሰጥ ያስረዳሉ።።ግጭት ውስጥ የገቡት አካላት የተፈጠረውን ችግር አክብደው ሳያዩ በቶሎ ወደ እርቅ እንዲመጡ ያደርጉበታል።

የባሌ ኦሮሞዎች የስጋ አልያም የጋብቻ ዝምንድና ያላቸው ሰዎች በሚጋጩበት ወቅት በዘመዳማቾች መሀከል ግጭት መከሰቱ ያለ መሆኑን በመግለጽ የተጋጩት ዘመዳሞች ዞረው የሚገናኙ በመሆናቸው ክፉ መነጋገር፣ቂሚ በቀል መያያዝ እንደሌለባቸው በማስረዳት እንዲታረቁ ያስማማሉ።

Sogidda hinwaadani waan darbe hinyaadani

**ጨው አይጠብሱም ያለፈን አያስቡም/አያስታውሱም**

ጨውን መጥበስ ዋጋ እንደሌለው ሁሉ ያለፈን ማስታዎስ እንደዚያው ነው። የባሌ ኦሮሞዎች ይህንን ምሳሌያዊ አነጋገር የሚናገሩት የሟች ወገኖችን ለእርቅ በሚጠየቁበት ጊዜና በእርቁ መጨረሻ ቀን ላይ ነው።

በቅድሚያ ሽማግሌዎች የሟች ወገኖችን እርቅ ሲጠይቁ ላለፈው ነገር ማሰብ ዋጋ እንደሌለው፣ ያንን እያሰቡ ቢበሳጩ የሚለውጡት ነገር እንደሌለ፣ እንደውም በራሳቸው ላይ ሌላ ሀዘን፣ ሌላ ችግር፣ ሌላ በሽታ እንደሚያመጡ ለማስረዳት ነው።

በመጨረሻ የእርቅ ቀን ደግሞ ሁሉም (የሟችና የገዳይ) ወገኖች ያለፈውን ነገር (ትተው) ረስተው ወደፊት በሰላምና በፍቅር አብረው መኖር እንዳለባቸው ለመምከር ይናገሩታል።

የገዳይ ወገኖች ያለፈውን ነገር እያሰቡ በንዴት መብሰልሰላቸው ምንም እንደማይጠቅማቸው። "Bobaan garaa foon hinwaadu" (የሆድ ውስጥ እሳት (ትኩሳት) ስጋ አይጠብስም)። በማለት ይመክሯቸዋል። ጥቅም ለሌለው፣ ለውጥ ለማያመጣ ነገር እራሳቸውን ማስጨነቅ እንደማይገባቸው ፣ እርቁን በሙሉ ልብ በንፁህ ሆድ ተቀብለው ሰላም እንዲያወርዱ ለማድረግ ይናገሩታል።

Gaalii hiriya duraa ilaala

**ግመል የቀደመውን ይከተላል**

በባሌ ቆላማ አካባቢ የሚገኙ ኦሮሞዎች ከግመሎቻቸው ውስጥ ቅልጥፍና ያለውን ከልጅነቱ ጀምረው በመሪነት ያሰለጥኑታል። ሌሎች ግመሎችም እሱን ይከተሉታል። እሱ በጣም የሰለጠነ ስለሆነ ወዴት መምራት እንዳለበት ጠንቅቆ ያውቃል። መሪውን ለመከተል ደግሞ ከፊት ያለውን መከተል ያስፈልጋል። ከፊት ያለውን ካልተከተሉ ሲጠፉ፣ በአውሬ ሊበሉ ይችላሉ።

የባሌ ኦሮሞዎች ይህንን ምሳሌያዊ አነጋገር የሚናገሩት ግጭት ውስጥ የገቡት አካላት የሽማግሌዎቹን ምክር ሰምተው በደንቡ በባህሉ መሰረት ወደ እርቅ እንዲመጡ ለማድረግ ነው። የገዳይና የሟች ወገኖች ባህሉን አክብረው በጉማ ስርዓት ለመዳኘት እንዲፈቅዱ ይጠይቁበታል። እምቢ ያለው፣ የፊቱን የአባቶችን ስርዓት አልከተል በሚለው ላይ ሊደርስ የሚችለውን መከራ ያሳስቡበታል።

Abbaan iyyu ollan dirmata

**ባለቤት ከጮኸ ጎረቤት ይደርሳል።**

በባሌ ኦሮሞዎች ባህል መሰረት የግድያ ግጭት ሲከሰት ግጭቱን የሚመለከቱት ገለልተኛ ወገን ሽማግሌዎች ናቸው። እነዚህ ሽማግሌዎች ነብይ ባለ መሆናቸው የግድያ ግጭት መከሰት አለመከሰቱን አያውቁም። በማህበረሰቡ ባህል መሰረት የግድያ ግጭት መከሰቱን ለገለልተኛ ወገን ሽማግሌዎች ማሳወቅ ያለባቸው ገዳይ፣ የገዳይ ቤተሰብና የገዳይ ጎሳዎች ናቸው። እነዚህ ወገኖች የተፈጠረው ችግር ተባብሶ የበለጠ ብጥብጥ እንዳያስከትል በቶሎ ለገለልተኛ ጎሳ ሽማግሌዎች ማሳወቅ ይጠበቅባቸዋል። ሽማግሌዎቹ ይህንን ተረትና ምሳሌ የሚናገሩት አንድ ግጭት ሲፈጠር በቅርብ ያለ አካል በቶሎ ለሽማግሌዎቹ ማሳወቅ እንዳለበት ለማስገንዘብ ነው። ማንም አንድ ወንጀል ሰርቶ መደበቅ እንደሌለበት መደበቅ መፍትሄ እንደማይሆን ለመጠቆም ነው።

Hantunni dhalte dhalte eegen hafnaan oti

አይጥ ወልዳ ወልዳ ጭራ ሲቀር ሲጥ አለች፡፡

ይህን ምሳሌያዊ አነጋገር የሚናገሩት ብዙ ጊዜ አንድ ጉዳይ ተጀምሮ ማለቂያው አቅራቢያ ችግር ሲያጋጥመው ነው፡፡ በጉማ ስርዓት ወቅት የሚችና የገዳይ ወገኖች በጉማው ተስማምተው መጨረሻ ላይ በጥቂት ነገር ላይስማሙ ይችላሉ፡፡ ከማያስማሙ ጉዳዮች ወስጥ ደግሞ የግድያው አይነትና የሚከፈለው የከብት መጠን ተጠቃሽ ናቸው፡፡ ሽማግዎች ይህንን ምሳሌያዊ አነጋገር በመጠቀም የሚችና የገዳይ ወገኖች በመጨረሻ ያሳዩት ነገር አግባብ አለመሆኑን፣በትንሽ ነገር ሽምግልናው መቅረት እንደሌለበት ፣ የቀረው ነገር ላይ ተቻችለውና ተስማምተው ወደ እርቅ መምጣት እንዳለባቸው ያስገነዝቡበታል፡፡

### 6.2. አፈታሪክ በግጭት አፈታት ወቅት ያለው ሚና

አፈ ታሪክ ባለፈ ታሪክ ላይ ተመስርቶ የሚነገር ሲሆን በአብዛኛው በአንድ በተወሰነ አካባቢ ከተፈጸመ እውነተኛ ታሪክ አንድ ገፅታ በመውሰድ ስነቃላዊ ፈጠራ ተጨምሮበት የሚነገር ነው፡፡ አፈታሪክ በታሪክ የነበረው ሰው ያከናወናቸውን ተግባራት መልካምነት ወይም መጥፎነት ለማረጋገጥ ይነገራል፡፡ በእውነት ተፈጽመዋል በሚባሉ ታሪካዊ ክንዋኔዎች ላይ በመመስረት የክንዋኔዎቹን ሁኔታ ለምሳሌ ስለ ንጉሶች፣ በጎሳዎች መሀከል ስለተደረገ ግጭት ወይም ጦርነት፣ ስለተካሔደው የእርቅ ስርዓት፣ ስለተሰጠው ፍርድ ወዘተ. ይናገራል፡፡

አፈታሪክ ባለፈ ዘመን ተፈፀመ የተባለን ድርጊት በመያዝ ሰዎች ከአስቸጋሪ ገጠመኞች እንዴት እንደወጡ፣ ምን እንዳደረጉ ያሳያል፡፡ በተለያዩ አጋጣሚዎች ሰዎች በአንድነት በተሰበሰቡበት በንግግር መሀል ጣልቃ እየገባ ለነገር ማስረጃ፣ ለማስጠንቀቂያና ለማስተማሪያ ሊነገር ይችላል፡፡ አፈታሪክ የሚነገረው ለተዝናኖት ሳይሆን ለማስተማርና ለመምከር ነው (ዘሪሁን 1992)፡፡

የባሌ ኦሮሞ ሽማግሌዎች በማህበረሰቡ ውስጥ አንድ ግጭት ሲፈጠር ያን ግጭት ለመፍታት በሚያደርጉት ሂደት ውስጥ አፈ ታሪክ ይናገራሉ፡፡ የሚናገሯቸው አፈ ታሪኮች ግጭት ውስጥ የገቡትን አካላት ለመምከር፣ ለማሳመን፣ ለማስተማር የሚረዱ ናቸው፡፡ ከዚህ በመቀጠል በተተኳሪ ቡድን ውይይት ላይ በአንድ መረጃ አቀባዬ የተነገረ አፈታሪክ በማቅረብ የአፈታሪኩ መነገር ያለውን ፋይዳ እንመለከታለን፡፡

Yeroo mootummaa Minilikk raayyaan isaanii araddaa bal'ifachuuf godina Baaleetti duule. Ergaan isaanii araddaa bal'ifachuuf qofa osoo hin taane achuumaaniis jiraattonni godinaa Kiristaana akka ta'an gochuu ture. Kanaafuu akkana jechuudhaan dhaamsa dabarsan. Iisin soomuutu isinirra jira jedhaniin. Haata'uutii jiraattoti ajaja raayyotaa kana deemanii jaarsotani himan. Jaarsonnis waan Amaarri isin ajaju hin didinaa, 'Ishii' jedhaatii galgala garuu aannan keessan dhugaa jedhanii gorsan (አቶ ከድር ጀማል፣ የታላሚ ቡድን ውይይት፣ ሚያዚያ 28፣ 2003ዓ.ም ጎባ የተናገሩት).

በሚኒሊክ ዘመነ መንግስት ነው። የሚንሊክ ወታደሮች የግዛት ማስፋፋት ሲያካሂዱ የአሁኑ የባሌ ዞን አካባቢ ይደርሱና ህዝቡን ይቆጣጠራሉ። ወታደሮቹ ከግዛት ማስፋፋት ጎንለጎን የሀይማኖት ማስፋፋትም ያካሂዱ ነበርና የዋቄፋና እምነት ተከታይ የነበረውን ህዝብ ክርስትናን ተቀበሉ ፁሙ ይሏቸዋል። በነገሩ ግራ የተጋቡት የባሌ ኦሮሞዎች ጉዳዩን ለሽማግሌዎች በመውሰድ "አማራው ፁሙ ይላል ምን እናድርግ" በማለት ይጠይቃሉ። የመፆም ትርጉም ያልገባቸው ሽማግሌዎች "መፆም ምንድን ነው?" በማለት ጉዳዩን ያመጡትን ሰዎች ይጠይቋቸዋል። ሰዎቹም "አማራው ስጋና ወተት አትብሉ ከስጋና ከወተት ፁሙ አለ ምን እናድርግ?" ይላሉ። በዚህ ጊዜ ሽማግሌዎች "አማራው ወተት አትጠጡ ስጋ አትብሉ አለ? እንግዲያውስ እናንተ ማድረግ ያለባችሁ እሺ በሏቸው። የአማራን ቃል እሺ በሉ ማታ ማታ ወተታችሁን ጠጡ" አሏቸው ይባላል።

ከዚህ አፈታሪክ ብዙ ነገር እንረዳለን። ህዝቡ ያጋጠመውን ችግር በሙሉ ለሽማግሌዎች የማማከር የቆየ ባህል እንዳለው ያስገነዝባል። ሽማግሌዎች ይህንን አፈ ታሪክ በመናገር ማህበረሰቡ የሚያሳስበውን ጉዳይ በሙሉ ወደ እነሱ ይዞ በመምጣት እንዲያማክራቸው ያደርጉበታል።

አፈታሪኩ በተነገረበት አውድ ያለውን ትርጉም ስንመለከት ሽማግሌዎች አንድን ነገር ሲወስኑ ነገሩ ሊያመጣ የሚችለውን ችግር በደንብ መርምረው ግራ ቀኙን አይተው መሆን እንዳለበት ያሳስባል። በአፈታሪኩ የቀረቡት ሽማግሌዎች አማራው መሬታችንን መቆጣጠሩ ሳያንስ እንዴት ጹሙ ይላል። ያውም የእለት ተእለት ምግባችን ከሆኑት ወተትና ስጋ፤ ይህ የሀይማኖት የህልውና ጉዳይ ነው፤ ስለዚህ እሺ አትበሏቸው ቢሉ ሊደርስ የሚችለውን ጉዳት መገመት

አይከብድም፡፡ ግዛት የሚያስፋፉት እሺ. ባይባሉ ሀይል ስላላቸው የሚወስዱት እርምጃ የከፋ ሀይል ሊሆን ይችላል፡፡ በዚህ ጊዜ የዛ ህዝብ እጣ ፈንታ ሞት፣ ስደት፣ ችግር፣ ይሆናል፡፡

እሺ. ብለው ወተት ካልጠጡ ስጋ ካልበሉም እጣ ፈንታቸው በሽታና ሞት ነው የሚሆነው፡፡ ምክንያቱም የማህበረሰቡ የገቢ. ምንጭ በአብዛኛው ከእርሻ እና ከከብት እርባታ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ማህበረሰቡ በብዛት የእንስሳት ተዋፅዖን ለምግብነት የሚጠቀም ማህበረሰብ ነው፡፡

ሽማግሌዎቹ ይህንን ሁሉ በማመዛዛን የሰጡት ውሳኔ (ምክር) ግን ሰላምን የሚፈጥር፣ የማህበረሰቡን ህይወት የተረጋጋ የሚያደርግ ነው፡፡ አሁንም ድረስ የባሌ ሽማግሌዎች ይህን አፈታሪክ በመናገር ለሽምግልና የሚመረጡ ሽማግሌዎች የያዙትን ጉዳይ አገላብጠው መመልከት፣ የሚሰጡት ውሳኔ የሚያመጣውን ጉዳትና ጥቅም በጥልቀት መመርመር፣ ፍረዳቸው ለማህበረሰቡ ጠቃሚ መሆኑን መገንዘብ እናዳለባቸው ይመክሩበታል፡፡

### 6.3. ተረት በግድያ ግጭት አፈታት ወቅት ያለው ሚና

ዘሪሁን (1992፣29) የተረትን ፋይዳ ሲገልጽ ተረት የማህበረሰቡን ወግና፣ ልማድ፣ ስነምግባርና አጠቃላይ አመለካከት ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡ ማህበረሰቡ ሰናይ፣ እኩይ ብሎ የመደባቸውን የስነ ምግባር መልኮች ያንጸባርቃሉ፡፡ ሰናዩን በማሞገስና በማጠንከር፣ እኩዩን ደግሞ በማውገዝና በማንቋሸሽ የማህበረሰቡን ታዳጊዎች አስተሳሰብ በተወሰኑ አቅጣጫዎች ለመምራት ይጠቅማል፡፡ ሽማግሌዎች ለልጆችና ለወጣቶች ተረት በመንገር የማህበረሰባቸው መሰረት የሆኑትን ልዩ ልዩ ገጠመኞች ያስረዳሉ፣ ባህላቸውን ጠብቀው፣ አንድነታቸውን አጠንክረው፣ እንዴት መኖር እንደሚገባቸው ያሳውቃሉ ይላል::

የባሌ ኦሮሞዎች በማህበረሰቡ ውስጥ በተለያዩ ምክንያቶች የሚከሰቱ ግጭቶችን በሚፈቱበት ወትት ተረቶች በመናገር ግጭቱ እንዲፈታ፣ በግጭቱ ውስጥ የገቡት አካላት መሀከል ቂም በቀል እንዳይኖርና ዘላቂ ሰላም እንዲፈጠር ያደርጋሉ፡፡

የባሌ ኦሮሞዎች በተለያዩ ማህበራዊ አጋጣሚዎች ላይ ሀሳባቸውን ግልፅ ለማድረግ ተረት ይናገራሉ፡፡ ለተለያዩ ጉዳዮች በተረት መፍትሔ ይሰጣሉ፡፡ በመቀጠል የባሌ ኦሮሞዎች በማህበረሰቡ ውስጥ በተለያዩ ምክንያቶች የሚከሰቱ ግጭቶችን ለመፍታት የሚተርቷቸውን ተረቶች በመጀመሪያ በመገኛ ቋንቋቸው (ኦሮምኛ) በማቅረብ በመቀጠል ተረቶቹን በአማርኛ በመተርጎም በግጭት አፈታት ሒደት ያላቸውን ሚና እንተነትናለን፡፡

## ተረት አንድ

## GOORSA JAARSAA

Naannoo tokko keessa jaarsi dulloomaan tokko ture. Jaarsi kun lafaa ka'ee hojii hojjechuu waan hin dandeenyeef teessoorra taa'ee ganamaafi galgala ijoolleesaa gorsa. Ijoolleensaa garuu gorsa isaa nuffanii ati jaarsa nana yeroo hundumaa achi teessee nu hin gorsin nuyyuu waan gochuu qabnu beeknaa" jedhan. Jaarsichis dubbii isaanii kanatti gaddee "haa ta'u ijoollee koo mee akkuma isin jettan haa ta'u" jedhe.

Guyyaa gaaf tokko galgala ijoolleen horii galchanii harree irraanfatan. Erga galchanii maa'essa jaarsi akkka harreen irraanfatamte hubatee akka harree halaake. Ergasii barbaadanii galchan. Kanaafuu hima jaarsaa dhaggeeffachuun waan baay'eef nama gargaara jedhamaa.

## የአማርኛ ትርጉም

## የሽማግሌ ምክር

በአንድ አካባቢ አንድ እርጅና የተጫጫናቸውና ከተቀመጡበት መነሳት የማይችሉ ሽማግሌ ነበሩ። እኚህ ሽማግሌም ልጆች ነበሯቸው ልጆቻቸውን ሁሌ ይመክሯቸው ነበር ነገር ግን ልጆቹ ለዚህ ሽማግሌ ምክር ንቀት ነበረባቸውና አይሰሟቸውም ንቀታቸውም በእሽታ ያሳልፉት ነበር።

ታዲያ ከእለታት ባንድ ቀን የዚህ ሽማግሌ ልጆች ከብቶች ካሰማሩበት ሲመለሱ ከከብቶቹ መካከል አህያ ረስተው መጥተው ነበር። ሽማግሌው በዚህን ሰአት ልጆቹ አህያ መስክ ጥለው መምጣታቸውን እንዲያስታውሱ እንደ አህያ ጮሁላቸው ይሄን ግዜ ልጆቹ አህያ ረስተው መምጣታቸውን በማስታወስ ተመልሰው በመሄድ እህያዋን ይዘው መጡ። ከዚህ ጊዜ በኃላ ሽማግሌን ማክበር ምክራቸውን መስማት ጠቃሚ እንደሆነ ተገነዘቡ።

## ትንታኔ

በተረቱ ውስጥ እንደምንመለከተው የሽማግሌው ልጆች ሽማግሌው አርጅቷል ፣ ከተቀመጠበት አይንቀሳቀስም፣ ዝም ብሎ መምከር ብቻ ነው የሚያውቀው፣ በማለት ምክሩን አይቀበሉትም። ሽማግሌው ግን ሁልጊዜ እነሱን ከመምከር አልተቆጠበም። በዚህም በመናደድ ሁለተኛ እንዳይመክራቸው ያሳስቡታል። የምናደርገውን እናውቃለን አትምከረን ይሉታል። ሽማግሌው ግን እሺ ብሎ ቢቀበልም በተለያየ መንገድ ምክር መለገሱን አላቆመም ነበር። በተረቱ እንደተመለከትነው ዘዴውን በመቀያየር እስከ መጨረሻው ድረስ ታግሎ ንብረትን ከጥፋት ልጆቹን ከስህተት ታድጓል።

የባሌ ኦሮሞዎች ይህን ተረት የሚናገሩት በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉ ሽማግሌዎች በጣም ትዕግስተኛ እና ቻይ መሆን እንዳለባቸው ለማሳሰብና በሚደርስባቸው ወቅታዊ (ጊዜያዊ) ችግር ተሸንፈው የማህበረሰቡ ሰላም እንዲዛባ ማድረግ እንደሌለባቸው ለመምከር ነው። በተረቱ ውስጥ እንደቀረበው ሽማግሌ እስከመጨረሻው ድረስ ነገርን በመከታተል መፍትሔ መስጠት የተበደለን ማስካስ፣ ያጠፋን መምከር፣ መቅጣት እንዳለባቸው ይገልፁበታል።

በግጭት ውስጥ የገቡት ወገኖችም የሽማግሌዎችን ምክር መስማት እና ወደ እርቅ መምጣት እንዳለባቸው ያስረዱበታል። የሽማግሌዎችን ምክር የማይቀበሉ ከሆነ የሚያጋጥማቸው መጥፎ ነገር እንደሆነ ያሳስቡበታል። በተረቱ እንደተገለፀው ሽማግሌዎች ሀሳባቸውን በተለያየ ዘዴ ሊገልፁ ይችላሉ። ግጭት ውስጥ የገቡት አካላት ሽማግሌዎቹ ለምን እንዲህ አሉ? ለምን እንዲህ አደረጉ? በማለት በተለይ የሚተርቷቸው ተረቶች መገንዘብ እንደሚገባ ያስረዱበታል።

## ተረት ሁለት

### MURTII HAQAA

Bakka duulanitti waraabessi goromsa booji'e. obbo leenci ammo sangaa booji'e. duulaa galanii otuma wajjin taa'anii goromsi sa'aa sun dhalee bulee ganamaan leenci, "Sangaan koo dhale," jedheen waraabessaan. "Maaloo kiyyatu dhale," jedheen waraabessi. Dinnaan waraabessi dhaqee abbaa saatti himate. Himannaan abbaansaa dhufee, "Maaloo mucaa maaf akkana goota?" jedheen. "Jaarsummaan isiniif haa ilaallu," jedheen. Jaarsummaaf bineensota bosonaa

mara lakkaawwatan.. Achumaan hunduu dhufan. Qamaleen qofti haftee jarreen kaan dhufan. Martinuu waraabessatti raggaasisan. Warraabessis, "qamaleen dhuftu malee murtii kana hin fudhu," jedheen. Walii galuudhaan qamaleetti ammas ergan. Achumaan, qamaleen dhufte, leenci, "maaloo maaliif hamma ammaatti turte" jedhee dheekkame. Achumaan, "maaloo yaa gooftaa koo nan rakkadhe," jetteen. "Maal rakkatte" jedhee leenci gaafate. Achumaan qamaleen akkaana jettee deebisteef, "lafa tokkotu baqaqe isa suphuuttan ture," jetteen. Achumaan leenci, "biyya kamitti lafti baqaqee supham," jedheen. "Atihoo biyya kamitti sangaan dhalee," jettee deebisteef. Kanumaan waraabessaaf murte jedhama.

## የአማርኛ ትርጉም

## የእውነት ፍርድ

አንድ ግዜ ጅብና አንበሳ ለዘመቻ አብረው ይወጣሉ። ከዘመቻው በኋላ ሲመለሱ ምርኮ ይዘው ተመለሱ። በዚያን ግዜ አንበሳው የማረከው የደለበ በሬ ሲሆን አያ ጅቦ ደግሞ ጊደር ነበር።

ታዲያ አብረው ከቆዩ በኋላ ጊደሯ ለሊት ወለደች በዚህን ጊዜ አንበሳ ጠዋት በጊዜ በመነሳት የተወለደውን ጥጃ ወደሱ በሬ በማስጠጋት ለጅብ "አየህ በሬዩ ወለደ" አለው ጅብም "እንዴት ሊሆን ይችላል? የወለደችው የኔ ጊደር ነች" ቢለው አንበሳው አሻፈረኝ ብሎ ካደ።

ከዚህ በኋላ ጅብም ለአባቱ ተናገረ የጅቡም አባት አንበሳውን "ለምን እንደዚህ ታደርጋለህ ልጄ በማለት በሉ ሽምግልና እንይላችሁ" ካለ በኋላ በዱር ያሉት አራዊቶች ሁሉ ለሽምግልና እንዲጠሩ ተደረገ። ታዲያ ለሽምግልና የመጡት ሁሉም በጅብ ላይ ፈረዱበት። ይሁንና ጅብ ጦጢት በሽምግልናው ላይ ከተጠሩት መሀከል ቀርታ ነበርና "እሷ መጥታ ፍርድ ካልሰጠች በቀር የተፈረደውን ፍርድ አልቀበልም" ብሎ አሻፈረኝ አለ።

የኃላ ኃላ ጦጢት በስንት ፍለጋ ተገኝታ ተጠራች አያ አንበሳ "እንዴት ትጠፊያለሽ" ብሎ ተቆጣት ጦጢትም "በጣም ተቸግሬ ነው የቀረሁት" አለች። አንበሳም "ምን አይነት ችግር" ብሎ ጠየቃት እኔ ያለሁበት አካባቢ መሬት ተሰንጥቃ እሱን ስሰፋ ነበር የጠፋሁት ስትል አንበሳም

ቀበል አድርጎ በየት ሀገር ነው መሬት ተሰንጥቆ የሚሰፋው ቢላት ጦጢትም በተራዋ አንተስ በዬት ሀገር ነው በሬ ጥጃ የሚወልደው በማለት ለጅብ ፈረደችለት ይባላል፡፡

ትንታኔ

በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ በተለያዩ ምክንያቶች ግጭት ሊከሰት ይችላል፡፡ ይህን ግጭት ለመፍታት የሚረዱ እንደየሀገሩ እና እንደየባህሉ የተለያዩ ተቋማት ይኖራሉ፡፡ በባሌ ኦሮሞዎች ዘንድ በማህበረሰቡ ውስጥ የሚከሰቱ ግጭቶችን ለመፍታ ከሚያገለግሉ ተቋማት ውስጥ አንዱና ዋነኛው የሀገር ሽማግሌዎች ተቋም ነው፡፡ የሀገር ሽማግሌዎች ባህላዊ ተቋም በማህበረሰቡ ውስጥ ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው ነው፡፡ ማህበረሰቡ ሽማግሌዎች የሚሰጡት ፍርድ ሐቅ፣ ውሳኔያቸውም ትክክል ነው ብሎ ያምናል፡፡ ስለዚህ ሽማግሌዎቹ የማህበረሰቡን እምነት ማጣት፣ እውነት ማዛባት፣ ፍርድ ማዛባት አይጠበቅባቸውም፡፡ ይህ ተረት የሚተረተውም ይህን ጉዳይ ለማስረዳት ነው፡፡

በተረቱ ውስጥ አንበሳ እና ጅብ የኔ ጊደር ናት የወለደችው፣ የኔ በሬ ነው የወለደው በሚል ክርክር ሽማግሌዎች ጋር ይሔዳሉ፡፡ ለሽማግሌዎቹ የቀረበው ጉዳይ ቀላልና ለፍርድም የማያስቸግር ነው፡፡ ሽማግሌዎቹ ግን የሰጡት ፍርድ በሀቅ ላይ ያልተመሰረተና ፍትህን ያዛባ ነው፡፡ ይህንን ያደረጉበት ምክንያት ደግሞ እውነታውን አጥተውት አይደለም፡፡ በሬዬ ወለደ የሚለው አንበሳ ፍርዱ ለሱ ካልሆነ እንደሚበላቸው ስለሚያውቁ ነው፡፡

ሽማግሌዎቹም ይህን ተረት በመተረት ሽምግልና የሚቀመጡ አካላት የሚች ወይም የገዳይ ወገን ከፍርድ በኃላ ያጠቃን ይሆናል በማለት ፍትህን እንዳያጓድሉ፣ በገንዘብ፣ በንብረት (በጉቦ) ተታለው እውነት ያልሆነ ፍርድ እንዳይሰጡ እና ለእውነት እንዲቆሙ ያደርጉበታል፡፡ ለሽምግልና ከተቀመጡት ውስጥ አብዛኞቹ አንድ አቋም ስለያዙ ብቻ ሁሉም ወደ ብዙሀኑ መሳብ እንደሌለበት ያሳውቁበታል፡፡ ብዙሃኑን ሳይሆን እውነትን ብቻ መያዝ እንደሚያስፈልግ ያስረዱበታል፡፡

የጦጣዋን የነገር አያያዝ አፅንኦት በመስጠትም ሽማግሌዎቹ የጀመሩትን ጉዳይ በስልት ከዳር ማድረስ እንደሚገባቸው እና አስፈሪ በሚመስል ሁኔታ ውስጥ እንኳ ቢሆን እዚህ ሽምግልና ላይ ከተሳተፍኩ ችግር ይደርስብኛል ብሎ ከመቅረት በሽምግልናው ተሳትፈው እውነቱን መፍረድ እንዳለባቸው ያስገነዝቡበታል፡፡ መተው ወይም መቅረት ችግሩ እየተስፋፋና እየተባባሰ

እንዴሄድ ከማድረግ ውጪ እንደማያበርደው በመግለፅ ሽማግሌዎቹ የተከሰተውን ግጭት በቁርጠኝነት ለመፍታት መስራት እንደሚገባቸው ያስረዱበታል፡፡

**ተረት ሶስት**

Murtti qarrutee

Bara durii waraabessaafi jaldeessatu “anamoo situ bareeda” jedhanii wal mormaa turan. Kanumarraa kan ka’e, waldhabbii kana mirkaneessuuf eenyutu bareeda kan jedhuuf qotee bulaa tokko bira dhaqan. Yeroo kana “nu lamaan keessaa eenyutu bareeda” jedhanii isa gaafatan. Qotee bulaan sunis lamaan isaanii eerga sirriitti ilaalee booda yoo waraabessatu bareeda jedhe jaldeessi midhaan na jalaa balleessa, yoo jaldeessa jedhee waraabessi loon koo na duraa fixa maalan godha jedhee eerga yaadee booda, “lamaan keessanuu achi garagalaa” jedhee harka lamaaniin lamaan isaanii tuqe, isaanis ana ana jechaa gammadaa utaalaa deeman jedhama.

**የአማርኛ ትርጉም**

**የብልጥ ውሳኔ**

በድሮ ጊዜ ጅብና ዝንጀሮ “በቁንጅና እኔ እበልጣለሁ” “እኔ ነኝ ቆንጆ” በማለት ይጨካከራሉ፡፡ በዚህም በጣም ከተጨቃጨቁ በኃላ በአካባቢው ወደሚገኝ አንድ ገበሬ ዘንድ በመሄድ እሱን ጠይቀው ማን ቆንጆ እንደሆነ እንዲፈርድላቸው ለማድረግ ተስማምተው ወደ ገበሬው ቤት ይሔዳሉ፡፡ ገበሬው ቤት ከደረሱ በኃላ “ገበሬውን ከሁለታችን ቆንጆ ማነው?” በማለት ይጠይቁታል፡፡ ገበሬውም ለመፍረድ ግራ ይጋባል፡፡ ዝንጀሮ ነው ቆንጆ ብል ጅብ ከብቶቼን ይጨርስብኛል፡፡ ቆንጆ ጅብ ነው ብል ዝንጀሮ ሰብሌን ያጠፋብኛል፡፡ በማለት ትንሽ ካሰበ በኃላ “ሁለታችሁም ወደዛ ዙሩ” ይላቸዋል፡፡ ጅብና ዝንጀሮም እንደታዘዙት ፊታቸውን ከገበሬው አዙረው ይቆማሉ፡፡ [ከሁለታችሁ ቆንጆ የሆነውን በእጄ ጭራውን እነካለሁ ይላቸዋል፡፡] ከዛም በሁለት እጁ የሁለቱንም ጭራ ይነካል፡፡ ጅብና ዝንጀሮም ጭራቸው በመነካቱ “እኔ ነኝ ቆንጆ” “እኔ ነኝ ቆንጆ” እያሉ በደስታ ወደመጡበት ተመለሱ ይባላል፡፡

## ትንታኔ

በተረቱ ውስጥ በግልፅ እንደሚታየው በሁለት አካላት መካከል የሚፈጠር ማንኛውንም ግጭት እልባት ፍለጋ ወደ ሽማግሌዎች ይሔዳሉ፡፡ ዝንጀሮ እና ጅብ በመካከላቸው የተፈጠረውን ውዝግብ ለሽማግሌ ሲያቀርቡ እናያለን፡፡ በዚህም የባሌ ሽማግሌዎች በማህበረሰቡ ውስጥ በግለሰቦች፣ በባልና ሚስት፣ በወንድማማቾች፣ በጎሳዎች ወዘተ. መሀከል የሚከሰት ማንኛውም አይነት ግጭት ተባብሶ ወደ ከፋ ደረጃ ከማምራቱ በፊት ለሽማግሌዎች መነገር እንዳለበት ያስገነዝቡበታል፡፡

በተረቱ ውስጥ እንደተመለከትነው ገበሬው ለአንዱ አካል ቢፈርድ ሊደርስበት የሚችለውን ችግር አመዛዝኖ ሁለቱንም የሚያስደስትና እሱንም ከስጋት የሚያድን ፍርድ ይሰጣል፡፡ የባሌ ሮሞዎች ይህንን ተረት በመተረት ሽምግልና የሚቀመጡ ሰዎች ፍርድ ለመስጠት ከመቻኮል ነገሩን በጥልቀት በመመርመር፣ የሚሰጡት ውሳኔ በማህበረሰቡ ውስጥ ሊያደርስ የሚችለው ውጤት መገመት፣ በሚች እና በገዳይ ወገኖች መሀከል የሚፈጥረውን የተረጋጋ ሰላም ወይም የከፋ ጉዳት በማጤን ፍርድ መስጠት እንደሚገባቸው ያስረዱበታል፡፡

# 7.ማጠቃለያና ይሁንታዎች

## 7.1. ማጠቃለያ

ይህ ጥናት የባሌ ኦሮሞዎች በመካከላቸው ሆነ ከሌሎች ህዝቦች ጋር የሚከሰቱ ግጭቶችን ለመፍታት የሚጠቀሙበት ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት ላይ ያተኮረ ነው፡፡ በመሆኑም ማህበረሰቡ ለግድያ ግጭት አይነቶችን፣ የጉማ አይነትና የግድያ ግጭት ባህላዊ አፈታት ስርዓት በጥናቱ ለማየት ተሞክሯል፡፡

ስለግድያ ግጭት ምንነት፣ ስለግድያ ግጭት መነሻ ምክንያቶች፣ ስለግድያ ግጭት አይነቶች፣ ስለሚከፈለው የደም ካሳ (ጉማ) መጠንና አይነት እንዲሁም ስለግድያ ግጭት ባህላዊ አፈታት ስርዓት በባህል እውቀታቸው፣ በአስታራቂነታቸው፣ በንግግር ችሎታቸው .ወዘተ የታወቁ የሀገር ሽማግሌዎች፣ የሀይማኖት አባቶች፣ ነጋዴዎች እና የመንግስት ሰራተኞች ጋር በተደረገ ቃለመጠይቅ የታላሚ ቡድን ውይይት መረጃ ተሰብስቧል፡፡

በማህበረሰቡ ውስጥ የግድያ ግጭት ሲከሰት ግጭቱ ተባብሶ ወደ ከፋ ደረጃ ከመድረሱ በፊት የሚችና የገዳይ ወገኖችን ለማስታረቅና በቂም በቀል እንዳይፈላለጉ ለማድረግ የሚያከናውኗቸውን ባህላዊ የግድያ ግጭት መፍቻ ስርዓቶች ለመመልከት በጎባ ወረዳ አንጋሶ ቀበሌ ገበሬ ማህበር ተፈጥሮአዊ መቼት በማዘጋጀት ምልከታ ተካሂዷል፡፡

በዚህ ጥናት መሰረት የባሌ ኦሮሞዎች በማህበረሰቡ ውስጥ ሚከሰትን ግጭት ለመፍታት የሚጠቀሙበት ስርዓት ሴሬ ጉማ እንደሚባል፣ ሴሬ ጉማ ለግድያ ግጭት ብቻ ሳይሆን ለእንስሳት፣ ለአካል ጉዳት እና ለሞራል መነካት የሚያገለግል ስርዓት እንደደሆነ ለማወቅ ተችሏል፡፡

በማህበረሰቡ ውስጥ የግድያ ግጭት እንዲከሰት መንስኤ የሚሆኑ ጉዳዮች በአብዛኛው የማህበረሰቡ የገቢ ምንጭ ከሆኑት ከእርሻና ከከብት ማርባት ጋር የተያያዙ እንደሆኑ፣ ማህበረሰቡ የግድያ ግጭት አይነቶችን በግጭቱ ውስጥ ከተሳተፉት አካላት ማንነት በመነሳት በቤተሰብ ውስጥ፣ በዘመድ መካከል፣ በጎሳ ውስጥ፣ በጎሳዎች መካከልና ኦሮሞ ካልሆኑ ህዝቦች ጋር የሚደረግ በማለት በአምስት እንደሚከፋፍሏቸው ጥናቱ ያሳያል፡፡ ለግድያ ግጭት የሚከፈለው ጉማ እንደግድያው ሁኔታ፣ እንደተጋጪዎቹ ማንነትና ቀረቤታ፣ እንደሚች ያታ

የተለያየ እንደሆነና የሚከፈለው ጉማም እንደየዘመኑ ሁኔታና እንደማህበረሰቡ የገቢ ምንጭ በሞት፣ በመሬት፣ በከብት እና በገንዘብ እንደነበር ከጥናቱ ለማወቅ ተችሏል፡፡

በማህበረሰቡ ባህል መሰረት ለግድያ ግጭት የሚከፈለው ጉማ አይነት በግድያው ሁኔታ ላይ በመመስረት 'ኦኮ'፣ 'ሀምቢሳ' እና 'ረፊሳ' በመባል እንደሚከፈል፣ ጉማ የሚከፈልበት የሰውነት አካል ሶስት መቶ ስልሳ እንደሆነ ጥናቱ ያሳያል፡፡

በባሌ ኦሮሞዎች የግድያ ግጭት ባህላዊ አፈታት ስርዓት ላይ ከፍተኛ ሚና ያላቸው 'ራያ አንባ' (Rayyaa Anbaa) የገለልተኛ ወገን ሽማግሌዎች ናቸው፡፡ ራያ አንባዎች ከሟች እና ከገዳይ ጎሳ ውጪ ሲሆኑ ብዛታቸው ሀያ አምስት ነው፡፡ ከሀያ አምስቱ ስምንቱ 'ቀርቱ'፣ ስምንቱ 'ጮይቱ'፣ ስምንቱ 'ቆፕቱ' ሲሆኑ የቀረው አንዱ የሁሉም ሰብሳቢ 'ቀራ' ነው፡፡ ራያ አንባዎች ገዳይን እና የገዳይ ጎሳዎችን ከሟች ጎሳ ለማስታረቅና ተመልሰው ወደግጭት እንዳያመሩ ለማድረግ ባህላዊ የግድያ እርቅ ስርዓት በመፈፀም ወዘተ. የማህበረሰቡ ሰላምና ደህንነት እንዳይደፈርስ ለማድረግ የሚጫወቱት ሚና ከፍተኛ እንደሆነ ጥናቱ ያሳያል፡፡

ማህበረሰቡ ለግድያ ግጭት ያለው አመለካከት የግድያ ግጭት መከሰት አይገባውም ከተከሰተም በፍጥነት መፍትሔ ማግኘት አለበት የሚል እንደሆነ፣ ባህላዊው የግድያ ግጭት መፍቻ ተቋም ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ስነልቦናዊ ፋይዳዎች እንዳሉት ከጥናቱ ማወቅ ተችሏል፡፡

የባሌ ኦሮሞዎች በተለያዩ ማህበራዊ ግንኙነቶች ወቅት ሀሳባቸውን በአጭርና ግልፅ ለማድረግ ከሚጠቀሙባቸው ምሳሌያዊ አነጋገሮች፣ አፈታሪኮችና ተረቶች ውስጥ ከግድያ ግጭት ምንነት፣ ዓይነቶች፣ መነሻ ምክንያቶች፣ ከገለልተኛ ወገን ሽማግሌዎች ሚና እና ከባህላዊ የእርቅ ስርዓቱ ጋር ግንኙነት ያላቸውን በመሰብሰብ ለናሙና የተመረጡት በግድያ ግጭት አፈታት ስርዓት ያላቸውን ሚና ለማሳየት ተሞክሯል፡፡

## 7.2 ይሁንታዎች

በዚህ ጥናት የቀረቡት የባሌ ኦሮሞ ማህበረሰብ ባህላዊ የግጭት መፍቻ ተቋማትና የግጭት አፈታት ስርዓት በነበሩበት ቢቀጥሉ ለአሁኑም ሆነ ለቀጣዩ ትውልድ ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖራቸዋል፡፡ በባህላዊው ስርዓት እና በተቋማቱ የበለጠ ለመጠቀምና ማህበራዊ ፋይዳቸውን እንደያዙ እንዲቆዩ ለማድረግ የሚከተሉትን ይሁንታዎች መተግበሩ መልካም ይመስለኛል፡፡

በማህበረሰብ ውስጥ በተለያዩ ምክንያቶች የሚከሰቱ የተለያዩ ግጭቶችን የሚፈቱት የሀገር ሽማግሌዎች እና የግድያ ግጭትን የሚፈቱት ራያ አንባዎች የተከሰተው ግጭት መፍትሔ እስኪያገኝ ድረስ ደከመኝ፣ ሰለቸኝ፣ ስራ አለብኝ .ወዘተ ሳይሉ ይለፋሉ፤ይደክማሉ፡፡ ነገር ግን እነዚህ ሽማግሌዎች ከመንግስት፣ ከማህበረሰቡና ከታራቂዎቹ የሚያገኙት ጥቅም የለም፡፡ የነሱ ጥረት የማህበረሰቡን ሰላምና ደህንነት ለመጠበቅ ነው፡፡ ቢሆንም አንድ ስራ እንጀራ የማያበላ ከሆነ ሰራተኛው እስከመጨረሻው በዛ ስራ ይቀጥላል ብሎ ማሰብ የዋህነት ይመስለኛል፡፡ ስለዚህ እነዚህ ማህበራዊው ህይወት ሰላማዊ እንዲሆን የሚተጉት የሀገር ሽማግሌዎች በበጎ ተግባራቸው እንዲቀጥሉ ለማድረግ መንግስት፣ የክልሉ መስተዳደር፣ የዞን እና የወረዳ የሰላምና ደህንነት አካላት ለስራቸው እውቅና መስጠት፣ መተዳደሪያ በሚሆን ክፍያ፣ በሞራልና በማቴሪያል ማገዝ፤

ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓቱን እና ሌሎች የማህበረሰቡን ባህላዊ እውቀቶች በጥናት ላይ በመመስረት በስርዓተ ትምህርቱ ውስጥ በማካተት፤በተለይ በማህበረሰቡ ቋንቋ ትምህርት በሚሰጥባቸው ደረጃዎች በህብረተሰቡ እና በቋንቋ የትምህርት ዓይነቶች ውስጥ በማካተት፣ ከተቻለም "የአካባቢ ባህል" የሚል የትምህርት አይነት በመጨመር አዲሱ ትውልድ የማህበረሰቡን ባህላዊ እውቀትና ዘመናዊውን ትምህርት ጎን ለጎን እንዲማር ማድረግ፤

የማህበረሰቡን ባህላዊ እውቀት የሚፃረሩ አካላትን እንቅስቃሴ ማስወገድና ማህበረሰቡን በልማዳዊ ደንቦች በነፃነት እንዲጠቀም ማበረታታት፤

የማህበረሰቡን ባህላዊ የግጭት መፍቻ ተቋማት ምንነት፣ አጀማመር፣ ማህበራዊ ፋይዳ እና አውዳዊ ክዋኔ ባህሉን በደንብ ከሚያውቁ የእድሜ ባለፀጋዎች በመጠየቅ በቴፕ፣ በፎቶ እና በቪዲዮ ካሜራ በመቅረፅ፣ ወደፅሁፍ መመለስና ማደራጀት፣ ለፊልም፣ ለትውፊታዊ ቴአትር፣ ለስነፅሁፍ እና ለሙዚቃ ግብዓት የሚሆኑበትን ሁኔታ ማመቻቸት፤

ባህላዊ የግጭት መፍቻ ስርዓቱ በተለያዩ ማህበረሰቦች ውስጥ ከሚተገበሩ መሰል ጠቃሚ ልማዳዊ ደንቦች ጋር ተቀናጅቶ ከኢትዮጵያ ዘመናዊ የህግ ሰነዶች ጋር ሊሰራ የሚችልበት ዘዴ መቀየስ፤

የሀገር ሽማግሌዎች እና የመደበኛ ፍርድ ቤት ዳኞች በመቀራረብ፣ በመረዳዳትና በመመካከር የሚሰሩበትን ሁኔታ ማመቻቸት፤

## ዋቢ መጻህፍት (Reference)


ሙሉጌታ ነጋሳ፤ በአደአ ሊበን ወረዳ የኦሮሞ ሴረ ጉማ ከግጭት አፈታት አንፃር፤ የኤም ኤ ዲግሪ ማሟያ ፅሁፍ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሁፍ ትምህርት ክፍል፣ 1997።

ማህተመ ስላሴ ወልደመስቀል፤ <u>የአባቶች ቅርስ</u>፣ አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት

ሰለሞን ሳህሌ፤ ባህላዊ የግጭት አፈታት በሲቡ ሲሬ ኦሮሞዎች፤ የኤም ኤ ዲግሪ ማሟያ ፅሁፍ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሁፍ ትምህርት ክፍል፣ 1997።

ብርሃኑ ለሜሶና ታቦር ዋሰሚ፤ <u>የኦሮሞ ህዝብ ታሪክ</u>፤ አዲስ አበባ፣ አ.የ 1993።

ብርሃን አሰፋ፤ "ባህላዊ የግጭት በወግዲ እና በቦረና ወረዳዎች"፤ የኤም ኤ ዲግሪ ማሟያ ፅሁፍ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሁፍ ትምህርት ክፍል፣ 2002።

አምሳሉ አክሊሉ፤ <u>አጭር የኢትዮጵያ ስነፅሁፍ ታሪክ</u>፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሁፍ ትምህርት ክፍል፣ 1978።

አበበ መርዕድ፤ "በጎባ ወረዳ የኦሮሞ ብሔረሰብ የመመገቢያ ቁሳቁስ አሰራር፣ አገልግሎትና ባህላዊ ፋይዳ ትንተና"፤ የኤም ኤ ዲግሪ ማሟያ ፅሁፍ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሁፍ ትምህርት ክፍል፣ 1997።

አወሉ አብዲ እና ሌሎች(አዘጋጆች)፣ <u>የኦሮሚያ ሚሊኒየም በድሬ ሼክ ሁሴን</u>፣ ባሌ ሮቤ ሶላር ማተሚያ፣ 2000።

አየለ ፍቅሬ፤ "ባህላዊ የግጭት አፈታት በባህር ዳር ነገዴ/ወይጦ/ ብሔረሰብ"፤ የኤም ኤ ዲግሪ ማሟያ ፅሁፍ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሁፍ ትምህርት ክፍል፣ 1998።

ኦሮሚያ ባህልና ቱሪዝም ኮሚሽን፣ <u>የኦሮሞ ታሪክ - እስከ አስራስድስተኛው ክፍለ ዘመን</u>፤ አዳማ፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1996።

የኢትዮጵያ ህዝቦች አካዳሚ፤ <u>የኦሮምኛ መዝገበ ቃላት</u>፣ አዲስ አበባ፣ 1996ዓ.ም።

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል፣ አማርኛ መዝገበ ቃላት፣ አዲስ አባባ ዩኒቨርሲቲ ማተሚያ ቤት፣ 2001::

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት፣ ነጋሪት ጋዜጣ፣ አዲስ አባባ፣ 1987::

የኦሮሚያ ባህልና ማስታወቂያ ቢሮ፣ "SADAA"፣ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት፣ 1991::

የወንድወሰን አውላቸው፤ የሰባት ቤት ጉራጌ ባህላዊ አስተዳደርና ግጭት አፈታት፤ የኤም ኤ ዲግሪ ማሟያ ፅሁፍ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሁፍ ትምህርት ክፍል፣ 1997::

የወንጀለኛ መቅጫ ህግ፤ አዲስ አበባ፤ ብርሃና ሰላም ማተሚያ ቤት 1948::

ደስታ ተክለወልድ፤ ዐዲስ የአማርኛ መዝገበ ቃላት፣ አዲስ አበባ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት::

ፈቃደ አዘዘ፡ የስነቃል መምሪያ፤ አዲስ አበባ፣ አልፋ አታሚዎች፣ 1991::

ፍትሐብሄር ሕግ፤ አዲስ አባባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ፣ 1952::

ፍትሐነገስት ንባብና ትርጓሜ፤ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1958::

ዘሪሁን አስፋው፤ የስነፅሁፍ መሰረታውያን፤ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት፣ 1992::

Arsi. Bale Rural development Project. Atlas of Bale Zone. Regional State of Oromoia, Bale zone Department of Finance and Economic Development Printed, 2004.

Augsburger W. David. Conflict Mediation Across Cultures. Louisville London: Westminster John Knoz press. 1992.

Assefa Abebe "Conflict: Its causes and Resolutions. Theoretical Sources paper" pastoralism in South Omo: Towards an Integrated Development. Proceeding of the workshop held in Jinka (South Omo) October 11-15, 2001.

Bender, Marvinhionel et.al (ed.). Language in Ethiopia. London: Oxford University press, 1976.

Bendeman, Hanneli. "Alternative dispute Resolution in the work place: The South African experience" Africa Journal of Conflict Resolution. Vol.17.No 1, Durban: Accord 2007.

Bliss, Frank. Management of Confliction Communal Level. GTZ GALPO. Project. A Training Manual Addis Ababa, Dec 2002.

Bowman, Prudence K. and Larry Ray. The Conflict Resolution Training program Leaders Manual. 2002.

Coser, Lewis A. The Functions of Social Conflict. New York. The Free Press 1956.

--------, Continuities in the Study of Social Conflict, New York: the Free press, 1970.

Dejene and Abdurahman. The Root Causes of Conflict among the Southern Pastorial Communities of Ethiopia: A Case Study of Borana and Degodia. Addis Ababa OSSREA 2001.

Desalegn Chemeda et.al. Indigenous System of Conflict Resolution in Oromia Ethiopia. CAB International. Community-based Water Law and Watert Resource Management Reform in Developing Countries (eds B. van Koppen, et.al

Deusdendit, Nukuranziza, R.K and Levis. Eds. Developing a Culture of Peace And Human Rights In Africa. KAS: June, 2003.

Deutsch, M. The Resolution of Conflict. New Haven: Yale University press, 1973.

Dorson, Richard M. ed. Folklore and Folklife an Introduction. Chicago: The University of Chicago press, 1972.

Federal Democratic Republic of Ethiopian Population Census Commission. Summary and Statistical Report of the 2007 population and housing census (population size by age and sex). Addis Ababa, 2008.

Fisher, J. Ronald. social psychology an Applied Approach. New York. St. Martins Press, 1982.

Goba "AANA" Administration Office "Five years strategic plan for Rural water, sanitation and Hygiene program (2005/06 — 2009/10)" unpublished, Dec. 2005.

Goldstein, Kenneth. A Guide for filed workers in Folklores. Pennsy/ vania: Gale Research Company. 1974(American Folklore Society, Folklore Association inc.)

Habtamu Wondimu. Hand Book of Peace and Human Rights Education in Ethiopia. Addis Ababa OSSREA 2008.

---------------"Conflict Resolution in the Families of Nine ethnic Groups in Ethiopia."The Ethiopian Journal of Education. Vol. XVIII No 2, Addis Ababa University: Institute of Educational Research, Dec. 1998.

Imbighe, T.A. The OAU (AU) and OAS in Regional Conflict Management: A Comparative Assessment. Ibadan: Spectrom Books Limited. 2003.

Jeong, Ho-wan. Peace and Conflicts: An Introduction. England Ashoate Publishing Ltd, 2000.

Koul, Lokesh. Methodology of Educational Research. New Dalhi: Vikas Publishing House PVT. Ltd, 2006.

Kuper, Adam and Jessica Kuper eds. The Social Science Encyclopedia. 2nd ed. London: Rutledge 1996

Levinson, David and Melvin Ember.eds. Encyclopedia of Cultural Anthropology. Vol.2 New York: Henery Holt and Company, 1996.

Malan, Jannie. Africa's Attitudinal Relations and Traditions Art of Dealing with Conflict. (Paper Presented at the all Africa Conference on African principles of Conflict Resolution and Reconciliation, Nov. 8-12 Addis Ababa, Ethiopia, 1999.

Medhane Tadesse. The Quest for Conflict Settlement in Ethiopia's Territory. Addis Ababa: Eventstifing, 2004.

Mesfin Yilma and Mesfin Bantayehu. Dealing with the Large Scale Violence: Is Comprehensive Academic Training Needed? (Paper Prepared on Conflict Resolution for a workshop Organized by APCMC on Behalf of Initiative Africa, Dec, 6-7) Addis Ababa, Ethiopia, 2007.

Mike and Cook, Doing Ethnography. London, SAGE pub,2007

Mitchell Malese. Knowledge Base Essay. Underlying Cause of Intractable Conflict. http://www.beyond intractability.org/about/about.JSP. 2003.

Nader, L. "Conflict Anthropological Aspect" International Encyclopedia of the Social Science. Vol.3.New York: Macmillan Company and the Free Press. 1968: 230-241.

Nhema. Alfred G. ed. The Quest for Peace in Africa. Addis Ababa: OSSREA, 2004.

Ogundipe, Titilayo. The Necessity of African Principle of Conflict Resolution. (Paper Presented at the all Africa Conference on African Principles of

conflict resolution and reconciliation, Nov. 8-12) Addis Ababa Ethiopia, 1999.

Pendergast, John. Post Conflict Programming. Osterville: Life and peace Institute, 2004.

Rabar,B and Karimi. Indigenous Democracy:Traditional Conflict Resolution Mechanism in Pokot,Turkana,Samburu,and Marakwet. Intermediate Technology Development Group Eastern Africa.2004

Rubin. J,D. Pruitt and S.kim. Social Conflict Escalation, Stalemate and Settlement. 2nd ed. New York: Mc Gran: Hill, 1995.

Schellenberg, James A. Conflict Resolution Theory, Research and Practice. Albany State University at New York Press, 1996.

Stuart, Williams. Bale Mountain A Guidebook. Addis Ababa; United printers, 2002.

Tirsit Girshaw. Indigenous Conflict Resolution Mechanism in Ethiopia (paper presented for First National Conference on Federalism, Conflict and Peace Building, May 5-7). Addis Ababa, Ethiopia, 1999.

Toumani, Adadou Toure. Conflict Prevention and Management in Africa: A permanent change. Development Center of the Organization for Economic Cooperation and Development (OECD). 1998: 49-56

Woodhouse, Tom and Oliver Ramsbotham. (eds.) Peace Keeping and Conflict Resolution. New York: Frank Class and co. Ltd, 2000.

# አባሪ አንድ የፎቶግራፍ መግለጫ

ፎቶግራፍ አንድ የጎባ ወረዳ የCR መዝገብ ፎርም



Guyyaa 24-8 20..

Waajjira Poolisii Magaalaa Gobbaatti
Gobba

dhimmi waaee araaraa kan ilaallatu yommuu ta'u
kunis walitti bu'insa obboo Baayyee Mucee fi
obboo Nuguusee Lataa wal dhaban ilaalchisee
nuti waraqaan jaarsaa lola namoota kanaa
ilaalee jedha isaniitiin obboo Baayee muceetiif
Birrii Nuguusee poolisa biraa qabu akka kennam
uuf jenne araaraan [illegible] jira
Akkasumas waraqaan waldhabne jedha keenyan
fixxachuu keenya malattoo keenyan mirkaneessine
jira 1ffaa Baayee Mucee
2ffaa Nuguusee Lataa
Jaarsonni [illegible]
1ffaa Balaay Makonnin
2ffaa Ababaa Tasfaayee
3ffaa Mulaalu Akilook
4ffaa [illegible] Kabada

24/9/2003

ፎቶግራፍ ሁለት ራያ አምባዎች በቅንብር ተፈጥሮአዊ መቼት ሽምግልና ተቀምጠው



ፎቶግራፍ ሶስት አቶ ጃርሶ ለራያ አምባዎች የጥናቱን አላማ ሲያስረዱ



ፎቶፍራፍ አራት ሽማግሌዎች በአለንጌ ስምምነታቸውን ሲገልፁ



ፎቶግራፍ አምስት ዘጠኙ ራያ አምባዎች በረኮ ስርዓት ሽምግልና ሲያከናውኑ



ፎቶግራፍ ስድስት አጥኚው ከራያ አምባዎች መረጃ ሲሰበስብ



ፎቶግራፍ ሰባት ለረኮ ስትዓት የታረደው በግ



ፎቶፍራፍ ስምንት አጥኚው ከቁልፍ መረጃ አቀባዮች መረጃ ሲሰበስብ



ፎቶግራፍ ዘጠኝ ራያ አምባዎች ከበግ ቆዳ ጎልጋውን ሲያዘጋጁ



ፎቶግራፍ አስር ራያ አምባዎች ለረኮ ስርዓት የሚያስፈልገውን ጨውና ማር ይዘው



አባሪ ሁለት በባህላዊ የግጭት አፈታት ወቅት የሚነገሩ ምሳሌያዊ አነጋገሮች

Jaarsaafi waaqi akka tonkichaa dansaa.

Jaarsi ajjeesee nama kaasa.

Jaarsi antuutaa warraa waa ba'a warri jaarsa hin qabne ni bada.

Jaarsiifi qalqalloon, guutu malee hin dhaabbatu.

Jaarsi tokko ka waa falu,tokko ka waa falfalu.

Mammaaksi bifa dubbiiti jobbiin bifa loonii.

Inhuqqata malee, dhugaan hinbadu.

Dhadhaan ibiddaa bu'e hin deebi'u.

Jaarsa bulee waa hima.

Ibiddi dhaamu daaraan nama hingubu.

Hammatullee dubbii jaarsaa hintuffatan.

Soogidda hinwaadan, waandabre hinyaadan.

Ariitiin buna guba bunni afaan nama guba.

Badiin guyaa tokko, Jireenni guyyaa heduu.

Bishaan hanguma dhaqaban olqaban.

Cubbuun cabaan nama galti.

Dalagaan abbuma eggata.

Duuti seenaa dhabde hinjirtu.

Wanjalaafi daaymi xiqqaa hinqabu.

## አባሪ ሦስት

## የመረጃ አቀባዮች ዝርዝር

| ተ.ቁ | ሙሉ ስም | ፆታ | ዕድሜ | ብሔረሰብ | የመኖሪያ አድራሻ | ስራ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አቶ ሽምሰዲን ሺፋ | ወ | 41 | ኦሮሞ | ሲናና | የሲናና ወረዳ የባህልና ቱሪዝም ቢሮ ሃላፊ |
| 2 | አቶ ጃርሶ በልዳ | ወ | 53 | ኦሮሞ | ጎባ | የጎባ ወረዳ የባህልና ቱሪዝም ቢሮ ሃላፊ |
| 3 | አቶ ሀጂ በከር | ወ | 61 | ኦሮሞ | ጎባ | የጎባ ወረዳ የገጠር ልማት ቢሮ ሃላፊ |
| 4 | አቶ ከድር ጀማል | ወ | 74 | ኦሮሞ | ጎባ | አርሶ አደር |
| 5 | አቶ ቲልሞ ሲዴ | ወ | 88 | ኦሮሞ | ጎባ | አርሶ አደር |
| 6 | አቶ ሀሰን አቢዮ | ወ | 27 | ኦሮሞ | ሲናና | የባሌ ዞን ባልና ቱሪዝም ቢሮ ምክትል ተጠሪ |
| 7 | አቶ አብዲ ከማል | ወ | 69 | ኦሮሞ | ሲናና | አርሶ አደር |
| 8 | አቶ ጎበና ባቲ | ወ | 75 | ኦሮሞ | ጎባ | አርሶ አደር |
| 9 | አቶ አማን በሽር | ወ | 35 | ኦሮሞ | ሲናና | የባሌ ዞን ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ሃላፊ |
| 10 | ሃጂ ረሺድ`ሃጂ አደም | ወ | 67 | ኦሮሞ | ሲናና | አርሶ አደር |
| 11 | አቶ በዳሶ በልዳ | ወ | 63 | ኦሮሞ | ጎባ | አርሶ አደር |
| 12 | አቶ ማማ ቃሲም | ወ | 45 | ኦሮሞ | ጎባ | አርሶ አደር |
| 13 | አለቃ ተስፋዬ ወ/ዩሀንስ | ወ | 74 | ኦሮሞ | ሲናና | መሪ ጌታ |
| 14 | ወ/ሮ በድሪያ አወል | ሴ | 39 | ኦሮሞ | ጎባ | የጎባ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ተጠሪ |
| 15 | አቶ ጫጮ ከንፈልቻ | ወ | 113 | ኦሮሞ | ጎባ | አርሶ አደር |

## አባሪ አራት የባሌ ዞን ካርታ



# ማረጋገጫ

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ የኔ የግል ስራ መሆኑንና በፅሁፉ ውስጥ የተጠቀምኩባቸውን ተዛማጅ ፅሁፎችና መረጃዎች በሙሉ በትክክል የጠቀስኩ መሆኔን አረጋግጣለሁ።

ስም፡ ለታሪክ ተሾመ

ፊርማ ___________________

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በዓብአዊ ሳይንስ ፋኩልቲ የኢትዮጵያ ስነ-ፅሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት

አዲስ አበባ

ሰኔ 2003ዓ.ም